# የቤተሰብ ዳራ የአንብቦ መረዳት ችሎታን የመተንበይ ድርሻ፤ በአምስተኛና በሰባተኛ ክፍል ተማሪዎች ተተኳሪነት

በ

አስቴር አስራት ዳኘው

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የስነ ሰብ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጋዜጠኝነትና ተግባቦት ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ፣ ስነጽሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

ድህረ ምረቃ መርሀ ግብር

አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

ሰኔ፣ 2010

# የቤተሰብ ዳራ የአንብቦ መረዳት ችሎታን የመተንበይ ድርሻ፤ በአምስተኛና በሰባተኛ ክፍል ተማሪዎች ተተኳሪነት

በ

አስቴር አስራት ዳኘው

አማካሪዎች

ዶ/ር ታመነ ኪቲላ

ዶ/ር ሙላት አስናቀ

በተግባራዊ ስነልሳን የኢትዮጵያ ቋንቋዎችን ማስተማር የፍልስፍና ዶክትሬት ዲግሪ  ማሟያ የቀረበ ጥናታዊ ጽሁፍ

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የስነ ሰብ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጋዜጠኝነትና ተግባቦት ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ፣ ስነጽሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

ድህረ ምረቃ መርሀ ግብር

አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

ሰኔ ፣ 2010

## አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

## የስነ ሰብ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጋዜጠኝነትና ተግባቦት ኮሌጅ

## የአማርኛ ቋንቋ፣ ስነጽሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

## የድህረ ምረቃ መርሀ ግብር

የቤተሰብ ዳራ የአንብቦ መረዳት ችሎታን የመተንበይ ድርሻ በአምስተኛና በሰባተኛ ክፍል ተማሪዎች ተተኳሪነት፤ በሚል ርዕስ በተግባራዊ ስነልሳን የኢትዮጵያ ቋንቋዎችን ማስተማር የፍልስፍና ዶክትሬት ዲግሪ ማሟያ በአስቴር አስራት ዳኘው የቀረበው ይህ ጥናት የዩኒቨርሲቲውን የጥራትና የወጥነት መስፈርት ስለማሟላቱ በፈታኞች ተረጋግጦ ተፈርሟል፡፡

## የፈተና ቦርድ አባላት

አማካሪ---------------------------------------------- ፊርማ --------------------- ቀን -------------

አማካሪ---------------------------------------------- ፊርማ --------------------- ቀን -------------

የውጭ ፈታኝ ---------------------------------------ፊርማ----------------- ቀን ----------------

የውስጥ ፈታኝ ---------------------------------- ፊርማ --------------------- ቀን -------------

# ማረጋገጫ

የቤተሰብ ዳራ የአንብቦ መረዳት ችሎታን የመተንበይ ድርሻ በአምስተኛና በሰባተኛ ክፍል ተማሪዎች ተተኳሪነት፤ በሚል ርዕስ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በስነ ሰብ፣ ቋንቋዎች ጥናት፣ ጋዜጠኝነትና ተግባቦት ኮሌጅ፣ የአማርኛ ቋንቋ ስነጽሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል በተግባራዊ ስነልሳን የኢትዮጵያ ቋንቋዎችን ማስተማር የፍልስፍና ዶክትሬት ዲግሪ ማሟያ ያቀረብኩት ይህ ጥናት ከዚህ በፊት በማንኛውም አካል ያልተሰራ የራሴ ወጥ ስራ መሆኑንና የተጠቀምኩባቸው ድርሳናትም በትክክል የተጠቀሱና ዋቢ የተደረጉ መሆኑን እንዲሁም አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የጥናቱ ህጋዊ ባለቤት መሆኑን በፊርማየ አረጋግጣለሁ፡፡

ስም ---------------------------------------------------

ፊርማ ---------------------------------------------------

ቀን ---------------------------------------------------

# ምስጋና

በመጀመሪያ ይህ ጥናት ተጀምሮ እስኪጠናቀቅ ድረስ ረቂቁን በማረም፣ ማስተካከያ በመስጠት፣ ጥናቱ የተነሳበትን አላማ እንዳይስት አቅጣጫ በማስያዝና ጠቃሚ ምክሮችንና ገንቢ አስተያየቶችን በመስጠት ድጋፍቸው ላልተለየኝ አማካሪዎቼ ዶክተር ታመነ ኪቲላና ዶክተር ሙላት አስናቀ ልባዊ ምስጋናየን እያቀረብኩ አክብሮታቸውንም አደንቃለሁ፡፡

በመቀጠል በርዕስ አመራረጥ፣ በሴሚናር፣ በትልመ ጥናቱና በደረጃ ማበልጸጊያ ጊዜ ጠቃሚ ምክር በመስጠት ከመነሻው እንዲስተካከል አስተዋጽዖ ላበረከቱት መምህሮቼ ዶክተር ማረው አለሙ፣ ዶክተር ሙሉሰው አስራቴ፣ ዶክተር ጌታሁን አማረ፣ ዶክተር ጌታቸው እንዳላማውና ዶክተር ገረመው ለሙ ያለኝ ምስጋና ላቅ ያለ ነው፡፡ በስታትስቲክስ ስራው ስልጠና በመስጠትና እንዴት እንደሚሰራ በማሳየት የተባበረኝን አቶ ጥላሁን ግደይና ተጨማሪ የስታትስቲክስ እውቀት ያስጨበጠኝን ዶክተር ታምሬ አንዷለምን ፈጣሪ ያክብርልኝ ብያለሁ፡፡ ለጥናቴ የሚጠቅሙ ጽሁፎችንና መጽሀፍትን በመስጠት የተባበርከኝ አስፋው ጌትነት ላንተም ትልቅ ምስጋና አለኝ፡፡

በእውቀት፣ በገንዘብና በሞራል ሁሌም ከጎኔ የማትለየው አባቴ ዶክተር አስራት ዳኘው ላንተ የሚሆን የምስጋና ቃላት የለኝም፡፡ ብርታቴ ለሆነችው እናቴ ጎኔ ልጅእንዲህ፣ ፍቅራቸውና ድጋፍቸው ለማይነጥፈው ቤተሰቦቸ ላቀች ልጅእንዲህ፣ ዶክተር ፍታለው ልጅእንዲህ፣ አባይነሽ አስራት፣ ሰላማዊት አስራት፣ ገብረመድህን አስራትና አማኑኤል አስራት ምስጋናየ ከፍተኛ ነው፡፡ ሁሌም በርች የምትሉኝ ጓደኞቼና የስራ ባልደረቦቼ በሙሉ ከልብ አመሰግናለሁ፡፡

የመጨረሻ ሳይሆን በመጨረሻ መረጃ በምሰበስብበት ወቅት ከፍተኛ እገዛ ላደረጉልኝ የድል ችቦ ርዕሳነ መምህራን ሙላትና ጌታቸው፤ የቁልቋል ሜዳ ርዕሳነ መምህራን ንግስትና ብርቱካን፤ የዶናበርበር ርዕሳነ መምህራን እያሱና ወሰን፤ እንዲሁም የየትምህርት ቤቱ የአማርኛ መምህራን ህይወት፣ ሰብለወንጌል፣ ጥሩወርቅና ማርታ ከልብ አመሰግናለሁ፡፡ በተለይም የዶና በርበር የአማርኛ መምህርትና የትምህርት ቤቱ ዩኒት መሪ የሆንሽው ማርታ እጅግ አመሰግናለሁ፡፡ እንዲሁም ውድ ጊዜያቸውን መስዋዕት አድርገው መረጃ በመስጠት የተባበሩኝ የድልችቦ፣ የቁልቋል ሜዳና የዶና በርበር ተማሪዎችን ላመሰግን እወዳለሁ፡፡

# ማውጫ

**ርዕስ** **ገጽ**


ምስጋና ____ I

ማውጫ ____ I I

የሰንጠረዥ ዝርዝር ማውጫ ____ VIII

የስዕል ዝርዝር ማውጫ ____ X

አህጽሮተ ጥናት ____ XI

የቁልፍ ቃላት አቻ ትርጉም ____ XII

ምዕራፍ አንድ፡- መግቢያ ____ 1

1.1. የጥናቱ ዳራ ____ 1

1.2. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት ____ 13

1.3. የጥናቱ ጥያቄዎች ____ 20

1.4. የጥናቱ አላማ ____ 21

1.5. የጥናቱ ጠቀሜታ ____ 22

1.6. የጥናቱ ወሰን ____ 22

1.7. የጥናቱ ውስንነት ____ 24

1.8. የቁልፍ ቃላት ብያኔ ____ 25

ምዕራፍ ሁለት፡- የተዛማጅ ጽሁፍ ክለሳ ____ 28

2.1. መግቢያ ____ 28

2.2. የማንበብ ምንነት ____ 28

2.3. የአንብቦ መረዳት ንድፈ ሀሳብ ____ 29

2.4. የአንብቦ መረዳት ሞዴሎች ____ 36

2.5. የአንብቦ መረዳት ደረጃዎች ____ 38

2.6. የማንበብ ተነሳሽነት ______ 40
2.7. የቤተሰብ ዳራ ______ 46
2.8. የቀደምት ስራዎች ቅኝት ______ 49
2.9. የጥናቱ ንድፈሀሳባዊ ማዕቀፍ ______ 64
2.10. የጥናቱ ጽንሰሀሳባዊ ማዕቀፍ ______ 67
2.11. የምዕራፉ ማጠቃለያ ______ 68
**ምዕራፍ ሶስት፡- የአጠናን ዘዴ** ______ 71
3.1. መግቢያ ______ 71
3.2. የጥናቱ ንድፍና ስልት ______ 71
3.3. የትምህርት ቤትና የተጠኚዎች አመራረጥ ______ 72
3.4. የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ______ 74
3.4.1. የጽሁፍ መጠይቅ ______ 75
3.4.1.1. የቤተሰብ ዳራን የሚለካ መጠይቅ ______ 75
3.4.2. ፈተና ______ 78
3.4.2.1. የፈተና አዘገጃጀት ______ 78
3.4.2.2. የምንባብ አመራረጥ ______ 79
3.4.2.3. የፈተናዎች የይዘት ትክክለኝነትና ተገቢነት ______ 81
3.4.2.4. የፈተናው የውጤት ስርጭት ወጥነት ______ 81
3.4.2.5. የፈተናው የክብደት ቅለት መጠን ______ 82
3.4.2.6. የፈተናው የመለየት ብቃት/ አቅም ______ 84
3.4.3. የቡድን ውይይት ______ 85
3.5. የመረጃ መሰብሰቢያ አስተማማኝነት ______ 87
3.6. የመረጃ መተንተኛ ዘዴ ______ 89
3.7. የዋናው ጥናቱ ሂደት ______ 94
3.8. ስነምግባራዊ ትኩረቶች ______ 97
**ምዕራፍ አራት ፡- የሙከራ ጥናቱ ውጤት ትንተና፣ ማብራሪያና የተገኙ ተሞክሮዎች** ______ 99
4.1. መግቢያ ______ 99
4.2. የሙከራ ጥናቱ አላማዎች ______ **99**

4.3. ሙከራ ጥናቱ ንድፍና ስልት _______________________ 100

4.4. ሙከራ ጥናቱ ተሳታፊዎች አመራረጥ __________________ 100

4.5. የሙከራ ጥናቱ የመረጃ መሰብሰቢያዎች __________________102

4.6. የሙከራ ጥናቱ የመረጃ መተንተኛ ዘዴ __________________ 104

4.7. የሙከራ ጥናቱ ሂደት _____________________________ 105

4.8. ሙከራ ጥናቱ የውጤት ትንተና _______________________ 106

4.9. ከሙከራ ጥናቱ የተገኙ ተሞክሮዎች ____________________ 133

ምዕራፍ አምስት፡- የዋናው ጥናት ውጤት ትንተናና ማብራሪያ

5.1. መግቢያ _____________________________________ 135

5.2. የዋናው ጥናት የውጤት ትንተና _________________ 135

5.3. የዋናው ጥናት ውጤት ማብራሪያ ____________________ 156

ምዕራፍ ስድስት፡- ማጠቃለያ፣ መደምደሚያና የመፍትሄ ሀሳብ

6.1. ማጠቃለያ _______________________________ 162

6.2. መደምደሚያ _______________________________ 162

6.3. የመፍትሄ ሀሳብ _______________________________ 168

**ዋቢ መጻህፍት** ________________________________________ 171

አባሪዎች ____________________________________________ 189

አባሪ ሀ.፡- የዋናው ጥናት መረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ________189

ሀ.1. የቤተሰብ ዳራ የሚለካ መጠይቅ ______________________ 189

ሀ.2. የአምስተኛ ክፍል የአንብቦ መረዳት ፈተና ____________________ 192

ሀ.3. የሰባተኛ ክፍል የአንብቦ መረዳት ፈተና ______________________ 197

ሀ.4. የዋናው ጥናት የአንብቦ መረዳት ችሎታ የፈተና ውጤት __________ 203

ሀ.4.1. የ5ኛ ክፍል የአንብቦ መረዳት ችሎታ ድምር ውጤት ________ 203

ሀ.4.2. የ5ኛ ክፍል ፈተና የውጤት ስርጭት ወጥነት ______________205

ሀ.4.3. 5ኛ ክፍል ፈተና የቅለት ክብደት መጠን __________________206

ሀ.4.4. የ5ኛ ክፍል ፈተና የመለየት ብቃት ______________________207

ሀ.4.5.የሰባተኛ ክፍል የአንብቦ መረዳት ችሎታ ድምር ውጤት _____ 208

ሀ.4.6.የ7ኛ ክፍል ፈተና የውጤት ስርጭት ወጥነት ______________ 210

ሀ.4.7. የ7ኛ ክፍል ፈተና የክብደት ቅለት መጠን _________________ 211

ሀ.4.8. የ7ኛ ክፍል ፈተና የመለየት ብቃት/አቅም ________________ 212

ሀ.5. የአንብቦ መረዳት ፈተናዎችን የይዘት ትክክለኘነት መገምገሚያ ቅጽ___ 213

ሀ.5.1 ስለአንብቦ መረዳት ፈተናዎች የይዘት

ትክክለኘነት የባለሙያዎች ግምገማ ________________ 214

አባሪ ለ፡- የሙከራ ጥናቱ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች

ለ.1. የቤተሰብ ዳራን የሚለካ መጠይቅ _____________________________ 215

ለ.2. የማንበብ ተነሳሽነትን የሚለካ መጠይቅ _________________________ 220

ለ.3. የ8ኛ ክፍል የአንብቦ መረዳት ችሎታ መለኪያ ፈተና _____________ 226

ለ.4. የ7ኛ ክፍል የአንብቦ መረዳት ችሎታ መለኪያ ፈተና ______________ 232

ለ.5. የ6ኛ ክፍል የአንብቦ መረዳት ችሎታ መለኪያ ፈተና ______________ 238

ለ.6. የ5ኛ ክፍል አንብቦ መረዳት ችሎታ መለኪያ ፈተና _______________ 243

ለ.7. የሙከራ ጥናቱ የአንብቦ መረዳት ችሎታ ውጤት

ለ.7.1. የ5ኛ ክፍል የሙከራ ፈተና ድምር ውጤት ________________ 248

ለ.7.2. የ5ኛ ክፍል የሙከራ ፈተና ውጤት የስርጭት ወጥነት _______ 249

ለ.7.3. የ5ኛ ክፍል የሙከራ ፈተና የቅለት ክብደት መጠን _________ 250

ለ.7.4. የ5ኛ ክፍል የሙከራ ፈተና የመለየት ብቃት _______________ 251

ለ.7.5. የ6ኛ ክፍል የሙከራ ፈተና ድምር ውጤት ________________ 252

ለ.7.6. የ6ኛ ክፍል የሙከራ የውጤት ስርጭት ወጥነት __________ 253

ለ.7.7. የ6ኛ ክፍል የሙከራ ፈተና የቅለት ክብደት መጠን ___________ 254

ለ.7.8. የ6ኛ ክፍል የሙከራ ፈተና የመለየት ብቃት ___________ 255

ለ.7.9. የ7ኛ ክፍል ሙከራ ፈተና ድምር ውጤት _____________ 256

ለ.7.8. የ7ኛ ክፍል የሙከራ ፈተና የውጤት ስርጭት ወጥነት _ 257

ለ.7.9. የ7ኛ ክፍል የሙከራ ፈተና የክብደት ቅለት መጠን ____ 258

ለ.7.10. የ7ኛ ክፍል የሙከራ ፈተና የመለየት ብቃት __________ 259

ለ.7.11. የ8ኛ ክፍል የሙከራ ፈተና ድምር ውጤት __________ 260

ለ.7.12. የ8ኛ ክፍል ሙከራ ፈተና የውጤት ስርጭት ወጥነት __ 261

ለ.7.13. የ8ኛ ክፍል የሙከራ ፈተና የክብደት ቅለት መጠን ____ 262

ለ.7.14. የ8ኛ ክፍል የሙከራ ፈተና የመለየት ብቃት __________ 263

ለ.8. የሙከራ ጥናቱ የማንበብ ተነሳሽነት ውጤት

ለ.8.1. የ5ኛ ክፍል የሙከራ የማንበብ ተነሳሽነት ውጤት ____________ 264

ለ.8.2. የ5ኛ ክፍል የሙከራ ተነሳሽነት ውጤት ስርጭት ወጥነት ____ 265

ለ.8.3. የ5ኛ ክፍል በሙከራ ጥናት በ11 የማንበብ ተነሳሽነት

መለኪያዎች የተገኘው ውጤት __________________________ 266

ለ.8.4. የ6ኛ ክፍል የሙከራ የማንበብ ተነሳሽነት ውጤት _______ 268

ለ.8.5. የ6ኛ ክፍል የሙከራ ተነሳሽነት ውጤት ስርጭት ወጥነት ______269

ለ.8.6. የ6ኛ ክፍል ክፍል በሙከራ ጥናት በ11 የማንበብ

ተነሳሽነት መለኪያዎች የተገኘው ውጤት ________________ 270

ለ.8.7. የ7ኛ ክፍል የሙከራ የማንበብ ተነሳሽነት ውጤት _________ 272

ለ.8.8. የ7ኛ ክፍል የሙከራ ተነሳሽነት ውጤት ስርጭት ወጥነት ___ 273

ለ.8.9.የ7ኛ ክፍል ክፍል በሙከራ ጥናት በ11

የማንበብ ተነሳሽነት መለኪያዎች የተገኘው ውጤት ___________274

ለ.8.10. የ8ኛ ክፍል የሙከራ የማንበብ ተነሳሽነት ውጤት ______ 276

ለ.8.11. የ8ኛ ክፍል ተነሳሽነት ውጤት ስርጭት ወጥነት ______ 277

ለ.8.12. የ8ኛ ክፍል ክፍል በሙከራ ጥናት በ11 የማንበብ

ተነሳሽነት መለኪያዎች የተገኘው ውጤት _______________ 278

ሐ. የዋናው ጥናት የድህረት ትንተናና፣ የቲቴስት

ውጤቶች ሙሉ ሰንጠረዥ_____________________________________ 355

# የሰንጠረዥ ዝርዝር ማውጫ


1. ሰንጠረዥ 2.1፡- ከአይነታዊ ምርምር የተገኙ የማንበብ ተነሳሽነት መለኪያዎች (Dimensions of Reading Motivation: Results from Qualitative Studies) ________ 41
2. ሰንጠረዥ 2.2፡- ከ Wainer& Piper (2010) ጥናት የተገኘ የአማርኛ ቋንቋ አፈፃፀም የአንብቦ መረዳትና ሌሎች የማንበብ ተግባራት ውጤት ንጽጽር በክልል ደረጃ ---------- 57
3. ሰንጠረዥ 3.1፡- በዕጣ ንሞና ለጥናቱ የተመረጡና መረጃውን የሰጡ ተማሪዎች ________ 77
4. ሰንጠረዥ3.2፡-የመረጃ መሰብሰቢያዎች አስተማማኝነት በክሮንባኽ አልፋ (Cronbach's Alpha) ________ 88
5. ሰንጠረዥ 3.3. በጥናቱ የተካተቱ ተላውጦዎችና በኤስፒኤስ ኤስ የኮድ ስያሜየቸው ________ 89
6. ሰንጠረዥ 4.1፡- የቤተሰብ ዳራ ለአንብቦ መረዳት ችሎታ ያለው ተናጠላዊ አስተዋጽኦና የጉልህነት ደረጃ በድህረት ትንተና (multiple regression analysis) ________ 111
7. ሰንጠረዥ 4.2፡- የቤተሰብ ዳራ ለማንበብ ተነሳሽነት ያለው ተናጠላዊ አስተዋጽኦና የጉልህነት ደረጃ በድህረት ትንተና (multiple regression analysis) ________ 116

8. ሰንጠረዥ 4.3፡- የማንበብ ተነሳሽነትና የአንብቦ መረዳት ችሎታ ተዛምዶ በፒርሰን የተዛምዶ መወሰኛ /Pearson correlation coefficient/ ____ 120

9. ሰንጠረዥ 4.4፡- በሴትና ወንድ ተማሪዎች መካከል የማንበብ ተነሳሽነትና የአንብቦ መረዳት ችሎታ አማካይ ልዩነት ንጽጽር በነጠላ የልይይት ትንተና (one way ANOVA) ____ 122

10. ሰንጠረዥ 4.5፡- በተማሪዎች የክፍል ደረጃ መካከል የማንበብ ተነሳሽነት አማካይ ልዩነት ንጽጽር በነጠላ የልይይት ትንተና (one way ANOVA) ____ 123

11. ሰንጠረዥ 5.1፡- ጾታ በክፍል ደረጃ ያለው ስብጥር ብዛትና መቶኛ ስሌት __136

12. ሰንጠረዥ 5.2፡- የቤተሰብ መዋቅር በድግግሞሽና በፐርሰንታይል ____137

13. ሰንጠረዥ 5.3፡- የቤተሰብ ብዛት በድግግሞሽና በፐርሰንታይል ____ 138

14. ሰንጠረዥ 5.4፡- የቤተሰብ የት/ት ደረጃ በድግግሞሽና በፐርሰንታይል ____ 139

15. ሰንጠረዥ 5.5፡- የቤተሰብ ስራ በድግግሞሽና በፐርሰንታይል ____ 140

16. ሰንጠረዥ 5.6፡- የቤት ውስጥ ግብዓት በድግግሞሽና በፐርሰንታይል ___ 140

17. ሰንጠረዥ 5.7፡- የኢኮኖሚ ደረጃ በድግግሞሽና በፐርሰንታይል ____ 141

18. ሰንጠረዥ 5.8፡- የማህበራዊ ደረጃ በድግግሞሽና በፐርሰንታይል ____ 142

19. ሰንጠረዥ 5.9፡- የተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ችሎታ አማካይ በክፍል ደረጃና በጾታ ____ 142

20. ሰንጠረዥ 5.10፡- የዋናው ጥናት የቤተሰብ ዳራ ለአንብቦ መረዳት ችሎታ ያለው አስተዋጽኦና የጉልህነት ደረጃ በድህረት ትንተና (5ኛ ክፍል) ____ 144

21.ሰንጠረዥ 5.11፡- የቤተሰብ ዳራ ለአንብቦ መረዳት ችሎታ ያለው ተናጠላዊ አስተዋጽኦና የጉልህነት ደረጃ በድህረት ትንተና (7ኛ ክፍል) ______ 148

22.ሰንጠረዥ 5.12፡- በሴትና ወንድ ተማሪዎች መካከል የአንብቦ መረዳት ችሎታ አማካይ ልዩነት ንጽጽር በነጻ ናሙና ቲ ቴስት ______ 152

## የስዕል ዝርዝር ማውጫ

1. ስዕል አንድ፡- በአንብቦ መረዳት ችሎታ ላይ ተጽዕኖ ፈጣሪ ነገሮች ______ 8
2. ስዕል ሁለት፡- የባህሪያውያን የማንበብ እድገት ሂደት ______ 30
3. ስዕል ሶስት፡- የአዕምሯውያን የንባብ ሂደት ______ 33
4. ስዕል አራት፡- የቅድመማንባታውያን የማንበብ ሂደት ______ 34
5. ስዕል አምስት፡- የአንባቢ፣ የጽሁፍና የአውድ ተራክቦ ______ 36
6. ስዕል ስድስት፡ የ Bronfenbrenner የስነምህዳር ስርዓት ንድፈሀሳብ ______ 65
7. ስዕል ሰባት፡- የጥናቱ ጽንሰ ሀሳባዊ ማዕቀፍ ______67

# አህጽሮተ ጥናት

የዚህ ጥናት ዋና አላማ የቤተሰብ ዳራ የአንብቦ መረዳት ችሎታን የመተንበይ ድርሻውን መለየት ነው፡፡ ተሳታፊዎች በዶና በርበር የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት በ2010 ዓ.ም ትምህርታቸውን በመከታተል ላይ የሚገኙ በዕጣ ንሞና የተመረጡ 151 የአምስተኛና 170 የሰባተኛ ክፍል ተማሪዎች ናቸው፡፡ ከተሳታፊዎች መረጃ የተሰበሰበው በሶስት የተለያዩ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ነው፡፡ እነሱም የጽሁፍ መጠይቅ፣ ፈተናና የቡድን ውይይት ናቸው፡፡ ፈተናው አንብቦ መረዳት ችሎታን፣ መጠይቁ የቤተሰብ ዳራን ለመለካት ሲያገለግል የቡድን ውይይቱ ደግሞ ተጨማሪ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ በመሆን አገልግሏል፡፡ የተሰበሰቡት መረጃዎች አስተማማኝነት፣ ተገቢነትና የውጤት ስርጭት ወጥነት ተሰልቶ ከተረጋገጠ በኋላ ሁሉም መረጃዎች በተንባይና ገላጭ ስታትስቲክሶች አማካኝነት ተተንትነው ተብራርተዋል፡፡ የተገኘው መረጃ የፓራሜትሪያዊ መፈተሻ ዘዴዎችን ለመጠቀም የሚያስችል በመሆኑ ተግባራዊ የተደረጉት የመተንተኛ ዘዴዎች የህብረ ድህረት ትንተናና የነጻ ናሙና ቲቴስት ናቸው፡፡ በትንተናው መሰረት የቤተሰብ ዳራ የአንብቦ መረዳት ችሎታን ጉልህ ተንባይ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ከቤተሰብ ዳራ ዝርዝር ተላውጦዎች የአንብቦ መረዳት ችሎታን በከፍተኛ ደረጃ የተነበዩት የቤተሰብ የኢኮኖሚ ደረጃና የቤተሰብ የትምህርት ደረጃ ናቸው፡፡ የቤተሰብ የኢኮኖሚ ደረጃ መለኪያ የሆኑት ወርሀዊ ገቢና ß= 0.5ና ገቢ ከአካባቢ ጋር ሲነጻጸር ß= 0.119 የቤተሰብ የትምህርት ደረጃ ß= 0.382 ከፍተኛ የመደበኛ ቤታ ዋጋ በማምጣት ከሌሎች ተላውዎች በተሻለ ጉልህ ተንባይ ሆነዋል፡፡ ይህ ውጤት በሁለቱም የክፍል ደረጃ ተቀራራቢ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በተጨማሪነት የታየው ሌላው ጥያቄ የአንብቦ መረዳት ችሎታ በጾታ ልዩነት እንዳለው መቃኘት ሲሆን የወንዶች አማካኝ ችሎታ ከሴቶች የተሻለ ሆኖ ቢገኝም በሁለቱ መካከል ያለው ልዩነት ጉልህ እንዳልሆነ በትንተናው ተረጋግጧል፡፡ የአምስተኛ ክፍል ተማሪዎች ወንዶች 22.51 ሲሆን የሴቶቹ 21. 63 የሰባተኛ ክፍል ወንዶች 17.74 የሴቶች 17.13 ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ከዚህ ውጤት በመነሳትም በትምህርት ቤት ውስጥ የኢኮኖሚ ችግር ያለባቸውን ልጆች ድጋፍ ማድረግና ያልተማሩ ወላጆችን የተለያዩ የመሰረታዊ ትምህርት እንዲያገኙ ማድረግ የሚሉ የመፍትሄ ሀሳቦች ተሰጥተዋል፡፡ ለሴቶች የተለያዩ ድጋፎችን መስጠት የሚል ስነትምህርታዊ አንድምታ ተሰጥቷል፡፡ በተጨማሪም በረጅም ጊዜ የጥናት ስልት፣ ወላጆችንና መምህራንን ተሳታፊ በማድረግ፣ አጠቃላይ ከአንድ እስከ ስምንት የሚገኙ ተማሪዎችን በማካተት እንዲም በርካታ ናሙና ወስደው ማጥናት ይቻላል የሚሉ የምርምር ጥቆማዎችም ተሰጥተዋል፡፡

## የቁልፍ ቃላት አቻ ትርጉም

1. ተነሳሽነት (Motivation)
2. ውስጣዊ ተነሳሽነት (Intrinsic Motivation)
3. ውጫዊ ተነሳሽነት (Extrinsic Motivation)
4. አንብቦ መረዳት ችሎታ (Reading Comprehension)
5. የማንበብ ብቃት (Reading Performance)
6. የማንበብ ክሂል (Reading Skill)
7. ቤተሰባዊ ዳራ (Family Background)
8. የንባብ መጠን (Reading Amount)
9. የንባብ ምርጫ(Reading Choice)
10. የማንበብ ግለ ግምት (Reading Self- concept)
11. የማንበብ አመለካከት (Reading Attitude)
12. ለማንበብ የሚኖር በራስ መመካት (Reading Self efficacy)
13. የማንበብ ብልሀት (Reading Strategy)
14. የስነምህዳራዊ ስርዓት ንድፈሀሳብ (Ecological systems theory)

# ምዕራፍ አንድ

# መግቢያ

## 1.1. የጥናቱ ዳራ

በመማር ማስተማር ሂደት እንዲዳብሩ ትኩረት ከሚሰጣቸው አዕምሯዊና ተግባራዊ ክሂሎች መካከል የማንበብ ክሂል አንዱ ሆኖ ይጠቀሳል፡፡ ማንበብ ከተለያዩ ጽሁፎች መልዕክት መቀበያ መሰረታዊ ክሂል ነው (Knoll, 2000; Janan, 2011; Schiefele, Schaffner, Möller, & Wigfield, 2012; Anmarkrud & Braten, 2010 and Baker & Wigfield, 1999)፡፡ እንዲሁም ቀደም ሲል በማንበብ የተገኘን ነባር እውቀት በተገቢ መንገድ እንዴትና የት መጠቀም እንደሚቻል የመለየትና የመጠቀም ችሎታም ጭምር እንደሆነ Knoll (2000) ያስረዳሉ፡፡ አብዛኞቹ ማህበረሰቦች አጠቃላይ ለትምህርት ስኬት ማንበብ ወሳኝ እንደሆነ ያምናሉ (Janan, 2011)፡፡ ማንበብ ከትምህርትና ከማመዛዘን ብቃት ጋር ቀጥተኛ ተዛምዶ ስላለው ለማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና አዕምሯዊ እድገት ከፍተኛ ጠቀሜታ ይኖረዋል ተብሎ ይገመታል፡፡

ተማሪዎች በትምህርታቸው ውጤታማ ለመሆን፣ አካባቢያቸውን ለመረዳትና ለማህበረሰቡ የሚጠቅም ስራ ለመስራት ጠንካራ የማንበብ ችሎታ ሊኖራቸው ይገባል፡፡ ራሳቸውን፣ ቤተሰባቸውንና ሀገራቸውን ለመረዳት የማንበብ ችሎታ ያስፈልጋቸዋል (Guthrie, Hoa, Wigfield, Tonks, Humenic & Littles, 2007) ፡፡

ማንበብ በቋንቋ፣ በስነልቦና እንዲሁም በስነ ትምህርት የትምህርት ዘርፎች በሰፊው ምርምር እየተደረገበት የሚገኝ የጥናት መስክና በመጀመሪያዎቹ የትምህርት ደረጃዎች ቀዳሚ ትኩረት የሚሰጠው ክሂል ነው (Guthrie & Wigfield, 1999; Janan, 2011; Schiefele et al., 2012; Anmarkrud & Braten, 2010 and Baker& Wigfield, 1999)፡፡Kamil, Afflerbach, Pearson & Moje (2011) በማንበብ ዙሪያ የተሰሩ ምርምሮችን በመሰብሰብ በየአስር አመቱ በመጽሀፍ መልክ የሚያሳትሙ አርታኢዎች ሲሆኑ የማንበብ የምርምር ታሪካዊ ዳራ በእያንዳንዱ ዘመን የነበረው የትኩረት አቅጣጫ የተለያየ መሆኑን ይጠቅሳሉ፡፡ በእያንዳንዱ ክፍለ ዘመን የነበሩት ፍልስፍናዎች፣ ንድፈ ሀሳቦችና የመማር

ማስተማር መመሪያዎች በማንበብ የምርምር አይነትና የትኩረት አቅጣጫ የራሳቸውን አስተዋጽዖ አበርክተዋል (Kamil et al., 2011)፡፡

ከማንበብ ጋር ተያይዘው የሚነሱና በማንበብ ዙሪያ በሚሰሩ ምርምሮች ከፍተኛ ተጽዕኖ የሚፈጥሩ ንድፈ ሀሳቦች በዋናነት በሶስት ይከፈላሉ፡፡ እነሱም ባህርያውያን፣ አዕምሯውያን (የስኬማ ንድፈሀሳብ /Schema Theory) ና ቅድመ እውቀት ግንባታውያን (የማህበራዊ እድገት ንድፈ ሀሳብ /Social Development Theory/) ናቸው፡፡ የመጀመሪያውና ጥንታዊ ተብሎ የሚገለጸው የባህርያውያን ንድፈ ሀሳብ ነው፡፡ የባህርያውያን ንድፈ ሀሳብ የላይ ታችና የታች ላይ የንባብ ሞዴል መሰረት ነው፡፡ በዚህ ንድፈ ሀሳብ እይታ ማንበብ ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ ወይም ከታች ወደ ላይ እያደገ የሚሄድ ክሂል ነው፡፡ በሌላ አባባል ከድምጽ ተነስቶ ወደ ትርጉም የሚያድግ ነው፡፡ መማርም አንድ ተማሪ ለቀረበለት ማነቃቂያ ምላሽ የሚሰጥበት ሂደት እንደሆነ በዚህ ንድፈ ሀሳብ ይታመንበታል፡፡

በ1970ዎቹ አካባቢ በነበረው የማንበብ ትምህርት ሂደትና እድገት ጎልቶ የወጣውና በሌሎች ንድፈ ሀሳቦች ላይ ተፅእኖ ማሳደር የቻለው የአዕምሯውያን ንድፈ ሀሳብ ሌላው መገለጫ የሆነው የስኬማ ንድፍ ሀሳብ (Schema Theory) ነው፡፡ ንድፈ ሀሳቡ በአጠቃላይ የሰው ልጅ በተለያየ መንገድ ማንበብን ጨምሮ ያገኘውን እውቀት እንዴት በትውስታ ክፍል (Memory) እንደሚያደራጅና እንደሚገነባ የሚያሳይ ንድፈ ሀሳብ ነው፡፡ የስኬማ ንድፍ ሀሳብ የሚባለው የጽሁፉን አንባቢ የቋንቋና የመረጃ ሂደት አከናዋኝ፣ የእውቀት ክምችት ያለበት፣ ንቁና  የትርጉም መሥራች አድርጎ የሚመለከት ነው፡፡ Pearson (2009) እንደገለጹት የስኬማ ንድፍሀሳብ (Schema Theory) የትውስታ ክፍልን እንደ አንድ የአዕምሮ ክፍል የሚያይ ሲሆን የሰው ልጅ የህይወት ገጠመኝ ፣ ልምድና ሀሳብ የሚጠራቀሙትና ተገቢውን ጊዜ ጠብቀው ተግባር ላይ የሚውሉት በዚህ ክፍል ነው የሚል ሀሳብ የያዘ ነው፡፡ ይህ ንድፈ ሀሳብ በጊዜው ከፍተኛ ተቀባይነት ስለነበረው በአብዛኛው የአለም ክፍል አንሰራርቶ ሰፊ አገለግሎት ይሰጥ ነበር፡፡ በአጠቃላይ የመማር ማስተማር ሂደት በዝርዝር ሲታይ ደግሞ በማንበብ ዙሪያ በሚሰሩ ምርምሮች የራሱን አስተዋጽዖም አበርክቷል፡፡

Sheridan (1981) እንደሚያብራሩት ተማሪዎች በአካባቢያቸው ስላለው አለም ያላቸውን ነባር ዕውቀት በላይ ታች የንባብ ሂደት የመጠቀም ሁኔታ ስኬማ ይባላል፡፡ እንደ ስኬማ አገላለጽ ጽሁፉ ብቻውን በራሱ ትርጉም የለውም፡፡ ትርጉም የሚኖረው አንባቢው የራሱን ልምድ፣ ስሜትና የባህል እውቀት በመጠቀም መረዳት ሲችል ነው፡፡ በዚህ መልኩ ከተረዳ ደግሞ ስኬማ ይባላል፡፡ እንደ ስኬማ ንድፈ ሀሳብ ጽሁፍን አንብቦ የመረዳት ሂደት በጽሁፉና በአንባቢው ነባር እውቀት መካከል በሚደረግ ንቁ ተሳትፎ የሚፈጠር ነው፡፡

በማንበብ ሂደት አገልግሎት ላይ የሚውሉ ሶስት የስኬማ አይነቶች አሉ (Khalaji & Vafaeeseresht, 2012)፡፡ እነሱም የይዘት ስኬማ፣ መደበኛ ስኬማና ስነልሳናዊ ስኬማ ናቸው፡፡ የመጀመሪያው የይዘት የሚባለው ስኬማ አንባቢዎች በጽሁፍ ያለውን ክስተትና ድርጊት በህይወታቸው ካጋጠማቸው ተመሳሳይ ክስተትና ድርጊት ጋር እንዲሁም ከራሳቸው ባህል ጋር እያነጻጸሩ የሚገነዘቡበት ነው፡፡ መደበኛ የሚባለው ሁለተኛው የስኬማ አይነት አንባቢዎች ማንበብ ከመጀመራቸው በፊት ጽሁፉ ስለቀረበበት ቅርጽና ባህርይ የሚረዱበት የስኬማ አይነት ነው፡፡ ለምሳሌ ጋዜጣ ከደብዳቤ የተለየ ስለሆነ ጋዜጣ ለማንበብ የተዘጋጀ ሰው ምን ሊገጥመው እንደሚችል የሚገምትበት ነው፡፡ በአጠቃላይ አንባቢዎች ቅርጽን በማየት በጽሁፉ ሊያጋጥማቸው ስለሚችለው መዋቅር፣ ቃላት፣ ሰዋሰውና የጽሁፉ የመደበኛነት ደረጃ አስቀድመው የሚዘጋጁበት ስኬማ መደበኛ ስኬማ ነው፡፡ የመጨረሻው የስኬማ አይነት ስነልሳናዊ ስኬማ ሲሆን አንባቢዎች የቃላትን አነባበብ የሚገነዘቡበትና እርስ በርስ ተቀናጅተው እንዴት አረፍተ ነገር እንደሚመሰርቱ የሚረዱበት የስኬማ አይነት ነው (Khalaji & Vafaeeseresht,2012) ፡፡

ከ1980ቹ መካከለኛው ዘመን ጀምሮ የማህበረ ባህላዊ ቅድመ ግንባታውያን ንድፈ ሀሳብ እየተስፋፋ መጣ፡፡ በማህበረ ባህላዊ ቅድመ ግንባታውያን ንድፈሀሳብ በዋናነት የሚጠቀሰው የሩሲያዊው የስነልቦና ተመራማሪ Vygotsky የማህበረ ባህላዊ እድገት ንድፈሀሳብ (Socio-cultural Development Theory) ነው፡፡ በማህበረ ባህላዊ እድገት ንድፈ ሃሳብ የማንበብ ትምህርት የመማር ሂደት በማህበራዊ ግንዛቤ ላይ የተመሠረተ ነው የሚለው አመለካከት በሰፊው የተንሰራፋበት ንድፈ ሀሳብ ነው፡፡

ንድፈ ሀሳባዊ መሠረቱ እውቀት በማህበረሰብ ደረጃ ከዚያም በግለሰብ ደረጃ ይከሰታል፣ የሚለውና የማህበረ ባህላዊ እድገት መሰረታዊ ጽንሰ ሃሳብ የሆነው የጥግግ እድገት መጠን (Zone of Proximal Development — ZPD) የንድፈ ሀሳብ አፍላቂዎችንና የተመራማሪዎችን ትኩረት የሳበና ከፍተኛ ተቀባይነት ያገኘበት ወቅት ነው (Doolittle, Hicks, Triplett, Nichols & Young 2006)፡፡ Doolittle et al (2006) እንደሚያብራሩት በማህበራዊ እድገት ንድፈ ሀሳብ መሰረት እውቀትና ትርጉም የሚገኘው ከማህበረሰቡ ንቁ ተሳትፎ ነው፡፡ የተገኙት እውቀቶች አገልግሎታቸው እንዲሁም ጠቀሜታቸው ለማህበረሰቡ ነው፡፡ በሌላ አገላለጽ የእውቀት ምንጩም ማህበረሰቡ ነው ተጠቃሚውም ማህበረሰቡ ነው፡፡

በ1960ቹ አካባቢ የባህሪያውያን ንድፈ ሀሳብ መስፋፋቱ በማንበብ ዙሪያ በሚሰሩ ምርምሮች የታዋቂው BF Skinner ግኝት የሆኑት ማበረታታት፣ ማስለመድና የባህርይ ትንተና የሚሉት ጽንሰ ሀሳቦች በሰፊው አገልግሎት እንዲሰጡ አድርጓል (Gaffney& Anderson, 2000)፡፡ በ1970ቹ የአዕምሯውያን ሳይንስ መስፋፋት ጥናቶች ውስብስብ ወደ ሆነው የጽሁፍ ሂደትና የልዕለ ግንዛቤ ጭብጥ እንዲዘዋወሩ አድርጓል፡፡

ከ1980- 90ቹ የማህበራዊ ቅድመ ግንባታ ንድፈ ሀሳብ መስፋፋት አይነታዊ የምርምር ዘዴ ከመጠናዊና ከሙከራዊ የበለጠ እንዲሰራበት አድርጓል (Gaffney & Anderson, 2000)፡፡ ማንበብን ከቃላት፣ ከቋንቋና ጽሁፍ ጋር አያይዞ መስራቱ እየቀነሰ ከማህበረሰብ፣ ከባህል፣ ከተነሳሽነትና ከፍላጎት ጋር አያይዞ ማጥናት እየጨመረ የሄደበት ጊዜ እንደነበር Gaffney & Anderson (2000) ያስረዳሉ፡፡

እነዚህ ንድፈ ሀሳቦች የራሳቸው የሆነ ጠንካራና ደካማ ጎን ስላላቸው አንዱን ካንዱ ይበልጣል ብሎ ለመደምደም ያስቸግራል፡፡ አንድ አስተማሪ የተማሪዎቹን የአንብቦ መረዳት ችሎታ ለማዳበርና እድገቱን ስኬታማ ለማድረግ ጥሩ መመሪያ ያስፈልገዋል፡፡ በማንበብ ላይ የሚሰራ ተመራማሪም እንዲሁ ምርምሩን የሚያካሂድበት መመሪያ ያስፈልገዋል፡፡ ጥሩ መመሪያ ለመምረጥና ተገቢውን ብልሀት ለመጠቀም ደግሞ ሁሉንም ንድፈ ሀሳቦች መቃኘት እንዲሁም እንደ አማራጭ ማየት ይጠበቅበታል፡፡ በመሆኑም ይህ ምርምር ከሶስቱ የንድፈ ሀሳብ አይነቶች የቅርብ ጊዜና ለጥናቱ የተሻለ

የሆነውን የማህበረ ባህላዊ ቅድመ ግንባታውያን ንድፈ ሀሳብ ይከተላል። በማህበረ ባህላዊ ቅድመ ግንባታውያን ስር ከሚገኙ የተለያዩ ንድፈ ሀሳቦች ውስጥም የቤተሰብና የአካባቢ ተጽዕኖ ከፍተኛ ነው ብሎ የሚያምነው የብሮንፈርነር የስነ ምህዳር ስርዓት ንድፈሀሳብን (Bronferner Ecological system Theory) ይከተላል።

ከ1960 እስከ 1970 ባሉት ጊዜያት የአዕምሯዊያን የስነልቦና ምርምሮችና ለምርምር የሚሰጡት በጀቶች መብዛት በአንብቦ መረዳት ችሎታ ላይ በርካታ ምርምሮች እንዲሰሩ አግዟል። Kamil et al. (2011) እንደሚያስረዱት በአዕምሯዊ ሞዴል ላይ የሚያተኩር ማዕከል በ1975 በኢሊኖይስ ዩኒቨርሲቲ (University of Illinois) መቋቋምና Durkin ከ1978–79 የአንብቦ መረዳት መመሪያ ችግር ላይ በሰፊው መስራታቸው በማንበብ በተለይም የታተሙ ጽሁፎችን አንብቦ መረዳት ላይ በርካታ ምርምሮች እንዲሰሩ አድርጓል። የምርምሮች ትኩረትም የማንበብ መመሪያ ጥራትን ከፍ ማድረግን ግብ አድርገው የተነሱ ናቸው። በ1984 በታተመው ቁጥር አንድ የማንበብ ምርምር መጽሀፍ የተካተቱት ጥናቶች ትኩረታቸው ልዕለ አዕምሮታዊ ግንዛቤ፣ የመረዳት መመሪያ፣ መሳሪያዎችና ቴክኖሎጂ ላይ ነበር። በተከታዮቹ ሶስት አስርት አመታት በምርምሩ ዘዴ፣ ችግርና ትንተና ላይ ከፍተኛ አለመግባባት የነበረ ሲሆን በ1991 በታተመው ቁጥር ሁለት የማንበብ ምርምር መጽሀፍ ላይ ውዝግቡ በዝርዝር ቀርቧል (Kamil et al. 2011)።

Kamil et al. (2011) እንዳብራሩት በቁጥር ሁለት የታተሙት የማንበብ ምርምሮች ማህበራዊና አውዳዊ ጉዳዮችንም አካተዋል። በተጨማሪም የምርምር አይነቱ አይነታዊ ወይንስ መጠናዊ መሆን አለበት? ማንበብ በየትኛው ዘዴ ቢጠና ውጤታማ ይሆናል? የሚለውን ለማረጋገጥ በሁለቱም ዘዴዎች ምርምሮች የተሰሩበትና ክርክር የነበረበት ዘመን ነበር። በስነልሳን ዳራቸው የተለያዩ አንባቢዎችን ትኩረት ውስጥ አስገብቶ ለመጀመሪያ ጊዜ ማጥናት፣ የተለያዩ የጽሁፍ ዘውጎችን በመጠቀም የማንበብ ችሎታን መለካት፣ መምህርን እንደ ተላውጦ ማየት፣ ትምህርት ቤቱ ያለውን ተሳትፎ መቃኘት፣ የጽሁፉን ተነባቢነት ከተማሪዎቹ ችሎታ አንጻር መዳሰስ ሁሉ የተጀመረው በዚሁ ጊዜ እንደሆነ Kamil et al. (2011) ገልጸዋል። በአጠቃላይ ከ1966- 2000 ባሉት ሰላሳ አራት አመታት ከ100,000 በላይ ጥናቶች በአንብቦ መረዳት ችሎታና በችሎታው ላይ ተጽዕኖ

በሚፈጥሩ ተላውጦዎች ዙሪያ ተሰርተዋል፡፡ ጥናቶቹ በእይታቸው፣ በፍልስፍናቸው፣ በስነ ዘዴያቸውና በጥራታቸው እየተሻሻሉ መምጣታቸውን ከላይ የተጠቀሱት አርታዒዎች አስረድተዋል፡፡ የጥናቶቹ ውጤት የአንብቦ መረዳት ችሎታን ሊያሳድጉና ሊያዳበሩ የሚችሉ የተለያዩ ዘዴዎችን ጠቁመዋል፡፡

የማንበብ ምርምር መጽሀፍ ቁጥር ሶስት በ2000፣ ቁጥር አራት ደግሞ በ2011 የታተመ ሲሆን ሁለቱም ቅጾች በይዘት የተለያዩ ጉዳዮችን ይዘዋል፡፡ በቁጥር ሶስት በጣም የተለያዩ አውዶችን ከማንበብ ጋር አያይዘው ማጥናት የጀመሩበት ነው፡፡ የማንበብ ተነሳሽነት ከአንብቦ መረዳት ችሎታ ጋር በማዛመድ ማጥናት የተጀመረውም በዚህ ዘመን ነው፡፡ በዚሁ ዘርፍ (በማንበብ ተነሳሽነት) ከሀያ በላይ ምርምሮችን የሰሩትና በተለያዩ ጆርናሎች ያሳተሙት Guthrie & Wigfield ማንበብን ከተነሳሽነትና ከተሳትፎ ጋር አዛምደው ያጠኑት ጥናት በቁጥር ሶስት መጽሀፍ ላይ የሚገኝ ሲሆን የማንበብ ተነሳሽነት ለአንብቦ መረዳት ወሳኝ መሆኑን የገለጹበት ምርምር ነው፡፡

የማንበብ ምርምር መጽሀፍ አርታዒዎቹ Kamil et al. (2011) በቅኝታቸው እንደገለጹት በአሁኑ ዘመን የምርምሮቹ የትኩረት አቅጣጫ በጣም ጠንካራና አድካሚ የሆኑ የምርምር ዘዴዎችን ማዘጋጀት እንዲሁም በተለያዩ አውዶች፣ በተለያዩ ሰዎችና በልዩ ልዩ ልምምዶች የማንበብን ውጤታማነት መፈተሽ ነው፡፡ Kamil et al. (2011) ያነሱት በቀደሙት ጊዜያት ያልታየው ሌላው ጠቃሚ ነጥብ በማንበብ ሂደትና እድገት መካከል ስላለው ልዩነት ነው፡፡ ማንበብ ፊደላቱን አውቆ በትክክል ማለት መቻሉ ላይ ብቻ የሚቆም ሳይሆን በህይወት ዘመን ሁሉ ከሚያጋጥሙ የተለያዩ የጽሁፍ አይነቶች ጋር ራስን እያግባቡ እውቀትን የማዳበር የማያቋርጥ ሂደት ነው፡፡

በኢትዮጵያ ዘመናዊ ትምህርት የተጀመረበት ዘመን ብዙም ሩቅ የሚባል አይደለም፡፡ ነገር ግን ከጥንት ጀምሮ በቤተ ክርስቲያናትና በመስጊዶች የሀይማኖት ትምህርት ሲሰጥ ቆይቷል፡፡ የባህላዊ ትምህርት የቆየ ታሪክ ቢኖረውም ሀይማኖታዊ ጽሁፎችን ማንበብ ለተወሰኑት ብቻ የተሰጠ ነበር (Aselefech, 2014& Ibrahim, 2012)፡፡ የሀይማኖታዊ ጽሁፎችንም ቢሆን የሚያነቡት የቤተክርስቲያን አገልጋዮች እና/ወይም ሸኾች ብቻ

ነበሩ፡፡ እንዲያውም በኦርቶዶክስ የክርስትና እምነት ተከታዮች የሚያነብ ሰው ከድግምት ጋር ስለሚያያዝ አንባቢ ሰው ከመጥፎ ድርጊት ጋር ተያይዞ በማህበረሰቡ ይፈራ ነበር፡፡

በኢትዮጵያ ዘመናዊ (የምዕራባውያን) ትምህርት አንድ ተብሎ መሰጠት የተጀመረው በ1908 ዓ.ም በአጼ ሚኒሊክ ዘመነ መንግስት ነበር፡፡ ዘመናዊ ትምህርት እየተስፋፋ ሲሄድም በተማሩ ሰዎችና በመኳንንቱ ማንበብ እየተለመደ በመምጣቱ የሚያነብ ሰውም አዋቂና ዘመናዊ ተደርጎ ይወሰድ ነበር፤ በተለይም በአጼ ሀይለስላሴ ዘመነ መንግስት፡፡ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርትም ከመጀመሪያ ደረጃ ጀምሮ እስከ ዩኒቨርሲቲ ድረስ መሰጠት የተጀመረውም በዚህ ዘመን ነበር፡፡ የአማርኛ ትምህርት ከአንደኛ ደረጃ እስከ ዩኒቨርሲቲ ድረስ መሰጠቱ በክሂሎች ላይ የተለያዩ የማስተማሪያ መሳሪያዎች (የመማሪያ መጻህፍት) እንዲዘጋጅ አስተዋጽኦ አድርጓል (ጌታቸው፣ 1986)፡፡

ከዘመናዊ ትምህርት መስፋፋት በኋላ የማንበብ ክሂልን ከእንግሊዘኛና ከአማርኛ ቋንቋ ጋር በማዛመድ ጥናት መደረግ ተጀመረ፡፡ በሀይስላሴ ዘመነ መንግስት እንግሊዘኛ የትምህርት መስጫ ቋንቋነቱን ከፈረንሳይኛ ተቀብሎ ሰፊ አገልግሎት ይሰጥ ስለነበርና ከእንግሊዘኛ ቋንቋ ችሎታ ደግሞ በጣም ወሳኝ የነበረው ክሂል ማንበብ ስለነበረ በማንበብ ክሂል ላይ ምርምር ይደረግበት ነበር (Abebe, 2012)፡፡ ምንም እንኳን በደርግ ዘመን እንግሊዘኛ እየተዳከመ ቢሄድም ለሀገርኛ ቋንቋዎች የተሰጠው ትኩረት መቀጠሉን ግን Abebe (2012) ያስረዳሉ፡፡

ከአማርኛ ቋንቋ የማንበብ ክሂል ጋር በተያያዘ የተሰሩት ምርምሮች በአብዛኛው የጽሁፉ ተነባቢነት የዳሰሱ (ጌታቸው 1986)ና የሺጥላ (2000)፣ ከማስተማሪያ ዘዴ ጋር ተያይዘው የተሰሩ የኔሰው (1990)፣ እንግዳ (1990)፣ ግሩም (2003)፣ ዘውዱ (2008)ና እንድሪስ (2009) የክፍል ውስጥ አተገባበርን የፈተሹ ይታያል (2003)ና ይሻሙ (2002) ናቸው፡፡ የአንብቦ መረዳት ችሎታን ከስብዕና፣ ከንባብ ልምድ እንዲሁም የፍጥነት ንባብን ከአካዳሚያዊ ውጤት ጋር በማዛመድ ያጠኑ በድሉ (1988)፣ ታምራት (2003)ና ብርሀን (2003) ይጠቀሳሉ፡፡ ነገር ግን ልክ በአለም ላይ እንደታየው ለውጥ ከዚህ ወደ እዚህ ሄዷል ብሎ የንባብ ምርምር አካሄዱን መደምደም አይቻልም፡፡ ምክንያቱም የአማርኛ ቋንቋ የማንበብ ችሎታን በተመለከተ ምርምር መካሄድ የተጀመረው በአሁኑ

ክፍለ ዘመን በመሆኑና የተሰሩትም ቁጥራቸው ዝቅተኛ ስለሆነ የምርምር አቅጣጫውን መወሰን ያስቸግራል፡፡

ንባብ በበርካታ ነገሮች ተጽዕኖ የሚደርስበት ክሂል ሲሆን ተጽዕኗቸው አሉታዊም አወንታዊም ሊሆን ይችላል፡፡ እነዚህ ተጽዕኖ ፈጣሪ ነገሮች የአንባቢው ባህርይ፣ የጽሁፉ አጠቃላይ ሁኔታና የአቀራረቡ ብልሀት ተብለው በሶስት አበይት ክፍሎች እንደሚከፈሉ Janan (2011) ያስረዳሉ፡፡ በሌላ አባባል አንብቦ የመረዳት ችሎታ በአንባቢው ችሎታና ማንነት፣ በአንባቢው ማህበራዊና ቤተሰባዊ ዳራ፣ በትምህርት ቤቱ ሁኔታ፣ በአስተማሪውና ከቀረበው ጽሁፍ በሚያገኘው መረጃ አይነት፣ ባህርይና ግልጽነት ተጽዕኖ ሊደርስበት ይችላል፡፡ እነዚህ ተጽዕኖ ፈጣሪ ነገሮች እንደሚከተለው በስዕል ቀርበዋል፡፡




**ስዕል አንድ፡- በአንብቦ መረዳት ችሎታ ላይ ተጽዕኖ ፈጣሪ ነገሮች**

ከስዕሉ እንደሚታየው ከተማሪው ጋር ተያይዘው ከሚነሱ ተጽዕኖ አድራሽ ነገሮች አንዱ የቤተሰብ ዳራ ነው፡፡ Khayyer (1994) & Baker et al. (1997) እንደሚያስረዱት የቤተሰብ ዳራ አንድ ሰው ከተጸነሰበት ጊዜ ጀምሮ እስከ ህይወቱ ፍጻሜ ድረስ የሚኖረውን

የቤተሰብ ኢኮኖሚያዊ፣ ትምህርታዊ፣ ማህበራዊና ስሜታዊ ሁኔታዎችን እንዲሁም የአካባቢ ሁኔታ ያካትታል፡፡

ማንኛውም ሰው ከሌሎች ሰዎች ተነጥሎ ብቻውን መኖር አይችልም፡፡ በማህበራዊ መዋቅር ውስጥ መኖር የግድ ነው፡፡ በማህበራዊ መዋቅር ውስጥ ተካቶ መኖሩ ደግሞ በአዕምሯዊና ስሜታዊ እድገቱ ላይ ተጽዕኖ እንዲደርስበት ያስገድደዋል፡፡ ተጽዕኖ አድራሽ ተብለው ከማህበራዊ መዋቅር (ከአካባቢ) ጋር በተያያዘ የሚጠቀሱ በርካታ ተላውጦዎች ውስጥ ቤተሰባዊ ዳራ በዋናነት ይጠቀሳል (Khayyer, 1994)፡፡ የቤተሰብ ዳራ የአንድ ሰው ቤተሰብ የሚኖረው የትምህርት፣ የኢኮኖሚ፣ የባህል፣ የማህበራዊ የልምድና የማህበራዊ ደረጃን ይመለከታል፡፡

እንደ አጠቃላይ ሲታይ የቤተሰብ ዳራ የሚለው እምቅ ሀረግ የቤተሰብ ትምህርትን፣ የቤተሰብ እውቀትን፣ የቤተሰብ ባህልን ገቢንና የቤተሰብ መዋቅርን ቢመለከትም ትኩረቱና ውስጣዊ መዋቅሩ ግን እንደ ምርምሮች የተለያየ ነው (Brese & Mirazchiyski, 2010)፡፡ ለምሳሌ፡- የትምህርታዊ ጽሁፎችን የማንበብ ችሎታ እድገት ጥናት (Progress in Reading Literacy Study (PIRLS)ና የአለም አቀፍ ምዘና መርሀ ግብር (Programme for International Student Assessment (PISA) ለትምህርት የሚጠቅሙና በቤት ውስጥ በሚገኙ (መጽሀፍት፣ ኮሚፒውተር፣ ካልኩሌተር፣ ዲክሽነሪ በመሳሰሉ) የተለያዩ የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች ላይ አተኩሮ የሚሰራ ሲሆን የሂሳብና ሳይንስ ልምድ ጥናት Trends in Mathematics and Science Study (TIMSS) የቤተሰብ ገቢን፣ የማህበራዊ ደረጃና የትምህርት ደረጃን በቤት ውስጥ ካሉ ግብዓቶች ጋር ጨምሮ የሚያጠና ነው (Campbell, Kelly, Mullis,  Martin & Sainsbury, 2001)፡፡ የትምህርታዊ ጽሁፎችን የማንበብ ችሎታ እድገት ጥናት በሚል ርዕስ የሚሰራው ምርምር ከ2001 ጀምሮ እስከ 2016 ድረስ በአምስት አመት አንዴ የሚካሄድ የረጅም ጊዜ ጥናት ነው፡፡ በዚህ ጥናት የቤተሰብ ዳራ ከኦኮኖሚና በቤት ውስጥ ከሚገኙት የተለያዩ መርጃ መሳሪያዎች ጋር አያይዞ ያጠናና የሚያጠና ሲሆን በጊዜ ሂደት የመርጃ መሳሪያዎች ውስጥ ኮሚፒውተር፣ ሞባይል የመሳሰሉ የኢንተርኔት መገልገያ እቃዎችን ጭምር በጥናቱ ያካትታል፡፡

በተመሳሳይ መልኩ Lindo (2007) እንደሚያብራሩት በቤተሰብ ዳራ ስር የቤተሰብ ማህበረ ኢኮኖሚያዊ ደረጃ፣ የቤተሰብ አባላት ቁጥር፣ የትምህርት ደረጃ፣ የእናት አባት የስራ ሁኔታና ሌሎችም ይጠቀሳሉ፡፡ የቤተሰብ ዳራ በተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ችሎታ ላይ ተጽዕኖ እንደሚፈጥርና ተጽዕኖውም ከማህበረሰብ ማህበረሰብ፣ ከቤተሰብ ቤተሰብ እንዲሁም ከባህል ባህል የተለያየ እንደሚሆን የተለያዩ ጥናቶች ውጤት ያሳያል (Sirin, 2005, Oakes & Rossi, 2003)፡፡

ከትምህርት ጥራት ጋር ተያይዘው የሚሰሩ በርካታ ጥናቶች እንደሚያሳዩት የተማሪዎች ቤተሰባዊ ዳራ ከአጠቃላይ የትምህርት ውጤት ጋር ተዛምዶ አለው (Brese & Mirazchiyski, 2010)፡፡ አንዳንዴም ተዛምዶው ከፍተኛ ይሆናል፡፡ በመሆኑም የቤተሰብ ዳራ በተለያዩ የትምህርት መስኮች በሚገኙ ተመራማሪዎች ትኩረት ተሰጥቶት የተጽዕኖው መጠን ይጠናል፡፡ ከነዚህ መካከል "የትምህርት እድል እኩልነት" በሚል ርዕስ በኮልማንና ጓደኞቹ የተደረገው ምርምር በግንባር ቀደምትነቱና በሰፊነቱ ይጠቀሳል (Brese & Mirazchiyski, 2010)፡፡ Brese & Mirazchiyski, (2010) እንደሚያስረዱት በትምህርት ስታትስቲክስ ብሄራዊ ካውንስል ከፍተኛ ድጋፍ ተደርጎለት የተሰራው የኮልማንና ጓደኞቹ ጥናት ውጤት እስካሁንም ድረስ የማህበራዊ ሳይንስ ተመራማሪዎች ትኩረት እንደሳበ ነው፡፡ በምርምሩ ሂደትና ውጤት ምክንያትም ለሌሎች ጥናቶች መሰራትም መነሻ ምክንያት ሆኗል፡፡

የትምህርት ስታትስቲክስ ብሄራዊ ካውንስል ዋነኛ አላማ የቤተሰብ ዳራ የሚመዝኑ መለኪያዎችን መቃኘት ለትምህርት ግብዓት ከሚያገለግሉ መመዘኛዎች ጋር ያለውን ተዛምዶ መመርመርና የመረጃ አሰባበሰብ ሂደቱን ማፋጠን ነው፡፡ የቤተሰብ ዳራ ከትምህርት ውጤት ጋር ያለውን ተዛምዶ ዘርዘር አድርገው ለማየት ከማንበብ ጋር ብቻ አያይዘው ካጠኑ ተመራማሪዎች መካከለም Levy, Gong, Hessels, Evans, & Jared (2006)ና Hiebert & Kamil (2005) ይጠቀሳሉ፡፡ እነዚህ ተመራማሪዎች እንደገለጹት የተማሪዎች ቤተሰባዊ ዳራ በአንብቦ መረዳት ችሎታ ላይ ተጽዕኖ ያሳድራል ወይም ከአንብቦ መረዳት ችሎታ ጋር አሉታዊና አወንታዊ ተዛምዶ አሳይቷል፡፡

ከተማሪው ጋር በተገናኘ ከሚነሱት ተጽዕኖ ፈጣሪ ነገሮች በተጨማሪነት የሚጠቀሰው ተላውጦ ተነሳሽነት ነው። ተነሳሽነት (motivation) የሚለው ቃል ለመንቀሳቀስ (to Move) የሚል ትርጉም ካለው የላቲን ግስ ከ 'Movere' የተገኘ ሲሆን በአንድ እንቅስቃሴ ላይ የሰዎችን ምርጫ፣ ስሜት፣ ጥረት የሚያሳይ በተለያዩ ግፊቶች የሚገኝና አንድ ነገር እንዲሰራ የሚያደርግ ባህርይ ነው (Dornyei, 2001)። በሌላ አባባል ሰዎች አንድን ነገር ለመስራት ለምን እንደሚወስኑ፣ ለምን ያህል ጊዜ ድርጊቱን እንደሚቀጥሉበትና ለማግኘት ምን ያክል እንደሚጥሩ የሚወስን የሰው ልጅ ባህርይ ነው። ተነሳሽነት የመማር አላማን ለማሳካት የሚደረግ ውስጣዊ ግፊት እና ስለሚማሩት ቋንቋ ሊኖር የሚችል አዎንታዊ አመለካከት ነው (Gardener, 2003)።

መማርን ከተነሳሽነት ነጥሎ ለማየት መሞከር ተገቢ እንዳልሆነ በርካታ ምሁራን ያስረዳሉ። ምክንያቱም ተነሳሽነትና ውጤት የማይነጣጠሉ ነገሮች ናቸው። Dornyei (2001) እንደሚያስረዱት ጥሩ የመማር ተነሳሽነት ካለ ጥሩ ውጤት ይመጣል። ጥሩ ውጤት ማምጣት ደግሞ የበለጠ ተነሳሽነትን ይጨምራል። በተቃራኒው አሉታዊ ተነሳሽነት መኖር ዝቅተኛ ውጤት ያስከትላል የውጤት ማነስ ደግሞ ተነሳሽነትን ያዳክማል። ስለዚህ መማርና ተነሳሽነት እርስ በርስ የተያያዙና ተከታታይነት ያላቸው ናቸው።

እንደ Gardener (2003) ማብራሪያ የመማር ማስተማር ሂደቱን ውጤታማ ለማድረግ የመምህራንና የተማሪዎች ተነሳሽነት ወሳኝ ነው። ተማሪዎች ለመማር፣ ተግባራቱን በአግባቡ ለማከናወን፣ የግል ፍላጎታቸውንና ምርጫቸውን ለማስፈጸም ተነሳሽነት ወሳኝ ነው። ተነሳሽነት ወደ ግብ የሚያደርስ ባህሪ በመሆኑ ተነሳሽነት ያለው ሰው ሀይሉንና ያለውን አቅም በስፋት እንዲጠቀም ያደርጋል። ተነሳሽነት ያለው ተማሪ አንድን ተግባር በንቃት ይከታተላል። ለመማር ያስቀመጠው ግብ ስለሚኖረውም አጠቃላይ ግንዛቤው ከጊዜ ወደ ጊዜ እየሰፋ ይሄዳል። ፍላጎታቸውም ከፍተኛ ስለሚሆን በስራቸው ውጤታማ ይሆናሉ። ስለሆነም ተነሳሽነት ለቋንቋ ትምህርትም ዋናው መሰረታዊ ጉዳይ ነው (Dornyei, 2001)።

ተማሪዎች ቋንቋን በተነሳሽነት ከተማሩ ባህሉን በቀላሉ መረዳት ይችላሉ፡፡ ምክንያቱም ቋንቋና ባህል የማይነጣጠሉ በመሆናቸው ተማሪው ለቋንቋው ያለው ፍላጎት ለባህሉም እንዲኖር ያደርጋል፡፡ በተመሳሳይ ለባህል ያለው ፍላጎትም ለቋንቋው መማር ተነሳሽነት መፈጠር ሚና አለው (Gardener, 1985)፡፡ ቋንቋ ለማህበረሰቡ ተገቢውን ጥቅም እንዲሰጥ በክሂሎቹና ክሂሎቹን ተጽዕኖ በሚፈጥሩባቸው ነገሮች ዙሪያ ምርምር ማድረግ አስፈላጊ ነው፡፡ በጥናት የተደገፈ የመማር ማስተማር ሂደት የተማሪዎችን የማንበብ ተነሳሽነት ያሳድጋል፡፡ የማንበብ ተነሳሽነት ማደግ ደግሞ የአንብቦ መረዳት ችሎታን ያዳብራል፡፡ የቋንቋ መማር ማስተማር ሂደት ትኩረት ከሚሰጣቸው ጉዳዮች ውስጥ የማንበብ ክሂል አንዱ ነው፡፡ ለቋንቋ ትምህርት ተነሳሽነት ወሳኝ እንደሆነው ሁሉ አንብቦ ለመረዳትም የማንበብ ተነሳሽነት ወሳኝ ነው፡፡

የማንበብ ተነሳሽነት አንድ ግለሰብ በማንበብ ተግባራት ለመሳተፍ ያለውን ዝግጁነትና ፍላጎት ያትታል (Schiefele et al., 2012)፡፡ ተነሳሽነት በመማርና በትምህርት ውጤት ላይ ያለው ተጽዕኖ የስነትምህርታዊ፣ የስነልቦናና የቋንቋ ባለሙያዎች የምርምር ትኩረት ሆኖ ቆይቷል፤ አሁንም ድረስ ምርምር እየተደረገበት የሚገኝ የጥናት መስክ ነው (Schiefele et al,. 2012)፡፡ የአብዛኞቹ የምርምር ውጤቶች እንደሚያሳዩት ተነሳሽነት በአጠቃላይ የማንበብ ብቃት ላይ ተጽዕኖ ይኖረዋል፤ እንዲሁም ተነሳሽነት የማንበብ ብቃትን በዋናነት የሚተነብይ ተላውጦ ሆኖ ተገኝቷል (Wigfield & Guthrie, 2008; Retelsdorf, Koller & Moller, 2011 and Taboada et al., 2009)፡፡

የማንበብ ተነሳሽነት ዝርዝር ተላውጦዎች ከአንብቦ መረዳት ችሎታ ጋር ያላቸውን ተዛምዶ በተመለከተ የተለያዩ ምርምሮች ተካሂደው የተለያዩ ውጤቶች ታይተዋል፡፡ ውጫዊ ተነሳሽነት ያላቸውና ውስጣዊ ተነሳሽነት ያላቸው ተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ችሎታቸው ጋር ያለው ተዛምዶ ልዩነት እንዳለው አንዳንድ ጥናቶች ያሳያሉ (Schiefele et al, 2012):: የተዛምዶው መኖርና አለመኖር እንዲሁም የጉልህነት ደረጃ በጾታ፣ በትምህርት ደረጃ በጽሁፉ አይነት የተለያየ ሊሆን እንደሚችል (Guthrie et al (2007) ይገልጻሉ፡፡ ይህ ጥናትም የቤተሰብ ዳራ የአንብቦ መረዳት ችሎታን የመተንበይ ድርሻውን በመመርመር ላይ ያተኮረ ነው፡፡

## 1.2. የጥናቱ አነሳሽ ችግር

በአሁኑ ዘመን ማንበብ ለማንኛውም የሰው ልጅ የዕለት ከዕለት እንቅስቃሴ ወሳኝ ክሂል እንደሆነ እሙን ነው፡፡ Alderson (2003) እንደገለጹት ማንበብ የህይወት መሰረት ነው፡፡ ማንኛውም ሰው ምግብ ለማዘጋጀት የሚያስተምሩ መጻህፍትን ለማንበብ፣ የትራፊክ ምልክቶችን ለመለየት፣ የጉዞ አቅጣጫ ጠቋሚዎችን ለመረዳት እንዲሁም ቀላል የሚባሉ ስራዎችን ሁሉ ለመስራት የማንበብ ችሎታ ያስፈልገዋል፡፡ በተለይ ተማሪዎች ምርምር ለማዘጋጀት፣ በኮሚፒዩተር ለመጠቀም፣ በትምህርታቸው ውጤታማ ለመሆን፣ ስራ ለመፈለግም ሆነ ለመቀጠር፣ በስራው ላይ ስኬታማ ለመሆን ማንበብ ይጠበቅባቸዋል፡፡ Campbell, et al (2001) እንደሚያስረዱት የማንበብ ክሂል ለፈጠራና ለግላዊ እድገት ጠቀሜታ ስላለው በመጀመሪያዎቹ የትምህርት ደረጃዎች ከማንኛውም ክሂል በበለጠ ትኩረት የሚፈልግ ነው፡፡ እንዲሁም ታዳጊ ህጻናት በማህበረሰባቸው ውስጥ ወይም በሰፊ ህብረተሰብ ውስጥ የመሳተፍ ችሎታቸውን እንዲያሳድጉ ያደርጋል ዝግጁነታውንም ይጨምራል፡፡

የማንበብ ክሂል በራስ ተነሳሽነት ሲካሄድ ደግሞ የበለጠ ውጤታማ እንደሚያደርግ Guthrie et al. (2007) ያስረዳሉ፡፡ ለዕለት ከዕለት ቀላልና ከባድ እንቅስቃሴዎች ሁሉ እውቀት ያስፈልጋል፡፡ እውቀት ለማግኘት ዋናው መንገድ ደግሞ ማንበብ ሲሆን ለማንበብ የማንበብ ተነሳሽነት ያስፈልጋል፡፡ የማንበብ ተነሳሽነትንና የአንብቦ መረዳት ችሎታን ለማዳበርና ለማጠናከር በዙሪያው ያሉትን የቤተሰብ ዳራ የመሳሰሉ ተላውጦዎች ተጽዕኖ ምን ያህል እንደሆነ ማወቅ ተገቢ ነው፡፡

የቤተሰብ ዳራን ከአጠቃላይ የትምህርት ውጤትና ብቃት ጋር በማዛመድ ማጥናት ከተጀመረ በርካታ አመታትን አስቆጥሯል፡፡ በዚህ ረገድ የኮልማንና ጓደኞቹ ጥናት በዋናነት ይጠቀሳል፡፡ ከዛም በኋላ በዝርዝር ከአንብቦ መረዳት ችሎታ ጋር፣ ከሂሳብ ትምህርት ጋርና ከሳይንስ ጋር በማቀናጀት አለም አቀፍ ምርምሮች ሲካሄዱ ቆይተዋል፤ እየተሰሩም ይገኛሉ፡፡ ከነዚህም ውስጥ የትምህርታዊ ጽሁፎችን የማንበብ ችሎታ እድገት ጥናት (Progress in Reading Literacy Study (PIRLS) 2001፣ 2006፣ 2011ና 2016፣ የአለም አቀፍ ምዘና መርሀ ግብር (Programme for International Student

Assessment (PISA)2006 የሂሳብና ሳይንስ ልምድ ጥናት Trends in Mathematics and Science Study (TIMSS) 2006፣ 2011ና 2016 ይጠቀሳሉ፡፡ የቤተሰብ ዳራን ከአንብቦ መረዳት ጋር በማዛመድ እንዲሁም የመተንበይ ድርሻው ምን ያህል እንደሆነ ለማወቅ የተሰሩ ምርምሮችም አሉ፡፡ እነሱም Sirin (2005), Oakes & Rossi (2003), Levy et al (2006),Hiebert & Kamil (2005) Khayyer (1994)ና Lindo (2007) ናቸው፡፡

PIRLS በዋናነት የተማሪዎችን የአንብቦ መረዳት ችሎታ ለመለካት የሚያስችል መሳሪያ የሚያዘጋጅና በረጅም ጊዜ ጥናት የሚለካ ነው (Mullis, Martin & Sainsbury, 2015)፡፡ Mullis et al (2015) እንደገለጹት የትምህርታዊ ጽሁፎችን የማንበብ ችሎታ እድገት ጥናት የተጀመረው በ2001 ሲሆን በየአምስት አመቱ ሪፖርት የሚደረግበት ሰፊና ተከታታይ አለም አቀፍ ምርምር ነው፡፡ ዋና አላማው የአንብቦ መረዳት ችሎታን ማዳበር ሲሆን በሁለት አበይት አላማዎች ከፍሎ ያያል፡፡ አንደኛው ትምህርታዊ ጽሁፎችን አንብቦ መረዳት ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ መረጃን ለማግኘትና ለመጠቀም የሚያስችል ችሎታ ማስገኘት ነው፡፡

የ PIRLS ጥናት በርካታ ተላውጦዎችን የዳሰሰ ሲሆን መረጃ የሰበሰበው ከተማሪዎች፣ ከመምህራን፣ ከትምህርት ቤቱና ከስርዓተ ትምህርት ቀራጮች ነው፡፡ ለተማሪዎች ከሚበተነው መጠይቅ ውስጥም የቤተሰብ ዳራን የሚለካ መጠይቅ ተዘጋጅቶ ይቀርባል፡፡ የቤተሰብ ዳራን የሚለካው የጽሁፍ መጠይቅ በውስጡ በቤት ውስጥ የሚጠቀሙበት ቋንቋ፣ በቤት ውስጥ የሚገኙት መጽሀፍት፣ ለመማር የሚረዱና በቤት ውስጥ የሚገኙ ቁሳቁሶችን ያካተተ ነው፡፡

ከ2001 እስከ 2016 ባሉት አስራ ስድስት አመታት አራት ሰፋፊ የምርምር ውጤቶች በ2001፣ በ2006፣ በ2011ና በ2016 ይፋ ሲሆኑ የጥናቶቹ ውጤት የሚያሳየው የቤተሰብ ዳራ በአንብቦ መረዳት የሚያደርሰው ተጽዕኖ ወይም አንብቦ መረዳትንና የማንበብ ተነሳሽነትን የመተንበይ ድርሻ እንደ የሀገራቱ የተለያየ መሆኑን ነው (Mullis et al, 2015)፡፡ ከቤተሰብ ዳራ በተጨማሪ የአንብቦ መረዳት ችሎታ በጾታ የሚለያይ መሆኑንና አለመሆኑን ባደረጉት ጥናት በተወሰኑት ሀገራት ሴቶች የተሻለ የአንብቦ

መረዳት ችሎታ ሲኖራቸው በአንዳንድ ሀገራት ደግሞ ወንዶቹ የተሻለ አማካይ ውጤት እንዳሳዩ ውጤታቸው ያሳያል፡፡

የማንበብ ችሎታን ከሚተነብዩት ተላውጦዎች መካከል የቤተሰብ ዳራ አንዱ ሆኖ ቢጠቀስም ከምርምሮቹ መረዳት እንደሚቻለው ግን የመተንበይ ደረጃው ከሀገር ሀገር ከምርምር ምርምር እንዲሁም ከመለኪያ መለኪያ የተለያየ መሆኑን ነው፡፡ የምርምር ውጤቶች የተለያየ መሆን የቤተሰብ ዳራና የአንብቦ መረዳት ችሎታ መለኪያ ፈተናውና መጠይቁ ከጊዜ ጊዜ እየተሻሻለና እየተለወጠ መምጣት እንዲሁም በማንበብ ላይ ተጽዕኖ የሚፈጥሩ ተላውጦዎች በሙሉ አለመካተታቸው ይህ የጥናት ጭብጥ እንደገና መዳሰስ እንዳለበት ያሳያል፡፡

ከዚህ በተጨማሪ የቤተሰብ ዳራ የአንብቦ መረዳት ችሎታንና የማንበብ ተነሳሽነትን የመተንበይ ድርሻውና የአንብቦ መረዳት ችሎታና የማንበብ ተነሳሽነት ተዛምዶ በአሜሪካ (Cox & Guthrie (2001), Guthrie et al. (1996), Guthrie & Wigfield (1999), Guthrie et al. (2007)፣ በጀርመን (Schiefele et al. (2012)፣ በኖርዌይ (Andreassen & Bråten, 2010 Anmarkrud & Braten 2009) ፣ በቻይና (Law, 2009)፣ በዩናይትድ ኪንግደም (Logan et al., 2011)፣ በአውስትራሊያ (Colon et al., 2006) ና በሌሎች ሀገራት የተፈተሸ ቢሆንም በኢትዮጵያ በተለይም በአማርኛ ቋንቋ የአንብቦ መረዳት ችሎታ ለመጠናቱ ግን ከተዳሰሱት ድርሳናት መረጃ አልተገኘም፡፡ ይህም ጥናቱ እንዲካሄድ ከሚያስችሉ ምክንያቶች ውስጥ አንዲጠቀስ ያደርገዋል፡፡

በኢትዮጵያ የአማርኛ የአንብቦ መረዳት ችሎታ ዝቅተኛ እንደሆነ በዘርፉ የተካሄዱ ምርምሮች ውጤት ያሳያል (ጌታቸው 1986፣ ማስተዋል፣ 1989፣ እንግዳ 1992፣ ብርሀን 2003፣ ግሩም 2003፣ ታምራት 2003፣ ዘውዱ 2008፣ እንድሪስ 2009)፡፡ የአንብቦ መረዳት ችሎታ ዝቅተኛ የሆነበት ምክንያት ለማስተማሪያነት የቀረቡት ምንባቦች ተነባቢነት ሊሆን እንደሚችል ጌታቸው (1986) በማብራራት በአስረኛ ክፍል የመማሪያ መጽሀፍ ከሚገኙ ምንባቦች የተወሰኑትን መርጠው በተለያየ ዘዴ በመተንተን የምንባቦችን ጠንካራና ደካማ ጎን አሳይተዋል፡፡ የጌታቸው ጥናት የአንብቦ መረዳት ችሎታን ከሚያደክሙት ተጽዕኖ ፈጣሪ ነገሮች አንዱ የሆነውን ቢዳስስም በተማሪው

ሳይሆን በማስተማሪያ መሳሪያው ላይ ማተኮሩ ጥናቱን ውስን ያደርገዋል፡፡ የየሽጥላ (2000) ጥናትም ዘመኑ የ2000ዓ.ም መሆኑና የክፍል ደረጃውን ወደ ዘጠነኛ ዝቅ ማድረጉ ቢለየውም ግምገማው ከጌታቸው ጥናት ጋር ተቀራራቢ ነው፡፡

የማስተማሪያ ዘዴው ሌላው በአንብቦ መረዳት ላይ ተጽዕኖ ፈጣሪ ተላውጦ እንደሆነ ጠቅሰው ያጠኑት የኔሰው (1990)፣ እንግዳ (1990)፣ ግሩም (2003)፣ ዘውዱ (2008) እና እንድሪስ (2009) ናቸው፡፡ የኔሰው ተራክቧዊ የንባብ ክሂል ማስተማሪያ ሞዴልን፣ እንግዳ የላይ ታች የንባብ ማስተማሪያ ሞዴልንና ግሩም የታች ላይ የንባብ ማስተማሪያ ሞዴልን፣ ዘውዱ ሚና ለዋጭ ዘዴንና እንድሪስ የቴክስት ውቅር ብልሀት ስልጠናን በመጠቀም የአንብቦ መረዳት ችሎታን ለማዳበር ያለውን ውጤታማነትና ተግባራዊነት ፈትሸዋል፡፡ ጥናቶቹ የአንብቦ መረዳት ችሎታ ላይ ማተኮራቸው ከዚህ ጥናት ጋር ቢያመሳስላቸውም በተማሪው ሳይሆን በማስተማሪያ ዘዴው ብቻ ላይ ማተኮራቸው ክፍተት እንዳላቸው ያሳያል፡፡

ሚና ለዋጭ ዘዴ የተማሪዎችን የአንብቦ መረዳት ችሎታና የማንበብ ተነሳሽነት ለማዳበር ያለውን ሚና በሰባተኛ ክፍል ተማሪዎች በማተኮር የፈተሹት ዘውዱ (2008) ናቸው፡፡ ይህን የማስተማሪያ ዘዴ ከአንብቦ መረዳት ችሎታ ባሻገር የማንበብ ተነሳሽነት የማዳበር ሂደቱን መመልከታቸው ተገቢ ቢሆንም ከቤተሰብ ዳራ ጋር አያይዘው የሰሩት ነገር የለም፡፡

በቴክስት ውቅር ብልሀቶች ማንበብን መማር በስድስተኛ ክፍል ተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ችሎታ ላይ ያለውን ቀጥተኛና ኢቀጥተኛ ተጽዕኖ የፈተሹት እንድሪስ (2009) ናቸው፡፡ በጥናቱ ከአንብቦ መረዳት ችሎታ በተጨማሪ የንባብ ትኩረት፣ የንባብ ግለ ብቃትና የማንበብ ተነሳሽነትን ቃኝተዋል፡፡ እንድሪስ (2009) የተለያዩ የማንበብ ክሂሎችን (ትኩረት፣ ግለብቃት፣ ተነሳሽነት) በጥናታቸው ቢያካቱም ትኩረታቸው ሁሉም ንዑሳን ክሂሎች በቴክስት ውቅር ብልሀቶች ያመጡትን ለውጥ እንጅ እርስ በርስ ያላቸውን ተዛምዶ አለማየታቸው ጥናቱ ክፍተት እንዳለው ያሳያል፡፡ በተጨማሪም ሁሉም ያተኮሩት በማስተማሪያ ዘዴውና በብልሀት ስልጠናው ላይ ብቻ ነው፡፡ ተማሪው

ወደ ትምህርት ቤት ይዟቸው የሚመጣው ቤተሰባዊ ጉዳዮችና ከማንነቱ ጋር የተገናኙት ተላውጠዎችን ትኩረት አድርጎ የተሰራ ጥናት የለም።

ከተማሪው ማንነት ጋር ተያይዘው የሚነሱ ተላውጠዎች ያላቸውን ዝምድናና ተጽዕኖ ያጠኑት በድሉ (1988)ና ብርሀን (2003) ናቸው። በድሉ የአንብቦ መረዳት ችሎታ ከተሳታፊነት ጭምትነት የስብዕና አይነት ጋር በማዛመድ የሰሩ ሲሆን ብርሀን ደግሞ የአንብቦ መረዳት ችሎታን ከንባብ ልምድ ጋር በማዛመድ ሰርተዋል። የበድሉ (1988)ና የብርሀን (2003) ጥናት በስብዕናና በማንበብ ልምድ ላይ ብቻ የተገደበ በመሆኑ ይህ ጥናት ያልታዩትንና ወሳኝ የሆኑትን የቤተሰብ ዳራ ተላውጠዎች የሚኖራቸውን ተጽዕኖ የሚዳስስ ይሆናል።

በአማርኛ የአንብቦ መረዳት ችሎታ ላይ የተለያዩ ዘዴዎችን በመጠቀም ሙከራዊ፣ ቃኝና ተዛምዷዊ ምርምሮች ቢካሄዱም በጥናቶቹ እንደ መፍትሄ የተጠቆሙት የማስተማሪያ ዘዴዎችና ሞዴሎች ብቻ ናቸው። ዘዴዎችና ሞዴሎች እንዲሁም የብልሀት ስልጠና መሰጠቱ ብቻ ግን የአንብቦ መረዳት ችሎታን ከፍ የሚያደርጉ አይደሉም። አጥኚዎች እራሳቸው እንደ ጠቆሙት በማንበብ ዙሪያ ሌላ ተጨማሪ ምርምር ማካሄድ አስፈላጊ ነው። ይህ ጥናትም ሁሉም መጠናት አለበት ብለው ከጠቀሷቸው ጥቁምታዎች ውስጥ ሊመደብ ይችላል።

በተለይም በተማሪዎች የቤተሰብ ዳራ ዙሪያ ምርምር ማድረጉ ለሚደረጉት የተለያዩ ሙከራዊ ጥናቶች መሰረት እንደሚሆን በአጥኚዋ ይታመናል። ምክንያቱም በማንበብ ላይ ተጽዕኖ ከሚፈጥሩት ሶስት አበይት ተላውጠዎች (የአንባቢው ስብዕናና ማንነት፣ የመማር ማስተማር ሁኔታና የጽሁፉ ባህርይ) ከአንባቢው ጋር የተገናኙት የቤተሰቡ ሁኔታ ከአንብቦ መረዳት ችሎታው ጋር ያለውን ተዛምዶ ማየቱ ለሌሎች ችግር ፈቺ ምርምሮች መነሻነት ወሳኝ ስለሆነ ማጥናቱ ተገቢ ነው። ዘውዱ (2008)ና እንድሪስ (2009) የማንበብ ተነሳሽነትን በተመለከተ የሰሩት ስራ ቢኖርም በሁለቱ ተላውጠዎች መካከል ያለውን ተዛምዶ ግን አለማሳየታቸው ጥናቱ መሰራት እንዳለበት ያሳያል።

በኢትዮጵያ በአንብቦ መረዳት ችሎታና በቤት ውስጥ የሚገኙ መጽሀፍት በማዛመድ ከተጠኑት የሚጠቀሰው የ Wainer& Piper (2010) ጥናት በመላው ሀገሪቱ በሚገኙ

ስምንት ክልሎች (አማራ፣ አዲስ አበባ፣ ሀረሬ፣ ትግራይ፣ ኦሮሚያ፣ ደቡብ ህዝቦች፣ ቤኒሻንጉል ጉሙዝና ሶማሊያ) ላይ የተወሰኑ ወረዳዎችን እንደ ናሙና በመወሰድ በመጀመሪያ ደረጃ ተማሪዎች የማንበብ ደረጃን (ፊደል መለየትን)ና አንብቦ መረዳትን ለመዳሰስ የሞከረ ጥናት ነው። የ Wainer& Piper (2010) ጥናት የመጀመሪያ ደረጃ የማንበብ አሰሳ በሚል መነሻነት የትምህርት ሚኒስቴር ከሌሎች አጋር ድርጅቶች ጋር በመተባበር ያስጠናው ሀገር አቀፍ ጥናት ነው። በጥናቱ ትኩረት የተደረገባቸው ቋንቋዎች አማርኛ፣ ትግርኛ፣ ኦሮምኛ፣ ሲዳምኛ፣ ሶማሊኛና ሀረርኛ ናቸው።

ከማንበብ ተግባራት ውስጥ የአንብቦ መረዳት ችሎታን ብቻ ሳይሆን በትክክል ማንበብ መቻልን፣ ድምጽን/ፊደልን/ መለየት፣ የድምጽ ፍሰትን፣ አዳዲስ ቃላትን የማንበብ ፍሰት፣ ድምጽ አውጥቶ የማንበብ ችሎታንና የአዳምጦ መረዳት ችሎታን ጭምር ዳሰዋል።

በጥናቱ ከስምንቱ ክልሎች ውስጥ በ338 ትምህርት ቤቶች በመማር ላይ የሚገኙ 13,079 የሁለተኛና የሶስተኛ ክፍል ተማሪዎች የጥናቱ ተሳታፊ ሆነዋል። በጥናቱ ከማንበብና ከማዳመጥ ጋር ከተገናኙት መረጃዎች በተጨማሪ የተማሪዎችን የቤተሰብ ዳራ የሚለካ መጠይቅ ለተማሪዎች፣ ለመምህራንና ለርዕሳነ መምህራን ተበትኗል። የቤተሰብ ዳራን የሚለካው መጠይቅ የተበተነው የትምህርት ቤትና የመማሪያ አካባቢ ከተማሪዎች የትምህርት ውጤት ጋር ያለውን ተዛምዶ ለመለየት ነው።

የጥናቱ ውጤት እንደሚያሳየው በኢትዮጵያ በሁሉም ክልሎች በአፍ መፍቻ ቋንቋቸው የሚማሩ የአንደኛ ደረጃ ተማሪዎች የማንበብ ክሂል ዝቅተኛ ስለሆነ ለቀላል የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች መልስ መስጠት የቻሉት ከ50% የማይበልጡ ናቸው። በአማራ ክልል ያለው የአንብቦ መረዳት ችሎታ ማነስ ከሌሎቹ ጎልቶ ይታያል። የአማራ ክልል ተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ችሎታ ከሌሎች የአማርኛ አፊ ፊት ተናጋሪ ክልል ተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ችሎታ ጋር ሲነጻጸር ከሀረሬ 50.9%ና ከአዲስ አበባ 43.7% ቀጥሎ በ28.5% በሶስተኛ ደረጃ ላይ ይገኛል። በአንብቦ መረዳት ችሎታ ላይ እንደ ታየው ሁሉ በቃላዊ የንባብ ፍሰት ትክክለኝነት ላይ በአማራ ክልል የሚገኙ

የሁለተኛና የሶስተኛ ክፍል ተማሪዎች ከቤኒሻንጉል ጉምዝ የተሻለ ከአዲስ አበባና ከሀረሬ ክልል ያነሰ ሆኖ በ23.4% በሶስተኛ ደረጃ ተገኝቷል፡፡

በ2000፣ በ2004 እና በ2007 የተከናወኑት የጥናት ውጤቶች የተማሪዎች የማንበብ ችሎታ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየቀነሰ የሄደ መሆኑን ያሳያሉ (Wainer& Piper, 2010)፡፡ በአጠቃላይ ከ50% በላይ የሚሆኑት የአንደኛ ደረጃ ተማሪዎች ቀላል የአንብቦ መረዳት ችሎታ መለኪያ ጥያቄዎችን መመለስ አይችሉም፡፡ በመሆኑም በማንበብ ትምህርት ዙሪያ አስፈላጊውን ዝግጅት በማድረግ ለለውጥና ለትግበራ መስራት ያስፈልጋል የሚል አስተያየት ተሰጥቷል፡፡ ከተሰጡት አስተያየቶች ውስጥ የአንብቦ መረዳት ብልሀቶችን እንዲጠቀሙ ማበረታታት፣ በማንበብና የማንበብ መመሪያ ላይ ትኩረት ማድረግ፣ ማንበብን አስቀድመው እንዲጀምሩ ማድረግና በቤታቸው ውስጥ የተለያዩ መጽሀፍትን እንዲያነቡ ማድረግ እንደ መፍትሄ ከተጠቆሙት ውስጥ ይጠቀሳል፡፡

በአጠቃላይ ሲታይ አንብቦ መረዳት ለትምህርት እድገት መሰረታዊ የሆነ ክሂል ቢሆንም በአብዛኛው የኢትዮጵያ ተማሪ ማንበብ እንደ ከባድ ስራ (የማይወደድ) ሆኖ ሲታይ ይስተዋላል፡፡ በተለይም Wainer& Piper (2010) የአንደኛ ደረጃ ተማሪዎችን የማንበብ ችሎታ በሀገሪቱ የተለያዩ አካባቢዎች የሁለተኛና የሶስተኛ ክፍል ተማሪዎችን ወስደው ባጠኑት ጥናት በአፋር፣ በአማራ፣ በደቡብ ህዝቦችና በትግራይ የማንበብ ችሎታቸው በአማካኝ ከ50% በታች መሆኑ ችግሩን ቁልጭ አድርጎ ያሳይል፡፡

የዚህ ጥናት አጥኝም በሁለተኛ ደረጃም ሆነ በሶስተኛ ደረጃ በሚገኙ የትምህርት ተቋማት በምታስተምርበት ጊዜ የተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ችሎታ ዝቅተኛ እንደሆነ አስተውላለች፡፡ እይታውም የአንብቦ መረዳት ችሎታቸው ከቤተሰብ ዳራ ጋር ይገናኛልን? የሚል ጥያቄ እንዲፈጠር አስችሏል፡፡ የዚህ ጥያቄ መፈጠር ጥናቱን ለማጥናት እንደ ዋና አነሳሽ ምክንያት ሆኗል፡፡

ከዚህ ዋና አነሳሽ መንስኤ በተጨማሪ ከላይ የተዘረዘሩት በቤተሰብ ዳራ፣ በአንብቦ መረዳትና በማንበብ ተነሳሽነት ዙሪያ የተሰሩት የውጭ ሀገር ጥናቶች ውጤት መለያየት፣ የቤተሰብ ዳራ ከአንብቦ መረዳት ችሎታ ጋር ያለው ተዛምዶ እንደሁም የመተንበይ ድርሻ በኢትዮጵያ አለመፈተሽ፣ የመለኪያዎች ትርጉምና ጥራት ከጊዜ ወደ

ጊዜ እየተለወጠና እየተሻሻለ መምጣትና የቴክኖሎጂ እድገት በማንበብ ላይ እያደረሰ ያለው አስተዋጽኦ አለመካተት ጥናቱን ለማጥናት ድጋፍ ሰጭ ምክንያት ሆነው ይጠቀሳሉ፡፡

## 1.3. የጥናቱ መሰረታዊ ጥያቄዎች

ይህ ጥናት ከላይ የተጠቀሱትን ምክንያቶች መነሻ አድርጎ ተጠኝዎችን መርጦ፣ መረጃ ሰብስቦ ከተነተነ በኋላ የሚከተሉትን ጥያቄዎች ይመልሳል ተብሎ ይታሰባል፡፡

1. የቤተሰብ ዳራ የአንብቦ መረዳት ችሎታን በመተንበይ ረገድ ድርሻው ምን ያህል ነው?
    - 1.1. የቤተሰብ መዋቅር የአንብቦ መረዳት ችሎታን በመተንበይ ረገድ ድርሻው ምን ያህል ነው?
    - 1.2. የቤተሰብ የትምህርት ደረጃ የአንብቦ መረዳት ችሎታን በመተንበይ ረገድ ድርሻው ምን ያህል ነው?
    - 1.3. የቤተሰብ የስራ ሁኔታ የአንብቦ መረዳት ችሎታን በመተንበይ ረገድ ድርሻው ምን ያህል ነው?
    - 1.4. የቤት ውስጥ ግብዓት የአንብቦ መረዳት ችሎታን በመተንበይ ረገድ ድርሻው ምን ያህል ነው?
    - 1.5. የቤተሰብ የኢኮኖሚ ደረጃ የአንብቦ መረዳት ችሎታን በመተንበይ ረገድ ድርሻው ምን ያህል ነው?
    - 1.6. የቤተሰብ የማህበራ ደረጃ የአንብቦ መረዳት ችሎታን በመተንበይ ረገድ ድርሻው ምን ያህል ነው?

H1= የቤተሰብ ዳራ የአንብቦ መረዳት ችሎታን የመተንበይ ድርሻው አለው፡፡

2. የቤተሰብ ዳራ የአንብቦ መረዳት ችሎታን የመተንበይ ድርሻው በክፍል ደረጃ ልዩነት አለው?

Ho= የቤተሰብ ዳራ የአንብቦ መረዳት ችሎታን የመተንበይ ድርሻው በክፍል ደረጃ ልዩነት የለውም፡፡

3. የተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ችሎታ ከጾታ አንጻር ልዩነት ያሳያል?

Ho= የተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ችሎታ ከጾታ አንጻር ልዩነት አያሳይም፡፡

H1= በአንብቦ መረዳት ችሎታ በሴቶችና በወንዶች አማካይ መካከል ልዩነት አለ፡፡

4. ከቤተሰብ ዳራ ተላውጦዎች ተማሪዎች ለአንብቦ መረዳት ችሎታየና ለማንበብ ተነሳሽነቴ ይጠቅሙኛል ብለው የሚያስቧቸው ነገሮች ምን ምን ናቸው?

## 1.4. የጥናቱ አላማዎች

**የጥናቱ ዋና አላማ፡-** የዚህ ጥናት ዋና አላማ የቤተሰብ ዳራ የአንብቦ መረዳት ችሎታን የመተንበይ ድርሻውን መለየት ነው፡፡ ከዚህ ዋና አላማ በተጨማሪ የሚከተሉትን ዝርዝር አላማዎች አሳክቷል፡፡

### የጥናቱ ዝርዝር አላማዎች፡-

1. የቤተሰብ ዳራ የአንብቦ መረዳት ችሎታን የመተንበይ ድርሻውን መለየት፤
2. የቤተሰብ ዳራ የአንብቦ መረዳት ችሎታን የመተንበይ ድርሻው በክፍል ደረጃ ያለውን ልዩነት መፈተሽ፤
3. የማንበብ የአንብቦ መረዳት ችሎታ በጾታ የሚለያይ መሆንና አለመሆኑን መፈተሽ፤

4. ከቤተሰብ ዳራ ተላውጦዎች ተማሪዎች ለአንብቦ መረዳት ችሎታየና ለማንበብ ተነሳሽነቴ ይጠቅሙኛል ብለው የሚያስቧቸው ነገሮችን መዘርዘር ናቸው፡፡

## 1.5. የጥናቱ ጠቀሜታ

የማንበብ ትምህርት አላማ በጸሁፉና በአንባቢው መካከል ያለውን ተግባቦት ማፋጠን ነው፡፡ የማንበብ ክሂል ማንበብ በሚችለው ማህበረሰብ ዘንድ የሚኖረው መረጃን የማቀበልና የመግለጽ ተግባር ጉልህ ነው፡፡ በመሆኑም ከማንበብ ክሂል ጋር ቅርበት ያላቸውን ተላውጦዎች የዝምድና መጠን እንዲሁም የመተንበይ ድርሻ መለየት ለአንብቦ መረዳት ሂደቱ የጎላ ሚና ይኖረዋል፡፡ ከዚህ በመነሳት ይህ ጥናት ለመምህራን፣ ለስርዓተ ትምህርት ቀራጮች፣ ለተማሪዎች እንዲሁም ለተማሪ ወላጆች የሚከተሉት ጠቀሜታዎች ይኖሩታል፡፡

1. የቤተሰብ ዳራ የአንብቦ መረዳት ችሎታን የመተንበይ ድርሻውን ምን ያክል እንደሆነ ለማወቅ ይጠቅማል፡፡
2. የቤተሰብ ዳራ የአንብቦ መረዳ ችሎታን የመተንበይ ድርሻው በክፍል ደረጃ ይለያያል
3. የተማሪዎችን የማንበብ ልምድ ለማዳበርና ለማሳደግ የቤተሰብን ሚናና ተጽዕኖ ለመለየት ያስችላል፡፡
4. ጾታ በአንብቦ መረዳት ችሎታ ላይ ያለውን ልዩነት ለማረጋገጥ ይረዳል፡፡
5. በዚህ ርዕስ ዙሪያ ምርምር ለሚሰሩ ሰዎች እንደግብዓት በመሆን ያገለግል፡፡

## 1.6. የጥናቱ ወሰን

የጥናቱ ትኩረት በባህር ዳር ክፍለ ከተማ ከሚገኙ የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በመሆኑ በክፍለ ከተማው ከሚገኙ የአንደኛ ደረጃ ሁለተኛ ሳይክል ትምህርት ቤቶች ውስጥ በዕጣ ንሞና ሶስት ትምህርት ቤቶች ተመርጠዋል፡፡ የተመረጡት ትምህርት ቤቶች የድል ችቦ የመጀመሪያ ደረጃ ሙሉ ሳይክል ትምህርት ቤት፣ የቁልቋል ሜዳ

የመጀመሪያ ደረጃ ሙሉ ሳይክል ትምህርት ቤትና የዶና በርበር የመጀመሪያ ሙሉ ሳይክል ትምህርት ቤት ናቸው፡፡

የድልችቦ የመረጃ መሰብሰቢያዎቹ አስተማማኝነትና ተገቢነት ለመገምገም የተመረጠ ሲሆን የቁልቋል ሜዳ የሙከራ ጥናቱ የተካሄደበት ነው፡፡ የዶና በርበር የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት ደግሞ ዋናው ጥናት የተካሄደበት ነው፡፡ ከአምስተኛ ክፍል 151 ከሰባተኛ ክፍል 170 ተማሪዎች የዋናው ጥናት ተሳታፊዎች ሆነው ተመርጠዋል፡፡ በአጠቃላይ ዋናው ጥናት በ321 ተማሪዎች ላይ የተወሰነ ነው፡፡

የዚህ ጥናት ዋና አላማ የቤተሰብ ዳራ የአንብቦ መረዳት ችሎታን የመተንበይ ድርሻውን መመርመር ነው፡፡ በጥናቱም የአንብቦ መረዳት ችሎታና የቤተሰብ ዳራ የሚሉ ሁለት አበይት ተላውጦዎች ተካተዋል፡፡ ጥናቱ የተላውጦዎችን የእርስ በርስ ተዛምዶንና የመተንበይ ድርሻቸው መለየት እንጂ የምክንያትና ውጤት ትስስርን አይፈትሽም፡፡ ከሁለቱ ርዕሰ ጉዳዮች አንዱ ላይ በማተኮር ጥናት ማካሄድ የተለመደ በመሆኑ ለዚህ ጥናት የተመረጠው ገላጭ ተዛምዷዊ የምርምር ስልት ነው፡፡ ጥናቱ በዋናነት የቤተሰብ ዳራ የአንብቦ መረዳት ችሎታን የመተንበይ ድርሻው ምን ያክል እንደሆነ ፈትሿል፡፡

በመሆኑም ከተላውጦ አንጻር በአንብቦ መረዳት ችሎታና በቤተሰብ ዳራ ላይ ተወስኗል፡፡ የአንብቦ መረዳት ችሎታ የሚባለው በዚህ ጥናት አንድ ምንባብ አንብበው ለቀረበላቸው ጥያቄ መልስ የሚሰጡበትን ችሎታ ነው፡፡ መረዳት የሚለውን የአዕምሮ እውቀት ደረጃ የሚመለከት ነው፡፡ ማብራራት፣ መተንተንና መገምገም የሚሉትን አይዳስስም፡፡ ምክንያቱም ጥናቱ ይዞት ከተነሳው አላማ አንጻር አስፈላጊ ስላልሆነ ነው፡፡

ቤተሰባዊ ዳራ በዋናነት ከሚፈተሹት ተላውጦዎች ስር የሚካተት ሲሆን እምቅ ሀሳቦችን የያዘ ተላውጦ እንደሆነ ይታወቃል፡፡ ለጥናቱ ከማንበብ ጋር የሚያያዙት ቤተሰባዊ ጉዳዮች (የቤተሰብ መዋቅር፣ የቤተሰብ ብዛት፣ የወላጅ ወይም ያሳዳጊ የትምህርት ደረጃ፣ የወላጅ ወይም ያሳዳጊ የስራ አይነት፣ የቤተሰብ ኢኮኖሚያዊ ደረጃ፣ የቤተሰብ የማህበራዊ ደረጃና የቤት ወስጥ ግብዓት) በጥናቱ ተካተዋል፡፡

የቤተሰብ መዋቅር ከማን ጋር ትኖራለህ/ሽ፣ የቤተሰብ የትምህርት ደረጃ የእናት የአባትና የአጠቃላይ ቤተሰብ፣ የቤተሰብ ስራ የእናት/የሴት አሳዳጊ/ና የአባት/የወንድ አሳዳጊ/ የቤተሰብ የኢኮኖሚ ደረጃ በወርሀዊ ገቢና ገቢ ከአካባቢ ጋር በማነጻጸር እንዲሁም የቤት ውስጥ ግብዓት በአካባቢው ከሚገኙ ነገሮች አንጻር ተወስኖ ቀርቧል፡፡ የቤተሰብ ዳራ ተላውጦዎቹ በአጠቃላይና በተናጠል አንብቦ የመረዳት ችሎታንና የማንበብ ተነሳሽነትን የመተንበይ ደረጃቸውም ተሰልቷል፡፡

## 1.7. የጥናቱ ውስንነት

ይህ ጥናት ሙከራ ጥናቱ በሚካሄድበት ወቅት በርካታ ተላውጦዎችን የዳሰሰ ነበር፡፡ በጥናቱ ተካተው የነበሩት ተላውጦዎች የቤተሰብ ዳራ፣ የአንብቦ መረዳት ችሎታና የማንበብ ተነሳሽነት ናቸው፡፡ ነገር ግን የጥናት ውጤቱ እንደሚያሳየው የአንብቦ መረዳት ችሎታና የማንበብ ተነሳሽነት ያላቸው ተዛምዶ ዝቅተኛና ጉልህ ያልሆነ ነው፡፡ አስራ አንዱም የማንበብ ተነሳሽነት መለኪያዎች በተናጠል ከአንብቦ መረዳት ችሎታ ጋር ያላቸው ተዛምዶ ተሰልቶ የተገኘው ውጤት የሚያሳየው በአንብቦ መረዳት ችሎታና በማንበብ ተነሳሽነት መካል ተዛምዶ እንደሌላቸው በመሆኑ በዋናው ጥናት የማንበብ ተነሳሽነት የሚለው ተላውጦ ሳይካተት ቀርቷል፡፡

ሌላው ውስንነት እያንዳንዱ ተላውጦ እርስ በርስ ያለውን ግንኙነትና ነጻ ተላውጦው ጥገኛ ተላውጦውን የመተንበይ ድርሻውን ማየት አስፈላጊ በመሆኑ በርካታ ናሙናዎችን ወስዶ መስራት አለመቻሉ አንድ ውስንነት ነው፡፡ በእያንዳንዱ የክፍል ደረጃ ያለውን የንሞና መጠን በዚህ ጥናት ከተመረጠው ከፍ ብሎ በስፋት መስራት አለመቻሉ ውስንነቱን ያሳያል፡፡

ከዚህ በተጨማሪ በክፍል ደረጃ ያለውን ልዩነት ለማየት ሲባል ይህ ጥናት የተካሄደው በሁለት የክፍል ደረጃዎች ብቻ ነው፡፡ ነገር ግን በመጀመሪያ ደረጃ በሚገኙ በሁሉም የክፍል ደረጃዎች ላይ ጥናቱ አለመካሄዱ ሌላው ውስንነት ነው፡፡

## 1.8. የቁልፍ ቃላት ብያኔ

1. **የቤተሰብ ዳራ** (Family Background)፡- ቤተሰቦች (ወላጆች ወይም አሳዳጊዎች፣ እህት፣ ወንድም፣ ዘመድ ወይም አብረው የሚኖሩ ሰዎች) የሚኖራቸው ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ሀይማኖታዊና ትምህርታዊ ሁኔታን የሚመለከት ነው፡፡

2. **የቤተሰብ መዋቅር** (**Family structure**)**፡-** የቤተሰብ መዋቅር ተማሪዎች አብረውት የሚኖሩትን ሰው ማንነት ወይም ቅርበት ይመለከታል፡፡ ማለትም ተማሪው አብሯቸው የሚኖሩት ሰዎች ከተማሪው ጋር ያላቸውን ቅርበት ወይም የስጋ ዝምድና የሚመለከት ነው፡፡

3. **የቤተሰብ ማህበራዊ ደረጃ** (**Family Social status**)**፡-** የቤተሰብ ማህበራዊ ደረጃ ሲባል ከተማሪው የትምህርት ሁኔታ ወይም የትምህርት ቤት አካባቢ ጋር በተገናኘ ወላጅ ወይም አሳዳጊ የሚያደርጋቸውን ማህበራዊ ተሳትፎዎች ይመለከታል፡፡

   ለምሳሌ፡-

   .በትምህርት ቤት የወላጅ ኮሚቴ ሆኖ መሳተፍ፣

   በልማት ጉዳዮች መሳተፍ

4. **የቤት ውስጥ ግብዓት** (**Home fasility**)**፡-** ተማሪዎች ለአንብቦ መረዳታቸውና ለማንበብ ተነሳሽነታቸው ሊያግዟቸው የሚችሉ በቤት ውስጥ የሚገኙ የተለያዩ ቁሳቁሶችን ይመለከታል፡፡ ይህ ሲባል ግን ለአንብቦ መረዳት ችሎታቸው ሆን ተብሎ የሚደረገውን ብቻ ሳይሆን ለመኖር ተብለው የሚሟሉላቸውን ነገር ግን በተዘዋዋሪ ለማንበብ ችሎታና ለማንበብ ተነሳሽነት የሚያገለግሉ ቁሳቁሶችን ይመለከታል፡፡

   ለምሳሌ፡- የግል ክፍል መኖር

5. **የአንብቦ መረዳት ችሎታ** (Reading Comprehension)፡- ከተጻፉ ጽሁፎች ጋር በሚደረግ ተራክቦና ተሳትፎ ትርጉም የማውጣትና የመገንባት ሂደት ነው፡፡ በተመሳሳይ የተጻፉ ጽሁፎችን ለመገንዘብ የሚደረግ ንቁና ውስብስብ ሂደት፣ ትርጉምን መተንተንና ማዳበር እንዲሁም እንደ ጽሁፉ አይነት፣ አላማና ሁኔታ ተገቢ ትርጉም የመስጠት ሂደት ነው፡፡ በዚህ ጥናትም ከተጻፉ ጽሁፎች ጋር በሚደረግ ተራክቦ ትርጉም የማውጣት ሂደት የሚለውን ይመለከታል፡፡

6. **ለማንበብና መጻፍ ማንበብ** (Reading literacy)፡- በማህበረሰቡ የሚጠበቁ እንዲሁም በግለሰብ ደረጃ ዋጋ የሚሰጣቸውን የቋንቋ ቅርጽ የመረዳትና የመጠቀም ብቃት ለማንበብና መጻፍ ማንበብ ይባላል፡፡ ለመማር ማንበብ፣ በማህበረሰቡ ውስጥ ከሚገኙ አንባቢዎች ጋር ለመቀላቀል እንዲሁም ለመዝናናት የሚደረግ የንባብ ሂደትንም ይመለከታል፡፡

7. **የማንበብ ተነሳሽነት** (Reading Motivation)፡- ተማሪዎች ለማንበብ ርዕስ፣ ሂደትና ግብዓት የሚኖራቸው ግላዊ ግብ፣ ዋጋና እምነት የማንበብ ተነሳሽነት ይባላል፡፡ በሌላ አገላለጽ የማንበብ ተነሳሽነት ተማሪዎች በሚያነቡበት ጊዜ የሚኖራቸው የራስ መተማመን፣ ፍላጎትና የመነቃቃት ስሜት የማንበብ ተነሳሽነት ነው፡፡

8. **የማንበብ ተነሳሽነት መለኪያዎች** (Reading Motivation Dimensions):- የማንበብ ተነሳሽነት ዘርፎች ሲሆኑ ማንኛውም ሰው ለማንበብ ሲነቃቃ ወይም ሲነሳሳ ይዞት የሚነሳውን ምክንያት የሚመለከት ነው፡፡ በሌላ አባባል ለማንበብ ፍላጎት እንዲያድርበት ያደረገውን ምክንያት ይመለከታል፡፡ ከዚህም አንጻር ውስጣዊና ውጫዊ ተብለው ይከፈላሉ፡፡ እያንዳንዳቸውም በስራቸው የተለያዩ አይነቶችን (መለኪያዎችን) ይዘዋል፡፡

9. **ዴሚ ተላውጦ** (**Dami Variable**)፡- ዴሚ ተላውጦ የሚባለው በአማራጭነት የቀረበው መልስ እንደ አብይ ተላውጦ ሆኖ እራሱን ችሎ በኤስ ፒ ኤስ ኤስ ሲመዘገብ ነው፡፡

ምሳሌ፡- ስራ የሚል ጥያቄ ቢኖርና ገበሬ፣ ነጋዴ፣ መምህር፣ ሹፌር ወ. ዘ. ተ. የመሳሰሉ አማራጭ ቢኖር ወደ ትንተና ሲገባ እያንዳንዱ አማራጭ እንደ ተላውጦ ሲመዘገብ ዴሚ ተላውጦ ይባላል፡፡

10. **ትንበያ** (Pridiction)፡- ከአንዱ ተላውጦ ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ ተላውጦዎች ላይ የተገኘን መረጃ መሰረት በማድረግ ስለሌላው ተላውጦ መግለጽ ትንበያ ይባላል፡፡ የምክንያትና ውጤት ትስስርን አይፈትሽም፡፡ ነገር ግን ከተዛምዷቸውና የግንኙነታቸው መጠን በመነሳት ስለሌላው ተላውጦ መግለጽ ትንበያ ነው፡፡

11. **ድህረት** (Regression)፡- ከአንድ ወይም ከዚያ በላይ ተላውጦዎች በመነሳት ስለሌላው ተላውጦ ለመናገር ወይም ለመተንበይ ሲታሰብ የመተንበይ ሂደቱን ለማከናወን የሚያገለግል መተንተኛ ዘዴ ነው፡፡

# ምዕራፍ ሁለት

# የተዛማጅ ጽሁፍ ክለሳ

## 2.1. መግቢያ

በምዕራፍ አንድ የጥናቱ ዳራ፣ የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት፣ የጥናቱ መሰረታዊ ጥያቄዎች፣ የጥናቱ አላማዎች፣ የጥናቱ ጠቀሜታ፣ የጥናቱ ወሰን፣ የጥናቱ ውስንነትና የቁልፍ ቃላት ብያኔ ቀርበዋል፡፡ በዚህ ምዕራፍ ደግሞ የአንብቦ መረዳት ምንነት፣ የአንብቦ መረዳት ንድፈ ሀሰብ፣ የአንብቦ መረዳት ሞዴሎች፣ የአንብቦ መረዳት ደረጃዎች፣ የማንበብ ተነሳሽነት፣ የቤተሰብ ዳራ፣ በጥናቱ ዙሪያ የተካሄዱ የቀደምት ስራዎች ቅኝት፣ በኢትዮጵያ በአንብቦ መረዳት ዙሪያ የተሰሩ ስራዎች ቅኝት፣ የጥናቱ ንድፈ ሀሳባዊ ማዕቀፍና የጥናቱ ጽንሰ ሀሳባዊ ማዕቀፍ በዝርዝር ይቀርባሉ፡፡

## 2.2. የማንበብ ምንነት

ማንበብ በመጀመሪያዎቹ የትምህርት ደረጃዎች ለተማሪዎች ከሚያስፈልጓቸውና እጅግ ከሚጠቅሟቸው ክሂሎች አንዱ ነው (Campbell, Kelly, Mullis, Martin & Sainsbury 2001)፡፡ Campbell, et al (2001) እንደሚያብራሩት የማንበብ ክሂል ለፈጠራና ለግላዊ እድገት ጠቀሜታ ስላለው በመጀመሪያዎቹ የትምህርት ደረጃዎች ከማንኛውም ክሂል በበለጠ ትኩረት የሚፈልግ ነው፡፡ እንዲሁም ታዳጊ ህጻናት በማህበረሰባቸው ውስጥ ወይም በሰፊ ህብረተሰብ ውስጥ የመሳተፍ ችሎታቸውን እንዲያሳድጉ ያደርጋል ዝግጁነታውንም ይጨምራል፡፡ በሌላ አገላለጽ በቅድመ ትምህርት ጊዜ ወላጆች በቤት ውስጥ ሊያዳብሩት የሚገባ በመጀመሪያ ደረጃ የሚያስፈልግ ክሂል ነው፡፡

ውስብስብ የሆነው የማንበብ ሂደት በተለያዩ የትምህርት መስኮች በርካታ ምርምር ተሰርቶበታል፤ እየተሰራበትም ይገኛል (Janan, 2011)፡፡ ነገር ግን በብያኔው፣ በሂደቱ፣ በአቀራረቡና በዘዴው ውጤታማነት ዙሪያ አሁንም ድረስ አንድ ወጥ ድምዳሜ ላይ

አልተደረሰም፡፡ ብያኔውና በየጊዜው የነበረውን የትኩረት መውጣትና መውረድ፣ መስፋትና መጥበብ Stahal (1998) ሲገልጹት በማንበብ ውስጥ አጠቃላይ ከሆነው የቃላት ስነ ዘዴ ወደ ድምጽ መለየት ከዚያም አጠቃላይ ወደ ሆነው የቋንቋው መመሪያ ተሸጋግረናል ሽግግሩም የምርምሩን አቅጣጫ እንዲቀያየር አድርጎታል ይላሉ፡፡ የምርምሩ ትኩረት መለያየት ደግሞ ማንበብን የተለያየ ብያኔና ባህርይ እንዲኖረው አድርጓል፡፡ ከባህርያቶቹ መካከል የታተሙ ጽሁፎችን መረዳት፣ ቋንቋውን መገንዘብና በታተሙ ገጾች አማካኝነት አዕምሮን የማሳደግ ጥበብ ይጠቀሳሉ (Walcutt, 1967):: Walcutt (1967) እንደሚብራሩት ማንበብን ለመበየን ሁለት ነገሮችን ግምት ውስጥ ማስገባት ያስፈልጋል፡፡ እነሱም በጊዜው ያንሰራራው ንድፈ ሀሳብና ተግባር ናቸው፡፡ Campbell, et al (2001) የአንብቦ መረዳት ችሎታን ሲተረጉሙት አንብቦ መረዳት ሰፊ ጽንሰ ሀሳብን የያዘ ሲሆን ፊደላትን አገጣጥሞ ቃላት መስርቶ ቃላትን ገጣጥሞ አረፍተ ነገር መስርቶ መልዕክት የመውሰድና መልዕክቱን የማንጸባረቅ ሂደት ነው፡፡ በሌላ አገላለጽ የአንብቦ መረዳት ችሎታ የተጻፉ ጽሁፎችን የመረዳት ችሎታና የተረዳውን ነገር ማህበረሰቡ ወይም ግለሰቡ በሚፈልገው መንገድ መጠቀም ማለት ነው፡፡

እንደ የዘመኑ የትምህርት ትኩረትና የሚገኙ የትምህርት መሳሪያዎች ልዩነት ለማንበብ የተለያየ ብያኔና ባህርይ እንዳሉት ቢገለጽም ከሁሉም እይታዎች የሚገኘው የጋራ ብያኔ ከሚታዩ ምልክቶች ወይም በምልክት አማካኝነት ከተጻፉ ጽሁፎች መልዕክት መቀበያ መንገድ መሆኑን ነው፡፡ በጥንትም ሆነ በአሁኑ ዘመን በማንበብ ላይ ያተኮሩ ተመራማሪዎች ሁሉ በዚህ ሀሳብ ይስማማሉ፡፡ ነገር ግን የቅርብ ጊዜ አጥኚዎች ዘመኑ ከፈጠራቸው የተለያዩ የመረጃ ምንጮች ጋር ለማጣጣም ከሚታዩ ምልክቶች ወይም ከሚጻፉ ጽሁፎች በተጨማሪ ከኤሌክትሮኒክስ መስኮቶችም መረጃዎችን የማግኘት ሂደት እንደሆነ Janan (2011) ያስረዳሉ፡፡

## 2.3. የአንብቦ መረዳት ንድፈ ሀሳቦች

Gaffney & Anderson (2000) ከ1965 እስከ 1998 ድረስ በማንበብ ዙሪያ ተሰርተው በአራት ጆርናሎች የታተሙ ምርምሮችን በመቃኘት ውጤታቸውንና የተከተሉትን ንድፈ ሀሳብ አሳይተዋል፡፡ እንደ Gaffney & Anderson (2000) ማብራሪያ የምርምሮቹ ንድፈ

ሀሳባዊ መሰረት ከባህሪያውያን ወደ አዕምሯውያን ከአዕምሯውያን ወደ ማህበረ ባህላዊያን ተለዋውጧል፡፡ በ1960ቹ አካባቢ የባህሪያውያን ንድፈ ሀሳብ መስፋፋቱ በማንበብ ዙሪያ በሚሰሩ ምርምሮች የታዋቂው BF Skinner ግኝት የሆኑት ማበረታታት፣ ማስለመድና የባህርይ ትንተና የሚሉት ጽንሰ ሀሳቦች በሰፊው አገልግሎት እንዲሰጡ አድርጓል (Gaffney& Anderson, 2000)::

እንደ ባህርያውያን ንድፈ ሀሳብ እይታ ማንበብ ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ ወይም ከታች ወደ ላይ እያደገ የሚሄድ ክሂል ነው፡፡ መማርም አንድ ተማሪ ለቀረበለት ማነቃቂያ ምላሽ የሚሰጥበት ሂደት እንደሆነ በዚህ ንድፈ ሀሳብ ይታመንበታል፡፡ በአንብቦ መረዳት ሂደት ውስጥ እንደ ማነቃቂያ የሚቆጠሩት የታተሙ ጽሁፎች ናቸው፡፡

እንደ ባህርያውያን (ቀዳማዊ የማንበብ ንድፈ ሀሳብ) እይታ የማንበብ ሂደት ከታች ወደ ላይ እየዳበረ የሚሄድ ነው፡፡ ማለትም ማንበብ የሚጀምረው ፊደላትን ከመለየት ሲሆን ወደ አጠቃላዩ ትርጉም የማውጣት ሂደት እያደገ ይሄዳል፡፡ የዚህ ንድፈ ሀሳብ አቀንቃኝ የሆኑት ተመራማሪዎች እንደ ሚያስረዱት የማንበብ እድገት በሚከተለውን ቅደም ተከተል መሰረት እየዳበረ የሚሄድ ነው፡፡




**ስዕል ሁለት፡- የባህርያውያን የማንበብ እድገት**

የማስተማር መመሪያቸው ለስነድምጽ ቅድሚያ ይሰጣል በመጀመሪያ ድምጹ ይለያል፡፡ በመቀጠል ያንን ድምጽ የሚወክለው ፊደል ከታወቀ በኋላ ራሳቸውን ችለው መጽሀፍ ማንበብ ይጀምራሉ ማለት ነው፡፡ በዚህ ንድፈ ሀሳብ ተማሪዎች ፍዝ እንዲሆኑ ይጠበቃል፡፡ በሌላ አባባል የተማሪዎች ተሳትፎ ዝቅተኛ ነው፡፡ አብዛኛውን ሚና የሚጫዎተው አስተማሪው ነው፡፡ መረጃ አቀባዩ መምህሩ ነው ተማሪዎች ደግሞ ተቀባዮች ናቸው፡፡ እንድሪስ (2009፣ 25) የባህርያውያን ንድፈ ሀሳብን እንዲህ ይገልጹታል፡፡

የባህርያዊያን የማስተማር ንድፍ በአወንታ ወይም በአሉታ መልሶም ገባ የሚጠናከር አነቃቂ ተግባርን በመፍጠር ላይ ያነጣጠረ ነው፡፡ ከፍተኛ እርከን ያላቸው የሀሳብ ተዛምዶዎች ወይም ቅበላዎች ጠቃሚ ተደርገውም አይታዩም፡፡ በአጭሩ የባህርያዊያን መማር ንድፈ ሃሳብ በአዕምሯዊ ክዋኔ ትስስሮች ጥናት ላይ የተመሰረተ፣ መማር እንደ ባህርይ ለውጥ የሚበየንበት፣ ማሰብ ከቅጽበታዊ የቀስቃሽ- ምላሽ ጥምረት የሚመነጭበት፣ ማሰብን ለመማር ትኩረት የማይሰጥበት፣ የቀስቃሽ- ምላሽ መማር ሞዴልን የሚከተል ነው፡፡ የንድፈ ሃሳቡ አላባዎችም ሁኔታዎችን መልመድ፣ ምላሽ መስጠት፣ መግራት፣ ማጠናከርና ቀድሞ የታቀደ ጥብቅ አሰራርን መከተል ናቸው፡፡

በሁለተኛ ደረጃ የሚጠቀሰው ንድፈ ሀሳብ በ1970ቹ የተስፋፋው የአዕምሯውያን ንድፈ ሀሳብ ነው፡፡ ይህ ንድፈ ሀሳብ ለተማሪው ስኬማ ሚናና ለታተመው ጽሁፍ ጠቀሜታ እኩል ትኩረት የሚሰጥ ንድፈ ሀሳብ ነው፡፡ የስኬማ ንድፈ ሀሳብ ተብሎም ይጠራል፡፡ ስኬማ ማለት አዕምሯዊ ግንባታ ማለት ሲሆን መረጃ በረጅም ጊዜ ትውስታ እንዲደራጅ የሚፈቅድ ነው (Huang, 2009)፡፡ Pearson (2009) የስኬማ ንድፈ ሀሳብን ሲያብራሩት በ1970ዎቹ ተቀባይነት ያገኘው ስኬማ በማንበብ ሂደት ቋንቋና መረጃን ከጽሑፍ ለይቶ ለማውጣት የሚያስችልና አንባቢን እንደ ትርጉም መስራች የሚያይ ንድፈ ሀሳብ ነው፡፡ እንድሪስ (2009፣ 26)

በስኬማ ንድፈ ሃሳብ መሰረት እውቀት በሚከማችበት መንገድ አምሳያ የማስተማር መማር ተግባራት አዲሱን ከነባሩ እውቀት ጋር ማስተሳሰር አለባቸው፤ ትስስር መፍጠሩም አዲሱን መረጃ በቀላሉ ዳግም ማስታወስ እንደ ሚያስችል ይታሰባል፡፡ ይህ ተዛምዶም መረጃን በስኬማ ላይ በመጨመር፣ ዳግም በማዋቀር የሚፈጠር ነው፡፡ ተዛምዶዎቹ በትስስር የሚፈጠሩ ሲሆኑ እነዚያ ትስስሮች መስመሮችን ሳይጠብቅ እንደ ተፈጠረ የማስታወሻ አሰፋፈር ተደርገው ይታሰባሉ፡፡ በስኬማ ንድፈ ሃሳብ አቀንቃኞች የሚታቀዱ ተግባራት የተማሪዎቹን ቀደምት እውቀት ማስታወስንና መረጃውን ከሚያውቁት ሀሳብ ጋር ማዛመድን የሚያካትቱ ናቸው፡፡

እንደ ስኬማ ንድፈ ሀሳብ ማንኛውም ጽሁፍ በራሱ ትርጉም የለውም፡፡ ጽሁፉ ትርጉም የሚኖረው አንባቢው የቀደመ እውቀቱን ተጠቅሞ የቀረበውን ጽሁፍ መረዳት ሲችል ነው (Huang, 2009)፡፡ እንደ Huang (2009) አገላለጽ ስኬታማ ንባብ የሚባለው ከዚህ በፊት በአዕምሮ ውስጥ ተደራጅቶ የተቀመጠውና ከእይታ ውጭ የሆነው እውቀት

በጽሁፍ ታትሞ ከሰፈረውና በአይን ከሚታየው መረጃ ጋር በትክክል መቀናጀት ሲችል ነው፡፡

Sheridan (1981) በተጨማሪ እንደ ሚያብራሩት ተማሪዎች በአካባቢያቸው ስለሚታየው እውነታና የህይወት ዑደት ያላቸውን ነባር ዕውቀት በላይ ታችና በታች ላይ የንባብ ሂደት የመጠቀም ሁኔታ ስኬማ ይባላል፡፡ እንደ ስኬማ አገላለጽ ጽሁፉ ብቻውን በራሱ ትርጉም የለውም፡፡ ትርጉም የሚኖረው አንባቢው የራሱን ልምድ፣ ስሜትና የባህል እውቀት በመጠቀም መረዳት ሲችል ነው፡፡ በዚህ መልኩ ከተረዳ ደግሞ ስኬማ ይባላል፡፡ እንደ ስኬማ ንድፈ ሀሳብ ጽሁፍን የመረዳት ሂደት በጽሁፉና በአንባቢው ነባር እውቀት መካከል በሚደረግ ንቁ ተሳትፎ የሚፈጠር ነው፡፡

በማንበብ ሂደት በጥቅም ላይ የሚውሉ የስኬማ አይነቶች የይዘት ስኬማ፣ መደበኛ ስኬማና ስነልሳናዊ ስኬማ ናቸው (Khalaji & Vafaeeseresht, 2012)፡፡ የመጀመሪያው የይዘት የሚባለው ስኬማ የአንባቢው ዳራ ወይም ለአለም ያለው ነባር እውቀት ሲሆን አዲሱን እውቀት ለማነጻጸር እንደ መሰረት የሚያገለግል ነው፡፡ በሌላ አገላለጽ አንባቢዎች በጽሁፍ ያለውን ክስተትና ድርጊት በህይወታቸው ካጋጠማቸው ተመሳሳይ ክስተትና ድርጊት ጋር እንዲሁም ከራሳቸው ባህል ጋር እያነጻጸሩ የሚገነዘቡበት ነው፡፡

መደበኛ የሚባለው ሁለተኛው የስኬማ አይነት በአብዛኛው ዘውግ ተኮር ስኬማ እየተባለ ይጠራል፡፡ ይህ ስኬማ አንባቢዎች የተጻፉ ጽሁፎችን ቅርጽና መዋቅራዊ ባህርይ በማየት ምን ሊገጥማቸው እንደሚችል አስቀድመው የሚገምቱበት ስኬማ ነው፡፡ ለምሳሌ መጽሄት ከልቦለድ የተለየ ስለሆነ ልቦለድ ለማንበብ የተዘጋጀ ሰው ምን ሊገጥመው እንደሚችል የሚገምትበት ነው፡፡ በአጠቃላይ አንባቢዎች ቅርጽን በማየት በጽሁፉ ሊያጋጥማቸው ስለሚችለው መዋቅር፣ ቃላት፣ ሰዋሰውና የጽሁፉ የመደበኛነት ደረጃ አስቀድመው የሚዘጋጁበት ስኬማ መደበኛ ስኬማ ነው፡፡ የመጨረሻው የስኬማ አይነት ስነልሳናዊ ወይም የቋንቋ ስኬማ ሲሆን ቃላትን ለማገናዘብ የሚያስፈልጉ ስነልሳናዊ መገለጫዎችንና እነዛ ቃላት አረፍተ ነገር የሚመሰርቱበትን መዋቅር የሚያካትት የስኬማ አይነት ነው (Huang, 2009)፡፡

ስኬማ ለአንባቢ የሚሰጠው ጠቀሜታ በርካታ ነው፤ ከነሱም የመጀመሪያው ዋናና ዝርዝር አላማዎችን ለአንባቢ በማሳዎቅ የአንባቢውን የትኩረት አቅጣጫ ለመወሰን ይረዳል፡፡ በመቀጠል በጽሁፉ ውስጥ ያልተሟሉ መረጃዎች ካሉ የቀደመ እውቀትን ተጠቅሞ ክፍተቱ እንዲሞላ ያግዛል፡፡ እንዲሁም ተገቢውን ተገቢ ካልሆነው ለይቶ ለማውጣት ያገለግላል፡፡ በመጨረሻም ነገሮችን በመገመት ለመረዳት ያገለግላል (Pearson 2009)፡፡

ቃላት፣ አረፍተ ነገሮችና የጽሁፍ ትርጉም አንባቢው ከማንበቡ በፊት ባለው ልምድና የቀደመ እውቀት ምክንያት ተጽዕኖ ስለሚደርስባቸው እንደሁኔታው ይለዋወጣሉ፡፡ የንባብ ሂደቱም የሚከተለውን አይነት አካሄድ ይኖረዋል፡፡




**ስዕል ሶስት፡- የአዕምሯውያን የንባብ ሂደት**

ሶስተኛው የማንበብ ንድፈ ሀሳብ የማህበረ ባህላዊ ቅድመ ግንባታውያን ነው፡፡ ከ1980ቹ መካከለኛው ዘመን ጀምሮ የማህበራዊ ቅድመ ግንባታውያን ንድፈ ሀሳብ እየተስፋፋ መምጣት የአዕምሯውያን ንድፈ ሀሳብ እየተዳከመ እንዲሄድ አድርጎታል፡፡ በዚህ ንደፈ ሀሳብ በዋናነት የሚጠቀሰው የሩሲያዊው የስነልቦና ተመራማሪ Vygotsky የማህበረ ባህላዊ እድገት ንድፈ ሀሳብ (Socio- cultural Development Theory) ነው፡፡ የማንበብ ትምህርት የመማር ሂደት በማህበራዊ ግንዛቤ ላይ የተመሠረተ ነው የሚለው አመለካከት በሰፊው የተንሰራፋበት ንድፈ ሀሳብ ነው፡፡

ንድፈሀሳባዊ መሠረቱ እውቀት በማህበረሰብ ደረጃ ከዚያም በግለሰብ ደረጃ ይከሰታል፣ የሚለውና የማህበራዊ እድገት መሰረታዊ ጽንሰ ሃሳብ የሆነው የጥግግ እድገት መጠን (Zone of Proximal Development — ZPD) የንድፈ ሀሳብ አፍላቂዎችንና

የተመራማሪዎችን ትኩረት የሳበና ከፍተኛ ተቀባይነት ያገኘበት ወቅት ነው (Doolittle, Hicks, Triplett, Nichols & Young 2006)፡፡ Doolittle et al (2006) እንደ ሚያብራሩት በዚህ ንድፈ ሀሳብ መሰረት እውቀትና ትርጉም የሚገኘው ከማህበረሰቡ ንቁ ተሳትፎ ነው፡፡ የተገኙት እውቀቶች አገልግሎታቸውም ለማህበረሰቡ ነው፡፡ በሌላ አገላለጽ የእውቀት ምንጩም ተጠቃሚውም ማህበረሰብ ነው፡፡ የንባብ ሂደቱም የሚከተለውን ይመስላል፡፡




**ስዕል አራት፡- የቅድመ ግንባታውያን የማንበብ ሂደት**

ከ1980- 90ቹ የማህበራዊ ቅድመ ግንባታ ንድፈ ሀሳብ መስፋፋት አይነታዊ የምርምር ዘዴ ከመጠናዊና ከሙከራዊ የበለጠ እንዲሰራበት አድርጓል (Gaffney & Anderson, 2000):: ማንበብን ከቃላት፣ ከቋንቋና ጽሁፍ ጋር አያይዞ መስራቱ እየቀነሰ ከማህበረሰብ፣ ከባህል፣ ከተነሳሽነትና ከፍላጎት ጋር አያይዞ ማጥናት እየጨመረ የሄደበት ጊዜ እንደነበር Gaffney & Anderson (2000) ያስረዳሉ፡፡

በ2011 በተዘጋጀው የማንበብ ምርምር መጽሀፍ አርታዒዎቹ Kamil et al. (2011) በቅኝታቸው እንደገለጹት ባለንበት ዘመን የምርምሮቹ የትኩረት አቅጣጫ በጣም

ጠንካራና አድካሚ የሆኑ የምርምር ዘዴዎችን ማዘጋጀት እንዲሁም በተለያዩ አውዶች፣ በተለያዩ ሰዎችና በልዩ ልዩ ልምምዶች የማንበብን ውጤታማነት መፈተሽ ነው፡፡ Kamil et al. (2011) ያነሱት በቀደሙት ጊዜያት ያልታየው ሌላው ጠቃሚ ነጥብ በማንበብ ሂደትና እድገት መካከል ስላለው ልዩነት ነው፡፡ ማንበብ ፊደላቱን አውቆ በትክክል ማለት መቻሉ ላይ ብቻ የሚቆም ሳይሆን በህይወት ዘመን ሁሉ ከሚያጋጥሙ የተለያዩ የጽሁፍ አይነቶች ጋር እራስን እያግባቡ እውቀትን የማዳበር የማያቋርጥ ሂደት ነው፡፡

በማንበብ ሂደት ዋናው መሰረታዊ ነገር መረዳት መቻል የሚለው ጽንሰ ሀሳብ እንደሆነ Paris & Hamilton (2009) ያስረዳሉ፡፡ ማለትም ካለመረዳት ማንበብ የቋንቋውን ድምጾች የማነብነብ ሂደት ብቻ ይሆናል፡፡ አንብቦ መረዳት በተለያየ መንገድ ሲበየን ይስተዋላል፡፡ ቀደምት ብያኔዎች ዋና ትኩረታቸው በማሰብና ምክንያት በመስጠት ላይ ነው ምሳሌ በParis & Hamilton (2009) የተጠቀሱት Thorndike:: ነገር ግን የቅርብ ጊዜ ብያኔዎች ትኩረታቸው በአንብቦ መረዳት ተራክቧዊና ግንባታዊ ሂደት ላይ ነው (Paris & Hamilton, 2009)፡፡

የምርምርና የእድገት ሪፖርት መረዳትን ከተጻፉ ጽሁፎች ጋር በሚደረግ ተራክቦና ተሳትፎ ትርጉም የማውጣትና የመገንባት ሂደት በሚል ይተረጉመዋል፡፡ በተመሳሳይ አንብቦ መረዳትን የተጻፉ ጽሁፎች ለመገንዘብ የሚደረግ ንቁና ውስብስብ ሂደት፣ ትርጉምን መተንተንና ማዳበር እና እንደ የጽሁፉ አይነት፣ አላማና ሁኔታ ተገቢ ትርጉም የመስጠት ሂደት እንደሆነ Paris & Hamilton (2009) ያስረዳሉ፡፡

ከላይ በተገለጹት የተለያዩ ባለሙያዎች የተሰጠው የአንብቦ መረዳት ብያኔ የምርምሩን ትኩረትና ስፋት ለውጥ ያሳያሉ፡፡ በመጀመሪያ ትኩረቱ የነበረው በአንባቢውና በጽሁፉ መካከል ባለው ግንኙነት አማካኝነት ከጽሁፉ ትርጉም የመለየት ሂደት ላይ ነበር፡፡ ከቆይታ በኋላ ግን የአንባቢውና የጽሁፉ ግንኙነት በአውድ ሲወሰን የሚያሳይ ነው፡፡ ከብያኔው እንደ ሚታየው ለውጡ በማንበብና በማንበብ ሂደት ሞዴል ተጽዕኖ እንደመጣ ያሳያል፡፡ የአንባቢ፣ ጽሁፉና አውዱ ተራክቦ እንደሚከተለው በስዕል ተቀምጧል፡፡




**ስዕል አምስት፡- የአንባቢ፣ የጽሁፍና የአውድ ተራክቦ Pearson, 2009**

## 2.4. የአንብቦ መረዳት ሞዴሎች

በ1960ቹና 1970ቹ የነበረው የአንብቦ መረዳት ሞዴል አንብቦ መረዳትን ከመጻህፍት፣ ከታሪኮችና ጆርናሎች መረጃ የመሰብሰብና የማቀናጀት ሂደት በሚል ይገልጹታል (Fox & Alexander, 2009)፡፡ በዚህ ዘመን ከአንባቢው የሚጠበቀው ግብዓት ከጽሁፉ ውስጥ ተገቢውን መልእክት ማውጣት ስለነበር በጊዜው ተስፋፍቶ አገልግሎት ይሰጥ የነበረው ሞዴል የማውጣትና የመሰብሰብ ሞዴል (*Extraction-Assembly Model)* ነበር (Fox & Alexander, 2009)፡፡

በ1980ቹ አካባቢ አንብቦ መረዳት እይታው ባለሁለት አቅጣጫ እንደሆነ Fox & Alexander (2009) ያስረዳሉ፡፡ ማለትም ጽሁፉን ለመረዳት የአንባቢው ቅድመ እውቀትና አውዱ ወሳኝ ናቸው፡፡ በዚህ ወቅት የነበረው የማንበብ ሂደት ሞዴል የመገንባትና የማዋሃድ ሞዴል (*Constructive-Integrative Model)* በጽሁፉ መልዕክት ላይ እያንዳንዱ ሰው የራሱን ግለሰባዊ መልስ እንዲሰጥ በመፍቀዱ ጽሁፉ ከአንድ በላይ ትርጉም ይኖረዋል (Fox & Alexander, 2009)፡፡

በ21ኛው ክፍለ ዘመን የአንብቦ መረዳት ትኩረት በተለያዩ ባህላዊና አማራጫዊ አውዶች ላይ ማጠንጠን ጀመረ (Fox & Alexander, 2009):: ምክንያቱም ከለውጡ መረዳት እንደሚቻለው ጽሁፍ በማህበረ ባህላዊ አውድና ማህበራዊ ተራክቦ መዳበሩንና አንብቦ መረዳት ውጤታማ የሚሆነው በተጠቀሱት ጉዳዮች ዙሪያ ማጠንጠን ሲችል ነው፡፡ እንደ Fox & Alexander (2009) ቅኝት አንብቦ መረዳት በመረጃ መረብ የሚገኙ መጽሀፎችን መጠቀም፣ ኮሚፒውተር በመጠቀም ዋቢዎችን ማጣቀስ፣ ዋቢዎችን በተገቢው ማደራጀት፣ በመረጃ መረብ የሚገኙ ጋዜጦችን ቅርጽና ዘውግ መለየት፣ የኮሚፒውተር ጽሁፎችን ከታተሙ ጽሁፎች ጋር ማወዳደር፣ የተጠቀሱ ምንጮችና በየመካከሉ የገቡ ስዕሎችና ግራፎችን ሚና መለየት፣ በኮምፒውተር የቀረቡ ጽሁፎችን ከድምጽና ምስል ጋር ማቀናጀትን ሁሉ ያካትታል:: የእነዚህ ነገሮች መካተት አዲሱን የተሻጋሪያዊ ኤክስቴንሽን ሞዴል እንዲታወቅ አድርጓል (Fox & Alexander, 2009)፡፡ በአጠቃላይ ከ1960ቹ ጀምሮ እስካለንበት ጊዜ ድረስ በአንብቦ መረዳት ላይ የተሰሩ ምርምሮች የማውጣትና የመሰብሰብ ሞዴል፣ የመገንባትና የማዋሀድ ሞዴልና ተሸጋጋሪያዊ ኤክስቴንሽን ሞዴል የሚባሉ ሶስት የተለያዩ ሞዴሎችን አስገኝቷል፡፡ የሞዴሎቹ መለያየትም በማንበብ ሂደት ላይ የራሱን አስተዋጽኦ ያበረክታል፡፡

ስለአንብቦ መረዳት ሌላው መነሳት ያለበት ነጥብ እንዴት ይለካል? የሚለው ጥያቄ ነው፡፡ Leslie & Caldwell (2009) እንዳስገነዘቡት አንብቦ መረዳትን መለኪያ ዘዴዎች መደበኛና ኢ መደበኛ ተብለው በሁለት ይከፈላሉ፡፡ ቀደምት የመደበኛ መለኪያ ዘዴዎች አጭር አንቀጽ መጠቀምና ምርጫን ያካትታሉ፡፡ ምርጫ በመጠቀም የሚለኩ ክሂሎችን በዘጠኝ ቡድኖች እንደሚከተለው ከፍለዋቸዋል፡፡ (1) የቃላትን ትርጉም ማስታወስ; (2) ከይዘቱ ውስጥ ያሉትን ቃላት ትርጉም ማጠቃለል; (3) የምንባቡን ቅርጽ መከተል (4) የምንባቡን ዋና ሀሳብ ማቀናጀት (5) በምንባቡ በግልጽ ወይም በስውር የቀረቡ ይዘቶችን መሰረት በማድረግ ለጥያቄዎች መልስ መስጠት (6) ሀሳቦችን በተለያየ አቅጣጫ መረዳት (7) ከይዘቱ ማጠቃለያ ማውጣት (8) የጸሀፊውን ቴክኒክ መለየትና (9) የጸሀፊውን አላማ ነጥብ ድምጸትና አካሄድ መለየት ናቸው፡፡

ከ1970ቹ እስከ 1980ቹ መጀመሪያ ባሉት ጊዜያት የአንብቦ መረዳት መለኪያ የሚያጠነጥነው ቅደም ተከተል በመጠበቅ፣ ዋናውን ሀሳብ በማግኘትና በማጠቃለል

ክሂሎች ላይ ሲሆን በ1980ቹ መጨረሻ አካባቢ ረጅም ምንባቦችን እንዲሁም ቀደምት እውቀትና ብልሀትንም በመጨመር መለካት ተጀመረ (Leslie & Caldwell, 2009)፡፡ ነገር ግን በ2000 መግቢያ ላይ አንብቦ መረዳትን ለመለካት የምንባቡ፣ የጥያቄዎቹ፣ የሰዎቹ፣ የምንባቡ ዘውግና ጭብጥ የመሳሰሉ ተላወጦዎች ተጽዕኖ አብሮ መታየት እንደ ተጀመረ Leslie & Caldwell (2009) ያስረዳሉ፡፡ ከዚህ በተለየ መልኩ የአንብቦ መረዳት መደበኛ መለኪያ መሳሪያ ጥያቄዎችን፣ ማስታወስ ወይም እንደ ገና ማለት፣ ኢ መደበኛ የማንበብ አጋጣሚዎች፣ ግልጽ ውይይቶች ፣ አረፍተ ነገር የመለየት ተግባራትና የተለያዩ የመለኪያ ዘዴዎችን በዋናው ስር ማደራጀት የመሳሰሉ ኢ መደበኛ መለኪያ መሳሪያዎችን ያካትታሉ (Leslie & Caldwell, 2009)፡፡

## 2.5. የአንብቦ መረዳት ደረጃዎች

የተለያዩ ሰዎች የአንብቦ መረዳት ችሎታ ደረጃን በተለያየ መንገድ ሲከፍሉት ይስተዋላል፡፡ አብዛኞቹ ጥናቶች መሰረት የሚያደርጉት ችሎታው ከሚለካበት መሳሪያ አንጻር ነው (Schiefele et al.,2012)፡፡ አብዛኞቹ ጥናቶች የተማሪዎችን የመረዳት ብቃት የሚለኩት ምንባብ አዘጋጅተው ከምንባብ ጋር በተገናኙ የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች ነው፡፡ እነዚህ ጥያቄዎች በአብዛኛው በምርጫ የጥያቄ አቀራረብ ስልት የሚዘጋጁ ናቸው፡፡ ጥያቄዎቹ በተመራማሪው/ዋ/ ሊዘጋጁ ይችላሉ ወይም በሀገር አቀፍ ደረጃ የተዘጋጁ መደበኛ ጥያቄዎች ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ሌሎች ጥናቶች ደግሞ የቃላትን ቀጥተኛ ትርጉም እንዲሁም የቃላት አውዳዊ ፍችንም ጭምር ያካተቱ ሊሆኑ ይችላሉ Becker et al., 2010; Cox & Guthrie, 2001; Lau & Chan, 2003; Law, 2008; Unrau & Schlackman, 2006)፡፡ ቀሪዎቹ ደግሞ መሰረታዊ የአንብቦ መረዳት ክሂልን (ፊደል መለየት፣ ቃላትን መለየት፣ ንበት፣ ለተመሳሳይ ቃላት ትርጉም መስጠት (pseudoword))ን ያካትታሉ Chapman & Tunmer, 1995; Conlon, Zimmer-Gembeck, Creed, & Tucker, 2006; Nurmi & Aunola, 2005)፡፡ በሁሉም ጥናቶች ቃላትን መለየትና መረዳት የአንብቦ መረዳት አንዱ አካል ተደርገው ይወሰዳሉ፡፡

የአንብቦ መረዳት ችሎታን ከፍተኛ የአንብቦ መረዳት ችሎታና ዝቅተኛ የአንብቦ መረዳት ችሎታ ብለው ከመረዳት ደረጃ አንጻር ለሁለት የከፈሉት Schaffner, Schiefele& Ulferts

(2013) ናቸው፡፡ ዝቅተኛ የአንብቦ መረዳት ደረጃ የሚባለው መረዳቱ በቃላትና በሀረጋት ደረጃ ሲሆን ከፍተኛ የአንብቦ መረዳት ችሎታ የሚባለው በአንቀጽና በምንባብ ደረጃ መረዳት ሲቻል ነው፡፡ ደረጃውን በሶስት የከፈሉት ደግሞ Lau & Chan (2003) ናቸው፡፡ እነሱም ዝቅተኛ፣ መካከለኛና ከፍተኛ የአንብቦ መረዳት ችሎታ ሲሆኑ የመጀመሪያው ፊደልን መለየት ሁለተኛው ቃላትንና አረፍተ ነገሮችን መረዳትና ሶስተኛው ምንባቦችን መረዳት ናቸው፡፡

ከውስብስብነቱና ከአስቸጋሪነቱ አንጻር ለአራት የሚከፍሉት በ Schaffner et al., (2013) የተጠቀሱት Lenhard & Schneider (2006) እና Long, Oppy & Seely (1997)ና Carpenter, Miyake & Just (1995) ናቸው፡፡ አራቱ ደረጃዎች እርስ በርስ ተከታታይነትና ተለጣጣቂነት ያላቸው ናቸው፡፡ ከፊደል መለየት እስከ መተንተን ያለውን የሚያጠቃልሉ ናቸው፡፡

የእያንዳንዱን ቃል ትርጉም የማገናዘብ ችሎታ የአረፍተ ነገርንና የጽሁፎችን ትርጉም ለመረዳት መሰረት ነው፡፡ የቃላትን ትርጉም መለየት ከረጅም ጊዜ ትውስታ ከተቀመጠው የቃሉ ሌላ ትርጉም ጋር ለማገናኘት ይረዳል፡፡ ይህም አውዳዊ ፍች ለመስጠት አገልግሎት ይኖረዋል፡፡ በተጨማሪም የቃሉን ስነድምጻዊና ስነፍቻዊ ባህርይውን ለይቶ ለማጠቃለል ያግዛል (Aarnoutse & van Leeuwe, 1998; Duke & Carlisle, 2011)፡፡ በአንባቢው አዕምሮ ውስጥ የሚገኘው የቃላት መጠንና ጥራት ቃላትን ስኬታማ በሆነ መንገድ ለመረዳት እንደቅድመ ሁኔታ ያገለገላል፡፡

አረፍተ ነገርን መረዳት በተለመደ መዋቅር ቃላትን አገናኝቶና አዋህዶ መረዳትን ይጠይቃል (Schaffner et al, 2013)፡፡ ለዚህ አላማ ሲባል ስነመዋቅራዊና ስነፍቻዊ ትንተናዎችም ያስፈልጋሉ፡፡ ጽሁፍን በመረዳት ደረጃ አንባቢው የእያንዳንዱን አረፍተ ነገር መረጃ በመዋሀድ ወጥ ያለው ትርጉም ሊገነባ ይገባል፡፡ በአረፍተ ነገሮች መካከል ያለውን ግንኙነት ለመረዳት ምሳሌን መሰረት ያደረገ ማጣቀሻዎችን ሊጠቀም ይገባል፡፡ ጽሁፍን መረዳት ሁለት ነገሮችን ይይዛል እነሱም ጽሁፍ ተኮርና አውድ ተኮር ሞዴሎች ናቸው (Kintsch, 1998; Zwaan & Singer, 2003)፡፡ ጽሁፍ ተኮር ሞዴሉ በጽሁፉ በግልጽ የቀረበውን ይዘት የሚመለከት ሲሆን አውድ ተኮር ደግሞ በአዕምሮ

ውስጥ ያለውን ሁኔታ በጽሁፉ ካለው ጋር በማጣጣም የሚጠቀምና የሚያገናዝብ ነው፡፡ ይህ ሞዴል ቀደምት እውቀትን መጠቀምን በጣም የሚያበረታታ ነው (Zwaan & Singer, 2003)፡፡ በአጠቃላይ ሲታይ የአንብቦ መረዳት ደረጃዎች ፊደል ከመለየት፣ ቃላትን ከመረዳትና አረፍተ ነገርን ከመረዳት እስከ መገምገምና መተንተን የሚደርሱ ናቸው፡፡ ወይም የአንብቦ መረዳት ችሎታ ቃላትን መረዳት፣ አረፍተ ነገርን መረዳት፣ አንቀጽን መረዳትና ምንባብን መረዳት በሚባሉ አራት ደረጃዎች ይከፈላል፡፡

## 2.6. የማንበብ ተነሳሽነት

አንድ አንባቢ ለማንበብ ርዕስ፣ ሂደትና ግብዓት የሚኖረው ግላዊ ግብ፣ ዋጋና እምነት የማንበብ ተነሳሽነት ይባላል (Guthrie & Wigfield, 2000)፡፡ በሌላ አገላለጽ የማንበብ ተነሳሽነት የማንበብ ተግባራትንና ተሳትፎዎችን ለማበረታታት የሚያስችል የዝግጁነት ብቃት ነው (Schiefele et al., 2012; Wigfield & Guthrie,1997)፡፡ የማንበብ ተነሳሽነት ከጊዜ አንጻር ወቅታዊና ልማዳዊ ተብሎ በሁለት ሲከፈል ከሚያነቃቁት ነገሮች አንጻር ደግሞ ውስጣዊና ውጫዊ ተብሎ በሁለት ይከፈላል (Schiefele and et al, 2012)፡፡ ወቅታዊ የማንበብ ተነሳሽነት የሚባለው አንድ ሰው በአንድ ሁኔታ ውስጥ ለአንድ አላማ ሲል የተወሰነ ጽሁፍ ለማንበብ መፈለግ ሲሆን ልማዳዊ የሚባለው ደግሞ በተገኘው ትርፍ ጊዜ ሁሉ ለማንበብ የመፈለግ ውስጣዊ ባህርይ ነው፡፡ በሌላ አገላለጽ ልማዳዊ የማንበብ ተነሳሽነት በማንበብ ተግባራት ላይ የሚታይ ቋሚ ዝግጁነት ሲሆን ወቅታዊ ግን በሁኔታዎች የሚመጣ ጊዜያዊ ፍላጎት ነው፡፡ ይህ ጊዜያዊ ፍላጎት በተደጋጋሚ የሚከሰት ከሆነ ወደ ልማዳዊ ሊያድግ እንደሚችል Schiefele et al (2012) ያስረዳሉ፡፡

በሌላ መልኩ ከሚያነቃቁት ነገሮች በመነሳት የማንበብ ተነሳሽነት ውስጣዊና ውጫዊ ተብሎ ይከፈላል፡፡ አንድ ሰው ማንበብን በራሱ እንደ ጥቅም በማሰብ ወይም እርካታ ለማግኘት ብሎ ማንበብ ከቻለ ወይም ለማንበብ ከተነሳሳ ውስጣዊ ተነሳሽነት አለው ይባላል፤ በተጨማሪም ጽሁፉ በራሱ ስቦት ለማወቅ የሚያነብ ከሆነም ውስጣዊ ተነሳሽነት ይባላል፡፡ ነገር ግን የተለያዩ ውጤቶችን በመጠበቅ ማለትም በሌሎች ሰዎች ዘንድ ተቀባይነትን ለማግኘት ወይም በመምህርና በወላጅ ለመደነቅ ፈልጎ ማንበብ ውጫዊ ተነሳሽነት ይባላል (Schiefele and et al, 2012)፡፡ ውጫዊ ተነሳሽነት ያላቸው

አንባቢዎች አወንታዊ ግብዓቶችን ለማግኘት ወይም አሉታዊውን ለማስወገድ የሚያነቡ ናቸው፡፡ ለምሳሌ፡-አንድ ተማሪ ከፍተኛ ውጤት አምጥቶ በመምህሩ ለመመስገን ወይም ከወላጆቹ ሽልማት ለማግኘት የሚያነብ ከሆነ ውጫዊ ተነሳሽነት ያለው መሆኑን Wigfield & Guthrie (1997) ይጠቅሳሉ፡፡

ውስጣዊና ውጫዊ ተነሳሽነት በመለኪያነት ሲዘጋጁ እንደ የምሁራኑ አተያይና እንደ ምርምሩ አይነት (አይነታዊና መጠናዊ) ወደ ተለያዩ ዝርዝር ክፍሎች እንደ ሚሸነሸኑ Schiefele et al (2012) ያስረዳሉ፡፡ ምክንያቱም እያንዳንዱ ተላውጦ በማንበብ ባህሪና ብቃት ላይ የራሱ የሆነ ተጽዕኖ ስላለው ነው፡፡ እያንዳንዳቸውን ከምርምር አይነትና ከምሁራን እይታ አንጻር ተከፋፍለው በሚከተለው ሰንጠረዥ ቀርበዋል፡፡

**ሰንጠረዥ 2.1፡-**

***ከአይነታዊ ምርምር የተገኙ የማንበብ ተነሳሽነት መለኪያዎች (Dimensions of Reading Motivation: Results from Qualitative Studies)***

| Guthrie et al. (1996) | Greaney and Numan (1990) | Nolen (2007) | Schiefele and Schaffner (2012) |
|---|---|---|---|
| ጠንካራ ፍላጎት | - | ፍላጎትና አዲስ ነገር ማግኘት | - |
| ተሳትፎ | ማምለጥ፣ መነቃቃት፣ መዝናናት | ፍላጎትና መዝናናት | ምናባዊነት፣ መረጃ መውሰድ፣ መጓጓት፣ መዝናናት፣ መፍታታት |
| ተወዳዳሪነት | አጠቃላይ መማር | እፍረት ማስወገድ፣ | ተወዳዳሪነት |
| እውቅና | ማሸነፍ | - | ማህበራዊ አውድ |
| ውጤት | ጥሩ ውጤት ማምጣት፣ አጠቃላይ መማር | - | ብቃት |
| ተግዳሮት | አጠቃላይ መማር | አዲስ ነገር ማግኘት | - |
| ከስራ ለመራቅ | - | ከማንበብ መራቅ | |
| ማህበራዊ | - | ማህበራዊ አነሳሽ | ማህበራዊ አውድ |
| እድገት | - | እንደ ትምህርት ቤት ተግባር | የትምህርት ቤት ተግባር |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | | ማንበብ | |
| ኢንቨስትመንት | ግብ | ጥሩ ውጤት ለማምጣት ማንበብ | - |
| ለስሜት ለውጥ | ከመጥፎ ስሜት ለመውጣት፣ ለማምለጥ | - | ስሜትን ለመምራት፣ ከመጥፎ ስሜት ለመውጣት፣ ለመፍታታት |
| ሽልማት | - | - | - |
| ልምምድ | - | - | - |
| በራስ መተማመን | - | - | - |
| - | ትክክልና ስህተቱን ለመለየት | - | - |
| - | ከችግር ለመውጣት፣ ከሁኔታዎች ጋር ለመጣጣም | - | መኝታን ለማፋጠን (እንቅልፍን ለማምጣት) |
| - | - | - | ጊዜን ለማሳለፍ |

Guthrie et al. (1996) ጭብጥ ተኮር የንባብ መመሪያ ስልጠና የወሰዱ ተማሪዎችን ቃለመጠይቅ በማድረግ የሰበሰቡትን መረጃ መሰረት አድርገው የዘረዘሯቸው የማንበብ ተነሳሽነት ተላውጦዎች አስራ አራት ሲሆኑ እንደ ሚከተለው በዝርዝር ይቀርባሉ፡፡

- **ጠንካራ ፍላጎት** (Curiosity)፡- በግለሰብ ደረጃ የሚስቡ ርዕሶችን የበለጠ ለመማር የሚደረግ ጥረትን ይመለከታል፡፡
- **ተሳትፎ** (Involvement)፡- በመጽሀፍ ውስጥ የሚገኙ ገጸባህርያትን ችግር እንደ ራስ ማየት፣ ከምንባቡ ከሚገኙ ድርጊቶች ልምድ መቅሰምና ከታሪኩ ትምህርት ማግኘት የሚሉትን ያካትታል፡፡
- **ተወዳዳሪነት** (Competition)፡- ከሌሎች ተማሪዎች የበለጠ ከፍተኛ ውጤት ለማምጣት (ሌሎች ተማሪዎችን ለመብለጥ)

- **እውቅና** (Recognition)፡- በቤተሰብ፣ በጓደኛና በመምህራን ጥሩ አንባቢ ተብሎ ለመጠራት
- **ውጤት**(Grades)፡- በትምህርት ቤቱ የተሻለ ውጤት ለማምጣት
- **ተግዳሮት** (Challenge)፡- ውስብስብና አስቸጋሪ የንባብ መሳሪያዎችን መምረጥ
- **ከስራ ለመራቅ** (Work avoidance)፡- ከትምህርታዊ ንባብ ጋር የተገናኙ ስራዎችን ለማስወገድ (የሚያዝናኑ ጽሁፎች ላይ ብቻ በማተኮር ማንበብ)
- **ማህበራዊ** (Social)፡- ከቤተሰብ፣ ከጓደኛና ከተለያዩ ሰዎች ጋር የሚያገናኙ የንባብ ተግባራትን መምረጥ
- **ለማሟላት /ለመከበር/** (Compliance)፡- ከትምህርት ቤት በሚሰጥ አሳይንመንት ወይም በውጭ አካል ግፊት አማካኝነት ማንበብ
- **ኢንቨስትመንት** (Investment)፡- የረጅም ጊዜ ግብ ለማሳካት ልምድን የማከማቸት ሂደትን ይመለከታል፡፡ ለምሳሌ፡- ኮሌጅ ለመግባት፣
- **ለስሜት ለውጥ** (Emotional tuning)፡- በጊዜው የሚሰማውን ደስ የማይል ወይንም የሚያናድድ ስሜት ለመቀየር፣
- **ሽልማት** (Rewards)፡- በክፍል ውስጥ፣ በቤትና በትምህርት ቤት መጽሀፍ፣ ሜዳሊያ የመሳሰሉ ሽልማቶችን ለማግኘት፣
- **ልምምድ** (Utilitarian)፡- ጌሞች፣ የተለያዩ ሆቢዎችና የሚገባጠሙ ነገሮችን ህግና ቅደም ተከተል ለመማር፣
- **በራስ መተማን** (Efficacy)፡- የማንበብ ባህርያት በቁጥጥር ስር እንደሆኑ ሲሰማና በአንድ ሰው የማንበብ ችሎታ ላይ ለመተማመን፣

Greaney & Neuman (1990) ከተማሪዎች የማንበብ አላማ በስተጀርባ ያለውን ምክንያት ለመወሰን መጠናዊና አይነታዊ የምርምር ዘዴን በማቀናጀት ሰርተዋል፡፡ በመጀመሪያው ክፍል በተለያዩ ሀገራት የሚገኙ የስምንት፣ የአስርና የአስራ ሶስት አመት ተማሪዎችን ማንበብ ለምን እንደሚወዱ በጽሁፍ መልስ እንዲሰጡ ጠይቀዋል፡፡ በሁለተኛው ክፍል ደግሞ ከጽሁፍ ከተተነተኑት አረፍተ ነገሮች በመነሳት የማንበብ ተነሳሽነትን መለኪያ መሳሪያ አዘጋጅተዋል፡፡ በዚህም መሰረት አስር አበይት የተለያዩ የማንበብ ተነሳሽነት ተላውጦዎችን ማውጣት ችለዋል (ሰንጠረዥ አንድን ይመልከቱ)፡፡

የመጀመሪያው አጠቃላይ መማር የሚለው ሲሆን Guthrie et al. (1996) ከጠቀሱት ተወዳዳሪነት፣ ውጤትና ጥንካሬን ማሳየት ከሚሉት ተላውጦዎች ጋር ተመሳሳይነት ሲኖረው ለመማር፣ የተሻለ ለማንበብ ወይም ብቁ ለመሆን የሚል ብያኔ ይሰጡታል፡፡ ለመዝናናት የሚለው ቀጣይ ሀሳብ ስለሚያዝናና፣ ሳቢ ስለሆነ ወይም አስገራሚ ስለሆነ ተብለው የተጠቀሱትን ያካትታል፡፡ ሶስተኛው ለማምለጥ የሚል ሲሆን Guthrie et al. (1996) በአስራ አንደኛ ደረጃ ከጠቀሱት ለስሜት ለውጥ ከሚለው መለኪያ ጋር ተመሳሳይነት አለው፡፡ አራተኛ ደረጃ ላይ የሰፈረው መለኪያ ማነቃቃት (Stimulation) እነ Guthrie et al. (1996) ተሳትፎ ብለው ከገለጹት ሀሳብ ጋር ይጣጣማል፡፡ በቀጣይነት የሰፈረው የአንብቦ መረዳት ተነሳሽነት መለኪያ ጊዜን ለማሳለፍ ወይም ከማያስደስት ስሜት ለመውጣት የሚለው ነው፡፡

በስድስተኛ ደረጃ እንደ መለኪያነት የተጠቀሰው ‘ግብ’ አንባቢው ስራ ለማግኘት፣ ቤተሰብ ለመርዳት ወይም ለወደፊቱ ሀገሩን ለመርዳት ብሎ ለማንበብ የሚነሳሳበትን ምክንያት በመውሰድ የተዘጋጀ ነው፡፡ በ Guthrie et al. (1996) ያልተጠቀሰውና በነዚሁ አጥኝዎች የተገለጸውና ጥሩ ባህሪያትን ለመማር፣ ከታላላቆች ለመቅሰምና ትክክለኛ ለመሆን ማንበብ የሚሉትን ያስከተለው ሌላው መለኪያ ሞራላዊነት የሚለው ነው፡፡ ለራስ ዋጋ መስጠት፣ ከሁኔታዎች ጋር እራስን ለማጣጣምና ጥሩ ውጤት ለማምጣት የሚሉት በተከታታይ ከስምንት እስከ አስር ድረስ የተጠቀሱና በሌሎች ለመደነቅ ወይም ክብር ለማግኘት፣ ራስን በጊዜና በቦታ ለመወሰንና በፈተና ጥሩ ለመስራትና የቃላት እውቀትን ለማሳደግ የሚሉ መግለጫዎችን የያዙ መለኪያዎች ናቸው (Greaney & Neuman, 1990)፡፡

በሶስት አመት የረጅም ጊዜና ውህድ ዘዴ ጥናት ከአንደኛ እስከ ሶስተኛ ክፍል ያሉ ስልሳ ሰባት ታዳጊ ህጻናት ተማሪዎችን ከሁለት የተለያዩ ትምህርት ቤቶች በመውሰድ በእያንዳንዱ አመት ተማሪዎች ለማንበብ ያላቸው ተነሳሽነት በቃለመጠይቅ ከተማሪዎችና ከመምህራን መረጃ በመሰብሰብ የሰሩት ሌላው ተመራማሪ Nolen (2007) ናቸው፡፡ እንደ Nolen (2007) ገለጻ የተነሳሽነት ንድፈ ሀሳብ ተነሳሽነት በራሱ በማህበራዊ ደረጃ ይዳብራል ከሚለው አውድ ተነሳሽነትን የሚቀያይር ነጻ ተላውጦ ነው ወደ ሚለው ሀሳብ ይቀየራል፡፡ ምክንያቱም የእያዳንዱ ሰው ተነሳሽነት በተለያየ ሁኔታ ውስጥ

የተለያየ እንደ ሚሆንና በጊዜ ሂደት ሊዳብር እንደ ሚችል ነው፡፡ በዚህ ንድፈ ሀሳብ መነሻነት የማንበብ ተነሳሽነትን የሚለኩ ስምንት ተላውጦዎችን ያዘጋጁ ሲሆን ሁሉም መለኪያዎችን ከ Guthrie et al. (1996) ጋር ይጣጣማሉ (ሰንጠረዥ አንድን ይመልከቱ)፡፡

የመጀመሪያው ፍላጎት የሚለው በታሪኩ ካሉት ገጸ ባህርያት ጋር መሳተፍ፣ የግል ምርጫ የሆነውን ዘውግ፣ ጸሀፊና ርዕስ ለማግኘት ማንበብ የሚል ሲሆን በ Guthrie et al. (1996) ጠንካራ ፍላጎትና ተሳትፎ ብለው ከተገለጹት ጋር ተመሳሳይ ብያኔ ተሰጥቶታል፡፡ በተከታይነት የቀረበው ለመዝናናት የሚለው መለኪያ በምናብ ለመጠቀምና ለመዝናናት በሚል ተገልጿል፡፡ በሶስተኛ ደረጃ የተጠቀሰው አዲስ ነገር ማግኘት የሚለው መለኪያ ጥሩ አንባቢ ለመሆን፣ በማንበብ አዲስ ነገር ማግኘትና ጠንካራ መጻህፍትን በማንበብ ራስን መፈተን የሚሉ ዝርዝር ነገሮችን አካቷል፡፡ የትምህርት ቤት ተግባር ስለሆነ ማንበብ (የቤት ስራ ወይም አሳይመንት ስለተሰጠ)፣ ማንበብ ለወደፊቱ ህይወት ስለሚጠቅም (የተሻለ ስራ ለመያዝ)፣ ከእፍረት ራስን ለማዳን (ከሌሎች ጋር ሲነጻጸር ጥሩ የሚባል አንባቢ ለመሆን)፣ ከሌሎች ሰዎች ጋር ለመግባባት (ስለመጻህፍት ከሰዎች ጋር ለማውራትና ለመዝናናት)ና ማንበብን ማስወገድ (ጊዜ ስለሚወስድ) የሚሉት በተከታታይ ከአራት እስከ ስምንት የተገለጹ መለኪያዎች ናቸው፡፡

Schiefele & Schaffner (2012) በ Wigfield & Guthrie (1997b), Möller & Bonerad (2007) and እና Schaffner & Schiefele (2007a) የተዘጋጁ የአንብቦ መረዳት መለኪያዎችን በመቃኘትና ሀያ ስድስት የስድስተኛ ክፍል ተማሪዎችን ቃለ መጠይቅ በማቅረብ አስራ ሶስት የማንበብ ተነሳሽነት መለኪያዎችን አዘጋጅተዋል፡፡ እነዚህ መለኪያዎች ባንድም ሆነ በሌላ መልኩ ከላይ በተጠቀሱት ተመራማሪዎች የተገለጹና በሰንጠረዥ አንድ በአራተኛው ረድፍ ላይ የቀረቡ (ምናባዊነት፣ መረጃ መውሰድ፣ መጓጓት፣ መዝናናት፣ መፍታታት፣ ተወዳዳሪነት፣ ማህበራዊ አውድ፣ ብቃት፣ የትምህርት ቤት ተግባር፣ ስሜትን ለመምራት፣ ከመጥፎ ስሜት ለመውጣት፣ ጊዜን ለማሳለፍና ምኝታን ለማፋጠን (እንቅልፍን ለማምጣት) ናቸው፡፡ በአጠቃላይ በአይነታዊ የምርምር አይነት ከተሰሩት አራቱ ጥናቶች እንደ ምንረዳው የማንበብ ተነሳሽነትን ለመለካት የማንበብ ልምድ ዋና መለኪያ መሳሪያ መሆኑን ነው፡፡

በመጠናዊ የምርምር አይነት አስራ አንድ የማንበብ ተነሳሽነት መለኪያዎች በጽሁፍ መጠይቅ መልክ የሚዘጋጁ ሲሆን አስሩ (በራስ መተማመን፣ እድገት፣ ማህበራዊ፣ ከስራ ለመራቅ፣ ጥንካሬን ማሳየት፣ ውጤት፣ እውቅና፣ ተወዳዳሪነት፣ ተሳትፎ፣ ጠንካራ ፍላጎት) በአይነታዊ የምርምር አይነት Guthrie et al. (1996) ከጠቀሷቸው ጋር ተመሳሳይ ናቸው Schiefele and Schaffner (2012)፡፡ ጠቀሜታ የሚለው መለኪያ በጽሁፍ መጠይቁ የተካተተው አስራ አንደኛውና ስኬታማ አንባቢ ለመሆን የሚል ትርጉም ያለው ነው፡፡ በአይነታዊ የታዩት ልምምድ፣ ለስሜት ለውጥ፣ ሽልማትና ኢንቨስትመንት የሚባሉት መለኪያዎች በመጠናዊ የምርምር አይነት ግልጽ ባልሆነ ምክንያት አላካተቷቸውም፡፡

## 2.7. የቤተሰብ ዳራ

ቤተሰባዊ ዳራ የሚለው ጽንሰ ሀሳብ በጣም ሰፊና ውስብስብ ጉዳዮችን የያዘ በመሆኑ የንድፈ ሀሳብ አፍላቂዎች፣ ተመራማሪዎችና ጸሀፊዎች የተለያየ ብያኔና አከፋፈል ሲሰጡት ይስተዋላል፡፡ ቤተሰባዊ ዳራ ሲባል አንድ ሰው ከእናቱ ማህጸን ከተጸነሰበት ከመጀመሪያዋ ቀን ጀምሮ ያለውን የህይወት ኡደት የሚመለከት ሲሆን እናትና አባቱ ያንን ሰው ለመፍጠር ከነበራቸው እድሜ፣ ስሜት፣ የማህበረ ኢኮኖሚያዊ ደረጃ ጀምሮ ወደ ዚች ምድር ከተቀላቀለ በኋላ እናትና አባቱ ያላቸው የስራ የሀይማኖት የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ የቤተሰቡ አጠቃላይ አቀባበል፣ ቁጥር፣ የወንድምና የእህት መኖርና አለመኖር ከጎረቤትና አካባቢዎች ጋር ያለው መስተጋብር እስከ ህይወቱ ፍጻሜ ድረስ ያለውን ቤተሰባዊ ሁኔታ ሁሉ ይመለከታል (Lindo, 2007)፡፡ ከብያኔው መረዳት እንደሚቻለው ቤተሰባዊ ዳራ ውስጥ የሚጠቀሱ ተላውጦዎች በርካታ ሲሆኑ ለመለካት የማያስቸግሩ ዋና ዋና የሚባሉትና በአብዛኛው ተመራማሪ የሚጠቀሱ የጋራ የሆኑ ቤተሰባዊ ዳራዎች የሚከተሉት ናቸው (Lindo, 2007; Khayyer, 1994; Snow et al., 1991; Patterson et al., 1990; Jencks & Phillips, 1998; Duncan & Magnuson, 2005) ፡፡

### 2.7.1. ገቢ

የቤተሰብ ገቢ ማለት በጉልበትም ሆነ በአዕምሮ ስራ የሚመጣን ገንዘብ የሚመለከት እንደሆነ Snow et al. (1991) ያስረዳሉ፡፡ የቤተሰብ ገቢ ቤተሰባዊ ዳራን ለመለካት

የሚያስችል ዋነኛውና ጠቃሚው መስፈርት ነው። ምክንያቱም ከፍተኛ ገቢ ያለው ቤተሰብ ለልጆቹ የተለያዩ የመማሪያ መሳሪያዎችን ይገዛል፤ የጥናት ጊዜና ቦታ ያመቻቻል እንዲሁም የተሻለ ገቢና የትምህርት ደረጃ ያለው የጎረቤት ልጅ ያገኛል። በአጠቃላይ የገቢው ሁኔታ የማህበረ ባህላዊ ደረጃውን ይወስነዋል (Lindo, 2007; Khayyer, 1994; Snow et al., 1991; Patterson et al., 1990; Jencks & Phillips, 1998; Duncan & Magnuson, 2005) ።

### 2.7.2. ስራ

በአብዛኛው ተመራማሪ ትኩረት የሚሰጠውና ቤተሰባዊ ዳራን ለመለካት የሚያስችለው ሌላው መስፈርት የእናትና የአባት የስራ ሁኔታ ነው። ስራ ማለት እናት ወይም አባት ወይም ሁለቱም ለቤተሰቡ ማህበረ ኢኮኖሚያዊ ደረጃ የሚኖራቸውን ሀላፊነት ይመለከታል። የእናት እቤት መዋልና አባት ወደ ስራ መሄድ ወይም በተቃራኒው የእናት ስራ መሄድና አባት ቤት ውስጥ መዋል የተማሪውን የአረዳድ ሁኔታ ይወስነዋል። ከዛ በተጨማሪ የስራው አይነት፣ የመስሪያ ቤቱ ሁኔታና የስራ ደረጃ ሁሉ በዝርዝር መታየት ይኖርበታል (Lindo, 2007; Khayyer, 1994; Snow et al., 1991; Patterson et al., 1990; Jencks & Phillips, 1998; Duncan & Magnuson, 2005) ።

### 2.7.3. የቤት ውስጥ ግብኣት

በሶስተኛ ደረጃ የሚጠቀሰው የቤተሰባዊ ዳራ መለኪያ በቤት ውስጥ የሚገኙት የመማሪያ ግብዓቶች መጠንና አይነት ነው። በቤት ውስጥ የሚገኙት መጻህፍት ብዛት፣ ስዕሎች፣ ታሪካዊ ቅርሶች በአጠቃላይ ባህላዊና ትምህርታዊ ምንጮች በተማሪዎች የትምህርት ውጤት ላይ የራሳቸው ሚና ሲኖራቸው ሚናቸው ከሀገር ሀገር ከቦታ ቦታ ሊለያይም ይችላል። ምክንያቱም በአንዳንድ በትምህርት በበለጸጉ ሀገራት እንደዚህ አይነት መሳሪያዎችን በየቤቱ ማግኘት የተለመደ ሲሆን ትምህርት ባልተስፋፋባቸው የሶስተኛ አለም ሀገራት ደግሞ ሙሉ ለሙሉ እንደዚህ አይነት መሳሪያዎችን ማግኘት ይከብዳል። ያ ብቻ ሳይሆን የሚገኙት መጻህፍትና ስዕሎች አይነትና መጠን የተለያየ መሆኑ በራሱ የራሱ የሆነ አስተዋጽኦ ስላለው ያንን ለመለካት አስቸጋሪ ሆናል። ምክንያቱም

እያንዳንዱ መጽሀፍ የራሱ የሆነ ጠንካራና ደካማ ጎን አለው እንዲሁም መኖሩ ብቻ ሳይሆን የተማሪው የመጠቀምና ያለመጠቀም ሁኔታ ሁሉ የራሱ ተጽዕኖ ይኖረዋል (Lindo, 2007; Khayyer, 1994; Snow et al., 1991; Patterson et al., 1990; Jencks & Phillips, 1998; Duncan & Magnuson, 2005) ፡፡

### 2.7.4. የቤተሰብ መዋቅር

የቤተሰብ መዋቅር ሲባል የቤተሰቡ አሰተተዳደራዊ ሁኔታና አወቃቀር ምን ይመስላል የሚለውን የሚመለከት ነው፡፡ ማለትም የቤተሰቡ አስተዳዳሪ ማነው አባት እናት ወይስ እንጀራ አባት ሌላ ተደራቢ ቤተሰብና አያቶች አሉ የቤተሰብ መዋቅሩን የሚመራው ሰው ጾታና የስራ ሁኔታ ወይም በአንድ ወላጅ ብቻ የሚመራ መሆንና አለመሆን እንዲሁም የቤተሰቡ የርስ በርስ ቁርኝት በመዋቅሩ ውስጥ ይካተታል፡፡ የእያንዳንዱ ቤተሰብ የስራ ሁኔታና የገቢ መጠን፣ በትምህርት ላይ ያላቸው አቋም፣ ከተማሪው እድሜ ጋር ያላቸው ቅርበትና ርቀት ሁሉ በተማሪው የአንብቦ መረዳት ችሎታ ላይ የራሱን ተጽዕኖ ያሳድራል (Lindo, 2007; Khayyer, 1994; Snow et al., 1991; Patterson et al., 1990; Jencks & Phillips, 1998; Duncan & Magnuson, 2005) ፡፡

### 2.7.5. የትምህርት ደረጃ

የቤተሰብ የትምህርት ደረጃ በተማሪዎች የትምህርት ውጤት ላይ ተጽዕኖ እንደሚፈጥር እሙን ነው፡፡ በተለይም የእናት የትምህርት ሁኔታ ከአባት የትምህርት ሁኔታ በበለጠ ከተማሪዎች የትምህርት ውጤት ጋር ጠንካራ ግንኙነት አለው፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞ የቤተሰብ የማስተማር ስልት፣ የቤት ውስጥ መማር ሁኔታና የተማሪው ባህርይ ይጠቀሳል(Lindo, 2007; Khayyer, 1994; Snow et al., 1991; Patterson et al., 1990; Jencks & Phillips, 1998; Duncan & Magnuson, 2005) ፡፡

### 2.7.6. ሀይማኖት

በተለይም በሀገር አቀፍ ደረጃ መረጃ ሲሰበሰብና ሀይማኖታዊ ስብጥር ባለበት አካባቢ ጥናቱ ሲካሄድ የተማሪዎችን የሀይማኖት አይነት ማየቱ ጠቀሜታ ይኖረዋል (ብዙ ጊዜ

አንድ ሰው የቤተሰቡን ሀይማኖት ስለሚከተል)፡፡ ምክንያቱም በሀይማኖት ደረጃ ለመደበኛ ትምህርት ትኩረት የሚሰጥ ወይም የማይሰጥ ይኖራል፡፡ በርግጥ አንዳንድ ሀገራት በአንድ ሀይማኖት ብቻ ሊመሩ ይችላሉ፡፡ ጥናቱ በእንደዚህ አይነት ሀገራት ሲካሄድ ከቤተሰብ ዳራ ጋር አያይዞ ሀይማኖትን መቃኘቱ ላያስፈልግ ይችላል (Lindo, 2007; Khayyer, 1994; Snow et al., 1991; Patterson et al., 1990; Jencks & Phillips, 1998; Duncan & Magnuson, 2005) ፡፡

## 2.8. የቀደምት ስራዎች ቅኝት

የአንብቦ መረዳት ችሎታ በርካታ ነገሮች ተጽእና የሚፈጥሩበት የክሂል አይነት ሲሆን ተጽዕኗቸው አሉታዊም አወንታዊም ሊሆን ይችላል፡፡ እነዚህ ተጽዕኖ ፈጣሪ ነገሮች የአንባቢው ባህርይ፣ የጽሁፉ አጠቃላይ ሁኔታና የአቀራረቡ ብልሀት ተብለው በሶስት አበይት ክፍሎች እንደሚከፈሉ Janan (2011) ያስረዳሉ፡፡ በሌላ አባባል አንብቦ የመረዳት ችሎታ በአንባቢው ችሎታና ማንነት፣ በአንባቢው ማህበራዊና ቤተሰባዊ ዳራ፣ በትምህርት ቤቱ ሁኔታ፣ በአስተማሪውና ከቀረበው ጽሁፍ በሚያገኘው መረጃ አይነት፣ ባህርይና ግልጽነት ተጽዕኖ ሊደርስበት ይችላል፡፡

እነዚህ ተጽዕኖ ፈጣሪ ነገሮች ተጽዕኗቸው ምን ያክል እንደሆነ እንዲሁም ተጽዕኗቸው አወንታዊ ነው ወይስ አሉታዊ የሚለውን ለመለየት ብዙ ምርምሮች ተሰርተዋል፡፡ በዚህ ጥናትም ከጥናቱ ጋር ከፍተኛ ቅርበት ያላቸው ጥናቶች እንደሚከተለው በአጭሩ ቀርበዋል፡፡ በቅድሚያ የሰፈሩት የአንብቦ መረዳት ከቤተሰብ ዳራ ጋር በማያያዝ የተጠኑት ጥናቶች ሲሆኑ በመቀጠል የቀረቡት ደግሞ የማንበብ ተነሳሽነትን ከአንብቦ መረዳት ችሎታና ከቤተሰብ ዳራ ጋር በማዛመድ የተጠኑት ናቸው፡፡

የቤተሰብ ዳራን ከተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ችሎታ ጋር በማገናኘት ከሚያጠኑት መካከል PIRLS “የትምህርታዊ ጽሁፎችን የማንበብ ችሎታ እድገት ጥናት” በሚል ርዕስ በየአምስት አመቱ የሚያካሂደው ጥናት በግንባር ቀደምትነት ይጠቀሳል፡፡ ይህ ጥናት ከ2001 እ.ኤ.አ. ጀምሮ በየአምስት አመቱ የተማሪዎችን የአንብቦ መረዳት ችሎታ ከቤትና ከትምህርት ቤት አውድ ጋር በማዛመድ በተለያዩ 60 ሀገራት የሚያጠና አለም አቀፍ ጥናት ነው፡፡

PIRLS ጥናቱን በሚያካሂድበት ጊዜ የማንበብን አላማ ለሁለት፣ የአንብቦ መረዳት ሂደትን በአራት ክፍሎ ይቃኛል። አንደኛው የማንበብ አላማ በማንበብ መረጃን የማግኘትና የመጠቀም ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ትምህርታዊ ጽሁፎችን የማንበብ ልምድን ማዳበር ናቸው። እንደ PIRLS አገላለጽ የአንብቦ መረዳት የመጀመሪያው ሂደት በግልጽ የሰፈሩ መረጃዎች ላይ ማተኮርና ማውጣት ነው። ሁለተኛው ተፈላጊውን መረጃ መወሰን፣ ሶስተኛው መረጃዎችንና ሀሳቦችን መተንተንና ማዋሀድና አራተኛው ይዘቶችን መገምገምና መተቸት ናቸው (Mullis et al, 2015)። የጥናቱ ተሳታፊ ሀገራት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመሩ በ2016 በተደረገው ሪፖርት ከ60 በላይ ሀገራት ተሳትፈውበታል። ምርምሩ በዋናነት የሚመራው ቦስተን በሚገኝ አለም አቀፍ የምርምር ማዕከል ሲሆን በጸሀፊነት አምስተርዳም፣ በመረጃ ሂደት ሀምቡርግ፣ በስታስቲክስ ትግበራና ቁጥጥር እንዲሁም በንሞና ሂደት ካናዳና በጥያቄ ማዳበርና በስነ ትምህርታዊ ፈተናዎች እንግሊዝና አውስትራልያ የተሳተፉበት በጣም ትልቅ የሚባል የረጅም ጊዜ ጥናት ነው (Mullis et al, 2015)።

PIRLS በጥናቱ የሚያተኩረው በአራተኛ ክፍል ተማሪዎች ቢሆንም ከተማሪዎች በተጨማሪ ምንጊዜም ትምህርት ቤቱን፣ መምህራንና ወላጆችን የጥናቱ ተሳታፊ ያደርጋል። ስርዓተ ትምህርቱንና መመሪያውንም ይገመግማል (Mullis et al, 2015)። እንደ (Mullis et al, 2015) ገለጻ የቤተሰብ ዳራ የተማሪዎችን የአንብቦ መረዳት ችሎታ የሚተነብይ ተላውጦ ሆኖ ተገኝቷል። የመተንበይ ደረጃውና ሁኔታው ከሀገር ሀገር የተለያየ መሆኑን የጥናቱ ውጤት ያሳይል። የአንብቦ መረዳት ችሎታ መለኪያ መሳሪያዎችም ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተሻሻሉ መጥተዋል። በ2001፣ በ2006፣ በ2011ና በ2016 የተደረገው የምርምር ውጤት ሪፖርት እንደሚያሳየው የቤተሰብ ዳራ በአንብቦ መረዳት ችሎታ የመተንበይ መጠኑ ከፍተኛ ነው። እንደ መፍትሄም የተጠቆመው የተማሪዎችን የአንብቦ መረዳት ችሎታ ለማዳበር የቤተሰብ ዳራ ትኩረት ውስጥ መግባት እንዳለበትና የስርዓተ ትምህርት ቀራጮችና ትምህርት ቤቶችም ይህንን ነገር ማስፈጸም እንዳለባቸው ነው።

በ2001 በተደረገው የPIRLS ጥናት ትኩረት የተደረገበት የአንብቦ መረዳት ችሎታ በሶስት ይከፈላሉ። እነሱም የመረዳት ሂደት፣ የማንበብ አላማና የማንበብ ባህሪና

አመለካከት ናቸው (Campbell, et al, 2001)፡፡ የመረዳት ሂደትና የማንበብ አላማ የሚለኩት በጽሁፍ በተዘጋጁ የአንብቦ መረዳት ፈተና የሚለኩ ሲሆን የማንበበ አመለካከትና የማንበብ ባህርይ በጽሁፍ መጠይቅ ተለክተዋል፡፡ የመረዳት ሂደት ሲባል ዝርዝር ሀሳቦችን ማውጣት፣ ምንጮችን መጥቀስ፣ የተገኙትን መረጃዎችና ሀሳቦች መተርጎምና ማዋሀድ እንዲሁም ጽሁፍን መገምገምና መተቸት መቻል ነው፡፡ እነዚህን ደረጃዎች ማለፍ መቻል ማንኛውም አንባቢ አቀራረቡን እንዲያስተካክልና የመረዳት ችሎታውን እንዲፈትሽ የሚያስችለውን ልዕለ አዕምሮታዊ የብልሀት አጠቃቀም ለመጠቀም ያስችላል፡፡ በተጨማሪም አንባቢው ወደ ጽሁፉ ይዞት የሚመጣው ልምድና እውቀት ጽሁፉን ለመረዳት የሚጠቀምበትን ነው፡፡ የአንብቦ መረዳት ሂደትን በአራት ደረጃዎች ይከፍሉታል፡፡ እነሱም በግልጽ የቀረበው መረጃ ላይ ማተኮርና ማውጣት፣ ሁለተኛ በግልጽ ለቀረቡት መረጃዎች ቀጥተኛ ውሳኔ መስጠት፣ ሶስተኛ መረጃዎችንና ሀሳቦችን መተንተንና ማዋሀድ በመጨረሻም የቀረቡትን ይዘቶች፣ ቋንቋዎችና አውዳዊ ጉዳዮችን መገምገም ናቸው፡፡

የማንበብ አላማ ቀጥታ የሚገናኘው ሰዎች ለምን ያነባሉ ከሚለው ጋር ነው፡፡ ይህም ግላዊ ፍላጎት ስላላ ማንበብ፣ ለደስታ ማንበብ፣ በማህበረሰቡ ተሳታፊ ለመሆን ማንበብና ለመማር ማንበብ የሚሉ ምክንያቶችን ያካትታል፡፡ ለወጣት አንባቢዎች የማንበብ አላማ የሆነው ለፍላጎት፣ ለደስታ ወይም ለመማር ነው፡፡ የ2001 PIRLS ጥናት ትኩረት ያደረገው በሁለቱ የማንበብ አላማዎች ነው፡፡ እነሱም ለልምድ ማንበብና መረጃ ለማግኘትና ለመጠቀም ማንበብ ናቸው፡፡ ምክንያቱም ሁለቱ አላማዎች በተጠኚዎች እድሜ ጠቃሚዎች በመሆናቸው ነው፡፡

በዝቅተኛ የክፍል ደረጃዎች የሚገኙ ልጆች ከማንበብ ጋር የተገናኘ አመለካከታቸውንና ባህሪያቸውን የሚያገኙት ከትምህርት ቤትና ከቤት ነው፡፡ ትምህርት ቤት ውስጥ የሚያገኟቸው የተወሰኑና መደበኛ ሲሆኑ በቤት ውስጥ የሚያገኟቸው ደግሞ ተፈጥሯዊ፣ ኢ መደበኛና በልጆች የእለት ከዕለት ተግባራት ላይ ያተኮረ ናቸው፡፡ ሁለቱም ለህጻኑ የማንበብ እድገት የራሳቸው አስተዋጽዖ አላቸው፡፡ በበለጠ እያንዳንዱ ሁኔታ እርስ በርስ ስለሚደጋገፍ በቤትና በትምህርት ቤት መካከል ያለውን ተግባቦት ስለሚያፋጥን ለመማር የራሱ ጠቀሜታ ይኖረዋል፡፡ በህጻናት የአንብቦ መረዳት ችሎታ

ላይ ተጽዕኖ ከሚፈጥሩት ትምህርት ቤትና መኖሪያ ቤት ባሻገር የሚኖሩበትና የሚማሩበት ሰፊው አካባቢም ተጽዕኖ ይኖረዋል፡፡ ስለተጽዕኖው መረጃ ለማግኘትም PIRLS 2001 ተማሪዎች፣ ወላጆችና የትምህርት ቤቱ ርዕሳነ መምህራን በጽሁፍ መጠይቅ መረጃ ሰጥተዋል፡፡

የተማሪዎችን የማንበብና የመጻፍ ችሎታ እንዲሁም ከጽሁፉ መረጃ የመውሰድ ችሎታ ለመለካት የተጠቀሙት የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ የጽሁፍ መጠይቅና ፈተና አገልግሎት ላይ ውሏል፡፡ ለእያንዳንዱ ፈተና አላማውን መሰረት በማድረግ ሁለት ሁለት ሰዓት በመስጠት ተፈትነዋል፡፡ የተዘጋጁት ምንባቦች ከተማሪዎች የዕለት ከዕለት እንቅስቃሴ ጋር የተገናኙ ይዘቶችን ይዘዋል፡፡ ይህም በጊዜ እጥረት የሚመጣውን ችግርና የይዘት አዲስነት የሚያመጣውን መደናገር ለመቀነስ ታስቦ ነው፡፡ እንዲሁም ፈተናው የተለያየ አላማ ስላለው ለእያንዳንዱ አላማ በመከፋፈል ተሰጥቷል፡፡ የተወሰዱት ምንባቦች ከይዘት ተገቢነታቸው በተጨማሪ የተነባቢነታቸው ባህርይም በየሀገራቱ በሚገኙ ስርዓተ ትምህርት ባለሙያዎችና በትምህርት ባለሙያዎች ተገምግሟል፡፡ የመገምገሚያ መስፈርቶቹ ከዕድሜ ደረጃ ጋር ተመጣጣኝ መሆናቸው፣ ስርዓተ ጾታን መጠበቃቸው፣ ከዘርና ከጎሳ እንዲሁም ከሀይማኖት ንክኪ ነጻ መሆናቸው፡፡ ከስነልሳን ደረጃና ተፈጥሯዊነት ባህርይ ጋር መጣጣማቸው፡፡ ከመረጃ መጠን አንጻር ያላቸው ተገቢነት፣ ለመፈተን ከተሰጠው ጊዜ አንጻር ያለው ርዝመት ከ1000 ቃላት ያልበለጠ መሆን የሚሉት ሁሉ ታይተዋል፡፡ የፈተና አወጣጡ ምርጫና አጭር መልስ ስጥ ናቸው፡፡ ምርጫዎቹ አራት አራት አማራጮችን ይዘዋል፡፡ ጥያቄዎች ግልጽና ያልተንዛዙ ናቸው፡፡ አጭር መልስ ስጡ የሚሉት ጥያቄዎች ተማሪዎች በአግባቡ የተገነባ ምላሽ በጽሁፍ ይሰጡበታል፡፡ የጽሁፍ መጠይቅ በተጨማሪነት ለተማሪዎች፣ ለቤተሰብ፣ ለመምህርና ለትምህርት ቤት ርዕሳነ መምህራን አቅርቧል፡፡

Campbell, et al (2001) እንደገለጹት በ2001 በተደረገው የ PIRLS ጥናት ተሳታፊዎች እድሜያቸው ከዘጠኝ እስከ አስር የሚሆኑ የአራተኛ ክፍል ተማሪዎች ናቸው፡፡ የተመረጡት ተማሪዎች ስለማንበብና ለመማር እንዴት እንደሚነበብ ያውቃሉ፡፡ ጥናቱ በ35 ሀገራት መረጃ ሰብስቦ በተሰራው ውጤት የሴቶች የአንብቦ መረዳት ውጤት በሁለቱም የማንበብ ሂደቶች ከወንዶች ጉልህ በሆነ ደረጃ በልጦ ተገኝቷል፡፡ ይህ ውጤት

የታየው በሁሉም ሀገራት ተመሳሳይ ውጤት አምጥቷል፡፡ በከፍተኛዎቹ የአንብቦ መረዳት ችሎታዎች ማለትም በማብራራት፣ በመተርጎምና በመገምገም በጣም ከፍተኛ ልዩነት የታየባቸው ሀገራት አሉ፡፡ በተለይም ያደጉ ሀገራት የአንብቦ መረዳት ችሎታ ከተቀመጠው አማካይ ነጠብ በልጦ ተገኝቷል፡፡

Mullis, Kennedy, Martin & Sainsbury (2006) እንደገለጹት የ PIRLS የ2006 ጥናት አብዛኛው ነገሩ ከ2001 ጋር ተመሳሳይነት ያለው ነው፡፡ የማንበብ ብያኔው የማንበብ ሂደቱ፣ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴው፣ የመረጃ አሰባሰብ ሂደቱ ሁሉም በ2001 ከተደረገው ጥናት ጋር ተመሳሳይ ነው፡፡ በጥናቱ ከአጠቃላይ የአንብቦ መረዳት ሂደት ጀምሮ ጾታን፣ ዘርንና የቤት ውስጥ ሁኔታን ሁሉ ዳሷል፡፡ ከ2001 የሚለየው ዘርንና የቤት ውስጥ ግብዓትን በማካተቱ ነው፡፡ በውጤቱም የቤት ውስጥ ግብዓት ለአንብቦ መረዳት ተጽዕኖ እንዳለው አረጋግጧል፡፡ በአንብቦ መረዳት ውጤት የየሀገራቱና በጾታ ያለው ልዩነት ከ2001 ጋር ተመሳሳይ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

Mullis, Martin, Kennedy, Trong, & Sainsbury (2011) የ PIRLS የ2011 ጥናት በ2001ና በ2006 ከተካተቱት ተላውጦዎች በተጨማሪ የንባብ አውድ፣ የቤት ውስጥ ሁኔታ፣ የተማሪዎችን ዳራና ለማንበብ ያላቸውን አመለካከት፣ የማንበብን ስርዓተ ትምህርት፣ ስለመምህራን የትምህርትና የስልጠና ሁኔታ፣ የክፍል ውስጥ ባህርይና አተገባበርና የማንበብ መማርና ማስተማር የሚካሄድበት የትምህርት ቤቱ ሁኔታ ተካተዋል፡፡ የጥናቱ ውጤት የሚያሳየው የተሻለ የቤት ውስጥ ግብዓት ያላቸው ተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ውጤት ከሌላቸው የተሻለ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

የ PIRLS የ2016 ጥናት በ50 ሀገራት ተካሂዶ ውጤቱ የሚያሳየው የአንብቦ መረዳት ችሎታው እንደየሀገራቱ የተለያየ መሆኑን ነው፡፡ ከመሰረታዊ ክሂል እስከ ከፍተኛው የመረዳት ችሎታ ድረስ በተደረገው አሰሳ ከፍተኛ ልዩነት ታይቷል፡፡ የራሺያና የሲንጋፖር ተማሪዎች ከፍተኛውን ውጤት አሳይተዋል፡፡ አብዛኞቹ ሀገራ መሻሻል ሲያሳዩ የሁለት ሀገራት ግን ቀንሶ ተገኝቷል፡፡ የአንብቦ መረዳት ችሎታ በጾታ በተደረገው ንጽጽር ከ50ቹ ሀገራት በ48 ላይ ሴቶች ከወንዶች የተሻለ ውጤት አስመዝግበዋል፡፡ ለንባብ ከሚያግዙ ቁሳቁሶች አንጻር የተሻለ ግብዓት ያላቸው ተማሪዎች

የተሻለ አንባቢዎች ሆነው ተገኝተዋል፡፡ ወላጆቻቸው ለማንበብ የተሻለ አመለካከት ያላቸው ልጆች የተሻሉ አንባቢዎች ሆነው ተገኝተዋል፡፡ ጥሩ ትምህርት ቤት የሚማሩ ልጆች፣ ትምህርታቸውን በትክክል የሚከታተሉ ልጆች፣ ከቤተሰቦቻቸው ድጋፍ የሚያገኙ ልጆችና በመጀመሪያዎቹ የትምህርት ዘመናት ለማንበብ ትኩረት የሚሰጥባቸው ትምህርት ቤቶች የሚማሩ ልጆች የአንብቦ መረዳት ችሎታ ከፍተኛ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

የቤተሰብ ዳራን ከአንብቦ መረዳት ችሎታ ጋር በማዛመድ ያጠኑት Patterson et al. (1990) በጥናታቸው እንዳረጋገጡት የተማሪዎች የአንብቦ መረዳት፣ የሂሳብና የጽህፈት ክሂል ውጤት በቤተሰብ ገቢ፣ ዘር፣ ጾታና የሁለቱም ወላጆች ድጋፍ ጉልህ በሆነ መንገድ ይተነበያል፡፡ ልዩነቱም 25 ፐርሰንት ደርሷል፡፡ ማለትም ዝቅተኛ ገቢ ካላቸው ቤተሰቦች የሚመጡ ተማሪዎች፣ ጥቁር የአፍሪካ አሜሪካውያን፣ ወንዶችና በአንድ ወላጅ ብቻ ድጋፍ የሚደረግላቸው ልጆች ዝቅተኛ ውጤት አስመዝግበዋል፡፡ በተመሳሳይ Duncan & Magnuson (2005) ማህበረ ኢኮኖሚያዊ ደረጃን (ተማሪዎች በቤት ውስጥ ያላቸውን የመጻህፍት ብዛት፣ ተማሪዎች ወደ መዋለ ህጻናት የገቡበትን እድሜ፣ ህጻናት ሲወለዱ የነበራቸውን የክብደት መጠን፣ እናት ስትወልድ የነበረችበትን እድሜና ያገኘችውን የጤና ድጋፍ) ጥያቄ ውስጥ በማስገባት በአንብቦ መረዳት ፈተና ውጤት በአፍሪካ አሜሪካውያንና በአውሮፓ አሜሪካውን መካከል ልዩነት አግኝተዋል፡፡ እንደ Jencks & Phillips (1998) and Snow et al. (1991) የመሳሰሉ ተመራማሪዎችም ተመሳሳይ ውጤት አምጥተዋል፡፡ ከላይ የተዘረዘሩት ምርምሮች ምንም እንኳን ጉልህ ልዩነት እንዳለ ቢያረጋግጡም አንብቦ የመረዳት ችሎታን በተለየ የዳሰሱ ግን አልነበሩም ሂሳብንና ጽህፈትንም በአንድ ላይ አካተው ያጠኑ ናቸው፡፡

የአንድን ሰው ማህበራዊ መዋቅር የሚወስነው የተለመደ መስፈርት የራሱ ወይም የቤተሰቡ የኢኮኖሚ ሁኔታ እንደሆነ ይታወቃል፡፡ ይህ መስፈርት በቤተሰብ ገቢ፣ በሀብት፣ በኢኮኖሚ ደረጃናና በቅጥር ሁኔታ የሚለካ ይሆናል፡፡ የቤተሰብ ገቢ ማለት በጉልበትም ሆነ በአዕምሮ ስራ የሚመጣን ገንዘብ የሚመለከት ሲሆን ከአንብቦ መረዳት ጋር ተዛምዶ እንዳለው Snow et al. (1991) በጥናታቸው አረጋግጠዋል፡፡ ከገቢ ጋር ተቀራራቢ ይዘት ያላቸው የሀብት መጠንና የገቢ መጠን ሲሆኑ እነዚህ ነገሮችም

የተማሪውን የአንብቦ መረዳት ችሎታ የሚተነብይ ሲሆን የቅጥር ሁኔታው ትንበያ ግን ጉልህ አለመሆኑን በጥናታቸው ውጤት አሳይተዋል Snow et al. (1991)፡፡

በአጠቃላይ የቤተሰብ ዳራ በዝርዝር ደግሞ የቤተሰብ ገቢ፣ የቤተሰብ መዋቅር፣ የቤት ውስጥ ግብዓት፣ ሀይማኖት፣ ስራ፣ የጎረቤት ሁኔታ፣ የስደት ሁኔታ ዘርና ሌሎችንም ሙሉ በሙሉ በመውሰድ ወይንም የተወሰኑትን ብቻ በመውሰድ ከአጠቃላይ የትምህርት ውጤት ጋር በማዛመድ የሰሩ አሉ፡፡ በተለይም በአንብቦ መረዳት ጋር በማዛመድ የሰሩ አሉ፡፡ ከአንብቦ መረዳት ጋር የሰሩት ተዛምዶውንና የመተንበይ ደረጃውንም ጭምር የዳሰሱ ሲሆን አንድ ወጥ ምላሽ ያስገኙ ግን አልነበሩም (Lindo, 2007; Khayyer, 1994; Snow et al., 1991; Patterson et al., 1990; Jencks & Phillips, 1998; Duncan & Magnuson, 2005)፡፡

በኢትዮጵያ የቤተሰብ አያያዝ የትምህርት ተነሳሽነት ለትምህርት ያለው ግለ ግምት በትምህርት ውጤት ላይ ያለው ተጽእኖ በኢትዮጵያ በሚገኙ ዩኒቨርሲቲዎች በሚል ርዕስ አየለ (2012) የሰሩት ምርምር ይጠቀሳል፡፡ ምርምሩ ያካሄዱት በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ በወላይታ ሶዶ ዩኒቨርሲቲና በኮተቤ መምህራን ኮሌጅ ሲሆን በእድል ሰጭ የንሞና ዘዴ 2116 ሴት 760 ወንድ 1353 የአንደኛ አመት ተማሪዎችን በመምረጥ ነው፡፡ በተለያዩ የመተንተኛ ዘዴዎች የተሰበሰበው መረጃ ተተንትኖ የቤተሰብ አያያዝ በተማሪዎች የትምህርት ተነሳሽነት ላይ ተጽዕኖ እንዳለውና የማንበብ ተነሳሽነት ደግሞ በትምህርት ውጤት ላይ አወንታዊ ተጽዕኖ እንዳለው የጥናት ውጤቱ ያሳያል፡፡ ይህ ጥናት የቤተሰብ ድጋፍን የትምህርት ተነሳሽነትንና የትምህርት ውጤትን ማየቱ የቤተሰብ ዳራ፣ የማንበብ ተነሳሽነትና የአንብቦ መረዳት ችሎታን ተዛምዶ ከሚዳስሰው ከዚህ ጥናት ጋር በመጠኑ ይመሳሰላል፡፡ የአየለ ጥናት አጠቃላይ የትምህርት ውጤትን መዳሰሱ ሲሆን ይህ ጥናት ግን ቋንቋ ላይ ከቋንቋም የአንብቦ መረዳት ላይ ብቻ ማተኮሩ ዝርዝር መረጃ ለማግኘት ይጠቅማል፡፡ በተጨማሪም ይህ ጥናት የቤተሰብ ዳራን በጥልቀት የሚዳስስ ሲሆን የአየለ ግን የቤተሰብ አያያዝን ብቻ ያጠና መሆኑ ክፍቱን ለመሙላት ይህ ጥናት መጠናት አለበት ተብሎ በአጥኝዋ ይታመናል፡፡

የቤተሰብ ዳራ ከሚለው ተላውጦ ውስጥ በቤት ውስጥ የሚገኙ ቁሳቁሶችንና የቤተሰብ ድጋፍ የሚለውን ነጥሎ በመውሰድ ከአንብቦ መረዳት ችሎታ ጋር በማዛመድ የተሰራው

የነ Wainer& Piper (2010) ጥናት በኢትዮጵያ ከተሰሩት ውስጥ በዋናነት የሚጠቀስ ነው፡፡ የ Wainer& Piper (2010) ጥናት በመላው ሀገሪቱ በሚገኙ ስምንት ክልሎች (አዲስ አበባ፣ አማራ፣ ትግራይ፣ ኦሮሚያ፣ ሀረሬ፣ ደቡብ ህዝቦች፣ ቤኒሻንጉል ጉሙዝና ሶማሊያ) ላይ የተወሰኑ ወረዳዎችን እንደ ናሙና በመወሰድ በመጀመሪያ ደረጃ ተማሪዎች የማንበብ ደረጃን (ፊደል የመለየት)ና የአንብቦ መረዳት ችሎታ ያለበትን ደረጃ ከመዳሰስ በተጨማሪ ከሌሎች ተላውጦዎች ጋር ያለውን ተዛምዶም የዳሰሰ ጥናት ነው፡፡ በጥናቱ የተካተቱት የአፍ መፍቻ ቋንቋዎች አማርኛ፣ ትግርኛ፣ ኦሮምኛ፣ ሲዳምኛ፣ ሶማሊኛና ሀረርኛ ናቸው፡፡ የWainer& Piper (2010) ጥናት የመጀመሪያ ደረጃ የማንበብ አሰሳ በሚል መነሻነት የትምህርት ሚኒስቴር ከሌሎች አጋር ድርጅቶች ጋር በመተባበር የሰራው ሀገርአቀፍ ምርምር ነው፡፡ ከማንበብ ተግባራት ውስጥ በጥናቱ የተተኮረባቸው የአንብቦ መረዳት ችሎታ፣ በትክክል ማንበብ መቻልን፣ ድምጽን/ፊደልን/ መለየት፣ የድምጽ ፍሰትን፣ አዳዲስ ቃላትን የማንበብ ፍሰትና ፍጥነት፣ ድምጽ አውጥቶ የማንበብ ችሎታንና የአዳምጦ መረዳት ችሎታ ናቸው፡፡

በጥናቱ ተሳታፊ የሆኑት 13,079 የሁለተኛና የሶስተኛ ክፍል ተማሪዎች ከስምንቱ ክልሎች ከሚገኙ 338 ትምህርት ቤቶች በዕጣ ንሞና የተመረጡ ናቸው፡፡ ከነዚህም ውስጥ የአማርኛ ቋንቋ ተናጋሪ ከሆኑት 40 ወረዳዎች (ከአማራ ክልል 15፣ ከአዲስ አበባ 11፣ ከቤኒሻንጉል ጉምዝ 6ና ከሀረሪ 8) 130 ትምህርት ቤቶች፤ ከ130 ትምህርት ቤቶች ውስጥ ትምህርታቸውን በመከታተል ላይ የሚገኙ 5,237 የሁለተኛና የሶስተኛ ክፍል የአማርኛ አፊ ፍት ተማሪዎች በአማርኛው ቋንቋ የጥናቱ ተሳታፊ ሆነዋል፡፡

በጥናቱ ከማንበብና ከማዳመጥ ክሂል ጋር የተገናኙ መረጃዎች በዋናነት የተሰበሰቡ ሲሆን ከነሱ በተጨማሪ የተማሪዎችን የቤተሰብ ዳራ የሚለካ የጽሁፍ መጠይቅ ለተማሪዎች፣ ለመምህራንና ለርዕሳነ መምህራን ተበትኗል፡፡ የቤተሰብ ዳራን የሚለካው መጠይቅ የተበተነው የትምህርት ቤትና የመማሪያ አካባቢ ከተማሪዎች የትምህርት ውጤት ጋር ያለውን ተዛምዶ ለመለየት ነው፡፡

የጥናቱ ውጤት እንደሚያሳየው በኢትዮጵያ በሁሉም ክልሎች በአፍ መፍቻ ቋንቋቸው የሚማሩ የአንደኛ ደረጃ ተማሪዎች የማንበብ ክሂል ዝቅተኛ ስለሆነ ለቀላል የአንብቦ

መረዳት ጥያቄዎች መልስ መስጠት የቻሉት ከግማሽ የማይበልጡ ናቸው፡፡ በአማራ ክልል ችግሩ ጎልቶ ይታያል፡፡ ከሌሎች የአማርኛ አፈፊት ተናጋሪ ክልሎች ጋር ሲነጻጸር ከሀረሬ 50.9%ና ከአዲስ አበባ 43.7% ቀጥሎ በ28.5% በሶስተኛ ደረጃ ላይ ይገኛል፡፡ በተለያዩ የማንበብ ተግባራት ያስመዘገቡት ውጤት በሰንጠረዥ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

**ሰንጠረዥ 2.2**

***ከ Wainer& Piper (2010) ጥናት የተገኘ የአማርኛ ቋንቋ አፈ ፊቶች የአንብቦ መረዳትና ሌሎች የማንበብ ተግባራት ውጤት ንጽጽር በክልል ደረጃ***

| ክልሎች | የተማሪ ብዛት | የድምጽ ፍሰት | ስነድምጻዊ እውቀት | የቃላት ፍሰት | የቃላዊ ንባብ ፈሰት | የአንብቦ መረዳት |
|---|---|---|---|---|---|---|
| **አማራ** | 2316 | 47.7 | 73.6 | 24.7 | 23.4 | 28.5 |
| **አዲስአበባ** | 1312 | 76.1 | 82.9 | 46.3 | 25.1 | 43.7 |
| **ሀረሪ** | 320 | 92.9 | 82.5 | 52.5 | 46.4 | 50.9 |
| **ቤኒሻንጉል ጉምዝ** | 1289 | 37.5 | 61.2 | 20 | 22 | 24.2 |

ከሰንጠረዡ መረዳት እንደሚቻለው በሁሉም የማንበብ ተግባራት በአማራ ክልል የሚገኙ የአማርኛ አፈፊት ተማሪዎች ውጤት ከቤኒሻንጉል ጉምዝ በተሻለ ነገር ግን ከአዲስ አበባና ከሀረሪ አንሶ በሶስተኛ ደረጃ ይገኛል፡፡

በ2000፣ በ2004 እና በ2007 የተከናወኑት የጥናት ውጤቶች የተማሪዎች የማንበብ ችሎታ እያሽቆለቆለ የሄደ መሆኑን ያሳያሉ (Wainer& Piper, 2010)፡፡ በአጠቃላይ ከ50% በላይ የሚሆኑት የአንደኛ ደረጃ ተማሪዎች ቀላል የአንብቦ መረዳት ችሎታ መለኪያ ጥያቄዎችን መመለስ አይችሉም፡፡ በመሆኑም በማንበብ ትምህርት ዙሪያ አስፈላጊውን ዝግጅት በማድረግ ለለውጥና ለትግበራ መስራት ያስፈልጋል የሚል አስተያየት ተሰጥቷል፡፡ ከተሰጡት አስተያየቶች ውስጥ የአንብቦ መረዳት ብልሀቶችን እንዲጠቀሙ ማበረታታት፣ በማንበብና የማንበብ መመሪያ ላይ ትኩረት ማድረግ፣ ማንበብን አስቀድመው እንዲጀምሩ ማድረግና በቤታቸው ውስጥ የተለያዩ መጽሀፍትን እንዲያነቡ ማድረግ እንደ መፍትሄ ከተጠቆሙት ውስጥ ይጠቀሳል፡፡

ከአንባቢው ማንነት ጋር በተያያዘ ከሚጠቀሱት ውስጥ ለአንብቦ መረዳት የበለጠ አስተዋጽዖ ያለው የማንበብ ተነሳሽነቱ እንደሆነ Guthrie et al. (1999), Guthrie et al.

(2007), Retelsdorf et al. (2011), Taboada et al. (2009)& Wang & Guthrie (2004) ያስረዳሉ፡፡ ይህንን ንድፈ ሀሳብ ለማረጋገጥ እንዲሁም ሌሎች ተላውጦዎችን ለመቃኘት በነዚሁ ምሁራንና በሌሎችን ተመራማሪዎች ከተሰሩ ምርምሮች የተወሰኑትን እንደሚከተለው እንቃኛቸዋለን፡፡

Andreassen & Bråten (2010) በተለያዩ አማራጭ ያላቸው ፈተናዎች የአንብቦ መረዳት ተንባዮችን መመርመር በሚል ርዕስ በ180 የአምስተኛ ክፍል የኖርዎይ ተማሪዎች ላይ የውጫዊና ውስጣዊ የማንበብ ተነሳሽነትን፣ ቃላትን የማስታዎስ ችሎታን፣ የአጭር ጊዜ ትውስታ አቅምን እንዲሁም የማንበብ ብልሃት አጠቃቀምን ከማንበብ ችሎታ (በሶስት ደረጃ በመክፈል) ጋር በማዛመድ ጥናት አካሂደዋል፡፡ በውስጣዊ ተነሳሽነትና በሶስቱ የአንብቦ መረዳት ችሎታዎች መካከል ጉልህ ተዛምዶ ሲኖር በውጫዊ ተነሳሽነትና በአንብቦ መረዳት መካል ያለው ዝምድና ጉልህ አለመሆኑን የጥናታቸው ውጤት ያሳያል፡፡ በድህረት ትንተና ተሰልቶ የተገኘው ውጤትም ውጫዊ ተነሳሽነት የአንብቦ መረዳት ችሎታን እንደማይተነብይ፤ ውስጣዊ ተነሳሽነት ግን ጉልህ ተንባይ እንደሆነ ያሳያል፡፡

የህጻናት የማንበብ ተነሳሽነት መለኪያዎች ከአንብቦ መረዳት ውጤትና የማንበብ ተግባራት ጋር ያለው ተዛምዶ በሚል ርዕስ በአምስተኛና በስድስተኛ ክፍል የዩናትድ ስቴትስ ተማሪዎች ላይ ጥናት ያካሄዱት ተመራማሪዎች Baker & Wigfield (1999) ሲሆኑ ከተጠኝዎቹ መካከል 52% ነጮች ሲሆኑ 46% ደግሞ አፍሪካ አሜሪካውያን ናቸው፡፡ የማንበብ ተነሳሽነትን ለመለካት የጽሁፍ መጠይቅን፣ የአንብቦ መረዳት ችሎታን ለመለካት ደግሞ መደበኛ የምርጫና የአብራሩ ፈተናዎችን በመጠቀም በዘርና በጾታ ያለውን ልዩነትም ለመዳሰስ ሞክረዋል፡፡ የጥናታቸው ውጤት እንደሚያሳየውም በአብዛኛው ተዛምዶው ዝቅተኛ መሆኑንና በሴት ነጭ ተማሪዎች ላይ የተለየ ውጤት ማግኘታቸውን ነው፡፡ የሴት ነጭ ተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ችሎታ ከማንበብ ተነሳሽነት ጋር ጉልህ ተዛምዶ አለው፡፡

Baker & Wigfield (1999) ህጻናት ለማንበብ ያላቸው ተነሳሽነትና ከማንበብ ተግባራትና ከአንብቦ መረዳት ችሎታ ጋር ያለውን ተዛምዶ በተመለከተ ከስምንተኛ ክፍል እስከ አስረኛ ባሉ ሶስት ሺ ሰባት መቶ ጀርመናዊ ተማሪዎች ላይ ጥናት አካሂደዋል፡፡

ተዛምዶውም ወደዝቅተኛ ያደላ ($r < .30$) ነው፡፡ ነገር ግን ነጭ ተማሪዎችና ሴቶች ከውጫዊና ውስጣዊ ተነሳሽነት እንዲሁም ከማንበብ ችሎታ ጋር ጉልህ የሆነ ተዛምዶ እንዳላቸው አረጋግጠዋል፡፡ በተጨማሪም የሴት ነጭ ተማሪዎች የማንበብ ተነሳሽነት የማንበብ ችሎታን በጉልህ ደረጃ እንደሚተነብይና የሌሎች ተላውጦዎች ግን ጉልህ እንዳልሆነ የጥናታቸው ውጤት ያሳያል፡፡

Becker et al. (2010) ውጫዊና ውስጣዊ የማንበብ ተነሳሽነት የአንብቦ መረዳት ችሎታን ይተነብያልን? በሚል ርዕስ ከሶስተኛ እስከ ስድስተኛ ክፍል የሚገኙ የጀርመን ተማሪዎችን በረጅም ጊዜ ጥናት ለመዳሰስ ሞክረዋል፡፡ መረጃውን McElvany et al. (2008) በጀርመንኛ ቋንቋ ለመስራት የሰበሰቡትን ሙሉ በሙሉ ወስደው በተለየ ትንተና ስልት በመስራት ተመሳሳይ ውጤት (በውስጣዊ ተነሳሽነትና በአንብቦ መረዳት ችሎታ መካከል ጉልህ ተዛምዶ መኖሩን) አምጥተዋል፡፡ በተለይም በአራተኛ ክፍልና በስድስተኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ ውስጣዊ ተነሳሽነት የማንበብ ችሎታን እንደሚተነብይ ነገር ግን ውጫዊ ተነሳሽነት ተዛምዶው ጉልህና ትንበያውም አሉታዊ መሆኑንና የውስጣዊ ተነሳሽነት ትንበያ ዘላቂ እንዳልሆነ ትንተናቸው ያሳያል፡፡

የቤተሰብ ታሪክ፣ ግለ ግምትና አመለካከት ከማንበብ ችሎታ ጋር ያለው ተዛምዶ በታዳጊ ህጻናት ተተኳሪነት ምርምር ያካሄዱት ሌሎች ተመራማሪዎች Colon et al. (2006) ናቸው፡፡ ጥናቱ የተካሄደው በአውስትራሊያ በሚገኙ አማካኝ እድሜያቸው 11.9 በሆኑ የሰባተኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ ሲሆን የውስጣዊ ተነሳሽነት ተላውጦዎችን የማንበብ አመለካከት በሚል ርዕስ ተክተው አቅርበውታል፡፡ በማንበብ አመለካከት (ውስጣዊ ተነሳሽነት)፣ በግለ ግምትና በአንብቦ መረዳት ችሎታ መካከል አወንታዊና ጉልህ ተዛምዶ መኖሩን አረጋግጠዋል፡፡

በተማሪዎች የንባብ መጠን አነሳሽና አዕምሮታዊ ተጽዕኖ መፍጠር በሚል ርዕስ Cox & Guthrie (2001) በሁለት መቶ ሀምሳ አንድ የሶስተኛና የአምስተኛ ክፍል የተለያየ ዘር ያላቸው ተማሪዎች ላይ አምስቱን የማንበብ ተነሳሽነት መለኪያዎች በመጠቀም ምርምር አካሂደዋል፡፡ ለመዝናናት ማንበብ፣ ለትምህርት ቤት ማንበብና መጠኑ እንዲሁም የብልሃት አጠቃቀም ከአንብቦ መረዳት ችሎታ ጋር ያለውን ተዛምዶ በፒርሰን ፕሮዳክት

የተዛምዶ መወሰኛ ቀመር አስልተው ተዛምዶው ጉልህ አለመሆኑን አሳይተዋል፡፡ ይህ ውጤትም ተነሳሽነትን ከማንበብ ሳይንስ ጋር እንዴት ማጣጣም ይቻላል? በሚል መነሻ Guthrie et al. (1999) በ20 የሶስተኛና አምስተኛ ክፍል የተለያየ ዘር ያላቸው የአሜሪካ ተማሪዎች ላይ ምርምር ሰርተው ካገኙት ውጤት ጋር ተመሳሳይ ነው፡፡

የማንበብ ብልሀት አጠቃቀምና ተነሳሽነት በሆንግ ኮንግ ጥሩና ደካማ ተማሪዎች ላይ በሚል ርዕስ በአንድ መቶ ሀምሳ ዘጠኝ የሰባተኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ የሰሩት ተመራማሪዎች Lau & Chan (2003) ናቸው፡፡ የማንበብ ተነሳሽነትን ከሌሎች ለየት ባለ መልኩ ውስጣዊ፣ ውጫዊና ማህበራዊ ብለው በመክፈልና የማንበብ ብቃትን በመጨመር ከአንብቦ መረዳት ችሎታ ጋር በማዛመድ ሰርተው በውስጣዊ ተነሳሽነት ጥሩ አንባቢዎች ከደካማ አንባቢዎች ተሽለው ሲገኙ በውጫዊና ማህበራዊ ግን ጉልህ አይደለም፡፡ የሁሉም ቡድኖች የፈተና ውጤታቸውና ውስጣዊና ውጫዊ የማንበብ ተነሳሽነታቸው ጉልህ ተዛምዶ አሳይቷል፡፡ በማህበራዊና በማንበብ ብቃት ግን ጉልህ አይደለም፡፡

Law (2008) የውጫዊ ተነሳሽነት፣ የቤተሰብ ድጋፍ፣ የክፍል ውስጥ መመሪያ ልምምድና የማንበብ ብቃት ተዛምዶ በሁለተኛ ክፍል የቻይና ተማሪዎች ተተኳሪነት በሚል ርዕስ በሰባት መቶ ሰላሳ አራት ተማሪዎች ላይ ምርምር አካሂደው በውጫዊ ተነሳሽነትና በአንብቦ መረዳት ችሎታ መካከል ያለው ተዛምዶ ጉልህ አለመሆኑን አረጋግጠዋል፡፡ ነገር ግን የቤተሰብ ድጋፍ፣ ከቤት ውስጥ የመጽሀፍ መገኘትና የወላጅና የተማሪዎች የመመሪያ ትግበራ አመለካከት አሉታዊና ጉልህ ተዛምዶ እንዳላቸው የውጤት ትንተናቸው ያሳያል፡፡ በደካማና ጠንካራ ተማሪዎች የውስጣዊ ተነሳሽነት በአንብቦ መረዳት ብቃት ያለው ጠቀሜታ በሚል መነሻ በዚሁ ተመራማሪ በ2009 አንድ መቶ ሀያ የአምስተኛ ክፍል የቻይና ተማሪዎች ጥናት ተካሂዷል፡፡ የተወሰነ መለኪያ በ2008 ከሰሩት ምርምር ወስደው የተወሰኑትን ደግሞ ከአለምአቀፋዊው የተነሳሽነት መለኪያ በመጠቀም ውስጣዊ ተነሳሽነት ጉልህና አወንታዊ ተዛምዶ ውጫዊ ደግሞ ጉልህና አሉታዊ እንደሆነ አሳይተዋል፡፡ በድህረት ትንተና ስልት የተሰላው ውጤት የሚያሳየው ግን የትንበያ ደረጃው ጉልህ አለመሆኑን ነው፡፡

በጀርመን በሚገኙ ከአምስተኛ እስከ ስምንተኛ ባሉ ተማሪዎች የረጅም ጊዜ ጥናት ያካሄዱት ተመራማሪዎች Retelsdorf et al. (2011) ናቸው፡፡ የጥናቱ ዋና አላማ የማንበብ ተነሳሽነት በማንበብ ብቃት ላይ ያለውን ተጽዕኖ ለይቶ ማውጣት ነበር፡፡ በጥናታቸው ቤተሰባዊ ዳራ (በቤት ውስጥ የሚገኙትን መጻህፍት ብዛት)፣ ምክንያት የመስጠት ችሎታና የመቅዳት ችሎታ ተዳሰዋል፤ የማንበብ ግለ ግምታቸው አምስተኛ ክፍል እያሉ ተለክቷል፡፡ የውጤት ትንተናቸው እንደሚያሳየው የውስጣዊ ተነሳሽነት ተዛምዶው ጉልህነት በእያንዳንዱ ዝርዝር ተላውጦ የተለያየ ነው፡፡ ለመዝናናት ማንበብ ጉልህና አወንታዊ ተዛምዶ ሲያሳይ ለፍላጎት ማንበብ ደግሞ ደካማ ተዛምዶ አሳይቷል፡፡ ለውድድር ማንበብ ጉልህና አሉታዊ ተዛምዶ ማሳየቱን የውጤት ማብራሪያው ገልጿል፡፡ በጥናቱ ከተካተቱት ዝርዝር ተላውጦዎች መካከል ጾታ፣ ቤተሰባዊ ዳራ፣ ምክንያት የመስጠት ችሎታና ለፍላጎት ማንበብ የማንበብ ብቃት እድገትን እንደሚተነብይ የድህረት ትንተናቸው ያስረዳል፡፡

Logan et al. (2011) ጠንካራና ደካማ የማንበብ ችሎታ ባላቸው ተማሪዎች ላይ የውስጣዊ ተነሳሽነት ጠቀሜታ በሚል ርዕስ ከአራተኛ ክፍል እስከ ስድስተኛ ባሉ አንድ መቶ አስራ አንድ የዩናይትድ ኪንግደም ተማሪዎች ላይ ጥናት አካሂደዋል፡፡ ጥናቱ ከፍተኛ ችሎታ ያላቸውን ከዝቅተኞች ጋር ማወዳደር ሲሆን ከውስጣዊ ተነሳሽነት ዝርዝር መለኪያዎች ውስጥ ጠንካራ ፍላጎት፣ ጥንካሬን ማሳየትና ተሳትፎ ተካተዋል፡፡ ደካማ፣ መካከለኛና ጠንካራ አንባቢዎች የፈተና ውጤታቸውን መሰረት በማድረግ አማካኝ ተሰልቶ ከተለዩ በኋላ ቃላዊ ብቃታቸውንና የመቅዳት ችሎታቸውን ውስጣዊ ተነሳሽነት እንደሚተነብይና እንደማይተነብይ በድህረት ትንተና አስልተዋል፡፡ ውስጣዊ ተነሳሽነት የማንበብ ችሎታን እንደሚተነብይና ጉልህነቱ በደካማ ተማሪዎች ላይ እንደሚጎላ አረጋግጠዋል፡፡

የማንበብ ተነሳሽነትን ከአንብቦ መረዳት ችሎታ ጋር በማዛመድ ያጠኑት ሌሎች ባለሙያዎች Guthrie et al. (1999) ናቸው፡፡ ውጫዊና ውስጣዊ የማንበብ ተነሳሽነትን በአንድ ላይ አቀናጅተው የሚለኩ መጠይቆችን አዘጋጅተው ከማንበብ ችሎታ ጋር ተዛምዶውን በማስላት ጉልህ ያልሆነ ተዛምዶ እንዳለ አረጋግጠዋል፡፡ በሌላ መልኩ Wang & Guthrie (2004) የዩናይትድ ስቴትስና የቻይና ተማሪዎችን የማንበብ ተነሳሽነትና የአንብቦ መረዳት ችሎታ በማነጻጸር በሰሩት ጥናት ጉልህ ተዛመዶ እንዳለና ውስጣዊ

ተነሳሽነትና ውጫዊ ተነሳሽነትም እርስ በርስ እንደሚዛመዱ የጥናታቸው ውጤት ያሳያል፡፡ Guthrie et al. (2007) ተማሪዎች ስለተለያዩ መጻህፍት ያላቸውን ፍላጎት፣ የምንባብ ምርጫ፣ ከመጻህፍት ጋር ያላቸው ተሳትፎ፣ የማንበብ ማህበራዊ ገጽታና የማንበብ ስኬታማነት በተመለከተ በቃለመጠይቅ መረጃ ሰብስበው እነዚህ ተላውጦዎች የማንበብ ችሎታን የመተንበይ ደረጃቸውን በንጥል ድህረት ትንተና ተንትነውታል፡፡ በውጤታቸውም ፍላጎት፣ ምርጫና ተሳትፎ የማንበብ ችሎታ እድገትን በጉልህ ደረጃ እንደሚተነብይ ማህበራዊነትና ስኬታማነት ግን ጉልህ አለመሆናቸውን አሳይተዋል፡፡

በኢትዮጵያ ውስጥ የአንብቦ መረዳት ችሎታ ከተለያዩ ነገሮች ጋር በማዛመድ የተሰሩ ጥናቶች አሉ፡፡ ታምራት (2003) የአንብቦ መረዳትን ከአካዳሚያዊ ውጤት ጋር በማዛመድ በጎንደር በሚገኙ ሶስት የተመረጡ ትምህርት ቤቶች ላይ በሚማሩ የስድስተኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ ጥናት አካሂደዋል፡፡ የተማሪዎችን የአንብቦ መረዳት ችሎታ በሶስት የተለያዩ ፈተናዎች ተለክቶ በሶስቱም ዝቅተኛ መሆኑ ተስተውሏል፡፡ ከአካዳሚያዊ ውጤትና ከንባብ ፍጥነት ጋር ተዛምዶ እንዳለው የጥናቱ ውጤት ያሳያል፡፡ ይህ ጥናት ምንም እንኳን ስለአንብቦ መረዳት ችሎታ መዳሰሱ በመጠኑ ቢመሳሰልም ለተዛምዶ ያነሷቸው ተላውጦዎች የአካዳሚያዊ ውጤት በመሆኑና ይህ ጥናት ደግሞ የቤተሰብ ዳራን የሚዳስስ በመሆኑ ጥናቱ መካሄድ እንዳለበት ያሳያል፡፡

ተሳታፊነት፣ ጭምትነት የስብዕና አይነት ከድርሰት መጻፍና ከአንብቦ መረዳት ችሎታ ጋር ያለውን ተዛምዶ በኮሌጅ ተማሪዎች ላይ ያጠኑት በድሉ (1989) ተዛምዶ እንደሌለው በጥናታቸው አረጋግጠዋል፡፡ በድሉ ምንም እንኳን ከአንባቢው ባህሪይ ጋር የተገናኙ ተላውጦዎችን ማጥናታቸው በመጠኑ ቢመሳሰልም የቤተሰብ ዳራን አለመዳሰሱ ተጨማሪ ጥናት ለማሄድ ክፍተት እንዳለ ይጠቁማል፡፡

የአማርኛ ቋንቋን ትምህርት የአንብቦ መረዳት ችሎታ ከንባብ ልምድ ጋር በማዛመድ ጥናት ያካሄዱት ሌላው ተመራማሪ ብርሀን (2003) ሲሆኑ በዚህ ጥናት በጥናቱ የተካተቱት ተማሪዎች የንባብ ልምዳቸውንና እውቀታቸውን በተግባር የማዋል ብቃታቸውን ለመፈተሽ በቀረበው ፈተና ዝቅተኛ ውጤት አስመዝግበዋል፡፡ የውጤት ትንተናው እንደሚያሳየው የተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ ዝቅተኛ መሆኑን

ነው። የአንብቦ መረዳት ችሎታ ምን ይመስላል በሚል የተለያዩ ተመራማሪዎች በተለያየ ቦታ ጥናት አካሂደዋል። የሁሉም ውጤት የአንብቦ መረዳት ችሎታቸው ዝቅተኛ መሆኑን ነው ያሳዩት። ለምሳሌ ማስተዋል (1989) በአስራ አንደኛ ክፍል ተማሪዎች ጥናታቸውን አካሂደው የአፈ ፈቶችም ሆነ የኢ አፈፈቶች ችሎታቸው ዝቅተኛ መሆኑን አረጋግጠዋል።

የማስተማሪያ ዘዴ በተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ችሎታ ላይ የሚያደርሰውን ተጽእኖ ለመፈተሽ የተለያዩ የማስተማሪያ ዘዴዎችን በመጠቀም የፈተሹ ተመራማሪዎች አሉ። ከነዚህም ውስጥ ሚና ለዋጭ ዘዴ የተማሪዎችን የአንብቦ መረዳት ችሎታና የማንበብ ተነሳሽነት ለማዳበር ያለውን ሚና የፈተሹት ዘውዱ (2008) ናቸው። በጥናታቸው ተተኳሪ የነበሩት የአንደኛ ደረጃ የሁለተኛ ሳይክል የሰባተኛ ክፍል ተማሪዎች ናቸው። የሚና ለዋጭ ዘዴ የተማሪዎችን የአንብቦ መረዳት ችሎታና የማንበብ ተነሳሽነት ለማዳበር ያለው ሚና ከፍተኛ እንደሆነም የጥናታቸው ውጤት ያሳያል። የተለያዩ የማስተማሪያ ዘዴዎችን እየጠቀሱ ለክሂሉ ያላቸውን አስተዋጽኦ መፈተሽ ተገቢ ቢሆንም ከማስተማሪያ ዘዴውም ሆነ ከመማሪያ ብልሀቶች አስቀድሞ መታየት ያለበት ከተማሪው ማንነት ጋር ተያይዘው የሚነሱት ቤተሰባዊ ጉዳዮችና የተማሪው ማንነት ናቸው። በመሆኑም ይህ ጥናት ከተማሪው ማንነት ጋረ ተያይዞ ባለመሰራቱ ተጨማሪ ጥናት እንደሚያስፈልግ ጉድለቱ ያሳያል።

እንድሪስ (2009) ቴክስት ውቅር ብልሀት የተማሪዎችን የአንብቦ መረዳት ችሎታ፣ የማንበብ ተነሳሽነት፣ የማንበብ ትኩረትና የማንበብ ግለ ብቃት ለማዳበር ያለውን ሚና በስድስተኛ ክፍለ ተማሪዎች በማተኮር ምርምር አካሂደዋል። የጥናቱ ውጤት እንደሚያሳየውም የቴክስት ውቅር የብልሀት ስልጠናው ለማዳበር ያለው ሚና ጉልህ ነው። ምንም እንኳን የብልሀት ስልጠና ለተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ችሎታ፣ ለማንበብ ግለ ብቃትና ለማንበብ ተነሳሽነት ከፍተኛ አስተዋጽዖ እንዳለው የጥናት ውጤቱ ቢያሳይም ከመነሻው በአንብቦ መረዳት ችሎታ፣ በማንበብ ተነሳሽነት፣ በማንበብ ትኩረትና በማንበብ ግለ ብቃት መካከል ያለውን ግንኙነትና የተዛምዶ መጠን አለመፈተሹ ክፍተቱን ያሳያል። በእንግዳ (1992)፣ በግሩም (2003)፣ በየኔሰው (1990) እንዲሁም በጌታቸው (1986) የተጠኑት ጥናቶች ከማስተማሪያ ዘዴውና ከጽሁፉ

ተነባቢነት ጋር የተያያዙ መሆናቸው ያነሱት ተላውጦ ለአንብቦ መረዳት ወሳኝ ቢሆንም እነሱ ብቻ ያጠኑት ግን በቂ ባለመሆኑ ተጨማሪ ጥናት ማጥናት ማካሄድ አስፈላጊ በመሆኑ ይህ ጥናት ያልተዳሰሱትንና አስፈላጊ የሆኑትን ለማየት የተደረገ ጥናት ነው፡፡

## 2.9. የጥናቱ ንድፈ ሀሳባዊ ማዕቀፍ (theoretical Framwork of the study)

የተለያዩ ማህበራዊ፣ ስነልቦናዊና ምጣኔ ሀብታዊ ንድፈሀሳቦች ቤተሰብና አካባቢ በትምህርት ላይ የሚኖረውን ተጽዕኖ ይደግፋሉ፡፡ የተወሰኑት ትኩረት የሚያደርጉት እያንዳንዱ ሰው በሚያገኘው ገቢና ያ ገቢ በሚያደርሰው ተጽዕኖ (ለምሳሌ፡- የቤተሰብ ምንጭ ሞዴል /Family Resource Model/ና የሰው ልጅ እድገት ሞዴል/Model of Human Investment/) ሲሆን የተወሰኑት ደግሞ ከወላጅ ወደ ልጅና ከአካባቢ ወደ ልጅ በሚተላለፉት ልማዶችና ባህርያት ላይ ነው (ምሳሌ፡- የማህበራዊነትና የሚናዊ ሞዴል እይታ)፡፡

የቤተሰብ ምንጭ ሞዴልና የሰው ልጅ እድገት ሞዴል የግብዓቶች መጠን፣ በአስፈላጊው ጊዜ መገኘትና አለመገኘትና ሁኔታ በሰው ልጅ እድገት ላይ ተጽዕኖ አለው፡፡ በሌላ መልኩ የማህበራዊነትና ሚና ተቀባይ እይታዎች እንደሚሉት ወላጆች ወደ ልጆቻቸው የሚያስተላልፉት የባህርይ ሁኔታንና አካሄድን ነው፡፡ የብሮንፈንበርነር የስነምህዳር ስርዓት ንድፈ ሀሳብና የኮሎሞን የቤተሰብ ዳራ ሞዴል ሁለቱንም በአንድ ላይ አጣምረው የያዙ ናቸው (Havenman & Wolfe, 1995) ፡፡

የብሮንፈንበርነር የስነ ምህዳር ስርዓት ንድፈ ሀሳብ (Ecological systems theory) የሰው ልጅ እድገት በሚያደርገው ማህበራዊ ተራክቦና በዙሪያቸው በከባባቸው አለም እንዴት ተጽዕኖ እንደ ሚደርስበት የሚያጠናና ምላሽ የሚሰጥ ቲዎሪ ነው፡፡ እንደ ብሮንፈንበርነር እምነት የሰው ልጅ እድገት በአካባቢው ባሉት ማናቸውም ነገሮች ተጽዕኖ ይደርስበታል፡፡ በዚህ ንድፈ ሀሳብ መሰረት የአንድን ልጅ እድገት ለመረዳት በግለሰቡ ላይ ብቻ ማተኮር በቂ አይደለም፡፡ አካባቢውንም ጭምር መቃኘት ያስፈልጋል፡፡ የብሮንፈንበርነር የስነምህዳር ስርዓት ንድፈሀሳብ በሰው ልጅ ዙሪያ ያሉትን አካባቢያዊ

ነገሮች በአምስት ደረጃ ከፍሎ ያያቸዋል፡፡ እነሱም ትንሹ ስርዓት፣ ሰፊ ስርዓት፣ የለውጥ ስርዓት፣ የውጭ ስርዓትና ማዕከላዊ ናቸው፡፡ ደረጃቸው እንደሚከተለው በስዕል ቀርቧል፡፡




**ስዕል ስድስት፡- የ Bronfenbrenner የስነምህዳር ስርዓት ንድፈሀሳብ**

ከስዕሉ መረዳት እንደሚቻለው የሰው ልጅ እድገት በአካባቢው ባሉት ማንኛውም ነገሮች ተጽዕኖ ይደርስበታል፡፡ ተጽዕኖው በአምስት ደረጃ የሚከፈል ሲሆን እያንዳንዳቸውን በዝርዝር እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

**ትንሹ ስርዓት** (Microsystem)፡- ትንሹ ስርዓት የሚባለው ከግለሰቡ ጋር ቀጥተኛና ጥብቅ ቁርኝት ያላቸውን አካላት የሚመለከት ነው፡፡ እነሱም ቤተሰብ፣ ጎረቤት፣ ትምህርት ቤትና ጓደኛ ናቸው፡፡

**ማዕከላዊ ስርዓት** (Mesosystem)፡- የሚባለው በትንሹ ስርዓት የተገለጹትና ለግለሰቡ ቅርበት ያላቸው አካላት እርስ በርስ የሚያደርጉት መስተጋብር ነው፡፡ ማለትም ቤተሰብ ከጎረቤት፣ ቤተሰብ ከትምህርት ቤት ወ.ዘ.ተ. የሚያደርጉት ግንኙነት የልጁን እድገት ተጽዕኖ ያደርስበታል፡፡ እንደ ብሮንፈንበርነር ገለጻ በአንድ ሰው እድገት ላይ እነዚህ አካላት ከመኖራቸው በላይ እነሱ የሚያደርጉት መስተጋብር የሚያደርገው ተጽዕኖ ከፍተኛ ነው፡፡ ማለትም የአንድ ልጅ የአንብቦ መረዳት ችሎታ ትምህርት ቤት ከቤተሰብ በሚያደርገው የተራክቦ መጠን ሊጨምርና ሊቀንስ ይችላል፡፡

**የውጭ ስርዓት** (Exosystem)፡- የሚባለው ተማሪው ወይም ማንኛውም ልጅ በቀጥታ የማይሳተፍበት ነገር ግን በተዘዋዋሪ በእድገቱ ላይ ተጽዕኖ የሚፈጥሩ ነገሮችን የሚዳስስ ነው፡፡ እነሱም፡- የወላጅ የስራ ቦታ፣ የስራ እድገት ወይም መባረር፣ የትምህርት ቤቱ እርቀትና ቅርበት የመሳሰሉት ናቸው፡፡ የቤተሰብ የስራ ሰዓትና ፕሮግራም ልጁ ከወላጆቹ ጋር የሚኖረውን ጊዜ ሊገድበው ይችላል፡፡ ይህም ማለት ወላጆች በልጆች የአንብቦ መረዳት ችሎታ ላይ የሚያደርጉትን አስተዋጽኦ ሊጎዳው ወይም ሊያበረታታው ይችላል፡፡

**ሰፊ ስርዓት** (macrosystem)፡- የግለሰቡን ባህል፣ ዋጋና እምነት የሚለከት ነው፡፡

**የለውጥ ስርዓት** (Chronosystem)፡- የሚባለው በጊዜ ምክንያት በልጁ የሚመጡ የተለያዩ ለውጦችንና ሽግግሮችን ይመለከታል፡፡ ለአብነት አካላዊ ለውጥ፣ የወላጅ ፍች፣ የቤተሰብ ሞት፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ቀውስ የመሳሰሉት ይጠቀሳሉ፡፡

በአጠቃላይ የብሮንፈንበርነር የስነምህዳር ስርዓት ንድፈ ሀሳብ እንደሚለው የሰው ልጅ የእድገት ሂደት በግለሰቡ ስነልቦናዊ፣ አዕምሯዊና ስነህይወታዊ ባህርይ፣ በአካባቢው ባሉት ማንኛውም ነገሮች፣ በአውድና በጊዜ ኡደት በሚመጡ ለውጦች የተመሰረተ ነው፡፡ ይህ ጥናትም የተማሪው የአንብቦ መረዳት ችሎታ በግለሰቡ የማንበብ ተነሳሽነትና

የቤተሰብ ዳራ የሚያደርሰውን ተጽዕኖ መለየት በመሆኑ እንደ መሰረታዊ አድርጎ የሚነሳው ይህንን ንድፈ ሀሳብ ይሆናል፡፡

## 2.10. የጥናቱ ጽንሰ ሀሳባዊ ማዕቀፍ/ Conceptual Framwork of the study)

ይህ ጥናት የሚዳስሳቸው አበይት ተላውጦዎች የቤተሰብ ዳራ፣ የአንብቦ መረዳት ችሎታና የማንበብ ተነሳሽነት ናቸው፡፡ የቤተሰብ ዳራ በአንብቦ መረዳት ችሎታና በማንበብ ተነሳሽነት ላይ እንዲሁም የአንብቦ መረዳት ችሎታና የማንበብ ተነሳሽነት እርስ በርስ ተጽዕኖ ሊፈጥሩ እንደሚችሉ ስዕሉ ያሳያል፡፡ ጥናቱም ይህንን ሞዴል መሰረት አድርጎ ይከናወናል፡፡ በንዑስ ተላውጦነት የክፍል ደረጃና ጾታ አብረው ይታያሉ፡፡ አበይትና ንዑሳን ተላውጦዎች እርስ በርስ የሚኖራቸው ግንኙነት በቀጣዩ ስዕል ቀርቧል፡፡




**ስዕል ፡- የጥናቱ ጽንሰሀሳባዊ ማዕቀፍ**

## 2.11. የምዕራፉ ማጠቃለያ

በዚህ ምዕራፍ ዘጠኝ አበይት ርዕሶች ተዳሰዋል። እነሱም የማንበብ ምንነት፣ የአንብቦ መረዳት ችሎታ ንድፈ ሀሳቦች፣ የማንበብ ሞዴሎች፣ የማንበብ ደረጃዎች፣ የማንበብ ተነሳሽነት፣ የቤተሰብ ዳራ፣ የቀደምት ጥናቶች ቅኝት፣ የጥናቱ ንድፈ ሀሳባዊ ማዕቀፍና የጥናቱ ጽንሰ ሀሳባዊ ማዕቀፍ ናቸው። የማንበብ ምንነት በጊዜው የነበሩት ንድፈ ሀሳቦችና ንድፈ ሀሳቦችን ተከትሎ በማንበብ ዙሪያ የተካሄዱት የብያኔ ለውጦችና የምርምር ትኩረቶች እንዲሁም በመማር ማስተማር የተደረጉት ተግባራዊ ለውጦችና የአንብቦ መረዳት ምንነትና የምርምር ትኩረት በክፍል አንድና በክፍል ሁለት ተዳሰዋል። የተዳሰሱት ንድፈ ሀሳቦች ባህርያውያን፣ የአዕምሯውያንና የማህበረ ባህላዊ ቅድመ እውቀት ግንባታውያን ናቸው። እነዚህ ንድፈ ሀሳቦች በአንብቦ መረዳት ላይ ያላቸው መርህም ተገልጿል።

በማንበብ ዙሪያ በተለያዩ ዘመናት የተከሰቱ ንድፈ ሀሳቦችንና እነሱን መሰረት አድርገው በፈለቁት የማንበብ ሂደት ሞዴሎች ላይ ማብራሪያ ቀርቧል። ሞዴሎቹ በሶስት የሚከፈሉ ሲሆን እነሱም ትርጉም የማውጣትና የመሰብሰብ ሞዴል፣ የመገንባትና የማዋሃድ ሞዴልና የተሸጋጋሪያዊ ኤክስቴንሽን ሞዴል ናቸው። የነዚህ ሞዴሎች መሰረት የባህርያውያን፣ የአዕምሯውያን (የስኬማ ንድፈ ሀሳብ)ና የቅድመ እውቀት ግንባታውያን ንድፈ ሃሳብ በተከታታይ ነው። የሞዴሎች መለዋወጥ በማንበብ ሂደት የራሱን አስተዋጽዖ አበርክቷል።

በክፍል አራት አንብቦ መረዳት ችሎታ የሚከተላቸውን ደረጃዎችና እነዚህ ደረጃዎች እንደ የተመራማሪው ምን አይነት እይታ እንዳላቸው ተብራርቷል። ከአብዛኞቹ ተመራማሪዎች አንጻር የአንብቦ መረዳት ችሎታ አራት ደረጃዎችን ያልፋል። እነሱም ቃላትን መረዳት፣ አረፍተ ነገርን መረዳት፣ አንቀጽን መረዳትና ጽሁፍን መረዳት ናቸው።

በክፍል አምስት በአንብቦ መረዳት ላይ ተጽዕኖ ከሚፈጥሩ ተላውጦዎች መካከል የማንበብ ተነሳሽነት ምንነትና አይነቶቹ እንዲሁም እንደ የተመራማሪዎቹ ልዩነት

የመለኪያዎቹ ልዩነት ተዳሷል፡፡ የማንበብ ተነሳሽነት መለኪያዎች በርካታ ሲሆኑ በዋናነት ከአይነታዊና ከመጠናዊ የተገኙ ተብለው በአስራ አንድ ይከፈላሉ እነሱም በራስ ለመተማመን ማንበብ፣ ለተግዳሮት ማንበብ፣ ጠንካራ ፍላጎት ስላለ ማንበብ፣ ለተጠቃሚነት ማንበብ፣ ለተሳትፎ ማንበብ፣ ከስራ ለመራቅ ማንበብ፣ ለተወዳዳሪነት ማንበብ፣ ለውጤት ማንበብ፣ ለእውቅና ማንበብ፣ ለማህበራዊ ተራክቦ ማንበብና ለመከበር ማንበብ ናቸው፡፡ እነዚህ መለኪያዎች በተናጥልና በጋራ በአንብቦ መረዳት ችሎታ ላይ ያላቸው ተጽዕኖና አስፈላጊነት ተዳሷል፡፡

በስድስተኛ ደረጃ የቤተሰብ ዳራ ምንነት በስሩ የሚካተቱት ተላውጦዎች ብያኔና ከማንበብ ጋር ያላቸው ተዛምዶ ተዳሷል፡፡ ከቤተሰብ ዳራ ጋር ተያይዘው ከሚጠቀሱ ተላውጦዎች ውስጥም ዋና ዋና የሚባሉትና በጥናቱ የሚካተቱት ገቢ፣ ስራ፣ የቤት ውስጥ ግብዓት፣ የቤተሰብ መዋቅር፣ የስደት ሁኔታ፣ የትምህርት ደረጃ፣ ጎረቤትና ሀይማኖት ከማንበብ ጋር ያላቸው ቁርኝትና ብያኔ ተዳሶበታል፡፡

በሰባተኛ ደረጃ ከጥናቱ ጋር ቅርበት ያላቸው ቀደምት ጥናቶች ተዳሰዋል፡፡ በቅኝቱ ጆርናሎች፣ የሁለተኛና የሶስተኛ ዲግሪ መመረቂያ ጽሁፎችና በድርጅቶችና በተቋማት የተሰሩ ሀገር አቀፋዊና አለም አቀፋዊ ምርምሮች ተካተዋል፡፡ ጥናቶቹ ከዚህ ጥናት ጋር ምን እንደ ሚያመሳስላቸውና እንደ ሚለያቸው፤ እንዲሁም ይህ ጥናት ምን ክፍተት ሊሞላ እንደሚችል ተጠቁሟል፡፡

በስምንተኛ ደረጃ የሰፈረው ጥናቱ የተከተለው ንድፈ ሀሳባዊ ማዕቀፍ ነው፡፡ የቤተሰብ ዳራ በአንብቦ መረዳት ችሎታና በማንበብ ተነሳሽነት ላይ የሚኖረውን ተጽዕኖ የሚደግፉ ማህበራዊና ምጣኔ ሀብታዊ ንድፈ ሀሳቦች በርካታ ሲሆኑ ከዚህ ጥናት አላማ አንጻር ጥናቱ የተመሰረተው በብሮንፈብርነር የስነምህዳር ስርዓት ንድፈሀሳብ ላይ እንደሆነ ማብራሪያ ቀርቧል፡፡ የብሮንፈብርነር የስነምህዳር ስርዓት ንድፈሀሳብ እያንዳንዱ ሰው በዙሪያው ባሉት ማንኛውን ነገሮች ተጽዕኖ እንደሚደርስበት ገልጾ ተጽዕኖ ፈጣሪዎች በአጠቃላይ በአምስት ስርዓት ይከፍላቸዋል፡፡

በዘጠነኛ ደረጃ የሰፈረው የጥናቱ ጽንሰ ሀሳባዊ ማዕቀፍ ነው፡፡ ጽንሰ ሀሳባዊ ማዕቀፉ ጥናቱ የሚዳስሳቸውን ነጻና ጥገኛ ተላውጦዎች የእርስ በርስ ግንኙነት የሚያሳይ ነው፡፡

ይህ ግንኙነት ጥናቱ የሚከተለው ሞዴል፡፡ በጥናቱ የተነሱት ነጻ ተላውጦዎቹ የቤተሰብ ዳራ፣ ጾታና የክፍል ደረጃ ሲሆኑ ጥገኛ ተላውጦዎቹ የአንብቦ መረዳት ችሎታና የማንበብ ተነሳሽነት እርስ በርስ የሚኖራቸው የተላውጦ ግንኙነት በስዕል ቀርቦበታል፡፡

በቀጣዩ ምዕራፍ የጥናቱ ዘዴ የሚባለው ሶስተኛው ክፍል ሰፍሯል፡፡ የጥናቱ ዘዴ በጥናቱ የሚካተቱት ተጠኝዎች ማንነትና መጠን የክፍል ደረጃ እንዲሁም የተመረጡበት ምክንያት በዝርዝር ቀርቦበታል፡፡ በተጨማሪ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴና መተንተኛ ዘዴ እንዲሁም የአጠናን ሂደት፣ ስነምግባራዊ ትኩረትና የዋና ጥናቱ ሂደት ተዘርዝሯል፡፡

# ምዕራፍ ሶስት

# የአጠናን ዘዴ

## 4.1. መግቢያ

በዚህ ምዕራፍ የዋናው ጥናት የምርምር ስልት፣ የቦታና የጥናቱ ተሳታፊዎች አመራረጥ፣ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ብዛት፣ አዘገጃጀት፣ ትክክለኝነትና አስተማማኝነት፣ የመረጃ መተንተኛ ዘዴዎች አይነትና ባህርይ፣ የዋናው ጥናት የአጠናን ሂደትና በሙከራውም ሆነ በዋናው ጥናት የተደረጉ ስነምግባራዊ ትኩረቶች ተብራርተዋል፡፡

## 4.2. የጥናቱ ንድፍና ስልት

የዚህ ጥናት ዋና አላማ የቤተሰብ ዳራ የአንብቦ መረዳት ችሎታን የመተንበይ ድርሻውን በአምስተኛና በሰባተኛ ክፍል ተማሪዎች ተተኳሪነት ላይ መለየት ነው፡፡ በመሆኑም መጠናዊ የምርምር አይነትን ይከተላል፡፡ የተመረጠው የምርምር ንድፍም ተንባይ (ተዛምዷዊ) ሲሆን ገላጭ የምርምር ስልትንም ተከትሏል፡፡ ይህ ዘዴ የተመረጠው በተላውጦዎች መካከል ያለውን ተዛምዶና የተጽዕኖውን መጠን ለማሳየት የሚረዳ ዘዴ በመሆኑ ነው፡፡

የቤተሰብ ዳራ የአንብቦ መረዳት ችሎታን በምን ያክል ደረጃ እንደሚተነብይ በመጠናዊ የመተንተኛ ዘዴዎች ከተሰላ በኋላ በቁጥር የተገለጸው ደረጃ አይነታዊ በሆነ መልኩ ተብራርቷል፡፡

በተመረጠው የጥናት ንድፍ መሰረት የሙከራ ጥናቱ ተሳታፊዎች የምርምር መንገድን በመከተል ተመርጠዋል፡፡ የተመረጡት ተማሪዎችም የአንብቦ መረዳት ችሎታ መለኪያ ፈተና ወስደዋል፡፡ በተጨማሪም የቤተሰብ ዳራ የሚለካውን መጠይቅ ሞልተዋል፤ የቡድን ውይይትም አካሂደዋል፡፡

## 4.3. የትምህርት ቤትና የተጠኝዎች አመራረጥ

ይህ ጥናት በመጀመሪያ ደረጃ ሁለተኛ ሳይክል ተማሪዎች ላይ ያተኩራል። የመጀመሪያ ደረጃ ሁለተኛ ሳይክል የተመረጠበት ምክንያቶች የሚከተሉት ናቸው። አንደኛው ምክንያት በኢትዮጵያ በአማርኛም ሆነ በሌሎች የኢትዮጵያ ቋንቋዎች የቤተሰብ ዳራን ከአንብቦ መረዳት ችሎታ ጋር በማዛመድ ያጠናም ሆነ የመተንበይ ድርሻውን ለማየት የሞከረ ጥናት ማግኘት አለመቻሉ ነው። ነገር ግን በአለም አቀፍ ደረጃ የተሰሩ ምርምሮችን ለማየት እንደተሞከረው በአብዛኛው የተሰሩት በአንደኛ ደረጃ ሁለተኛ እርከን ተማሪዎች ላይ ነው።

ከላይ ከተጠቀሰው ምክንያት በተጨማሪ በሀገራችን የትምህርት እቅድ ለመማር ማንበብ የሚለው መርህ የሚጀምረው ከአምስተኛ ክፍል በመሆኑ ከአንብቦ መረዳት ችሎታ ጋር የተገናኙ ምርምሮችን ለመስራት ሲታሰብ ከአምስተኛ ክፍል መጀመሩ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ ነው።

እንዲሁም ለሁለተኛ ደረጃ የትምህርት እርከን የአንብቦ መረዳት ችሎታ መሰረቱ የአንደኛ ደረጃ የትምህርት እርከን የአንብቦ መረዳት ችሎታ ነው። ለአንብቦ መረዳታቸው ብቻ ሳይሆን ለአጠቃላይ ትምህርት መረዳት ዋና መሰረት ነው። አንብቦ መረዳት ሲታሰብ ደግሞ አብረው የሚነሱ ተጽዕኖ ፈጣሪ ተላውጦዎችም ናቸው። በመሆኑም በዙሪያው ያሉ የተለያዩ ነገሮችን ገና ከጅምሩ ጀምሮ ማጥናት የሚገባ በመሆኑ ከአንደኛ ደረጃ የሁለተኛ እርከን ተማሪዎች የአምስተኛና የሰባተኛ ክፍል ተማሪዎች ተመርጠዋል።

በሙከራ ጥናቱ አራቱንም የክፍል ደረጃ በማካተት የተሰራ ቢሆንም ከመተንተኛ ዘዴው አንጻር፣ ከመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ባህሪና የተጠኝዎች ብዛት አንጻር ሁሉንም ማካተት እንደማይቻል በሙከራ ጥናቱ ተረጋግጧል። በመሆኑም ከመረጃ መሰብሰቢያዎች አስተማማኝነትና በክፍል ደረጃ ያለውን ልዩነት ለማየት በአምስተኛና በሰባተኛ ላይ ተሰርቷል። በመጨረሻ የሚነሳው ምክንያት የጥናቱ አላማ የቤተሰብ ዳራ የአንብቦ መረዳት ችሎታን የመተንበይ ድርሻውን መለየት እንደመሆኑ ተጠኝዎች

ፈተናውን መፈተንና የቤተሰብ ዳራ የሚለካውን መጠይቅ መሙላት ይጠበቅባቸዋል፡፡ መጠይቁን በአግባቡ መሙላትና ፈተናውን መፈተን የሚችሉት ደግሞ ከአምስተኛ ክፍል ጀምሮ ያሉት ተማሪዎች በመሆናቸው ጥናቱ በአምስተኛና በሰባተኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ ያተኩራል፡፡

ከቦታ አንጻር ጥናቱ በየትኛውም የአማራ ክልል በሚገኙ የአንደኛ ደረጃ የሁለተኛ እርከን የአማርኛ አፈ ፈት ተናጋሪዎች ላይ መሰራት የሚችል በመሆኑ ለአጥኚዋ መረጃ ለመሰብሰብ እንዲሁም የመምህራንና የተማሪዎችን ትብብር ለማግኘት የሚያስችለው የባህርዳር ከተማ አስተዳደር ተመርጧል፡፡ የአማራ ክልል ዋና ከተማ በሆነችው ባህርዳር ከተማ አስተዳደር ውስጥ ሀያ ሶስት የመጀመሪያ ደረጃ ሙሉ ሳይክል የመንግስት ትምህርት ቤቶች ይገኛሉ፡፡ ከነዚህ ትምህርት ቤቶች ውስጥ በእጣ ንሞና ቀበሌ አስራ አራት የሚገኘው የዶና በርበር የመጀመሪያ ደረጃ ሙሉ ሳይክል ትምህርት ተመርጧል፡፡ የዕጣ ንሞና ተግባራዊ የተደረገው በዚህ ጥናት ባህርይ መሰረት ሁሉም ተማሪዎች እኩል መረጃ መስጠት ስለሚችሉ ሁሉንም ተተኳሪ ተማሪዎች ተሳታፊ ለማድረግ ነው፡፡

ከተመረጠው ትምህርት ቤት በሁለቱም የክፍል ደረጃዎች ከሚገኙ አራት አራት ሴክሽኖች ሁለት ሁለቱ በዕጣ ንሞና ተመርጠው ፈቃደኝነታቸው ተጠይቆ መጠይቁን ሞልተዋል፡፡ ፈተናውንም ወስደዋል፡፡ ከአምስተኛ “ሀ”ና “ለ” እንዲሁም ከሰባተኛ ክፍል “ሀ” ና “ለ” ሴክሽኖች ተመርጠዋል፡፡ ከተመረጡት ሴክሽኖች ከአምስተኛ “ሀ” 79 ከአምስተኛ “ለ” 75 በድምሩ 154 ተማሪዎች ከሰባተኛ “ሀ” 87 ከሰባተኛ “ለ” 85 በድምሩ 172 ተማሪዎች በጥናቱ ተመርጠዋል፡፡ የተመረጡ ተማሪዎችና በፈቃደኝነት መረጃውን የሰጡ ተማሪዎች ቁጥር እንደሚከተለው በሰንጠረዥ ቀርቧል፡፡

ሰንጠረዥ 3.1

*በዕጣ ንሞና ለጥናቱ የተመረጡና መረጃውን የሰጡ ተማሪዎች*

| | | 5ኛ ክፍል | | | 7ኛ ክፍል | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ሀ | ለ | ድምር | ሀ | ለ | ድምር |
| የተመረጡ ተማሪዎች ስብጥር | ወንድ | 41 | 38 | 79 | 41 | 42 | 83 |
| | ሴት | 38 | 37 | 75 | 46 | 43 | 89 |
| | ድምር | 79 | 75 | 154 | 87 | 85 | 172 |

የተመረጡት ተማሪዎች በዕለቱ ተገኝተው በትምህርት ቤቱ ምክትል ርዕሰ መምህር፣ በክፍሉ የአማርኛ መምህርትና በአጥኝዋ ስለምርምሩ አላማና አስፈላጊነት እንዲሁም ከነሱ ስለሚጠበቀው ስራና የሚሰጡት መረጃ ጠቃሚነት ዝርዝር መረጃ ማብራሪያ ከተሰጣቸው በኋላ ፈቃደኝነታቸው ተጠይቋል፡፡ ነገር ግን መጠይቁ በሚሞላበትና ፈተናውን በሚፈተኑበት ጊዜ ከአምስተኛ ክፍል 3 (ሁለት ሴት አንድ ወንድ) እንዲሁም ከሰባተኛ ክፍል 2 (1 ወንድ 1 ሴት) ተማሪዎች በግል ችግር ምክንያት ባለመገኘታቸው በ151 የአምስተኛና በ170 የሰባተኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ ዋናው ጥናት ተካሂዷል፡፡

ይህ የተማሪ ቁጥር ሲመረጥ ለማደራጀት ካለው አቅምና ሁኔታ በተጨማሪ የጥናቱን የተላውጦ አይነትና የመተንተኛ ዘዴ ባህርይ መሰረት በማድረግ ነው፡፡ በPallant (2010) የተጠቀሱት Tabachnick & Fidell (2007) እንደሚሉት አንድን ጥናት በድህረት ትንተና ለመተንተን ሲታሰብ የንሞና አወሳሰዱ ለአምስት ነጻ ተላውጦ ቢያንስ 15 ተሳታፊ መወሰድ አለበት የሚለውን መሰረት በማድረግ ነው፡፡ በዚህ ጥናት ደግሞ ከቤተሰብ ዳራ ጋር ተያይዘው የሚነሱት ተላውጦች በርካታ ስለሆኑ የሚዳሰሱት ጉዳዮችም በርካታ ተማሪን የሚፈልጉ ስለሆኑ 321 ተማሪዎች በጥናቱ ተካተዋል፡፡

## 4.4. የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች

የጥናቱን ዋናና ዝርዝር አላማ ከግንዛቤ በማስገባት ለዚህ ጥናት የተመረጡት የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች መጠይቅ፣ ፈተናና የቡድን ውይይት ናቸው፡፡ መጠይቁ

የቤተሰብ ዳራ የሚለካ ሲሆን ፈተናው የተማሪዎችን የአንብቦ መረዳት ችሎታ መለኪያ ሆኖ ተዘጋጅቷል፡፡ በሶስተኛ ደረጃ የተዘጋጀው የቡድን ውይይት ሲሆን ተጨማሪ መረጃ ለመሰብሰብ ያገለገለ ነው፡፡ የእያንዳንዳቸው አላማና ተግባር እንደሚከተለው በዝርዝር ቀርቧል፡፡

### 3.4.1.የጽሁፍ መጠይቅ

የጽሁፍ መጠይቅ አንዱ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ በመሆን አገልግሏል፡፡ ተግባራዊ የተደረገውም የተማሪዎችን የቤተሰብ ዳራ በተመለከተ መረጃ ለማግኘት ነው፡፡

#### 3.4.1.1. የተማሪዎችን የቤተሰብ ዳራ የሚለካ የጽሁፍ መጠይቅ

የተማሪዎችን ቤተሰባዊ ዳራ የሚለካው መጠይቅ የተዛማጅ ጽሁፎችንና ከቤተሰብ ዳራ ጋር ተቀራራቢነት ያላቸውን መጠይቆች መሰረት በማድረግ በተመራማሪዋ ተዘጋጅተው የቀረቡ ናቸው፡፡ ከተዳሰሱት ድርሳናት መካከል በዋናነት ትኩረት የተደረገባቸው የተዛማጅ ድርሳናት አራት ናቸው፡፡ እነሱም የትምህርታዊ ጽሁፎችን የማንበብ ችሎታ እድገት ጥናት (Progress in Reading Literacy Study (PIRLS), የአለም አቀፍ ምዘና መርሀ ግብር (Programme for International Student Assessment (PISA), የሂሳብና ሳይንስ ልምድ ጥናት Trends in Mathematics and Science Study (TIMSS)ና የ Lindo (2007) ጥናት ናቸው፡፡ ሶስቱ ጥናቶች በአለም አቀፍ ደረጃ የሚደረጉ ጥናቶች ሲሆኑ ከቤተሰብ ዳራ ጋር የተገናኙትንና ለተማሪው የሚቀርቡትን ጥያቄዎች በመምረጥ ሲሆን የመጨረሻው Lindo (2007) ለዶክቶሪያል ዲግሪ ማሟያ ከሰሩት ምርምር ውስጥ የተጠቀሙበት መጠይቅ በመዳሰስ ነው፡፡

የቤተሰብ ዳራ የሚለካው መጠይቅ 12 ጥያቄዎችን የያዘ ሲሆን በሶስት የአቀራረብ አይነት ቀርቧል (አባሪ 1.1ን ይመልከቱ)፡፡ ከአስራ ሁለቱ ጥያቄዎች ጥያቄ ቁጥር 3፣ 4፣ 5፣ 8፣ 9፣ 10፣ 11ና 12 ዝግ የጥያቄ አቀራረብን የተከተሉ ናቸው፡፡ ጥያቄ 1፣ 6ና 7 ቅይጥ የአቀራረብ አይነት ሲኖራቸው ጥያቄ ቁጥር 2 ደግሞ ክፍት የጥያቄ አቀራረብ አይነትን የተከተሉ ናቸው፡፡

ይህ መጠይቅ በሙከራ ጥናቱ አስራ ስምንት ጥያቄዎችን አካቶ ቀርቦ ነበር (አባሪ 2.1 ይመልከቱ)፡፡ በቅድመ ሙከራው ሁለቱ ጥያቄዎች ተወግደው አስራ ስድስት ጥያቄዎች ብቻ ቀርተዋል፡፡ የሙከራ ጥናቱ ከተደረገ በኂላም በቤተሰብ ዳራ መለኪያ መጠይቁ ላይ ተጨማሪ ማሻሻያዎች ተደርገዋል፤ አንዳንድ ጥያቄዎችም ተወግደዋል፤ አንዳንዶችም ተሻሽለዋል፡፡

ከሙከራ ጥናቱ በኂላ አራት ጥያቄዎች ተወግደዋል፤ ሶስት ጥያቄዎችም ማሻሻያ ተደርጎባቸዋል፡፡ ማሻሻያ ከተደረገባቸው ጥያቄዎች የመጀመሪያ የቤተሰብ መዋቅርን የሚለካው ከማን ጋር ትኖራለህ/ ትኖሪያለሽ? የሚለው ጥያቄ በሙከራ ጥናቱ ጊዜ ስምንት አማራጮችን ይዞ ቀርቦ ነበር፡፡ እነሱም አንደኛ ከእናት አባት ጋር፣ ሁለተኛ ከእናት ጋር ብቻ፣ ሶስተኛ ከአባት ጋር ብቻ፣ አራተኛ ከእናቴና ከእንጀራ አባቴ፣ አምስተኛ ከአባቴና ከእንጀራ እናቴ፣ ስድስተኛ ከሌሎች ዘመዶቼ ጋር፣ ሰባተኛ የስጋ ዝምድና ከሌላቸው ሰዎች ጋርና ስምንተኛ ብቻየና ሌላ ካለ ይገለጽ የሚሉ ነበሩ፡፡ ከሙከራ ጥናቱ በኂላ ስምንቱ አማራጮች የተንዛዙ ሆነው በመገኘታቸው በባለሙያዎች አስተያየት በአራት አማራጮች ተወስኖ ቀርበዋል፡፡ በባለሙያዎች አስተያየትና በሙከራ ጥናቱ በተገኘው ተሞክሮ ሌላ ማሻሻያ የተደረገበት የቤተሰብ ብዛትን የሚጠይቀው በቤተሰብ ምን ያክል ሰው ይኖራል? የሚለው ጥያቄ ነበር፡፡ ለዚህ ጥያቄ በሙከራ ጥናቱ ከ1 እስከ 3፣ ከ4 እስከ ስድስትና ከ7 በላይ በሚሉ ሶስት አማራጮች ተወስኖ ቀርቦ የነበረ ሲሆን በዋናው ጥናት በክፍት ጥያቄ መቅረቡ የተሻለ በመሆኑ ክፍት ጥያቄ ሆኖ በቁጥር ምላሽ እንዲሰጡ ተደርጓል፡፡

የቤተሰብ የትምህርት ደረጃ መለኪያ ሆነው የቀረቡት በቤተሰብ መደበኛ ትምህርት የተማረ ሰው አለ የሚለውና በቤተሰብ የተማረ ሰው ብዛት ስንት ነው? የሚሉት በሌሎች የቤተሰብ የትምህርት ደረጃን በሚለኩ ጥያቄዎች ስለሚመለሱ የተሳታፊዎችንና የአጥኝዋን ጊዜ ለመቆጠብ ሲባል ተወግደዋል፡፡ በተመሳሳይ ቤተሰቦችህ/ሽ እንድታነብ እንድታነቢ ምን ያክል ያበረታቱሀል፣ ያበረታቱሻል? የሚለው ከቤተሰብ ዳራ ይልቅ የቤተሰብ ድጋፍን የሚለካ ጥያቄ በመሆኑ ሙሉ በመሉ ተወግዷል፡፡

የቤት ውስጥ ግብዓት አንዱ የቤተሰብ ዳራን የሚለካ ጥያቂ ሆኖ ቀርቧል፡፡ ነገር ግን ከተጠኝዎቹ ባህርይ አንጻር ሲታይ በስድስት ተከፍለው ከቀረቡት አማራጮች ሞባይል የሚለው ተወግዷል፡፡ ምክንያቱም ከተሳታፊዎቹ መካከል 99.9% የሚሆኑት ተመሳሳይ ምላሽ በመስጠታቸው ጥያቄው በዋናው ጥናት የመረጃ ስብሰባ ወቅት ተወግዷል፡፡ ሙሉ ለሙሉ ተወግደው በሌላ የማህበራዊ ደረጃ መለኪያዎች የተተኩት የኢትዮጵያ የማህበራዊ ተሳትፎ መለኪያ የሆኑት እድር፣ እቁብና ማህበር ናቸው፡፡ እነዚህ ተላውጦዎች የተወገዱት በትንተና ወቅት ደጋፊ ተዛማጅ ጽሁፍ ያልተገኘላቸውና ከተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ችሎታ ጋር የማይዛመዱ በመሆናቸው ነው፡፡ በነሱ ምትክ ማህበራዊ ደረጃን እንዲለኩ የተደረጉት ቤተሰብ ትምህርት ቤት በሚያደረገው የተማሪ ወላጅ ስብሰባ ያለው ተሳትፎ፣ በትምህርት ቤት የልማት ኮሚቴነት መሳተፍና በትምህርት ቤት የዲሲፒሊን ኮሚቴነት መሳተፍ በሚሉት ተተክተዋል፡፡ በመጨረሻም በጥያቄ ቁጥር 18 በክፍት የአቀራረብ ስልት የቀረበው ጥያቄ ተወግዶ ለቡድን ውይይት እንዲቀርብ ተደርጓል፡፡

በአጠቃላይ በዋናው ጥናት የተካተቱት ተላውጦዎች የቤተሰብ መዋቅር (ከማን ጋር ትኖራለህ/ሽ/፣ የቤተሰብ ብዛት (ስንት የቤተሰብ አባል አለ)፣ የቤተሰብ የትምህርት ደረጃ (የሴትና የወንድ አሳዳጊ በተናጥል)ና ሁኔታ (በቤት ውስጥ የሚገኘው ከፍተኛው የትምህርት ደረጃ)፣ የቤተሰብ ስራ (የሴትና የወንድ አሳዳጊ በተናጥል)፣ ለማንበብ የሚረዱ የተለያዩ ቁሳቁሶች መኖርና አለመኖር (በአምስት የተለያዩ አማራጮች ተነጣጥሎ)፣ የቤተሰብ ገቢ (የእለት ምግብን ጨምሮ)ና ማህበራዊ ሁኔታ ናቸው፡፡ የእነዚህ ተላውጦዎች የጥያቄ አቀራረብ በምርጫ፣ በጻፍና በቅይጥ መልኩ ነው፡፡

ጥያቄዎቹ በተመራማሪዋ ከተዘጋጁ በኋላ በአጥኝዋ አማካሪዎች፣ በቋንቋ ባለሙያዎችና በስነልቦና ምሁራን ተገምግሟል፡፡ አላስፈላጊ ቃላትና አሻሚ ጽንሰ ሀሳቦች ተወግደዋል፡፡ ተገቢነታቸውን ለማረጋገጥም መረጃ ከመሰብሰቡ በፊትና ከተሰበሰበ በኋላ ተገቢነታቸው ተረጋግጧል፡፡ ውጤቱ ከተሰብሰበ በኋላም ተገቢ ምላሽ ማስገኘታቸው ለማረጋገጥ ምላሾች ላይ ተገቢ ግምገማ ተደርጓል፡፡

### 3.4.2.ፈተና

የተማሪዎችን የአንብቦ መረዳት ችሎታ ለመለካት አገልግሎት ላይ የዋለው የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ፈተና ነው፡፡ በሙከራ ጥናቱ አራት ለዋናው ጥናት ደግሞ ሁለት የተለያዩ ፈተናዎች ተዘጋጅተዋል፡፡ የእያንዳንዳቸው አዘገጃጀት፣ የይዘት ትክክለኝነት፣ የክብደት ደረጃ፣ የውጤት ስርጭትና አሰተማማኝነት ተሰልቷል፡፡ ዝርዝሩም ከዚህ በታች ቀርቧል፡፡

#### 3.4.2.1. የፈተና አዘገጃጀት

በተጠኝነት የሚመረጡት ተማሪዎች ከተለያየ የክፍል ደረጃ የተወሰዱ በመሆኑ ሁለት የተለያዩ ፈተናዎች ተዘጋጅተዋል፡፡ ለአምስተኛና ለሰባተኛ ክፍል ተማሪዎች የተዘጋጀው የተለያየ ፈተና ነው፡፡ ምንባቦቹ የሁሉም የተወሰዱት ከ2007 ተሻሽለው በተዘጋጁት አዲሶቹ የመማሪያ መጽሀፍትና የማስተማሪያ መጽሀፍት ላይ ነው፡፡ የእያንዳንዳቸው አዘገጃጀትና አወሳሰድ የተለያየ በመሆኑ በክፍል ደረጃ ቅደም ተከተል መሰረት እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

ለአምስተኛ ክፍል የተዘጋጀው ፈተና ሶስት ክፍሎች ያሉትና 30 የጥያቄ ቁጥር ያለው ነው (“አባሪ 1.3”ን ይመልከቱ)፡፡ የመጀመሪያው ክፍል 10 ጥያቄዎችን የያዘው የእውነት ሀሰት ጥያቄ ነው፡፡ ሁለተኛው 10 ጥያቄዎችን የያዘው የአዛምድ ጥያቄ ሲሆን ሶስተኛው ክፍል ደግሞ የምርጫ ጥያቄ ሆኖ 10 ጥያቄዎችን የያዘ ነው፡፡ ይህን የጥያቄ አወጣጥ ስልት መከተል ያስፈለገው ለአንደኛ ደረጃ ተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች ሲዘጋጁ ጥሩ የሚባሉ የአቀራረብ አይነቶች ምርጫ፣ አጭር መልስ ስጡ፣ እውነት ሀሰትና አዛምድ በመሆኑ ነው (Madsen, 1983)፡፡ አንድ የአንብቦ መረዳት ፈተና ሲዘጋጅ የተለያዩ የፈተና አይነቶችን ቢያካትት ተመራጭ ይሆናል (Madsen, 1983)፡፡

በሁለተኛ ደረጃ የተዘጋጀው የአንብቦ መረዳት ችሎታ መለኪያ ፈተና ለሰባተኛ ክፍል ሲሆን 25 የምርጫ ጥያቄዎችን ያካተተ ነው (“አባሪ 1.4.”ን ይመልከቱ) ፡፡ ፈተናው በምርጫ ብቻ የተገደበው በሶስት ምክንያቶች ነው፡፡ አንደኛው የመምህሯ የፈተና

አወጣጥ በዚህ አይነት የተለመደ መሆኑ ሁለተኛ ልጆቹ ክልላዊ ፈተና ለመውሰድ አንድ አመት የቀራቸው በመሆኑና ክልላዊ ፈተናው ምርጫን ብቻ የሚያካትት መሆኑና የተመረጠው ምንባብ ከሌሎች የፈተና አቀራረቦች ይልቅ ለምርጫ የተመቸ በመሆኑ እንዲሁም የተካተቱት አምስት የእውነት ሀሰት ጥያቄዎች በቅድመ ሙከራ ጥናቱ ወቅት አስተማማኝነታቸው ዝቅተኛ ሆኖ በመገኘቱ አምስቱም ተወግደው በ25 የምርጫ ጥያቄዎች ብቻ መረጃው ተሰብስቧል።

ለሙከራ ጥናቱ ተግባራዊ ተደርገው በዋናው የተወገዱት የስድስተኛና የስምንተኛ ክፍል ፈተዎችም ተዘጋጅተው ነበር። የስድስተኛ ክፍል የአንብቦ መረዳት ችሎታ መለኪያ ፈተና ባለ 30 ጥያቄ ሲሆን አምስተኛ ክፍል ላይ እንደተገለጸው የተለያዩ የጥያቄ አቀራረብ ስልቶችን መከተል አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ ሶስት የአጠያየቅ አይነቶች ተግባራዊ ተደርገዋል ("አባሪ 2.5"ን ይመልከቱ)። እነሱም የእውነት ሀሰት፣ የአዛምድና የምርጫ ናቸው። ከአጠቃላዩ 30 ጥያቄዎች ውስጥ 10 የእውነት ሀሰት፣ ሰባት የአዛምድና አስራ ሶስት የምርጫ ጥያቄዎች ተዘጋጅተው ቀርበዋል።

የስምንተኛ ክፍል የአንብቦ መረዳት ፈተና በአራተኛ ደረጃ ተዘጋጅቷል ("አባሪ 2.3"ን ይመልከቱ)። ፈተናው 30 ጥያቄዎችን ያካተተ ሲሆን ሁሉም የምርጫ የጥያቄ አቀራረብን ተከትለው የተዘጋጁ ናቸው። ሁሉም ምርጫ የሆኑበት ምክንያት ሀገር አቀፍ የአንደኛ ደረጃ የሁለተኛ ሳይክል መልቀቂያ ፈተና የሚወስዱ በመሆናቸው ከክልላዊ ፈተናው አወጣጥ ጋር ተቀራራቢ ለማድረግ ታስቦ ነው።

### 3.4.2.2. የምንባብ አመራረጥ

የአንብቦ መረዳት ችሎታ መለኪያ ፈተናው ሲዘጋጅ ትኩረት የተደረገበት ሌላው ጉዳይ የምንባብ አመራረጥ ሂደቱ ነው። ለሁሉም የፈተና አይነቶች የተለያዩ ምንባቦች ተዘጋጅተዋል። ምንባቦቹ የተወሰዱት የትምህርት ሚኒስቴርና የአማራ ክልል ትምህርት ቢሮ ከአሜሪካ ህዝብ በአሜሪካ ዓለም አቀፍ የልማት ድርጅት ጋር በመተባበር በ2007 ካሳተሙት የመማሪያና የማስተማሪያ መጽሀፍት ነው።

ምንባቦች ሲመረጡ የምንባብ መምረጫ መስፈርቶች የተወሰዱት ከ Campbell, et al (2001) የምንባብ መምረጫ መስፈርቶች ነው፡፡ እነሱም የመጀመሪያው የስርዓተ ትምህርት ባለሙያዎች የገመገሙት መሆን አለበት የሚል ሲሆን ይህንን መስፈርት በመውሰድ ምንባቦችን ከአዲሱ መማሪያ መጻፍ ተወስዷል፡፡ ይህም ምንባቡ ከእድሜያቸው ጋር ይመጣጠናል ለሚለው መለኪያ ጭምር መልስ ይሰጣል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ከሀይማኖት፣ ከዘርና ከስርዓተ ጾታ አድልዎ የጸዳ መሆን አለበት የሚለውን መስፈርት የሚያሟላ መሆኑ ጭምር ተለይቷል፡፡

በአምስተኛ ክፍል የመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ አስር ምዕራፎች ተካተዋል፡፡ እያንዳንዱ ምዕራፍ የአንብቦ መረዳት ችሎታን ሊያዳብሩ የሚችሉ ምንባቦችን ይዟል፡፡ ከነዚሁ ምንባቦች መካከል በምዕራፍ ሰባት ላይ የዱር እንስሳትን በተመለከተ የቀረበው ምንባብ ተመርጧል፡፡ ከመማሪያ መጽሀፉ ላይ የተመረጠበት ምክንያት በበርካታ ባለሙያዎች የተገመገመና የጸደቀ በመሆኑ የምንባቡን የክብደት ደረጃ መጠነኛ ለማድረግ ታስቦ ሲሆን ምዕራፍ ሰባት ከሌሎች ተለይቶ የተመረጠው መረጃው የሚሰበሰበው በመጀመሪያው ወሰነ ትምህርት በመሆኑ እንደማይማሩት እርግጠኛ ለመሆንና በሁለተኛው ወሰነ ትምህርት ከሚማሩት ውስጥ ደግሞ በይዘትና በስፋት የተሻለ ሆኖ በመገኘቱ ነው፡፡

በሰባተኛ ክፍል የመማሪያ መጽሀፍም በተመሳሳይ አስር ምዕራፎች ተካተዋል፡፡ ከአስሩ ምዕራፍ ሰባተኛው ተመርጦ ፈተናው ከተዘጋጀ በኋላ የይዘት ተገቢነቱን ለማረጋገጥ በቅድመ ፈተናው 15 ተማሪዎች ምንባቡ ሳይሰጣቸው ፈተናውን እንዲፈተኑ ተደርገው አብዛኞቹ ከግማሽ በላይ በመመለሳቸው ምንባቡ ውድቅ ተደርጎ ከመምህሩ መምሪያ ከቀረቡት አስር ምዕራፎች ስምንተኛው ምንባብ ለታሰበው አላማ እንዲውል በማሻሻል ተወስዷል፡፡

ከላይ ከተገለጹት ምክንያቶች በተጨማሪ ምንባቦቹ ሲመረጡ ትኩረት ውስጥ የገቡት ነገሮች በርካታ ናቸው፡፡ አንደኛ የምንባቡ ሳቢነት፣ ሁለተኛ ጥያቄ ለማውጣት ያላቸው ይዘት፣ ሶስተኛ ተነባቢነቱ ተሳታፊዎች መረጃ ከመስጠታቸው በፊት ያልተማሯቸው መሆናቸው ናቸው፡፡

### 3.4.2.3. የፈተናዎች የይዘት ትክክለኝነትና ተገቢነት

ለአምስተኛና ለሰባተኛ ክፍል የተዘጋጁት ፈተናዎች በሙከራ ጥናቱ በተገኘው ልምድ መሰረት ዋና ጥናቱ ከመካሄዱ በፊት የማመሳከሪያ ቅጽን መሰረት በማድረግ የይዘት ትክክለኝነታቸውንና ተገቢነታቸውን ለመገምገም ተሞክሯል፡፡ የማመሳከሪያ ቅጹ እንድሪስ (2009) Hughes (2003)፣ Brown (1996) ና Alderson, Campham& Wall (1995) ያዘጋጁትን የአንብቦ መረዳት ፈተና የይዘት ትክክለኝነት መገምገሚያ መስፈርት በመውሰድ ያዘጋጀውን በማሻሻል የተወሰደ ነው (አባሪ 1.6 ይመልከቱ)፡፡ የማመሳከሪያ ቅጹ አስራ ሶስት መስፈርቶች ያሉት ሲሆን ከበጣም ከፍተኛ እስከ ዝቅተኛ በሆነ ባለ አራት እስኬል የሊከርት መጠይቅ ነው፡፡

የፈተናውን የይዘትና የቅርጽ ትክክለኝነት እንዲገመግሙ ሶስት የቋንቋ ባለሙያዎች ተመርጠዋል፡፡ ሶስቱ የቋንቋ ባለሙያዎች የአንብቦ መረዳት ፈተናዎችን በአስራ ሶስት መለኪያዎች ገምግመው ነጥብ ሰጥተዋል (የሰጡት ነጥብ አባሪ 1.6.1. ይመልከቱ)፡፡ የሰጡትን ነጥብ የዳኞች ስምምነት (inter raters reliability) ተሰልቶ የተገኘው ነጥብ ለአምስተኛ ክፍል = 0.735 ሲሆን ለሰባተኛ ክፍል ደግሞ = 0.756 ነው፡፡ ይህ ውጤትም የአንብቦ መረዳት ፈተናዎቹ ያላቸው ይዘት ትክክለኝነቱ ተቀባይነት እንዲኖረው ያደርጋል፡፡

### 3.4.2.4. የፈተናዎቹ የውጤት ስርጭት ወጥነት

በሙከራ ጥናቱም ሆነ በዋናው ጥናት ወቅት የሁሉም የክፍል ደረጃዎች የአንብቦ መረዳት ውጤት ያለው የስርጭት ወጥነት የተለያዩ የስርጭት ወጥነት መፈተሻ ስልቶችን በመጠቀም ተፈትሿል፡፡ ለሙከራ ጥናቱ ለአራቱም የክፍል ደረጃ ለተዘጋጁ የአንብቦ መረዳት መለኪያ ፈተናዎችና የማንበብ ተነሳሽነት ውጤት ለዋናውም ጥናት ለአምስተኛና ለሰባተኛ ክፍል ተማሪዎች የተዘጋጀውን ፈተናና የማንበብ ተነሳሽነት ውጤቱ በድጋሚ የውጤት ስርጭቱ ተሰልቷል፡፡ ኮሞግሮቭ ስሚኖቭ ቴስት በመጠቀም በተደረገው ስሌት እንደሚያሳየው ሁሉም የፈተና ውጤቶች ስርጭታቸው ወጥ ሆኖ ተገኝቷል (ለዋናው የፈተና ውጤት አባሪ 1.5.3 እና አባሪ 1.5.8ን ይመልከቱ የሙከራ

ፈተና የውጤት ስርጭት ወጥነን ከ 2.7 ጀምሮ በእያንዳንዱ ዝርዝር ውጤት ስር ያለውን የውጤት ስርጭት ወጥነት ይመልከቱ)። የፈተናዎቹ ውጤት ስርጭት ወጥ ሆኖ መገኘቱ የመተንተኛ መንገዶቹ ፓራሜትራዊ መፈተሻዎች እንዲሆኑ የሚፈቅድ ነው። የማንበብ ተነሳሽነት ውጤቱም በተመሳሳይ ወጥነቱን ስለሚያሳይ የፓራሜትሪያዊ መፈተሻ ተግባራዊ ተደርጓል።

### 3.4.2.5. የጥያቄዎቹ የክብደት ቅለት መጠን

የዋናው ጥናቱ ከመካሄዱ በፊት የፈተናውን አስተማማኝነትና ትክክለኝነት ለማጣራት ከተሰራው ስራ አንዱ የፈተናዎችን የጥያቄ ክብደት ቅለት መጠን መፈተሽ ነበር። በመሆኑም በሙከራ ጥናቱም ሆነ በዋናው ጥናት ላይ ለመፈተሽ ተሞክሯል። በሙከራ ጥናቱ የተሳተፉት ተማሪዎች ከአራቱም የክፍል ደረጃ የተገኙ በመሆናቸው የአምስተኛ፣ የስድስተኛ፣ የሰባተኛና የስምንተኛ ክፍል ተማሪዎች በእያንዳንዱ ጥያቄ ላይ ያገኙት ተመዝግቦ በክፍል ደረጃቸው በመነጠል የእያንዳንዱ ጥያቄ የክብደት ቅለት መጠን ተሰልቷል።

የአምስተኛ ክፍል አንብቦ መረዳት ጥያቄዎች በሙከራ ጥናቱ ወቅት በ52 ተማሪዎች ላይ በተደረገው ፍተሻ ጥያቄ ቁጥር 22 ከባድ (ከ0.25 በታች)፣ ጥያቄ ቁጥር 1፣ 7፣ 8፣ 10፣ 11፣ 12፣ 13፣ 14፣ 15፣ 16፣ 17፣ 18፣ 19፣ 20፣ 21፣ 23፣ 24፣ 25፣ 26፣ 27፣ 28፣ 29ና 30 መካከለኛ (ከ0.25 እስከ 0.75) ና ጥያቄ ቁጥር 2፣ 3፣ 4፣ 5፣ 6ና 9 (ከ 0.75 በላይ) ቀላል የክብደትና ቅለት መጠን ታይቶባቸዋል (አባሪ 2.7.4 ይመልከቱ)። ቀላልና ከባድ የክብደት ቅለት መጠን ያሳዩት ሰባት ጥያቄዎች የተወሰነ ማሻሻያ ተደርጎባቸው ለዋናው ጥናት ቀርበዋል በዚህም መሰረት ጥያቄ ቁጥር 4 ብቻ ሲቀር ቀሪዎቹ መካከለኛ የክብደት መጠን ያላቸው ሆነው ተገኝተዋል (አባሪ 1.5.4. ይመልከቱ)። እንዲሁም መካከለኛ የክብደት መጠን የነበረው የጥያቄ ቁጥር 18 ቀላል የክብደት መጠን አሳይቷል።

የክብደት ቅለት መጠኑ የተሰላው ሌላው የአንብቦ መረዳት ችሎታ መለኪያ ፈተና ለሰባተኛ ክፍል የተዘጋጀው ፈተና ነው። በቅድመ ሙከራ ፈተናው ወቅት

ከአስተማማኝነት ጋር በተገናኙ ምክንያቶች 5 እውነት ሀሰት ጥያቄዎች ተወግደዋል፡፡ ከቅድመ ሙከራ በኋላ የሰባተኛ ክፍል የአንብቦ መረዳት ችሎታ መለኪያ ጥያቄዎች 25 ሲሆኑ በሙከራ ጥናቱ ወቅት በተደረገው የክብደት ቅለት ፍተሻ ጥያቄ ቁጥር ጥያቄ ቁጥር 1፣ 7፣ 13ና 18 ከ0.75 በላይ በመሆናቸው ከባድ ሆነው ሲገኙ ጥያቄ ቁጥር 24 0.13 የክብደት መጠን በማስመዝገቡ ከባድ ጥያቄ ሆኗል፡፡ ቀሪዎቹ ጥያቄዎች ከ0.25 እስከ 0.75 በሆነ ውጤት መካከለኛ የክብደት ቅለት መጠን በማስመዝገባቸው ምንም አይነት ማሻሻያ ሳይደረግባቸው ለዋናው ጥናት አገልግሎት እንዲሰጡ ተደርገዋል (አባሪ 2.7.14. ይመልከቱ)፡፡ ቀላልና ከባድ ጥያቄዎች የተወሰነ ማሻሻያ ተደርጎባቸው ለዋናው ጥናት ቀርበዋል፡፡ የዋናው ጥናት ውጤትን መሰረት በማድረግ በተሰራው የክብደት ቅለት መጠን ከባድ የሚባል ጥያቄ አልተመዘገበም፡፡ ሁለት ቀላል ጥያቄዎች ተስተውለዋል (አባሪ 1.5.9. ይመልከቱ)፡፡

የስድስተኛና የስምንተኛ ክፍል ተማሪዎች የፈተና ውጤትም በሙከራ ጥናቱ የክብደት ቅለት መጠናቸው ተሰልቷል፡፡ የስድስተኛ ክፍል ሰላሳ ጥያቄዎችን ያካተተ ሲሆን ከሰላሳዎቹ ጥያቄዎች ስድስቱ ቀላል ሲሆኑ ሀያ አራቱ ደግሞ መካከለኛ ክብደት አስመዝግበዋል (አባሪ 2.7.9ን ይመልከቱ)፡፡ የስምንተኛ ክፍል የአንብቦ መረዳት ፈተና ለሙከራ ጥናቱ በተመሳሳይ ሰላሳ ጥያቄዎችን አካቷል፡፡ ከሰላሳዎቹ ጥያቄዎች ጥያቄ ቁጥር 1፣ 12ና 30 ከ0.25 በታች የክብደት ቅለት መጠን በማስመዝገባቸው ከባድ ጥያቄዎች ሆነው ተገኝተዋል፡፡ ጥያቄ ቁጥር 3፣ 5፣ 14ና 16 ከ0.75 በላይ በመሆናቸው ቀላል ሲሆኑ ጥያቄ ቁጥር 2፣ 4፣ 6፣ 7፣ 8፣ 9፣ 10፣ 11፣ 13፣ 15፣ 17፣ 18፣ 19፣ 20፣ 21፣ 22፣ 23፣ 24፣ 25፣ 26፣ 27፣ 28ና 29 ከ0.25 እስከ 0.75 የክብደት ቅለት ደረጃ በማምጣት መካከለኛ የክብደት ቅለት መጠን ይዘው ለሙከራ ጥናቱ የመረጃ መሰብሰቢያ ሆነው አገልግለዋል (አባሪ 2.7.19ኝን ይመልከቱ)፡፡

በአጠቃላይ ሲታይ ለዋናው ጥናት አገልግሎት ላይ የዋሉት ፈተናዎች በተለይም የሰባተኛና የአምስተኛ ክፍል ፈተናዎች በአብዛኛው መካከለኛ የክብደት መጠን ያላቸው ሲሆን የተወሰኑ ቀላልና ከባድ ጥያቄዎችን አካቷል፡፡ ይህ መሆኑ በፈተና አወጣጥ ህግ መሰረት ተቀባይነት ስለሚኖረው በዚህ ፈተና የተገኘው የአንብቦ መረዳት ውጤትም ለትንተና መቅረቡ ተገቢ እንደሆነ ያሳያል፡፡ የጥያቄዎቹ የክብደት መጠን ብቻውን በቂ

ስለማይሆን በተጨማሪነት ተማሪዎችን የመለየት አቅሙም ተሰልቷል፡፡ ውጤቱም በቀጣዩ ርዕስ በዝርዝር ቀርቧል፡፡

### 3.4.2.6. **የጥያቄዎች የመለየት ብቃት/ አቅም**

የአንብቦ መረዳት ችሎታ መለኪያ ፈተናውን የመረጃ መሰብሰቢያ አድርጎ ለመጠቀም መፈተሽ ከሚገቡት ጉዳዩች አንዱ ፈተናው ጎበዝ፣ ሰነፍና መካከለኛ ተማሪዎችን ለመለየት ያለው ብቃት ወይም አቅም ነው፡፡ የጥያቄዎች የመለየት ብቃት በሙከራ ጥናቱና በዋናው ጥናት ተሰልቷል፡፡ በሙከራ ጥናቱ ተግባራዊ የተደረጉት አራት ፈተናዎችና ለዋናው ጥናት ተግባራዊ የተደረጉት ሁለት ፈተናዎች ያላቸው የመለየት ብቃት እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

የአምስተኛ ክፍል ፈተና የመለየት ብቃት በሙከራ ጥናቱ ተሰልቶ የጥያቄ ቁጥር 1፣ 3፣ 6፣ 9፣ 22ና 30 ከ0.2 በታች በማምጣት ዝቅተኛ የመለየት ብቃት ሲያሳዩ ጥያቄ ቁጥር 2፣ 4፣ 5፣ 7፣ 8፣ 10፣ 11፣ 14፣ 15፣ 16፣ 20፣ 21፣ 25፣ 26፣ 27፣ 28ና 29 ከ0.2 እስከ 0.5 በመሆናቸው መካከለኛ የመለየት ብቃት ሲኖራቸው ጥያቄ ቁጥር 8፣ 12፣ 13፣ 17፣ 18፣ 23ና 24 ከ0.56 በላይ በመሆን ከፍተኛ የመለየት ብቃት አስመዝግበዋል (አባሪ 2.7.5.ን ይመልከቱ)፡፡ ከተወሰኑ ማሻሻያዎች በኋላ እነዚሁ ጥያቄዎች ለዋናው ጥናት ተግባራዊ ተደርገው ድጋሚ የመለየት ብቃታቸው ተሰልቷል፡፡ ውጤታቸው የሚያሳየው ጥያቄ ቁጥር 18፣ 23ና 27 ከፍተኛ የመለየት ብቃት ሲያስመዘግቡ ጥያቄ ቁጥር 26 ዝቅተኛ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ቀሪዎቹ ሀያ ስድስት ጥያቄዎች መካከለኛ የመለየት ብቃት አላቸው (አባሪ 1.5.5. ይመልከቱ)፡፡

የሰባተኛ ክፍል የአንብቦ መረዳት ፈተና የመለየት ብቃት በሙከራ ጥናቱና በዋናው ጥናት ተሰልቷል፡፡ በሙከራ ጥናቱ ከ0.2 በታች በማምጣት ዝቅተኛ የመለየት አቅም ያሳዩት ጥያቄ ቁጥር 1፣ 9፣ 13፣ 18ና 24 ሲሆኑ ከ0.2 እስከ 0.55 በማምጣት መካከለኛ የመለየት ብቃት ያላቸው 2፣ 4፣ 6፣ 7፣ 8፣ 10፣ 11፣ 14፣ 15፣ 16፣ 17፣ 19፣ 20፣ 21፣ 22፣ 23ና 25 ናቸው (አባሪ 2.7.10ን ይመልከቱ)፡፡ መጠነኛ ማሻሻያ ተደርጎባቸው እነዚሁ ጥያቄዎች ለዋናው ጥናት ተግባራዊ ተደርገዋል፡፡ በዋናው የጥናት

ውጤት መሰረት ጥያቄ ቁጥር 8ና 11 ዝቅተኛ፣ ጥያቄ ቁጥር 15ና 23 ከፍተኛ መለየት ብቃት ሲያሳዩ ቀሪዎቹ ጥያቄዎች ከ0.2 እስከ 0.55 በማምጣት መካከለኛ የመለየት ብቃት እንዳላቸው ተረጋግጧል (አባሪ 1.5.10ን ይመልከቱ)፡፡

ከአምስተኛና ከሰባተኛ ክፍል በተጨማሪ በሙከራ ጥናቱ ውጤት መሰረት የመለየት ብቃታቸው የተረጋገጡት ፈተናዎች የስድስተኛና የስምንተኛ ክፍል ፈተናዎች ናቸው፡፡ በሁለቱም ፈተናዎች ዝቅተኛ፣ መካከለኛና ከፍተኛ የመለየት ብቃት ያላቸው ጥያቄዎች ታይተዋል፡፡ የስድስተኛ ክፍል አንብቦ መረዳት ለመለካት ከተዘጋጁት 30 ጥያቄዎች መካከል ጥያቄ ቁጥር 3፣ 5፣ 7፣ 9ና 20 ዝቅተኛ የመለየት ደረጃ የተስተዋለባቸው ሲሆኑ ጥያቄ ቁጥር 12፣ 14፣ 25፣ 29ና 30 ከፍተኛ የመለየት ብቃት ያላቸው ናቸው፡፡ ቀሪዎቹ አስራ ዘጠኙ ጥያቄዎች መካከለኛ የመለየት ብቃት አላቸው (አባሪ 2.7.10ን ይመልከቱ)፡፡ የስምንተኛ ክፍል ተማሪዎችን የአንብቦ መረዳት ችሎታ ለመለካት ከተዘጋጁት ሰላሳ ጥያቄዎች አስራአንዱ ጥያቄዎች ከ0.2 በታች በማምጣት ዝቅተኛ የመለየት ብቃት እንዳላቸው ሲያሳዩ አምስቱ ጥያቄዎች ከፍተኛ የመለየት ብቃት አላቸው፡፡ ቀሪዎቹ 14 ጥያቄዎች መካከለኛ መለየት አቅም እንዳላቸው የሙከራ ውጤቱን መሰረት በማድረግ የተሰራው የመለየት ብቃት ስሌት ያሳያል (አባሪ 2.7.20ን ይመልከቱ)፡፡ በአጠቃላይ ለዋናው ጥናት ተግባር ላይ የዋሉት ሰባተኛና የአምስተኛ ክፍል የአንብቦ መረዳት ችሎታ መለኪያ ፈተናዎች በአብዛኛው ከፍተኛና መካከለኛ የመለየት ብቃት ስላላቸው ተቀባይነት አግኝተዋል፡፡

### 3.4.3. የቡድን ውይይት

በሙከራ ጥናቱ ወቅት የቤተሰብ ዳራ የሚለው ተላውጦ የሚለካው መጠይቅ ይዞት የተነሳው አንድ ጥያቄ ነበር እሱም ከቤተሰብ ዳራ ጋር በተያያዘ ከሚነሱት ተላውጦዎች ለአንብቦ መረዳት ችሎታየና ለማንበብ ተነሳሽነቴ ይጠቅመኛል ብለው የሚያስቧቸውን ነገሮች እንዲዘረዝሩ የክፍት ጥያቄ ነው፡፡ ነገር ግን በሙከራ ጥናቱ ከተገኘው ምላሽ መረዳት እንደሚቻለው አይነታዊ መልሶችን ከጽሁፍ መጠይቅ ይልቅ በቡድን ውይይት መጠየቁ የተሻለ ስለሆነ ያንን ጥያቄ ለመመለስ የቡድን ውይይቱ ተግባራዊ ተደርጓል፡፡

የቡድን ውይይት አጠቃላይ ተማሪዎች ከአንብቦ መረዳት ችሎታ ጋርና ከማንበብ ተነሳሽነት ጋር አያይዘው ይረዱኛል ብለው የሚያስቧቸውን ነገሮች በተመለከተ መረጃ ለማግኘት ተካሂዷል፡፡ የቡድን ውይይቱ የተካሄደው በሁለት ቡድኖች ነው፡፡ በዋናው ጥናት ተሳታፊ ከነበሩት ተማሪዎች ከአምስተኛ ክፍል አስራ ሁለት ከሰባተኛ ክፍል አስራ ሁለት ተማሪዎች በአላማ ተኮር ናሙና ተመርጠዋል፡፡ ከተመረጡት ተማሪዎች ከአምስተኛ ክፍል ሁለት ተማሪዎች ከሰባተኛ ክፍልም ሁለት ተማሪዎች የቡድን ውይይቱ ሲካሄድ ባለመገኘታቸው የቡድን ውይይቱ በየቡድኑ በአስር አስር ተማሪዎች ተካሂዷል፡፡

የቡድኑን ተመሳሳይነት ለመጠበቅ የተለያዩ ጥንቃቄዎች ተወስደዋል፡፡ ለአብነት በእድሜ ለአምስተኛ ክፍል 10ና 11 እድሜ ያላቸው ሲሆኑ ለሰባተኛ ደግሞ 13ና 14 የሆኑት እንዲሳተፉ ተደርጓል፡፡ የጾታ ምጥጥን እንዲኖርም ሲባል ከእያንዳንዱ ጾታ እኩል ተሳታፊዎች ተመርጠዋል፡፡ በመሆኑም በመጨረሻ የተሳተፉት ከአምስተኛ ክፍል አምስት ወንድና አምስት ሴት እንዲሁም ከሰባተኛ ክፍል አምስት ወንድና አምስት ሴት ናቸው፡፡

ውይይቱ የተካሄደው በዶና በርበር የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት የመወያያ ክፍል ውስጥ ነው፡፡ ማለትም ተማሪዎች በተለያዩ ጉዳዮች እንዲወያዩባቸው የተሰራ አንድ ክፍል አለ ያንን ክፍል በመጠቀም ውይይቱ ተካሂዷል፡፡ ውይይቱ የክፍል ደረጃቸውን መሰረት በማድረግ በተከፈለው ሁለት ቡድን መሰረት በመክፍል በተለያዩ ቀናት ተካሂዷል፡፡ ታህሳስ 12፣ 2010 ከጠዋቱ 4፡00- 4፡45 የአምስተኛ ክፍል ተማሪዎች፤ ታህሳስ 13፣ 2010 ከጠዋቱ 4፡30- 5፡20 የሰባተኛ ክፍል ተማሪዎች በተቃራኒ ፈረቃ ተገኝተው ውይይቱን አድርገዋል፡፡

ውይይቱ የተደረገው በአማርኛ መምህራቸው መሪነት ሲሆን ተመራማሪዋ አቅጣጫ በመስጠትና በመከታተል ተሳትፋለች፡፡ መረጃው የተያዘው በተማሪዎችና በተመራማዋ በጽሁፍ ቃለጉባዔ በመያዝ ነው፡፡

## 3.5. የመረጃ መሰብሰቢያ አስተማማኝነት

የመረጃ መሰብሰቢያዎች አስተማማኝነትና ተገቢነት መረጃው ከመሰብሰቡ በፊትና ከተሰበሰበ በኋላ ተረጋግጧል፡፡ ከላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው ሁለት የተለያዩ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ተዘጋጅተዋል፡፡ እነሱም የአንብቦ መረዳት መለኪያ ፈተናና የማንበብ ተነሳሽነትና የቤተሰብ ዳራ መለኪያ መጠይቆች ናቸው፡፡ ባጠቃላይ ሁለት የተለያዩ ፈተናዎችና ሁለት የተለያዩ መጠይቆች ተዘጋጅተዋል፡፡ የቡድን ውይይትም ተካሂዷል፡፡

ሁሉም የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ከተዘጋጁ በኋላ ተገቢነታቸውንና ትክክለኝነታቸውን ለማረጋገጥ በመጀመሪያ በሁለት የሶስተኛ ዲግሪ የማህበራዊ ስነልቦና ተማሪዎችና በሶስት በተግባራዊ ስነልሳን አማርኛን ማስተማር የዶክትሬት ዲግሪ ተማሪዎች የይዘትና የላዕላይ ትክክለኝነታቸውን እንዲገመገሙ ተደርጓል፡፡ በመቀጠል ለተመራማሪዋ አማካሪዎች ተሰጥተው ድጋሚ ግምገማ ተደርጎባቸዋል፡፡ በመቀጠልም ፈተናዎቹን ብቻ በመነጠል በክፍል ደረጃው ለሚያስተምሩ ሶስት መምህራን በመስጠት የክብደት ደረጃውን እንዲገመግሙት ተደርጓል፡፡ ከመምህራኑና ከባለሙያዎቹ የተገኘውን መረጃ መሠረት በማድረግም መጨመር ያለባቸው ጥያቄዎች ተጨምረዋል፣ መሻሻል ያለባቸው ተሻሽለዋል፣ መወገድ ያለባቸው ተወግደዋል፣ የአሻሚነት ባህርይ የታየባቸውን በማብራራት ግልፅ የማድረግ ተግባራት ተከናውነዋል፡፡

ከስነልቦና ባለሙያዎች አስተያየት በመነሳት ከቤተሰብ ዳራ መለኪያ መጠይቁ የተካተቱት ሀይማኖት የመሳሰሉ መጠይቆች ትንተናው ላይ እንዳይካተቱ ተደርጓል፡፡ የቋንቋ ምሁራኑ በሰጡት አስተያየት መሰረት አሻሚ ቃላት ተወግደዋል፡፡ እንዲሁም በክፍል ደረጃው የሚገኙ የአማርኛ መምህራን በሰጡት አስተያየት መሰረት የምንባቡ መጠን ተቀንሷል፡፡ በተለይም የዝቅተኛ የክፍል ደረጃዎች (አምስተኛና ስድስተኛ) የምንባቡ ስፋት ከተማሪዎች አንብቦ ተረድቶ የማስታዎስ ችሎታ ጋር የተመጣጠነ አይደለም የሚል አስተያየት በመገኘቱ የምንባቡ ስፋት በመጠኑ ተቀንሷል፡፡ እንዲሁም የተወሰኑ ጥያቄዎች ተወግደው በምትኩ ሌሎች ጥያቄዎች ተተክተው የመረጃ መሰብሰቢያው ተዘጋጅቷል፡፡

የመረጃ መሰብሰቢያዎቹ ተዘጋጅተው ተገቢነታቸው በባለሙያዎች ከተገመገመ በኋላ አስተማማኝነቱን ለማረጋገጥ በተመረጡ የድል ችቦ ተማሪዎች ላይ መረጃው ተሰብስቦ በኮሚፒውተር ሰፍሮ አስተማማኝነቱ ተሰልቷል፡፡ የአንብቦ መረዳት ችሎታ መለኪያ ፈተናዎቹና የማንበብ ተነሳሽነት መለኪያ መጠይቁ አስተማማኝነት የተሰላው በክሮንባች አልፋ (Cronbach's Alpha) የአስተማማኝነት መለኪያ ነው፡፡ አሰተማማኝ መሆኑ ከተረጋገጠ በኋላ ዋናው ጥናት ተሰብስቧል፡፡ የዋናው ጥናት መረጃ አስተማማኝነትም ተሰልቶ አስተማማኝነቱ በመረጋገጡ ወደ ትንተናው ተገብቷል፡፡

የአንብቦ መረዳት ችሎታ መለኪያ ፈተናው አስተማማኝነትም የተሰላው በተመሳሳይ በክሮንባች አልፋ ሲሆን የእያንዳንዱ ክፍል ፈተና በተናጥል ተሰርቶ የተገኘው ውጤት እንደሚያሳየው ሁሉም ፈተናዎች አስተማማኝ መሆናቸውን ነው፡፡ የአምስተኛ ክፍል የአንብቦ መረዳት መለኪያ ፈተና አስተማማኝነት በሙከራ ጥናቱ (α=0.846)፣ በዋናው ጥናት (α=0.812) ና የሰባተኛ ክፍል የአንብቦ መረዳት መለኪያ ፈተና አስተማማኝነት በሙከራ ጥናቱ (α=0.722) ና በዋናው ጥናት (α=0.814) ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ይህም ከ0.65 በላይ ስለሆነ አስተማማኝ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ በአጠቃላይ የፈተናዎቹ አስተማማኝነት እንደሚከተለው በሰንጠረዥ ቀርቧል፡፡

**ሰንጠረዥ 3.2**

***የመረጃ መሰብሰቢያዎች አስተማማኝነት በክሮንባኸ አልፋ (Cronbach's Alpha)***

| የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች | | 5ኛ ክፍል | 7ኛ ክፍል |
|---|---|---|---|
| የአንብቦ መረዳት መለኪያ ፈተና | እውነት ሀሰት | 0.777 | - |
| | አዛምድ | 0.711 | - |
| | ምርጫ | 0.811 | 0.814 |

## 3.6. የመረጃ መተንተኛ ዘዴ

ከ321 ተጠኝዎች የተገኙት መረጃዎች ለትንታኔ ከመቅረባቸው በፊት መልሶች በትክክል ተጠየቃዊ በሆነ መንገድ መሞላታቸው ተጣርቷል፡፡ የተጣራው መረጃ ለትንተና በሚመች መልኩ ኮድ ተድጎ በውጤት መመዝገቢያ ሰንጠረዥ (ኮድ ሽት) ላይ በኮሚፒውተር ላይ ሰፍሮ ድጋሚ የማጣራት ስራ ተሰርተዋል፡፡ እንዲሁም የፈተና ውጤቶች አስተማማኝነት የክሮንባች አልፋ የአስተማማኝነት መለኪያ ዘዴ በመጠቀም አስተማማኝነቱ ተሰልቷል፡፡ የኮድ አደራረግ ሂደቱ እንደተላውጦዎቹ ባህርይ የተለያየ በመሆኑ የተለያዩ የኮድ አደራረግ ሂደቶችን (ዱሚ ኮድ፣ ይዘት ኮድ፣ ተጽዕኖ ኮድ) በመጠቀም እንደሚከተለው በሰንጠረዥ ሰፍሯል፡፡

**ሰንጠረዥ 3.3**

***በጥናቱ የተካተቱ ተላውጦዎችና በኤስፒኤስ ኤስ የኮድ ስያሜየቸው***

| ተላውጦ | የኤስፒኤስ ኤስ ስማቸው | የኮድ አደራረግ | |
|---|---|---|---|
| መለያ ቁጥር | Id no | በተራ ቁጥራቸው መሰረት | |
| ጾታ | Sex | 1=ወንድ<br>2= ሴት | |
| እድሜ | Age | በአመት | |
| የክፍልደረጃ | Grade | በቁጥር | |
| የቤተሰብ መዋቅር | Intact | 0= ሌሎች<br>1= ከእናት አባት ጋር መኖር | ዱሚ ተላውጦ |
| | Fathonl | 0=ሌሎች<br>1= ከአባት ጋር ብቻ መኖር | |
| | Mothonl | 0=ሌሎች<br>1=ከእናት ጋር ብቻ መኖር | |
| | Other | 0= ሌሎች<br>1=ከተለያዩ ሰዎች ጋር መኖር | |
| የቤተሰብ ብዛት | Famsize | በቁጥር | |
| | Fathedu | 1= መደበኛ ትምህርት ያልተማረ | |

| | | | |
|---|---|---|---|
| የቤተሰብ የትምህርት ደረጃ | | 2= አንደኛ/መለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ<br>3= ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ<br>4=ሰርትፍኬት/ ዲፕሎማ<br>5= የመጀመሪያ ዲግሪእና ወይም በላይ | |
| | Mothedu | 1= መደበኛ ትምህርት ያልተማረ<br>2= አንደኛ/መለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ<br>3= ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ<br>4=ሰርትፍኬት/ ዲፕሎማ<br>5= የመጀመሪያ ዲግሪእና ወይም በላይ | |
| | Famedu | 1= አንደኛ/መለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ<br>2= ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ<br>3=ሰርትፍኬት/ ዲፕሎማ<br>4= የመጀመሪያ ዲግሪእና ወይም በላይ | |
| የአባት ስራ | Farmer | 0= ሌሎች<br>1= ገበሬ | በዴሚ ተላውጦ የተመዘገቡ |
| | Fmerch | 0= ሌሎች<br>1= ነጋዴ | |
| | Fgev | 0= ሌሎች<br>1= የመንግስት ሰራተኛ | |
| | Fotherwork | 0= ሌሎች<br>1= የተለያዩ ስራዎች | |
| የእናት ስራ | housewif | 0= ሌሎች<br>1=የቤት እመቤት | |
| | Mfarmer | 0= ሌሎች<br>1=ገበሬ | |
| | Mmerch | 0=ሌሎች<br>1=ነጋዴ | |
| | Mgev | 0=ሌሎች<br>1= የመንግስት ሰራተኛ | |
| | Motherwork | 0= ሌሎች<br>1= የተለያዩ ስራዎች | |
| የቤት ውስጥ ግብዓት | 81 | 1= አዎ<br>2= አይደለም | |
| | 82 | 1= አዎ<br>2= አይደለም | |
| | 83 | 1= አዎ<br>2= አይደለም | |
| | 84 | 1= አዎ<br>2= አይደለም | |
| | 85 | 1= አዎ<br>2= አይደለም | |
| የቤተሰብ የኢኮኖሚ | Famieco | 1=ከ1000 ብር በታች | |

| | | |
|---|---|---|
| ደረጃ | | 2= ከ1000 እስከ 3000<br>3= 3001 እስከ 5000<br>4=5000- 10000<br>5= ከ10000 በላይ |
| | Income | 1= ከፍተኛ<br>2= መካከለኛ<br>3=ዝቅተኛ |
| የቤተሰብ ማህበራዊ ደረጃ በትምህርት ቤት ውስጥ | S1 | 1= አዎ<br>2= አይደለም |
| | s2 | 1= አዎ<br>2= አይደለም |
| | S3 | 1= አዎ<br>2= አይደለም |

ከሰንጠረዡ እንደቀረበው እንደየተላውጦዎቹ ባህርይ የተለያዩ የኮድ አደራረግ ሂደቶችን በመጠቀም በአግባቡ ተመዝግበዋል፡፡

ወደ ዋናው ትንተና ከመገባቱ በፊት ፐርሰንታይልን በመጠቀም በእያንዳንዱ የክፍል ደረጃ የሚገኙ የሴትና የወንድ ተማሪዎችን ምጥጥን ተሰልቷል፡፡ በእያንዳንዱ ተላውጦ ምን ያክል ተማሪዎች ከእናት አባት ጋር እንደሚኖሩ፣ ከአባት ጋር ብቻ እንደሚኖሩ ፣ ከእናት ጋር ብቻ እንደሚኖሩ በድግግሞሽና በፐርሰንታይል ተሰልቷል፡፡ እያንዳንዱ ምላሽ ምን ያክል ተማሪ እንደመረጠው የሁሉም ተላውጦ በድግግሞሽና በፐርሰንታይል ተሰልቷል (ዝርዝሩን ምዕራፍ አምስት ይመልከቱ)፡፡

እንዲሁም ገላጭ እስታትስቲክስን በመጠቀም የአንብቦ መረዳት ችሎታቸውና የማንበብ ተነሳሽነታቸው አማካይና መደበኛ ልይይት ተሰልቷል፡፡ በመቀጠልም ይዟቸው የተነሳቸውን ጥያቄዎች አይነትና ባህርይ መሰረት በማድረግ የተለያዩ የመተንተኛ ዘዴዎችን በመጠቀም ትንተና ተደርጓል፡፡

ፓራሜትሪያዊ የመተንተኛ ስልቶችን ለመጠቀም እንዲቻል በመጀመሪያ እሙኖቹ መሟላታቸው መረጋገጥ አለበት፡፡ የመጀመሪያው ተከታታይ ተላውጦዎቹ (Continuous variables) ያላቸውን የውጤት ስርጭት ወጥነት (Test of Normality) መቃኘት ነበር፡፡ ይህንም ለማረጋገጥ የሁለቱም የክፍል ደረጃዎች የአንብቦ መረዳት ችሎታ መለኪያ

ፈተና ውጤትና የማንበብ ተነሳሽነት ውጤት በተያያዥ አምድ ግራፍና በኮሞግሮቭ ስሚኖቭ ተሰልቶ ወጥነቱ ተሰልቷል (የፈተና ውጤቱንና የማንበብ ተነሳሽነት የውጤት ስርጭት ወጥነት ከአባሪ 1.5.3. ጀምሮ እስከ 1.7.5. ድረስ ይመልከቱ)፡፡

ይህ ጥናት ይዟቸው ከተነሳው አላማዎች የመጀመሪያው የቤተሰብ ዳራ የአንብቦ የመረዳት ችሎታን የመተንበይ ድርሻውን መለየት የሚል ሲሆን ይህንን አላማ ለማሳካት ተግባር ላይ የዋለው የመተንተኛ ዘዴ የህብረ ድህረት ትንተና (Multiple Regression Analysis) ነው፡፡ የህብረ ድህረት ትንተና የመተንተኛ ዘዴ ተግባራዊ የተደረገበት ምክንያት ትንበያን ለመስራት የሚያገለግለው ተገቢ የመተንተኛ በመሆኑ ሲሆን ከድህረት የትንተና አይነቶች ህብረ የተመረጠበት ምክንያት ደግሞ ከቤተሰብ ዳራ ጋር ተያይዘው የሚነሱት ተላውጦዎች በርካታ በመሆናቸው ሁሉንም በአንድ አካቶ የሚሰራ የመተንተኛ ዘዴ በመሆኑ ነው፡፡

የህብረ ድህረት ትንተና ተግባራዊ ሲደረግ አስቀድሞ መሟላት ያለባቸውና መፈተሽ ያለባቸው እሙኖች አሉ እነሱም የንሞና መጠን፣ መልቲኮሊኒያሪቲና ነጠላነት (Multicollinearity and Singularity)፣ አፈንጋጭነት (Outliers) ትክክለኝነት፣ ቀጥተኝነት፣ የጥገኛ ተላውጦ ወጥነትና (Normality, Linearity, Homoscedasticity, Independence of Residual) ናቸው፡፡ የንሞናው መጠን የነጻ ተላውጦዎችን መጠንና የጥናቱን ባህርይ መሰረት በማድረግ ተሟልቷል፡፡

የውጤት ስርጭት ወጥነቱ የተሰላውና ወጥ መሆኑ የተረጋገጠው የአምስተኛና የሰባተኛ ክፍል የአንብቦ መረዳት ችሎታ ውጤት እንደጥገኛ ተላውጦ (ተተንባይ) የቤተሰብ ዳራ ተላውጦዎች ደግሞ ተንባይ ሆነው ስሌቱ ከተሰራ በኋላ ዋናው ውጤት ከመተንተኑ በፊት የመልቲኮሊኒያሪቲና የነጠላነት ታይቷል፡፡ መልቲኮሊኒያሪቲ ተፈጠረ ማለት በነጻ ተላውጦዎች ወይም በተንባዮች መካከል ያለው የተዛምዶ መጠን ከ0.9 በላይ ከሆነ ማለት ነው፡፡ በዚህም መሰረት የቤተሰብ የትምህርት ደረጃ መለኪያ ሆኑት የአባት የትምህርት ደረጃ፣ የእናት የትምህርት ደረጃና በቤት ውስጥ ከፍተኛው የትምህርት ደረጃ እርስ በርስ ያሳዩት ተዛምዶ ከ0.9 በላይ ስለሆነ አማካይ ሆነው የአባት የትምህርት

ደረጃ ተወስዶ ሌሎች ተወግደዋል፡፡ በሌሎች ላይ የታየው ተዛምዶ ግን ከ0.9 በታች በመሆኑ ድህረት ትንተናው ላይ ተካተው ተሰርተዋል፡፡

ሌላው እሙን (Assumption) አፈንጋጭነት (Outliers) ነው፡፡ አፈንጋጭነት በጥገኛ ተላውጦውም ሆነ በነጻ ተላውጠው ላይ ሊከሰት የሚችል በጣም ከፍተኛ ወይም በጣም ዝቅተኛ ውጤት መታየት ነው፡፡ ይህንም ማየት የሚቻለው በመደበኛው ፕሎት ላይ ሲሆን ከ 3.3 እስከ -3.3 መካከል መገኘት አለበት በዚሀ ህግ መሰረት በዚህ የድህረ ትንተና ውጤት አፈንጋጭ ውጤት አልተስተዋለም፡፡

የአንብቦ መረዳት ችሎታ በጾታ ልዩነት እንዳለውና እንደሌለው ማረጋገጥ የጥናቱ አራተኛ አላማ ሲሆን ይህንን አላማ ለማሳካት የነጻ ናሙና ቲ ቴስት (Independent-Sample T- Test) ጥቅም ላይ ውሏል፡፡ የነጻ ናሙና ቲ-ቴስት ተግባራዊ የተደረገው ሁለት ቡድኖች በአማካይ ያላቸውን ልዩነት ለማነጻጸር የሚያስችል ተገቢው መተንተና ዘዴ ስለሆነና መረጃው ወጥ ሆኖ በመገኘቱ የፓራሜትሪያዊ መፈተሻ ለመጠቀም ስለሚያስችል ነው፡፡

በመጨረሻም ከቤተሰብ ዳራ ጋር በተያያዘ ተማሪዎች ለማንበብ ተነሳሽነቴና ለአንብቦ መረዳት ችሎታየ ይጠቅሙኛል ብለው የሚያስቧቸው ነገሮች መለየት ለሚለው አላማ መረጃው የተሰበሰበው በቡድን ተኮር ውይይት በመሆኑና ተገቢው የመተንተኛ ዘዴ አይነታዊ (በጽሁፍ መግለጽ) በመሆኑ መረጃው አይነታዊ በሆነ መንገድ ተተንትኗል፡፡

በአጠቃላይ በዚህ ጥናት መጠናዊና አይነታዊ የመተንተኛ ዘዴዎች ተግባራዊ የተደረጉ ሲሆን ከመጠናዊ የመተንተኛ ዘዴዎች መካከል ህብረ ድህረት የመተንተኛ ዘዴ፣ ፒርሰን የተዛምዶ መወሰኛ ቀመርና ነጠላ የልይይት ትንተና ተግባራዊ ተደርገዋል፡፡ ሁሉም መረጃዎች የተተነተኑት ኤስ ፒ ኤስ ኤስ ቨርዥን 20.0 (SPSS v20.0) በመጠቀም ነው፡፡

## 3.7. የዋናው ጥናት ሂደት

የሙከራው ጥናት ዓላማ በዋናው ጥናት ወቅት ተግባር ላይ የሚውሉ መሣሪያዎችን ጠንካራና ደካማ ጎኖች በመለየት አስቀድሞ ጥንቃቄ ለማድረግ ነበር፡፡ በመሆኑም ዋናውን ጥናት ለማካሄድ መሠረት በመሆን ያገለግላል በሚል እምነት ተከናውኗል፡፡ በሚከናወንበት ጊዜ የታዩት ጠንካራ ጎኖች ባሉበት እንዲቀጥሉ ተደርገው ደካማ ጎኖች ደግሞ ተሻሽለው ለዋናው ጥናት እንደግብዓት ተወስደዋል፡፡

የዚህ ጥናት ዋና አላማ የቤተሰብ ዳራ የተማሪዎችን የማንበብ ተነሳሽነትና የአንብቦ መረዳት ችሎታ የመተንበይ ድርሻውን መለየት ነው፡፡ ይህንን አላማ ለማሳካትም ጥናቱ እንደሚከተለው ተከናውኗል፡፡

በዋናነት የሚፈለገው ከተጠኚ ተማሪዎች የሚገኘው መረጃ በመሆኑ የመረጃ አሰባሰብ ሂደቱ እንዳይዛባ ከፍተኛ ጥንቃቄ ተደርጓል፡፡ በመጀመሪያ የጥናቱን አላማና በጥናቱ የሚዳሰሱትን ተላውጦዎች መሰረት በማድረግ በጥናቱ ሊካተቱ የሚገባቸው ተማሪዎች ቁጥር ተወስኗል፡፡ በስሌቱ መሰረት በአንድ የክፍል ደረጃ ከ100 በላይ ተማሪዎች መካተት ይኖርባቸዋል፡፡ በመሆኑም በታቀደው መሰረት ከአምስተኛ ክፍል ወንድ 79 ሴት 75 በድምሩ 154 ከሰባተኛ ክፍል ወንድ 83 ሴት 89 በድምሩ 172 ተማሪዎች በዕጣ ንሞና ተመርጠዋል፡፡ ከተማሪዎች ጋር በቀጥታ ከመገናኘት በፊት ከክፍሉ የአማርኛ መምህርት (የትምህርት ቤቱ ዩኒት መሪ)ና የትምህርት ቤቱ ርዕሳነ መምህራን ጋር ውይይት ተደርጓል ለማስተባበርና ለመርዳት ዝግጁ ሆነዋል፤ በአጋጣሚ የክፍሉ የአማርኛ መምህርትና የትምህርት ቤቱ ዩኒት መሪ አንድ ሰው ሆኖ መገኘት ለማስተባበር ከፍተኛ አስተዋጽዖ አበርክቷል፡፡ የተመረጡት ተማሪዎች ስም ዝርዝርና ጾታ ከተገኘ በኋላ ለብቻቸው ተጠርተው በአንድ አዳራሽ እንዲገኙ ተደርጓል፡፡ ለተገኙት ተማሪዎች ስለጥናቱ አላማ ዝርዝር ማብራሪያ ተሰጥቷቸዋል፡፡ በመቀጠል ስለመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች አይነትና ባህሪ እንዲሁም አስፈላጊነት በተመራማሪዋ፣ በክፍላቸው የአማርኛ መምህራንና በርዕሰ መምህሩ በዝርዝር ተነግሯቸዋል፡፡ ሁለት

አይነት መጠይቆችን እንደሚሞሉና የአንብቦ መረዳት ፈተናም እንደሚፈተኑ ተገልጾላቸዋል፡፡

ፈተናው ከአዲሱ መማሪያ መጽሀፍ እንደተዘጋጀና የአንብቦ መረዳት ችሎታቸውን ለመለካት እንደሚያገለግል ተገልጾላቸዋል፡፡ በተዘዋዋሪ ለትምህርታቸው ሊጠቅማቸውም እንደሚችል ተነግሯቸዋል፡፡ ፈተናውን በሚሰሩበት ጊዜ የራሳቸውን እንዲሰሩ፤ መቅዳትም ሆነ ማስቀዳት የተከለከለ መሆኑ ተነግሯቸዋል፡፡ ከፈተናው ግልጽ ያልሆነላቸው ነገር ካለ እጃቸውን በማውጣት እንዲጠይቁ መመሪያ ተሰጥቷቸዋል፡፡

የፅሁፍ መጠይቁ ሁለት አይነት እንደሆነና አንደኛው የቤተሰብ ዳራን የሚመለከት ሁለተኛው ደግሞ የማንበብ ተነሳሽነታቸውን የሚለካ በመሆኑ በራሳቸው እንዲሞሉት ተነግሯቸዋል፡፡ መጠይቁን በሚሞሉበት ጊዜ ስህተት ወይም ትክክል የሚባል ምላሽ እንደሌለና የማያውቁትን ጥያቄ መዝለል እንደሚችሉ ተነግሯቸዋል፡፡ የማንበብ ተነሳሽነት የሚለካው መጠይቅ አስራአንድ ክፍሎች እንዳሉት እያንዳንዳቸው ምን ማለት እንደሆኑ ተገልጾላቸዋል፡፡ ከገለጻው ያልገባቸው ወይም ግልጽ ያልሆነላቸው ነገር ካለ እንዲጠይቁ ተነግሯቸዋል፡፡ በሙከራ ጥናቱ ወቅት ከተገኘው ተሞክሮ በመነሳት የማንበብ ተነሳሽነትን ለሚለካው ጥያቄ ከመጀመራቸው በፊት ተቀራራቢና ለነሱ በጣም ቀላል የሆነ ምሳሌ በቃልም በጽሁፍም ቀርቦላቸዋል፡፡ የቀረበላቸው ምሳሌ “እንቁላል መብላት እወዳለሁ” የሚል አረፍተነገርና ከማንበብ ተነሳሽነት መለኪያው ጋር ተመሳሳይ የሆነ አማራጭ ነው፡፡

መረጃ በመሰብሰብ ሂደት የክፍሉ መምህራንና ርዕሳነ መምህራን እንዲሳተፉ ተደርጓል፡፡ ተሳታፊ የተደረጉበት ምክንያት ለ151 የአምስተኛና ለ170 የሰባተኛ ክፍል ተማሪዎችን በተመሳሳይ ሰዓት መጠይቅ ሰጥቶ ስለእያንዳንዱ ግልጽ ያልሆነ ጥያቄ ማብራሪያ እየሰጡ አንዲሞሉ ለማድረግ፣ የአንብቦ መረዳት ችሎታ መለኪያ ፈተና ለመፈተን፣ ለመቆጣጠርና ለመሰብሰብ በተመራማሪዋ ብቻ ስለማይቻል ነው፡፡ በተጨማሪነት ከተመራማሪዋ ይልቅ የክፍል አስተማሪዎቻቸውንና ርዕሳነ መምህራንን የማክበርና የመስማት ባህርይ በሙከራ ጥናቱ ላይ ስለተስተዋለ ነው፡፡

የመረጃ አሰባሰብ ሂደቱ በስድስት ቀናት ተከፋፍሏል፡፡ በመጀመሪያው ቀን ማለትም በህዳር ስድስት 2010 ዓ.ም አጠቃላይና ዝርዝር መግለጫ ለርዕሳነ መምህራንና ለአማርኛ መምህራን እንዲሁም ለዩኒት መሪዋ (አማርኛ መምህሯ) ቀርቦላቸው ትብብራቸው የተጠየቀበትና ይሁንታቸው የተገኘበት እንዲሁም በትምህርት ቤቱ ስላሉት የአምስተኛና የሰባተኛ ክፍል ተማሪዎች ብዛት የትምህርት ሰዓትና አጠቃላይ ሁኔታ መረጃ የተሰበሰበበት ቀን ነው፡፡

ቀጣዩ ቀን ማለትም ህዳር 7 2010 ዓ.ም የተመረጡትን ተማሪዎች በመሰብሰብ ስለምርምሩ አጠቃላይ አላማና ስለመረጃ መሰብሰቢያዎች ባህርይና ሁኔታ እንዲሁም ከነሱ ስለሚጠበቀው ነገር ሰፊ መግለጫ የተሰጠበት ቀን ነው፡፡ ካልፈለጉ ማቋረጥ እንደሚችሉ ጭምር ተነግሯቸው ፈቃደኝነታቸው የተጠየቀበት ቀን ነው፡፡

ህዳር 13 2010 ዓ.ም ሶስተኛው ቀን ሲሆን የቤተሰብ ዳራን የሚለካውን መጠይቅ እንዲሞሉ ተደርገዋል፡፡ በአራተኛው ቀን ማለትም ህዳር 28 የአንብቦ መረዳት ችሎታ መለኪያ ፈተናውን እንዲፈተኑ ተደርገዋል፡፡ በአምስተኛና በስድስተኛው ቀን ማለትም ታህሳስ አስራ ሁለትና አስራ ሶስት የቡድን ውይይቱ ተካሂዷል፡፡ ቀናቱን ማራራቅ ያስፈለገው አንደኛ ሁሉንም መረጃ የሚሞሉት በክፍል ውስጥ ስለሆነ የትምህርት ጊዜያቸውን እንዳይሻማባቸው፣ ሁለተኛ መሰልቸት እንዳይኖርና ሶስተኛ በሙከራ ጥናቱ ወቅት በርካታ ተማሪዎች እንዲያቋርጡ ያደረገው ምክንያት ተማሪዎች ለሀይማኖታዊ በዓላት ወደ ትምህርት ቤት አለመምጣታቸው ስለነበር ሀይማኖታዊ በዓላትን በማይነካ መልኩ ለማድረግ ነው፡፡ ይህ መደረጉም በዋናው ጥናት ተማሪዎች እንዳያቋርጡ ከፍተኛ እገዛ አድርጓል፡፡ ከአምስተኛ ክፍል ሶስት ከሰባተኛ ክፍል ሁለት ተማሪዎች በዕጣ ንሞናው ቢካተቱም ሙሉ መረጃው ሲሰበሰብ አልነበሩም፡፡ እነሱም በግል ችግርና በህመም ምክንያት ያቋረጡ ናቸው፡፡ ይህም የመረጃ አሰባበሰብ ሂደቱ ውጤታማ እንደነበር ያመለክታል፡፡

ለጥናቱ አስፈላጊ የሚባሉት መረጃዎች ከተሰበሰቡ በኋላ በትንትናው ላይ ስህተት እንዳይፈጠር ተማሪዎች የሞሏቸው መጠይቆች በትክክል መሞላታቸውን ለማረጋገጥ ቅድመ ትንተና ፍተሻ ተደርጓል፡፡ ከተጣራ በኋላ በመረጃ መመዝገቢያ ኮድ ሽት

ሰፍሯል፡፡ በመቀጠል የመረጃው አስተማማኝነት፣ ተገቢነት የውጤት ስርጭት ወጥነትና የይዘት ትክክለኝነት ተረጋግጧል፡፡ በመጨረሻም የተነሱትን አላማዎች ወይም መሰረታዊ ጥያቀዎች መሰረት በማድረግ ተገቢውን የመተንተኛ ዘዴ በመምረጥ ትንተና ተደርጎባቸዋል፡፡ ትንተናውን መሰረት በማድረግም ከዚህ በፊት የተጠኑ ጥናቶችንና ንድፈሀሳቦችን በማጣቀስ ማብራርያ ተሰጥቷል፡፡ ከጥናቶቹ ውጤት ጋር የተደጋገፉበትና የተለያዩበት ምክንያትም በአሳማኝ ማስረጃ ተብራርቷል፡፡ ከትንተናውና ከማብራሪያው በመነሳት መደምደሚያ ተሰጥቷል፤ የመፍትሄ ሀሳቦችም ተጠቁመዋል፡፡

## 3.8. ስነምግባራዊ ትኩረቶች

የሙከራ ጥናቱ ሲካሄድም ሆነ ዋናው ጥናት ሲካሄድ በመጀመሪያ ሁሉም የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ከተዘጋጁና ከተገመገሙ በኋላ ጥናቱ ወደ ሚደረግበት ቦታ ከመሄድ በፊት ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የትብብር ደብዳቤ ተጽፏል፡፡

በመቀጠልም የትብብር ደብዳቤውን በመያዝ በባህርዳር ከተማ በሚገኙትና ለዋናው ጥናት በዕጣ ንሞና ዘዴ ከተመረጠው የዶና በርበር የመጀመሪያ ደረጃ ሙሉ ሳይክል ትምህርት ቤት እንዲሁም ለሙከራ ጥናቱ በዕጣ ንሞና ከተመረጡት የድልችቦ የመጀመሪያ ደረጃ ሙሉ ሳይክል ትምህርት ቤትና የቁልቋል ሜዳ የመጀመሪያ ደረጃ ሙሉ ሳይክል ትምህርት ቤት ርዕሳነ መምህራን በመሄድ ፈቃድ ተጠይቋል፡፡ ይሁንታቸውንም በቀላሉ ማግኘት ተችሏል፡፡

የርዕሰ መምህራኑ ፈቃድ ከተገኘ በኋላ በመረጃ አሰባሰብ ሂደት ከሚረዱት የቋንቋ ምሁራን ጋር በመገናኘት ውይይት ተካሂዷል፡፡ ከውይይቱ በኋላ በትምህርት ቤቱ ከሚገኙ አጠቃላይ ተማሪዎች መካከል ለዋናው ጥናት የአምስተኛና የሰባተኛ ክፍል ተማሪዎች ለሙከራ ጥናቱ ደግሞ ከአምስተኛ እስከ ስምንተኛ ክፍል በመማር ላይ በሚገኙ ተማሪዎች መካከል በዕጣ ንሞና የተመረጡት ተማሪዎች ፈቃደኝነታቸውም ተጠይቋል፡፡

ከመምህራንና ከርዕሳነ መምህራን ጋር በመሆንም የተመረጡ ተማሪዎች ጋር በመገናኘት ስለጥናቱ አላማና አስፈላጊነት ማብራሪያ ተሰጥቷል፡፡ እነሱን የሚመለከተው መረጃ ሁሉ

በምስጢር ተይዞ ለጥናቱ ዓላማ ብቻ እንደሚውልና በጥናቱ ሂደትም መሳተፍ ካልፈለጉ አቋርጠው መውጣት እንደሚችሉ ተነግሯቸዋል፡፡ በመሆኑም በዋና ጥናቱም ሆነ በሙከራ ጥናቱ የተካተቱት ተማሪዎች ፈቃደኛ የሆኑት ብቻ ናቸው፡፡

# ምዕራፍ አራት

## 4. የሙከራ ጥናቱ ውጤት ትንተና፣ ማብራሪያና የተገኙ ተሞክሮዎች

### 4.1. መግቢያ

በዚህ ምዕራፍ ወደ ዋናው ጥናት ከመገባቱ በፊት የመረጃ መሰብሰቢያዎቹን ተገቢነት እንዲሁም የመተንተኛ ዘዴዎችን ትክክለኝነት ለማረጋገጥ በዋናው ጥናት ከሚሳተፉት ተማሪዎች ጋር ተቀራራቢነት ባላቸው ሌሎች ተማሪዎች የተደረገው የሙከራ ጥናት ትንተና እንዲሁም የተገኙት ተሞክሮዎች በዝርዝር ቀርበውበታል፡፡

### 4.2. የሙከራ ጥናቱ አላማዎች

የሙከራ ጥናቱ ሲካሄድ የተለያዩ አላማዎችን አንግቦ ነው፡፡ የመጀመሪያውና ዋነኛው አላማ የተዘጋጁት የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ለጥናቱ ተሳታፊዎች ያላቸውን ተገቢነት፣ ትክክለኝነትና አስተማማኝነት ለመፈተሽ ነው፡፡ ይህንንም ለማሳካት ከሙከራ ጥናቱ በፊትና በሙከራ ጥናቱ ከተጠኝዎች ጋር ተቀራራቢ እድሜና የክፍል ደረጃ ባላቸው ተማሪዎች ተሞክሮ ማሻሻያዎች ተደርገዋል፤ የተወሰኑት ተወግደዋል እንዲሁም ተጨምረዋል፡፡ ዝርዝሩ በምዕራፍ ሶስት ላይ ቀርቧል፡፡

የሙከራ ጥናቱ ተጨማሪ አላማ መረጃው በሚሰበሰብበት ወቅት መደረግ ስለሚገባቸው ጥንቃቄዎች፣ ተማሪዎቹ መጠይቁን ሞልቶ ለመጨረስና ፈተናውን ለመፈተን የሚያስፈልጋቸውን ጊዜ ለማወቅ ነበር፡፡ ይህንን በተመከተ ከሙከራ ጥናቱ የተገኙ ተሞክሮዎች በሚለው ንዑስ ርዕስ ስር በዝርዝር ያገኙታል፡፡ ሶስተኛው የሙከራ ጥናቱ አላማ በጥናቱ ለተሳታፊነት የተመረጡት ተማሪዎች ብዛትና አይነት ተገቢነት መገምገም ነበር፡፡ አራተኛ የጥናቱ አላማ የተነደፉትን መላምቶችና መሰረታዊ ጥያቄዎች ለመመለስ የተሰበሰበው መረጃ መተንተኛ ዘዴዎችን ተገቢነት ለማረጋገጥና በሂደቱ የሚገኙ ለውጦችን ለመገመገም ነበር፡፡

## 4.3. የሙከራ ጥናቱ ንድፍና ስልት

የዚህ ጥናት ዋና አላማ የቤተሰብ ዳራ የማንበብ ተነሳሽነትና የአንብቦ መረዳት ችሎታን የመተንበይ ድርሻውን በአንደኛ ደረጃ ሁለተኛ ሳይክል ተማሪዎች ተተኳሪነት ላይ መለየት ነው፡፡ ይህን ዋና አላማ ለማሳካት የተመረጠው የምርምር ንድፍ ተንባይ (ተዛምዷዊ) ሲሆን ገላጭ የምርምር ስልትንም ተከትሏል፡፡ ይህ ዘዴ የተመረጠው በተላውጦዎች መካከል ያለውን ተዛምዶና የተጽዕኖውን መጠን ለማሳየት የሚረዳ ዘዴ በመሆኑ ነው፡፡

የቤተሰብ ዳራ የማንበብ ተነሳሽነትንና የአንብቦ መረዳት ችሎታን በምን ያክል ደረጃ እንደሚተነብይ በመጠናዊ የመተንተኛ ዘዴዎች ከተሰላ በኋላ በቁጥር የተገለጸው ደረጃ አይነታዊ በሆነ መልኩ ተብራርቷል፡፡

በተመረጠው የጥናት ንድፍ መሰረት የሙከራ ጥናቱ ተሳታፊዎች የምርምር መንገድን በመከተል ተመርጠዋል፡፡ የተመረጡት ተማሪዎችም የአንብቦ መረዳት ችሎታ መለኪያ ፈተና ወስደዋል፡፡ በተጨማሪም የቤተሰብ ዳራ የሚለካውን መጠይቅና የማንበብ ተነሳሽነትን የሚለካውን መጠይቅ ሞልተዋል፡፡

## 4.4. የሙከራ ጥናቱ ተሳታፊዎች አመራረጥ

የአማራ ክልል ዋና ከተማ በሆነችው ባህርዳር ከተማ አስተዳደር ውስጥ አስራአንድ የመጀመሪያ ደረጃ ሙሉ ሳይክል የመንግስት ትምህርት ቤቶች ይገኛሉ፡፡ ከነዚህ ትምህርት ቤቶች ውስጥ በእጣ ንሞና ቀበሌ ዘጠኝ የሚገኘው የድል ችቦ የመጀመሪያ ደረጃ ሙሉ ሳይክል ትምህርት ቤትና ቀበሌ 16 የሚገኘው የቁልቋል ሜዳ የመጀመሪያ ደረጃ ሙሉ ሳይክል የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት ተመርጠዋል፡፡ የመጀመሪያው ትምህርት ቤት (የድል ችቦ) የተዘጋጀውን የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ አስተማማኝነትና ተገቢነት ለማረጋገጥና ለመፈተሽ የተመረጠ ሲሆን ሁለተኛው ትምህርት ቤት (የቁልቋል ሜዳ) ደግሞ የሙከራ ጥናቱን ለማካሄድ መረጃ የተሰበሰበበት ነው፡፡ የዕጣ

ንሞና ተግባራዊ የተደረገው ሁሉም ተማሪዎች እኩል መረጃ መስጠት ስለሚችሉ ሁሉንም ተተኳሪ ተማሪዎች ተሳታፊ ለማድረግ ነው።

ይህ የሙከራ ጥናት ያተኮረው ከአምስተኛ እስከ ስምንተኛ ክፍል በሚገኙ ሁሉም ተማሪዎች ላይ ነው። በዕጣ ንሞና ከተመረጡት ሁለት ትምህርት ቤቶች ውስጥ እያንዳንዱ የክፍል ደረጃ በሶስትና በአራት ሴክሽኖች ተመድቧል። በእያንዳንዱ ሴክሽን ከ41 እስከ 52 ተማሪዎች በድምሩ ከ82 እስከ 150 የሚደርሱ ተማሪዎች በመማር ላይ ይገኛሉ።

ከመጀመሪያው ትምህርት ቤት ከእያንዳንዱ የክፍል ደረጃ ከሚገኙ አራት አራት ሴክሽኖች ሁለት ሁለቱ በእጣ ንሞና ተመርጠው ፈተናውን ወስደዋል መጠይቁንም ሞልተዋል። ከአምስተኛ ክፍል ሀናለ ከስድስተኛ ክፍል ሀና ሐ፣ ከሰባተኛ ክፍል ሐናመ እና ከስምንተኛ ክፍል ሀናለ ሴክሽኖች ተመርጠዋል። ከተመረጡት ሴክሽኖች 80 የአምስተኛ ክፍል 82 የስድስተኛ ክፍል፣ 86 የሰባተኛና 83 የስምንተኛ ክፍል በድምሩ 331 ተማሪዎች በዕለቱ ተገኝተው ስለምርምሩ አላማ ማብራሪያ ተሰጥቷቸዋል። ፍላጎታቸውንም ተጠይቀዋል። ነገር ግን ከተመረጡት ተማሪዎች ከአምስተኛ ክፍል 10 ከስድስተኛ 15 ከሰባተኛ 12ና ከስምንተኛ 14 ተማሪዎች በማግስቱ መጠይቁ በሚሞላበትና ፈተናውን በሚፈተኑበት ቀን ባለመገኘታቸው። ከተፈተኑትና መጠይቁን ከወሰዱት ውስጥ ደግሞ በትክክል ባለመመለሳቸው 70 ያክል ተማሪዎች ተወግደው በ52 የአምስተኛ ክፍል፣ በ62 የስድስተኛ ክፍል፣ በ44 የሰባተኛ ክፍልና በ52 የስምንተኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ በተገኘው መረጃ የመረጃ መሰብሰቢያው አስተማማኝነትና ተገቢነት ተሰልቷል።

ለሙከራ ጥናት ከተመረጠው የቁልቋል ሜዳ የመጀመሪያ ደረጃ ሙሉ ሳይክል ትምህርት ቤትም  በተመሳሳይ ከእያንዳንዱ የክፍል ደረጃ ከሚገኙት ሶስት ሶስት ሴክሽኖች ሁለት ሁለት ሴክሽኖች ተመርጠዋል። ከአምስተኛ ክፍል ሀናለ፣ ከስድስተኛ ክፍል ሀናለ ከሰባተኛ ክፍለ ሀና ሐና ከስምንተኛ ክፍል ለናሐ ተመርጠው በክፍሉ ውስጥ የሚገኙት ተማሪዎች ሁሉም በጥናቱ ተሳታፊ ሆነዋል። መረጃው ለመሰብሰብ ሲጀመር በጥናቱ ላይ መረጃ ለመስጠት የተገኙት ተማሪዎች 302 ተማሪዎች ነበሩ ነገር

ግን በእጣ ንሞና ከተመረጡት 302 ያክል ተማሪዎች 25 ተማሪዎች ፍላጎት እንደሌላቸው በመግለጻቸው፤ 60 ያክል ተማሪዎች ደግሞ መጠይቁንና ፈተናውን በትክክል ባለመሙላታቸውና መጠይቁን ሞልተው ፈተናውን ባለመውሰዳቸው በተመሳሳይ ፈተናውን ወስደው መጠይቁን ባለመመለሳቸው ተወግደው የሙከራ ጥናቱ በ 217 ተማሪዎች ላይ ተካሂዷል፡፡

## 4.5. የሙከራ ጥናቱ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች

የጥናቱን ዋናና ዝርዝር አላማ ከግንዛቤ በማስገባት የተመረጡት የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች የቤተሰብ ዳራና የማንበብ ተሳሽነትን የሚለካ የጽሁፍ መጠይቅና የአንብቦ መረዳት ችሎታ መለኪያ ፈተና ናቸው፡፡ የቤተሰብ ዳራ የሚለካውን መጠይቅና ፈተና አላማና ተግባር በምዕራፍ ሶስት ላይ በዝርዝር ቀርቧል፡፡ በዚህ ምዕራፍ ለሙከራ ጥናቱ ጥቅም ላይ የዋለው የማንበብ ተነሳሽነት መለኪያ መሳሪያ በዝርዝር ይቀርባል፡፡

የማንበብ ተነሳሽነትን የሚለካው የጽሁፍ መጠይቅ የተወሰደው ዊግፊልድና ጉትሬ በ1997 ያዘጋጁትንና በስራቸው የተለያዩ ምርምሮች ውስጥ የተጠቀሙባቸውን በማሻሻልና ወደ አማርኛ በመቀየር ነው፡፡ እንደገና ወደ እንግሊዘኛ በመቀየር ነው፡፡ በመጠይቁ የተካተቱት ጥያቄዎች ብዛት 53 ሲሆን ሁሉም በሬቲንግ ስኬል የቀረቡ ባለአራት አማራጭ ዝግ ጥያቄዎች ናቸው (አባሪ 1.2ን ይመልከቱ)፡፡ የማንበብ ተነሳሽነት መለኪያዎቹ አስራ አንድ ሲሆኑ ሁሉም መለኪያዎች በዚህ ጥናት ላይ ተካተዋል፡፡

አስራ አንዱን የማንበብ ተነሳሽነት ዘርፎች የሚለኩት ጥያቄዎች ተሰባጥረው የቀረቡ ሲሆን በራስ ለመተማመን ማንበብን የሚለኩ ሶስት ጥያቄዎች፣ ለተግዳሮት ማንበብን የሚለኩ ስድስት ጥያቄዎች፣ ለእድገት ማንበብን የሚለኩ አምስት ጥያቄዎች፣ ለማህበራዊ ነገሮች ማንበብን የሚለኩ ሰባት ጥያቄዎች፣ ከስራ ለመራቅ ማንበብን የሚለኩ አራት ጥያቄዎች፣ ጥንካሬን ለማሳየት ማንበብን የሚለኩ አምስት ጥያቄዎች፣ ውጤት ለማግኘት ማንበብን የሚለኩ አራት ጥያቄዎች፣ ለእውቅና ማንበብን የሚለኩ አምስት ጥያቄዎች፣ ለተወዳዳሪነት ማንበብን የሚለኩ ስድስት ጥያቄዎች፣ ለተሳትፎ

ማንበብን የሚለኩ ስድስት ጥያቄዎችና ለተጠቃሚነት ማንበብን የሚለኩ ሁለት ጥያቄዎች ናቸው፡፡

በዚህም መሰረት ጥያቄ ቁጥር 7፣ 15ና 21 በራስ ለመተማመን ማንበብን፤ 2፣ 5፣ 8፣ 16ና 20 ለተግዳሮት ማንበብን 4፣10፣14፣19፣25 ና 29 ጠንካራ ፍላጎት ስላለ ማንበብን 6፣ 12፣ 22፣ 30፣ 33ና 35 ለተሳትፎ ማንበብን 17ና 27 ለተጠቃሚነት ማንበብን 13፣ 24፣ 32ና 40 ከስራ ለመራቅ ማንበብን 1፣ 9፣ 41፣ 44፣ 49ና 52 ለተወዳዳሪነት ማንበብን 18፣28፣ 37፣ 43ና 47 ለእውቅና ማንበብን 3፣38፣ 50ና 53 ለውጤት ማንበብን 11፣ 26፣ 31፣ 39፣ 42፣ 45ና 48 ለማህበራዊ ምክንያቶች ማንበብንና 23፣ 34፣ 36፣ 46ና 51 ለመከበር ማንበብን ይለካሉ፡፡

በመጠይቁ የሚቀርቡት ጥያቄዎች እያንዳንዳቸው ባለአራት አማራጭ ነጥብ መልስ መስጫ መለኪያዎችን መሰረት በማድረግ ተዘጋጅተዋል፡፡ አማራጮቹ አንደኛ ሙሉ በሙሉ አይገልጸኝም፣ ሁለተኛ በመጠኑ አይገልጸኝም፣ ሶስተኛ በመጠኑ ይገልጸኛልና አራተኛ ሙሉ በሙሉ ይገልጸኛል በሚለው ቅደም ተከተል መሰረት የቀረቡ ናቸው፡፡ ጥያቄ ቁጥር 13 "ቃላቶቹ ከባድ ሲሆኑ ማንኛውንም ነገር ማንበብ ያስጠላኛል"፣ ጥያቄ ቁጥር 24 "የቃላት ጥያቄዎችን አልወድም" ጥያቄ ቁጥር 32 "ውስብስብ ታሪኮች ማንበብ አያስደስተኝም"ና ጥያቄ ቁጥር 40 "በታሪኩ ውስጥ በርካታ ሰዎች ካሉበት ማንበብ አልወድም" የሚሉት ጥያቄዎች በአሉታ የቀረቡ በመሆናቸው በግልብጥ ኮድ(Reverse Code) ተመዝግበዋል፡፡

መጠይቁ ወደ አማርኛ ተተርጉሞ በአጥኚዋ አማካሪዎችና በተለያዩ የቋንቋና የስነልቦና ባለሙያዎች ከተገመገመ በኋላ የማስተካከያ ሀሳብ ተጨምሮባቸው ከድል ችቦና ከቁልቋል ሜዳ በተመረጡ ከአምስተኛ እስከ ስምንተኛ ክፍል ባሉ ተማሪዎች ላይ የሙከራ ጥናት ተደርጓል፡፡ አሻሚነት የታየባቸው አንዳንድ ቃላትና ሀረጋት በድጋሚ እንዲስተካከሉ ተደርጓል፡፡ አስተማማኝነቱ በዋናው ጥናት መረጃ መሰረት በክሮንባች አልፋ ተሰልቶ α= 0.91 ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ይህም ተቀባይነት ያለውን አስተማማኝነት ስለሚያሳይ ለዋና ጥናቱ መረጃ ለመሰብሰብ በጥቅም ላይ ውሏል፡፡ የዋናው ጥናት መረጃ አስተማማኝነትም ተሰልቷል፡፡ በስሌቱም መሰረት የአምስተኛ ክፍል α= 0.874ና

የሰባተኛ ክፍል α = 0.884 ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ይህም ተቀባይነት ያለው አስተማማኝነት ስለሚያሳይ ውጤቱ ወደ ትንተና ገብቷል፡፡ ከአጠቃላይ የማንበብ ተነሳሽነት አስተማማኝነት በተጨማሪም የአያንዳንዱ ዝርዝር መለኪያዎች አስተማማኝነትም ተሰልቷል (ዝርዝሩን በ3.5 ላይ ይመልከቱ)፡፡

## 4.6. የሙከራ ጥናቱ የመረጃ መተንተኛ ዘዴ

ከተጠኚዎች የተገኙት መረጃዎች ለትንታኔ ከመቅረባቸው በፊት መልሶች በትክክል ተጠየቃዊ በሆነ መንገድ መሞላታቸው ተጣርቷል፡፡ የተጣራው መረጃ ለትንተና በሚመች መልኩ ኮድ ተድጎ በውጤት መመዝገቢያ ሰንጠረዥ (ኮድ ሽት) ላይ በኮሚፒውተር ላይ ሰፍሮ ድጋሚ የማጣራት ስራ ተሰርተዋል፡፡ በመቀጠልም ይሄቸው የተነሳቸውን ጥያቄዎች አይነትና ባህርይ መሰረት በማደረግ የተለያዩ የመተንተኛ ዘዴዎችን በመጠቀም ትንተና ተደርጓል፡፡

ይህ ጥናት ይሄቸው ከተነሳው አላማዎች የመጀመሪያው የቤተሰብ ዳራ የአንብቦ የመረዳት ችሎታን የመተንበይ ድርሻውን መለየት የሚል ሲሆን ይህንን አላማ ለማሳካት ተግባር ላይ የዋለው የመተንተኛ ዘዴ የህብረ ድህረት ትንተና (Multiple Regression Analysis) ነው፡፡ እንዲሁም የቤተሰብ ዳራ የማንበብ ተነሳሽነትን የመተንበይ ድርሻ እንዳለው ለማረጋገጥ የተሰበሰበው መረጃ በህብረ ድህረት ትንተና (Multiple Regression Analysis) ተተንትኗል፡፡ የህብረ ድህረት ትንተና የመተንተኛ ዘዴ ተግባራዊ የተደረገበት ምክንያት ትንበያን ለመስራት የሚያገለግለው ተገቢ የመተንተኛ በመሆኑ ሲሆን ከድህረት የትንተና አይነቶች ህብረ የተመረጠበት ምክንያት ደግሞ ከቤተሰብ ዳራ ጋር ተያይዘው የሚነሱት ተላውጦዎች በርካታ በመሆናቸው ሁሉንም በአንድ አካቶ የሚሰራ የመተንተኛ ዘዴ በመሆኑ ነው፡፡ የጥናቱ ሶስተኛ አላማ የማንበብ ተነሳሽነትና የአንብቦ መረዳት ችሎታ ተዛምዶን መፈተሽ ሲሆን ይህንን አላማ ለማሳካት ተግባራዊ የተደረገው የመተንተኛ ዘዴ ፒርሰን የተዛምዶ መወሰኛ ቀመር ነው፡፡ በዚህም መሰረት የተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ችሎታ መለኪያ ፈተናውን ወስደው ታርሞ የተገኘው ውጤት የማንበብ ተነሳሽነታቸውን ከሚለካው መጠይቅ ጋር በትክክል በማስፈር ወደ ኤስ ፒ ኤስ ኤስ ተቀይሮ በፒርሰን ተሰርቷል፡፡

የአንብቦ መረዳት ችሎታና የማንበብ ተነሳሽነት በጾታ ልዩነት እንዳለውና እንደሌለው ማረጋገጥ የጥናቱ አራተኛ አላማ ሲሆን ይህንን አላማ ለማሳካት ነጠላ የልይይት ትንተና (One-Way Analysis of Variance (ANOVA)) ጥቅም ላይ ውሏል፡፡ በተመሳሳይ የማንበብ ተነሳሽነት በክፍል ደረጃ ልዩነት እንዳለውና እንደሌለው መፈተሽ የሚለው ተከታዩ አላማ በነጠላ የልይይት ትንተና ተፈትሾ የተገኘው ውጤት ተተንትኗል፡፡ በመጨረሻም ከቤተሰብ ዳራ ጋር በተያያዘ ተማሪዎች ለማንበብ ተነሳሽነቴና ለአንብቦ መረዳት ችሎታየ ይጠቅሙኛል ብለው የሚያስቧቸው ነገሮች መለየት ለሚለው አላማ መረጃው የተሰበሰበው በክፍት ጥያቄ በመሆኑና ተገቢው የመተንተኛ ዘዴ አይነታዊ (በጽሁፍ መግለጽ) በመሆኑ መረጃው አይነታዊ በሆነ መንገድ ተተንትኗል፡፡

በአጠቃላይ በዚህ ጥናት መጠናዊና አይነታዊ የመተንተኛ ዘዴዎች ተግባራዊ የተደረጉ ሲሆን ከመጠናዊ የመተንተኛ ዘዴዎች መካከል ህብረ ድህረት የመተንተኛ ዘዴ፣ ፒርሰን የተዛምዶ መወሰኛ ቀመርና ነጠላ የልይይት ትንተና ተግባራዊ ተደርገዋል፡፡ ሁሉም መረጃዎች የተተነተኑት ኤስ ፒ ኤስ ኤስ ቨርዥን 20.0 (SPSS v20.0) በመጠቀም ነው፡፡

## 4.7. የሙከራው ጥናት ሂደት

የሙከራው ጥናት ዓላማ በዋናው ጥናት ወቅት ተግባር ላይ የሚውሉ መሣሪያዎችን ጠንካራና ደካማ ጎኖች በመለየት አስቀድሞ ጥንቃቄ ለማድረግ ነው፡፡ በመሆኑም ዋናውን ጥናት ለማካሄድ መሠረት በመሆን ያገለግላል በሚል እምነት ተከናውኗል፡፡ የዚህ ጥናት ዋና አላማ የቤተሰብ ዳራ የተማሪዎችን የማንበብ ተነሳሽነትና የአንብቦ መረዳት ችሎታ የመተንበይ ድርሻውን መለየት ነው፡፡ ይህንን አላማ ለማሳካትም ጥናቱ እንደሚከተለው ተከናውኗል፡፡

በዋናነት የሚፈለገው ከተጠኝ ተማሪዎች የሚገኘው መረጃ በመሆኑ የመረጃ አሰባሰብ ሂደቱ እንዳይዛባ ከፍተኛ ጥንቃቄ ተደርጓል፡፡ በመጀመሪያ ለተማሪዎቹ ስለጥናቱ አላማ ዝርዝር ማብራሪያ ተሰጥቷቸዋል፡፡ በመቀጠል ስለመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች አይነትና ባህሪ እንዲሁም አስፈላጊነት በዝርዝር ተነግሯቸዋል፡፡ ፈተናው ከአዲሱ

መማሪያ መጽሀፍ እንደተዘጋጀና የአንብቦ መረዳት ችሎታቸውን ለመለካት እንደሚያገለግል ተገልጾላቸዋል፡፡ ፈተናውን በሚሰሩበት ጊዜ የራሳቸውን እንዲሰሩ፤ መቅዳትም ሆነ ማስቀዳት የተከለከለ መሆኑ ተነግሯቸዋል፡፡ ከፈተናው ግልጽ ያልሆነላቸው ነገር ካለ እጃቸውን በማውጣት እንዲጠይቁ መመሪያ ተሰጥቷቸዋል፡፡

የፅሁፍ መጠይቁ ሁለት አይነት እንደሆነና አንደኛው የቤተሰብ ዳራን የሚመለከትና ሁለተኛው ደግሞ የማንበብ ተነሳሽነታቸውን የሚለካ በመሆኑ በራሳቸው እንዲሞሉት ተነግሯቸዋል፡፡ የማንበብ ተነሳሽነት የሚለካው መጠይቅ አስራ አንድ ክፍሎች እንዳሉት እያንዳንዳቸው ምን ማለት እንደሆኑ ተገልጾላቸዋል፡፡ ከገለጻው ያልገባቸው ወይም ግልጽ ያልሆነላቸው ነገር ካለ እንዲጠይቁ ተነግሯቸዋል፡፡ በመጠይቁይ ትክክል ወይም ስህተት የሚባል መልስ እንዼለለም ተገልጾላቸዋል፡፡

መረጃ በመሰብሰብ ሂደት የክፍሉ መምህራንና ርዕሳነ መምህራን እንዲሳተፉ ተደርጓል፡፡ ተሳታፊ የተደረጉበት ምክንያት አንደኛ ከአምስት እስከ ስምንት የሚገኙ ተማሪዎችን በተመሳሳይ ሰዓት ፈተና ለመስጠትና ለመሰብሰብ በተመራማሪዋ ብቻ ስለማይቻል ነው፡፡ ሁለተኛው ምክንያት ስለጥናቱ አስፈላጊነትና የመረጃው መዛባት ስለሚያመጣው ጉዳት ተጨማሪ ማብራሪያ ለመስጠት አስፈላጊ ሆነው በመገኘታቸው ነው፡፡ ለጥናቱ አስፈላጊ የሚባሉት መረጃዎች ከተሰበሰቡ በኋላ በትንትናው ላይ ስህተት እንዳይፈጠር ተማሪዎች የሞሏቸው መጠይቆች በትክክል መሞላታቸውን ለማረጋገጥ ቅድመ ትንተና ፍተሻ ተደርጓል፡፡ በዚህም መሰረት ለጥናቱ ከተመረጡት 302 የአንደኛ ደረጃ የሁለተኛ እርከን ተማሪዎች መካከል 85 ተማሪዎች በትክክል ሞልተው ባለመገኘታቸው ተወግደዋል፡፡ በመጨረሻም የተጣራው መረጃ ትንተና ተደርጎበታል፡፡

## 4.8. የሙከራ ጥናቱ የውጤት ትንተና

በየመጀመሪያው የጥናቱ መሰረታዊ ጥያቄ ***"የቤተሰብ ዳራ የአንብቦ መረዳት ችሎታን የመተንበይ ድርሻው ምን ያክል ነው?"*** የሚል ሲሆን ይህን ጥያቄ ለመፈተሽ የህብረ ድህረት ትንተና (multiple regression analysis) ተግባራዊ ተደርጓል፡፡ ውጤቱም በሰንጠረዥ 1 ላይ እንደሚከተለው ተመልክቷል፡፡

**ሰንጠረዥ 4.1፡- የቤተሰብ ዳራ ለአንብቦ መረዳት ችሎታ ያለው ተናጠላዊ አስተዋጾና የጉልህነት ደረጃ በድህረት ትንተና (multiple regression analysis)**

| Model | Unstandardized Coefficients | | Standardized Coefficients | ቲ-ስሌት t | የጉልህነት ደረጃ Sig. |
|---|---|---|---|---|---|
| | ቤታ B | መደበኛ የአማካይ ስህተት Std. Error | ቤታ Beta | | |
| (Constant) | 22.667 | 5.487 | | 4.131 | .000 |
| ከአባት ጋር ብቻ | -.686 | 2.729 | -.017 | -.251 | .802 |
| ከእናት ጋር ብቻ | .700 | 1.002 | .054 | .698 | .486 |
| ከአባትና እንጀራእናት ጋር | -2.463 | 2.798 | -.062 | -.880 | .380 |
| ከእናትና እንጀራ አባት ጋር | 3.225 | 4.186 | .058 | .771 | .442 |
| ከዘመድ ጋር | -1.965 | 1.015 | -.160 | -1.937 | .054 |
| ከሌላ ሰው ጋር | -4.599 | 2.468 | -.142 | -1.863 | .064 |
| ብቻ | -4.077 | 3.113 | -.115 | -1.310 | .192 |
| የቤተሰብ መዋቅር | -1.180 | .574 | -.146 | -2.056 | .041 |
| የአባት የትምህርት ደረጃ | -.591 | .441 | -.149 | -1.341 | .182 |
| የእናት የት/ት ደረጃ | .303 | .467 | .064 | .649 | .517 |
| በቤት የተማረ ሰው መኖር | -.859 | .911 | -.072 | -.943 | .347 |
| ከፍተኛው የትምህርት ደረጃ | -.057 | .398 | -.014 | -.142 | .887 |
| የአባት ስራ 1. ገበሬ | .858 | 1.166 | .065 | .736 | .463 |
| 2. ነጋዴ | -1.102 | 1.081 | -.085 | -1.019 | .310 |
| 3. ሌላ | 2.586 | 1.032 | .217 | 2.507 | .013 |
| የእናት ስራ1. ገበሬ | -.732 | 1.883 | -.036 | -.389 | .698 |
| ነጋዴ | -.041 | 1.237 | -.003 | -.033 | .974 |
| የመንግስት ሰራተኛ | 1.863 | 1.136 | .138 | 1.640 | .103 |
| ሌላ | .050 | 1.126 | .003 | .044 | .965 |
| የቤተሰብ ድጋፍ | -.487 | .303 | -.127 | -1.609 | .109 |
| ቁሳ. 1. መጽሃፍት | -.485 | .475 | -.079 | -1.020 | .309 |
| ቁሳ.2. ጠረጴዛና ወንበር | 1.082 | .881 | .099 | 1.228 | .221 |
| ቁሳ 3. የግል ክፍል | -1.513 | 1.139 | -.110 | -1.328 | .186 |
| ቁሳ 4. ግል አልጋ | -.976 | .885 | -.092 | -1.102 | .272 |
| ቁሳ 5. ሞባይል | -.077 | .905 | -.006 | -.085 | .932 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| ቁሳ 6.የት/ት መርጃ መሳሪያ | -.228 | .943 | -.021 | -.242 | .809 |
| የወር ገቢ | .145 | .447 | .027 | .323 | .747 |
| የዕለት ምግብ | .675 | .925 | .058 | .730 | .466 |
| ገቢ ከአካባቢ ጋር ሲነጻጸር | -.349 | .404 | -.061 | -.864 | .389 |
| ማህበ 1. እድር | 1.671 | .972 | .135 | 1.719 | .087 |
| ማህበ 2. እቁብ | 1.657 | .779 | .153 | 2.126 | .035 |
| ማህበ 3. ማህበር | -1.379 | .840 | -.126 | -1.641 | .103 |

**Model Summary[b]**

| Model | R | R Square የተጋርቶሽ መጠን | Adjusted R Square | Std. Error of the Estimate |
|---|---|---|---|---|
| 1 | .482[a] | .232 | .098 | 5.074 |

ጥገኛ ተላውጦ፤ የአንብቦ መረዳት ችሎታ

የህብረ ድህረት ትንተና ውጤት እንደሚያመለክተው ከቤተሰብ ዳራ ጋር የተገናኙ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ትምህርታዊና ከስራ ጋር የተገናኙ ተላውጦዎች በተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ችሎታ ላይ የሚያበረክቱት ተጽዕኖ ($R^2$=0.232, F=1.729, p >0.05) በአብዛኛው ጉልህ ሆኖ አልተገኘም፡፡ በተወሰኑት ላይ ግን ጉልህ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ዝርዝሩ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

ከቤተሰብ መዋቅር ጋር ተያይዞ የሚነሳው ጥያቄ ከማን ጋር ትኖራለህ/ትኖሪያለሽ የሚለው  በአብዛኛው ከእናትና አባት ጋር የሚል ምላሽ በመገኘቱ ሌሎቹ አማራጮች ከዚሁ ጋር እርስ በርስ ተነጻጽረው የተገኘው ውጤት እንደሚያሳየው ከወላጆቻቸው ጋር በሚኖሩ ተማሪዎችና ከእናት ጋር ብቻ፣ ከአባት ጋር ብቻ፣ ከአባትና እንጀራ እናት፣ ከእናትና እንጀራ አባት፤ ከዘመድ፣ ከሌላ ሰው ጋርና ብቻቸውን በሚኖሩ ተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ችሎታ መካከል ጉልህ የሆነ ልዩነት እንደሌለው የህብረ ድህረት ውጤቱ ያሳያል፡፡

ከአባት ጋር ብቻ የሚኖሩ (B=-0.686, t=-0.251, p>0.05)፣ ከእናት ጋር ብቻ የሚኖሩ (B=0.700, t=0.698, p>0.05)፣ ከአባትና እንጀራ እናት ጋር የሚኖሩ (B=--2.463, t=-0.251, p>0.05)፣ ከእናትና እንጀራ አባት ጋር የሚኖሩ (B=3.225, t=0.771, p>0.05)፣ ከዘመድ(B=-1.965, t=-1.937, p>0.05)፣ ከሌላ ሰው ጋር (B=-4.599, t=-1.863, p>0.05)ና ለብቻ (B=-4.077, t=-1.310, p>0.05) በሚል የተመለከተው

ትንተና ተላውጦዎቹ በአንብቦ መረዳት ውጤት ላይ ያላቸው ተጽዕኖ በስታስቲክስ ጉልህ ያለመሆኑን ያሳያል፡፡

ከውጤቱ እንደተመለከተው ከእናት ጋር ብቻ መኖርና ከእናትና እንጀራ አባት ጋር መኖር ለተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ውጤት አወንታዊ ተጽዕኖ ሲኖረው ከአባት ጋር ብቻ፣ ከአባትና እንጀራ እናት፣ ከዘመድ፣ ከሌላ ሰው ጋርና ብቻ መኖር ግን በተቃራኒው አሉታዊ ተጽዕኖ ይኖረዋል፡፡ የአሉታዊና አወንታዊ ተጽዕኗቸው ግን ጉልህ አለመሆኑን የጉልህነት ደረጃው ያሳያል፡፡

ከዚሁ ጋር በተያያዘ የተነሳው ሌላው ተላውጦ የቤተሰብ ቁጥር ሲሆን ከሰንጠረዡ ላይ ($B=-1.180$, $t=-2.056$, $p<0.05$) በሚል ተመልክቷል፡፡ ይህም ማለት የቤተሰብ ቁጥር በአንብቦ መረዳት ችሎታ ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ አለው ማለት ሲሆን ተጽዕኖውም ጉልህ መሆኑን ያመለክታል፡፡ የአንድ ተማሪ ቤተሰብ ቁጥር በጨመረ ቁጥር የአንብቦ መረዳት ችሎታው ላይ አሉታዊ ጎኑ እየሰፋ ይሄዳል ማለት ነው፡፡ በሌላ አገላለጽ የቤተሰብ ቁጥር እየጨመረ በሄደ ቁጥር የተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ችሎታ እየቀነሰ ይሄዳል ማለት ነው፡፡

የቤተሰብ የትምህርት ደረጃና ሁኔታ ከቤተሰብ ዳራ ጋር በተያያዘ የሚነሳ ሌላው ተላውጦ ሲሆን በመጠይቁ የአባት የትምህርት ደረጃ፣ የእናት የትምህርት ደረጃ፣ በቤተሰብ የተማረ ሰው መኖርና አለመኖር እንዲሁም ከፍተኛው የትምህርት ደረጃ በሚል የቀረበ ሲሆን በድህረት ትንተናው እንደሚከተለው ውጤቱ ቀርቧል፡፡ የአባት የትምህርት ደረጃ ($B=-0.591$, $t=-1.341$ $p>0.05$)፣ የእናት የትምህርት ደረጃ ($B=0.303$, $t=0.649$ $p>0.05$)፣ በቤተሰብ የተማረ ሰው መኖርና አለመኖር ($B=-0.859$, $t=-0.943$ $p>0.05$)ና በቤተሰብ ያለው ከፍተኛ የትምህርት ደረጃ ($B=-0.057$, $t=-0.142$ $p>0.05$) በሚል የተመለከተው ትንተና የተላውጦዎቹ የተጽዕኖ መጠን ጉልህ ያለመሆኑን ያሳያል፡፡ የእናት የትምህርት ደረጃ አወንታዊ ተጽዕኖ ሲኖረው የአባት የትምህርት ደረጃ፣ በቤት ውስጥ የተማረ ሰው መኖርና አለመኖር የሚለው እንዲሁም ከፍተኛው የትምህርት ደረጃ በተከታታይ አሉታዊ ተጽዕኖ ቢስተዋልባቸውም ጉልህ ግን አይደለም፡፡

ከቤተሰብ ዳራ ውስጥ የሚጠቀሰው ሌላው ተጽዕኖ ፈጣሪ ተላውጦ የወላጅ ስራ ሲሆን የአባትና የእናት በሚል ተከፋፍሎ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡ በመጀመሪያ የሰፈረው የአባት ስራ የሚለው ገበሬ፤ የመንግስት ሰራተኛ፣ ነጋዴና ሌላ( ከሶስቱ አማራጮች ውጭ) የሚሉ አማራጮች ቀርበው በህብረ ድህረት ትንተና የተገኘው ውጤት የሚከተለውን ይመስላል፡፡ ገበሬ (B=0.858, t=0.736 p>0.05)፣ ነጋዴ (B=-1.102, t=-1.019 p>0.05)ና ሌሎች ስራዎች (B=2.586., t=2.507 p<0.05) ተመልክቷል፡፡ የህብረ ድህረት ትንተናው እንደሚያሳየው አባቶቻቸው የመንግስት ስራ የሚሰሩ ልጆች እንደማነጻጸሪያ ተወስደው ውጤቱ ሲታይ የመንግስት ሰራተኛ ልጆች የአንብቦ መረዳት ችሎታ ከገበሬ እንዲሁም ከነጋዴ ልጆች የአንብቦ መረዳት ችሎታ የጎላ ልዩነት አላሳየም፡፡ ነገር ግን  ሌላ ካለ ይገለጽ በሚለው ስር የተገለጹት የግንበኛ፣ የቄስ፣ የጡረተኛ፣ የአናጺ፣ የጋሪ ነጂ፣ የቀን ሰራተኛና የፋብሪካ ሰራተኛ ልጆች የአንብቦ መረዳት ችሎታቸው ከመንግስት ሰራተኛ ልጆች ጋር ሲነጻጸር የተሻለና ጉልህ መሆኑን ያሳያል፡፡ ይህም ማለት ሌሎች ስራዎችን ከሚሰሩ አባቶች የመጡ ልጆች የአንብቦ መረዳት ችሎታቸው ከፍተኛ ነው፡፡ ወይም ከመንግስት ሰራተኛ ልጆች የተሻለ ነው፡፡

የእናት ስራ አምስት አማራጮችን ይዞ የቀረበ ሲሆን የቤት እመቤት፣ ገበሬ፣ ነጋዴ፣ የመንግስት ሰራተኛና ሌሎች ሲሆን በአብዛኛው የተመረጠው የቤት እመቤት እንደማነጻጸሪያ ተወስዶ በድህረት ትንተና የተገኘው ውጤት የሚከተለው ነው፡፡ ገበሬ (B=-0.732, t=-.389 p>0.05)፣ ነጋዴ (B=-0.041, t=-0.033 p>0.05)፣ የመንግስት ሰራተኛ (B=1.863, t=1.640 p>0.05)ና ሌሎች (B=2.586, t=2.507 p>0.05) በሚል የተመለከተው ትንተና ተላውጦዎቹ በአንብቦ መረዳት ውጤት ላይ ያላቸው ተጽዕኖ በስታስቲክስ ጉልህ ያለመሆኑን ያሳያል፡፡

ከሰንጠረዡ ላይ እንደሚታየው እናቶቻቸው ነጋዴና ገበሬ የሆኑ ልጆች የአንብቦ መረዳት ችሎታ እናቶቻቸው የቤት እመቤት ከሆኑት ጋር ሲነጻጽር አሉታዊ ቢሆንም ልዩነቱ ግን ጉልህ ያለመሆኑን ውጤቱ ያሳያል፡፡ በሌላ መልኩ የእናቶቻቸው ስራ የመንግስት ሰራተኛና ሌላ (ጽዳት፣ የፋብሪካ ሰራተኛ፣ ቀን ሰራተኛ፣ ግንበኛ፣ ጡረተኛ) የሆኑት አወንታዊ ተጽዕኖ ቢኖረውም ከቤት እመቤቶች ጋር ሲነጻጸር ግን ጉልህ ያለመሆኑን ያሳያል፡፡ ማለትም እናቶቻቸው  የቤት እመቤት በሆኑና እናቶቻቸው ገበሬ፣ ነጋዴና

የመንግስት ሰራተኛ በሆኑ ልጆች የአንብቦ መረዳት ችሎታ መካከል የታየው ልዩነት ጉልህ አደለም፡፡

ቤተሰብ ተማሪዎች እንዲያነቡ ምን ያህል ያበረታታል የሚለው ከቤተሰብ ዳራ ጋር ተያይዞ የሚነሳው ሌላው ተላውጦ ሲሆን በድህረ ትንተናው እንደተመለከተው የተገኘው ውጤት አሉታዊ ቢሆንም ተጽዕኖው ግን ጉልህ አይደለም (B=-0.487, t=-0.127 p>0.05)፡፡ ማለትም የቤተሰብ ማበረታቻ በአንብቦ መረዳት ችሎታ ላይ የሚያመጣው ተጽዕኖ የጎላ አይደለም፡፡

በቤት ውስጥ የሚገኙ የተያዩ ቁሳቁሶች የሚለውና ከማህበረ ኢኮኖሚያዊ ተላውጦ ጋር ተያይዞ የሚነሳው ሀሳብ የተሳታፊዎቹን ሁኔታ በመመርኮዝ በአምስት አማራጮች ተወስኖ የቀረበ ሲሆን በድህረ ትንተናው የተገኘው ውጤት እንደሚከተለው ተመልክቷል፡፡ የመጀመሪያው ተማሪዎች በግል የሚኖሯቸውን መጽሀፍት የሚመለከተው የድህረት ትንተናው ውጤት አሉታዊና ጉልህ ያለመሆኑን ያሳያል (B=-0.485, t=-0.079 p>0.05)፡፡ ቀጣዮቹ አማራጮች የማጥኛ ጠረጴዛና ወንበር (B=1.082, t=0.099 p>0.05)፣ የግል ክፍል (B=-1.513, t=-0.110 p>0.05)፣ የግል አልጋ (B=-0.976, t=0.092 p>0.05)፣ የግል ሞባይል (B=-0.077, t=-006. p>0.05)፣ የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች (B=-0.228, t=-0.242 p>0.05) የሚል ውጤት ያሳዩ ሲሆን የግል መጽሀፍ፣ የግል ክፍል መኖር፣ የግል ሞባይል መኖርና የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች መኖር አሉታዊ ተጽዕኖ የማጥኛ ጠረጴዛና ወንበር መኖር ደግሞ አወንታዊ ተጽዕኖ ቢኖራቸውም ድርሻቸው ግን ጉልህ አለመሆኑን የድህረት ትንተና ውጤቱ ያሳያል፡፡

ከቤተሰብ ዳራ ጋር ተያይዞ ከሚነሱት ዋና ተላውጦዎች መካከል የቤተሰብ ወይም ያሳዳጊዎች የማህበረ ኢኮኖሚያዊ ደረጃ አንዱ ሆኖ ይጠቀሳል፡፡ የኢኮኖሚ መለኪያ ሆነው የቀረቡት ሶስት ጥያቄዎች የቤተሰብ ወርሀዊ ገቢ፣ ገቢው ከአካባቢው ጋር ሲነጻጸር ያለው ልዩነትና የቀን ምግብ ብዛት በድግግሞሽ የሚሉ ሲሆኑ በድህረት ትንተናው የተገኘው ውጤት የቤተሰብ ወርሀዊ ገቢ (B=0.145, t=0.027 p>0.05)፣ ገቢያቸው ከአካባቢው ጋር ሲነጻጸር (B=0.349, t=-061. p>0.05) በቀን ምን ያክል ትመገባለህ/ሽ (B=0.6750, t=0.058 p>0.05) የሚል ነው፡፡ ውጤቱ እንደሚያሳየው

ገቢና በቀን የሚመገቡት ብዛት አወንታዊ ገቢያቸው ከአካባቢው ጋር ሲነጻጸር ደግሞ አሉታዊ ተጽዕኖ ቢኖራቸውም ተጽዕኗቸው ጉልህ አይደለም፡፡

ሌላው ተላውጦ ማህበራዊ ጉዳዮችን የያዘ ሲሆን እድር እቁብና ማህበር ተብሎ በሶስት አበይት ክፍሎች ይከፈላል፡፡ ማህበራዊ ጉዳዮች በአብዛኛው በአንብቦ መረዳት ችሎታ ላይ አወንታዊ ተጽዕኖ ሲኖራቸው አሉታዊ ተፅዕኖም እንደሚከተለው ታይቷል፤ እድር (B=1.671, t=1.719 $p>0.05$) እቁብ (B=1.657, t=2.126 $p>0.05$) ማህበር (B=-1.379, t=-0.126 $p>0.05$) ናቸው፡፡ ከውጤቱ መረዳት እንደሚቻለው እድር አወንታዊ ማህበር ደግሞ አሉታዊ ተጽዕኖ ቢኖራቸውም ተጽዕኖአቸው ጉልህ አይደለም፡፡ እቁብ አወንታዊና ጉልህ ተጽዕኖ እንዳለው የድህረት ትንተና ውጤቱ አሳይቷል፡፡

ከሰንጠረዥ ለመረዳት እንደሚቻለው በዚህ የህብረ ድህረት ትንተና የነጻ ተላውጦዎች የተጋርቶ መጠን መለኪያ $R^2$( coefficient of determination) 0.232 ወይም 23.2% ነው፡፡ ምንም እንኳን እነዚህ ተላውጦዎች 23.2% ያክል ግንኙነት ቢኖራቸውም የጉልህነት ደረጃው ግን ከቤተሰብ አባላት ብዛት (መዋቅር)፣ የአባት ስራ (ሌሎች)ና ከማህበራዊ ጉዳዮች እቁብ በስተቀር ዝቅተኛ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ስለዚህ ከቤተሰብ መዋቅር (የአባላት ብዛት)፣ ከአባት ስራ ሌላ ካለ ይገለጽ በሚል የተገለጹት (ጡረተኛ፣ ቄስ፣ ግንበኛ፣ የቀን ሰራተኛ፣ የፋብሪካ ሰራተኛ)ና ከማህበራዊ ጉዳዮች አንዱ ከሆነው እቁብ በስተቀር ሌሎች ተላውጦዎች የአንብቦ መረዳት ችሎታን የመተንበይ ድርሻቸው ጉልህ አይደለም ማለት ነው፡፡ ከዚህ መነሳት የቤተሰብ ዳራ ተላወጦዎች የሆኑት አብረው የሚኖሩት ሰው፣ የቤተሰብ መዋቅር (የአባላት ብዛት)፣ የወላጅ ወይም የአሳዳጊ የትምህርት ደረጃ፣ የተማረ ሰው መኖርና አለመኖር፣ ከፍተኛው የትምህርት ደረጃ፣ የቤተሰብ ማበረታቻ፣ በቤት ውስጥ የሚገኙ የተለያዩ ቁሳቁሶች (መጽሀፍት፣ ማጥኛ ጠረጴዛና ወንበር፣ የግል ክፍል፣ የግል አልጋ፣ ሞባይልና የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች)፣ የቤተሰብ የወር ገቢ፣ ገቢው ከአካባው ነዋሪ ጋር ሲነጻጸር፣ በቀን የሚመገቡት ጊዜ በድግግሞሽ፣ የቤተሰብ ማህበራዊ ተሳትፎ (እድር፣ እቁብ፣ ማህበር) በአጠቃላይ ከአንብቦ መረዳት ችሎታ ጋር 23.2% የልይይት መጠን ይጋራሉ፡፡ ወይም አወንታዊና አሉታዊ ተጽዕኖ ያሳድራሉ ማለት ይቻላል፡፡

ጉልህ ተጽዕኖ የሚያሳድሩት የቤተሰብ መዋቅር፣ የአባት ስራና እቁብ ከአጠቃላዩ 23.2% ውስጥ 5.8% ይጋራሉ፡፡ የቤተሰብ መዋቅር የተዛምዶ ክፍል ድርሻው -0.113

ሲሆን በራሱ ተባዝቶ ወደ100 ሲቀየር 1.28% ይወስዳል፡፡ ከአባት ስራ ከቀረቡት አማራጮች ሌላ ካለ ይገለጽ የሚለው ተላውጦ የተዛምዶ ክፍሉ 0.162 ሲሆን በራሱ ተባዝቶ ወደ ፐርሰንት ሲቀየር 2.62% የልይይት መጠንን ይጋራል፡፡ ሌላው አሉታዊ ጉልህ ተጽዕኖ የሚያሳድረው ተላውጦ የማህበራዊ ተራክቦ ክፍል የሆነው እቁብ ሲሆን የተዛምዶ ድርሻው 0.138 በራሱ ተባዝቶ ወደፐርሰንት ሲቀየር ከአጠቃላዩ የተጋርቶ መጠን 1.9% ያህሉን የሚጋራ መሆኑን የተዛምዶ ክፍል ድርሻቸው ያሳይል፡፡ ቀሪውን ሌሎች ጉልህ ያልሆኑት ተላውጦዎች ይጋሩታል፡፡

በአጠቃላይ በቤተሰብ ዳራ ስር ከቀረቡት ሰላሳሶስት ተላውጠዎች እያንዳንዳቸው በአንብቦ መረዳት ችሎታ ላይ አሉታዊና አወንታዊ ድርሻ ቢኖራቸውም በአንብቦ መረዳት ችሎታ ላይ ጉልህ ተጽዕኖ እንዳላቸው የተረጋገጡት ግን የቤተሰብ መዋቅር (የቤተሰብ አባላት ብዛት)፣ የአባት ስራ (ሌሎች በሚለው የተዘረዘሩት ግንበኛ፣ ጡረተኛ፣ ቄስ፣ ጋሪ ነጅ፣ ቀን ሰራተኛ የመሳሰሉት)ና ማህበራዊ ጉዳይ የሆነው እቁብ ብቻ ናቸው፡፡ ከነዚህ ሶስት ተላውጦዎች የሁለቱ ተጽዕኖ ጉልህና አወንታዊ መሆኑን እንዲሁም የቤተሰብ መዋቅር የሚለው ደግሞ ጉልህና አሉታዊ እንደሆነ የድህረት ትንተናው ያመለክታል፡፡

በመቀጠል የተማሪዎች የቤተሰብ ዳራ የማንበብ ተነሳሽነትን የመተንበይ ጉልህ ድርሻ ይኖረው ወይም አይኖረው እንደሆነ፣ ካለውም የትኛው ተላውጦ የማንበብ ተነሳሽነትን እንደሚተነብይ ለማየት ተሞክሯል፡፡ ዝርዝሩ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

ሁለተኛው የጥናቱ መሰረታዊ ጥያቄ ***"የቤተሰብ ዳራ የማንበብ ተነሳሽትን የመተንበይ ድርሻው ምን ያክል ነው?"*** የሚል ሲሆን ይህን ጥያቄ ለመፈተሽ የህብረ ድህረት ትንተና (multiple regression analysis) ተደርጓል፡፡ ውጤቱም በሰንጠረዥ 2 ላይ እንደሚከተለው ተመልክቷል፡፡

**ሰንጠረዥ 4.2፡- የቤተሰብ ዳራ ለማንበብ ተነሳሽነት ያለው ተናጠላዊ አስተዋጾና የጉልህነት ደረጃ በድህረት ትንተና (multiple regression analysis)**

| የቤተሰብ ዳራ ዝርዝር ተላውጦዎች | Unstandardized Coefficients | | Standard izedCoef ficients | ቲ-ስሌት t | የጉልህነት ደረጃ Sig. |
|---|---|---|---|---|---|
| | ቤታBeta | መደበኛ የአማካይ ስህተት | ቤታ Beta | | |
| ከአባት ጋር ብቻ | 9.676 | 12.001 | .057 | .806 | .421 |
| ከእናት ጋር ብቻ | 8.206 | 4.408 | .147 | 1.861 | .064 |
| ከአባትና እንጀራእናት ጋር | 18.241 | 12.309 | .107 | 1.482 | .140 |
| ከእናትና እንጀራ አባት ጋር | 1.144 | 18.411 | .005 | .062 | .951 |
| ከዘመድ ጋር | -.413 | 4.463 | -.008 | -.092 | .926 |
| ከሌላ ሰው ጋር | .544 | 10.856 | .004 | .050 | .960 |
| ብቻ | -12.538 | 13.692 | -.082 | -.916 | .361 |
| የቤተሰብ መዋቅር | .444 | 2.525 | .013 | .176 | .861 |
| የአባት የትምህርት ደረጃ | .154 | 1.939 | .009 | .080 | .937 |
| የእናት የት/ት ደረጃ | 1.258 | 2.052 | .062 | .613 | .541 |
| በቤት የተማረ ሰው መኖር | 3.757 | 4.007 | .072 | .938 | .350 |
| ከፍተኛው የትምህርት ደረጃ | .820 | 1.751 | .046 | .468 | .640 |
| የአባት ስራ 1. ገበሬ | -.053 | 5.128 | -.001 | -.010 | .992 |
| 2. ነጋዴ | -2.804 | 4.756 | -.050 | -.589 | .556 |
| 3. ሌላ | .657 | 4.537 | .013 | .145 | .885 |
| የእናት ስራ1. ገበሬ | 6.884 | 8.283 | .078 | .831 | .407 |
| ነጋዴ | 8.304 | 5.442 | .119 | 1.526 | .129 |
| የመንግስት ሰራተኛ | -.748 | 4.995 | -.013 | -.150 | .881 |
| ሌላ | 5.200 | 4.952 | .080 | 1.050 | .295 |
| የቤተሰብ ድጋፍ | -3.110 | 1.332 | -.187 | -2.336 | .021 |
| ቁሳ. 1. መጽኀፍት | 3.428 | 2.090 | .130 | 1.641 | .103 |
| ቁሳ.2. ጠረጴዛና ወንበር | -2.896 | 3.877 | -.061 | -.747 | .456 |
| ቁሳ 3. የግል ክፍል | -1.810 | 5.012 | -.031 | -.361 | .718 |
| ቁሳ 4. ግል አልጋ | 4.434 | 3.892 | .096 | 1.139 | .256 |
| ቁሳ 5. ሞባይል | 1.592 | 3.981 | .030 | .400 | .690 |
| ቁሳ 6.የት/ት መርጃ መሳሪያ | 3.591 | 4.147 | .078 | .866 | .388 |
| የወር ገቢ | .269 | 1.967 | .012 | .137 | .891 |
| የዕለት ምግብ | 6.058 | 4.068 | .119 | 1.489 | .138 |
| ገቢ ከአካባቢ ጋር ሲነጻጸር | 4.029 | 1.777 | .164 | 2.267 | .025 |
| ማህበ 1. እድር | -3.842 | 4.275 | -.072 | -.899 | .370 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| ማህበ 2. እቁብ | -.941 | 3.428 | -.020 | -.275 | .784 |
| ማህበ 3. ማህበር | 1.645 | 3.696 | .035 | .445 | .657 |

**Model Summary[b]**

| Model ሞዴል | R | R Square የተጋርቶሽ መጠን | Adjusted R Square | Std. Error of the Estimate |
|---|---|---|---|---|
| 1 | .453[a] | .205 | .066 | 22.318 |

ጥገኛ ተላውጦ፤ የማንበብ ተነሳሽነት

የድህረት ትንተና ውጤት እንደሚያመለክተው በዝርዝር የቀረቡት የቤተሰብ ዳራ ተላውጦዎች በተማሪዎች የማንበብ ተነሳሽነት ላይ የሚያሳድሩት ተጽዕኖ ($R^2$=0.205, F=1.745, $p > 0.05$ & $p < 0.05$) ሆኖ ተገኝቷል። የተጽዕኖው የጉልህነት ደረጃ በተወሰኑት ላይ ብቻ ሲሆን የአብዛኞቹ ጉልህ ሆኖ አልተገኘም። የእያንዳንዳቸው የመተንበይ ድርሻ እንደሚከተለው በዝርዝር ቀርቧል።

ከጥያቄ አንድ እንደተገለጸው ሁሉ በማንበብ ተነሳሽነት ከተነሱት ጥያቄዎች የመጀመሪያው ከማን ጋር ትኖራለህ/ትኖሪያለሽ የሚለው ሲሆን በአብዛኛው ከእናትና አባት ጋር የሚል ምላሽ በመገኘቱ ከዛ ጋር እርስ በርስ ተነጻጽሮ የተገኘው ውጤት እንደሚያሳየው ከወላጆቻቸው ጋር በሚኖሩ ተማሪዎችና ከእናት ጋር ብቻ፣ ከአባት ጋር ብቻ፣ ከአባትና እንጀራ እናት፣ ከእናትና እንጀራ አባት፤ ከዘመድ፣ ከሌላ ሰው ጋርና ብቻቸውን በሚኖሩ ተማሪዎች የማንበብ ተነሳሽነት መካከል ጉልህ የሆነ ልዩነት እንደሌለው የህብረ ድህረት ውጤቱ ያሳያል።

ከአባት ጋር ብቻ የሚኖሩ (B=9.676, t=0.806, $p>0.05$)፣ ከእናት ጋር ብቻ የሚኖሩ (B=8.206, t=0.147, $p>0.05$)፣ ከአባትና እንጀራ እናት (B=18.241, t=1.482, $p>0.05$)፣ ከእናትና እንጀራ አባት(B=1.144, t=0.062, $p>0.05$)፣ ከዘመድ(B=-0.413, t=-0.092, $p>0.05$)፣ ከሌላ ሰው ጋር (B=0.542, t=0.004, $p>0.05$)ና ብቻ (B=-12.538, t=-0.916, $p>0.05$) በሚል የተመለከተው ትንተና ተላውጦዎቹ በማንበብ ተነሳሽነት ላይ ያላቸው ተጽዕኖ በስታስቲክስ ጉልህ ያለመሆኑን ያሳያል።

ከውጤቱ እንደተመለከተው ከወላጅ ጋር ከመኖር ጋር ሲነጻጸሩ ከዘመድ ጋር መኖርና ብቻ መኖር በማንበብ ተነሳሽነት ላይ ያላቸው ተጽዕኖ አሉታዊ ሲሆን ከአባት ጋር ብቻ፣

ከእናት ጋር ብቻ፣ ከእናትና እንጀራ አባት ጋር፣ ከአባትና እንጀራ እናት ጋርና ከሌላ ሰው ጋር መኖር አወንታዊ አስተዋጽዖ ቢኖራቸውም አስተዋጽኦቸው በስታስቲክስ ሲታይ ጉልህ አለመሆኑን የድህረት ትንተና ውጤቱ ያሳያል፡፡

ከቤተሰብ መዋቅር ጋር በተያያዘ የተነሳው ሌላው ተላውጦ የቤተሰብ ቁጥር ሲሆን ተጽዕኖው ከሰንጠረዡ ላይ (B=0.444, t=0.176, p>0.05) በሚል ተመልክቷል፡፡ ይህም ማለት የቤተሰብ ቁጥር በማንበብ ተነሳሽነት ላይ አወንታዊ ተጽዕኖ አለው ማለት ሲሆን ተጽዕኖውም ጉልህ አለመሆኑን ያመለክታል፡፡

የቤተሰብ የትምህርት ደረጃና ሁኔታ ከቤተሰብ ዳራ ጋር በተያያዘ የሚነሳ አብይ ተላውጦ ሲሆን በመጠይቁ የአባት የትምህርት ደረጃ፣ የእናት የትምህርት ደረጃ፣ በቤተሰብ የተማረ ሰው መኖርና አለመኖር እንዲሁም ከፍተኛው የትምህርት ደረጃ በሚሉ የተለያዩ አመራጮች የቀረበ ሲሆን የድህረት ትንተናው ውጤት እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡ የአባት የትምህርት ደረጃ (B=0.154, t=-0.080 p>0.05)፣ የእናት የትምህርት ደረጃ (B=1.258, t=0.613 p>0.05)፣ በቤተሰብ የተማረ ሰው መኖርና አለመኖር (B=3.757, t=0.938 p>0.05)ና በቤተሰብ ያለው ከፍተኛ የትምህርት ደረጃ (B=0.820, t=0.468 p>0.05) በሚል የተመለከተው ትንተና የተላውጦዎቹ የተጽዕኖ መጠን ጉልህ ያለመሆኑን ያሳያል፡፡ የእናት የትምህርት ደረጃ፣ የአባት የትምህርት ደረጃ፣ በቤት ውስጥ የተማረ ሰው መኖርና አለመኖር የሚለው እንዲሁም ከፍተኛው የትምህርት ደረጃ ሁሉም አወንታዊ ተጽዕኖ ቢኖራቸውም ጉልህ ግን አይደለም፡፡

የወላጅ ወይም ያሳዳጊ ስራ ከቤተሰብ ዳራ ውስጥ የሚጠቀሰው ሌላው ተጽዕኖ ፈጣሪ ተላውጦ ሲሆን የአባት ወይም የወንድ አሳዳጊና የእናት ወይም የሴት አሳዳጊ በሚል ተከፋፍሎ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡ በመጀመሪያው ጥያቄ የቀረበው የአባት ስራ ገበሬ፤ የመንግስት ሰራተኛ፣ ነጋዴና ሌላ ካለ ይገለጽ የሚሉ አራት አማራጮች ቀርበው በህብረት ድህረት ትንተና የተገኘው ውጤት የሚከተለውን ይመስላል፡፡ ገበሬ (B=-0.053, t=-0.010 p>0.05)፣ ነጋዴ (B=-2.804, t=-0.859 p>0.05)ና ሌሎች ስራዎች (B=0.657, t=0.145 p>0.05) ተመልክቷል፡፡ ይህም የሚያሳየው የገበሬና የነጋዴ ልጅ መሆን በማንበብ ተነሳሽነት ላይ የሚኖራቸው ተጽዕኖ አሉታዊ ሲሆን ሌሎች ስራዎችን መስራት ግን አወንታዊ ተጽዕኖ ይስተዋልበታል፡፡

የህብረ ድህረት ትንተናው እንደሚያሳየው አባቶቻቸው የመንግስት ስራ የሚሰሩ ልጆች እንደማነጻጸሪያ ተወስደው ውጤቱ ሲታይ የመንግስት ሰራተኛ ልጆች የማንበብ ተነሳሽነት ከገበሬ፣ ሌሎች ስራዎችን ከሚሰሩ እንዲሁም ከነጋዴ ልጆች የማንበብ ተነሳሽነት የጎላ ልዩነት አላሳየም፡፡ ማለትም በመንግስት ሰራተኛ ልጆችና በነጋዴ፣ በገበሬና የተለያዩ ስራዎችን በሚሰሩ ልጆች የማንበብ ተነሳሽነት መካከል የጎላ ልዩነት የለም፡፡

ከዚሁ ጋር ተያይዞ የቀረበው የእናት ስራ የሚለው የቤተሰብ ዳራ መለኪያ አምስት አማራጮችን ይዞ የቀረበ ሲሆን እነሱም የቤት እመቤት፣ ገበሬ፣ ነጋዴ፣ የመንግስት ሰራተኛና ሌላ ካለ ይገለጽ የሚሉ ናቸው፡፡ ከቀረቡት አማራጮች በአብዛኛው የተመረጠው የቤት እመቤት እንደማነጻጸሪያ ተወስዶ በድህረት ትንተና የተገኘው ውጤት የሚከተለው ነው፡፡ ገበሬ (B=6.884, t=0.831 $p>0.05$)፣ ነጋዴ (B=8.304, t=1.526 $p>0.05$)፣ የመንግስት ሰራተኛ (B=-0.748, t=-0.150 $p>0.05$)ና ሌሎች (B=5.200, t=1.050 $p>0.05$) በሚል የተመለከተው ትንተና ተላውጦዎቹ በአንብቦ መረዳት ውጤት ላይ ያላቸው ተጽዕኖ በስታስቲክስ ጉልህ ያለመሆኑን ያሳያል፡፡

ከድህረት ትንተናው ውጤት ላይ እንደሚታየው እናቶቻቸው ነጋዴና ገበሬ የሆኑ ልጆች የማንበብ ተነሳሽነት እናቶቻቸው የቤት እመቤት ከሆኑት ጋር ሲነጻጸር አወንታዊ ተጽዕኖ ቢኖረውም ልዩነቱ ግን ጉልህ ያለመሆኑን ውጤቱ ያሳያል፡፡ በሌላ መልኩ የእናቶቻቸው ስራ የመንግስት ሰራተኛና ሌላ (ጽዳት፣ የፋብሪካ ሰራተኛ፣ ቀን ሰራተኛ፣ ግንበኛ) የሆኑት አሉታዊ ተጽዕኖ ቢኖረውም በተመሳሳይ ከቤት እመቤቶች ጋር ሲነጻጸር ግን ጉልህ ያለመሆኑን የቤታ ዋጋቸው ያሳያል፡፡

ከቤተሰብ ዳራ ጋር ተያይዞ የሚነሳው ሌላው ተላውጦ ቤተሰብ ተማሪዎች እንዲያነቡ ምን ያህል ያበረታታል የሚለው ሲሆን በድህረ ትንተናው እንደተመለከተው የተገኘው ውጤት አሉታዊ ሲሆን ተጽዕኖውም ጉልህ ሆኖ ተገኝቷል (B=-3.110, t=-2.336 $p<0.05$)፡፡ ይህም ማለት ቤተሰብ እንዲያነቡ በጣም በገፋፉ ቁጥር የማንበብ ተነሳሽነታቸው እየቀነሰ የሚሄድ ሲሆን የማበረታት ደረጃው በመጠኑ ሲሆን ተነሳሽነታቸው እንደሚጨምር የጥናቱ ውጤት ያሳያል፡፡

በቤት ውስጥ የሚገኙና ተማሪዎች በግላቸው የሚጠቀሙባቸው የተያዩ ቁሳቁሶች የሚለው ተላውጦ በአምስት አማራጮች ተወስኖ የቀረበ ሲሆን በድህረ ትንተናው የተገኘው የእያንዳንዳቸው የቤታ ዋጋና የቲ ስሌት እንደሚከተለው ተመልክቷል፡፡ የመጀመሪያው ተማሪዎች በግል የሚኖሯቸውን መጽሀፍት የሚጠይቅ ሲሆን የድህረት ትንተናው ውጤት አወንታዊና ጉልህ ያለመሆኑን ያሳያል (B=3.248, t=1.641 p>0.05)፡፡ ቀጣዮቹ አማራጮች የማጥኛ ጠረጴዛና ወንበርና የግል ክፍል (B=-2.896, t=-0.747 p>0.05)ና (B=-1.810, t=-0.361 p>0.05) በተከታታይ አሉታዊ ተጽዕኖ ቢኖራቸውም የመተንበይ ድርሻቸው ግን ጉልህ አይደለም፡፡ የግል አልጋ (B=4.434, t=1.139 p>0.05)፣ የግል ሞባይል (B=1.592, t=0.400 p>0.05)፣ የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች (B=3.592, t=0.866 p>0.05) የሚል ውጤት ያሳዩ ሲሆን ተጽዕኖቸውም አወንታዊ ቢሆንም ጉልህ አለመሆኑን የድህረት ትንተና ውጤቱ ያሳያል፡፡

የቤተሰብ ወይም ያሳዳጊዎች የማህበረ ኢኮኖሚያዊ ደረጃ ከቤተሰብ ዳራ ጋር ተያይዞ ከሚነሱት ዋና ተላውጦዎች መካከል አንዱ ሆኖ ይጠቀሳል፡፡ ከተጠኝዎች ነባራዊ ሁኔታ በመነሳት ለዚህ ጥናት የኢኮኖሚ መለኪያ ሆነው የቀረቡት ሶስት ጥያቄዎች የቤተሰብ ወርሀዊ ገቢ፣ ገቢው ከአካባቢው ጋር ሲነጻጸር ያለው ልዩነትና የቀን ምግብ ብዛት በድግግሞሽ የሚሉ ሲሆኑ በድህረት ትንተናው የተገኘው ውጤት የቤተሰብ ወርሀዊ ገቢ (B=0.269, t=0.1377 p>0.05)፣ በቀን ምን ያክል ትመገባለህ/ሽ (B=6.058, t=1.489 p>0.05)ና ገቢያቸው ከአካባቢው ጋር ሲነጻጸር (B=4.029, t=2.267 p<0.05) የሚል ነው፡፡ ውጤቱ እንደሚያሳየው ገቢና በቀን የሚመገቡት ብዛት አወንታዊ ተጽዕኖ ቢኖራቸውም ተጽዕኗቸው ጉልህ አይደለም፡፡ ገቢያቸው ከአካባቢው ጋር ሲነጻጸር የሚለው ግን አወንታዊና ጉልህ ተጽዕኖ እንዳለው የድህረት ትንተናው ያመላክታል፡፡ ማለትም የተማሪዎቹ ቤተሰብ ገቢ ከአካባቢው የተሻለ በሆነ ቁጥር የማንበብ ተነሳሽነታቸው እየጨመረ ይሄዳል ማለት ነው፡፡

ማህበራዊ ጉዳዮችን የያዘው ከቤተሰብ ዳራ ጋር ተያይዞ የሚጠቀሰው ሌላው ተላውጦ ማህበራዊ ተራክቦ ሲሆን እንደሀገሪቱና የተጠኝዎች የአካባቢ ሁኔታ እድር እቁብና ማህበር ተብሎ በሶስት አበይት ክፍሎች ይከፈላል፡፡ ማህበራዊ ጉዳዮች በአብዛኛው አሉታዊ ተጽዕኖ ሲኖራቸው አወንታዊ ተፅዕኖም እንደሚከተለው ታይቷል፤ እድር (B=-3.842, t=0.899 p>0.05) እቁብ (B=-0.941, t=-0.275 p>0.05) ማህበር (B=1.645,

t=0.445 p>0.05) ናቸው፡፡ ከውጤቱ መረዳት እንደሚቻለው እድርና እቁብ አሉታዊ ማህበር ደግሞ አወንታዊ ተጽዕኖ ቢኖራቸውም ተጽዕኖአቸው ጉልህ አይደለም፡፡

ከሰንጠረዥ ሁለት ለመረዳት እንደሚቻለው በዚህ የህብረ ድህረት ትንተና የነጻ ተላውጦዎች የተጋርቶ መጠን መለኪያ $R^2$( coefficient of determination) 0.205 ወይም 20.5% ነው፡፡ ምንም እንኳን እነዚህ ተላውጦዎች 20.5% ያክል ግንኙነት ቢኖራቸውም የጉልህነት ደረጃው ግን ከቤተሰብ ድጋፍ (ማበረታቻ)ና ከገቢ በስተቀር ዝቅተኛ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ስለዚህ ከቤተሰብ ድጋፍና የቤተሰብ ገቢ ከአካባቢ ጋር ሲነጻጸር ከሚለው በስተቀር ሌሎች ተላውጦዎች የማንበብ ተነሳሽነትን የመተንበይ ድርሻቸው ጉልህ አይደለም ማለት ነው፡፡ ከዚህ መነሳት የቤተሰብ ዳራ ተላውጦዎች የሆኑት አብረው የሚኖሩት ሰው፣ የቤተሰብ መዋቅር፣ የወላጅ ወይም የአሳዳጊ የትምህርት ደረጃ፣የተማረ ሰው መኖርና አለመኖር፣ ከፍተኛው የትምህርት ደረጃ፣ የቤተሰብ ማበረታቻ፣ በቤት ውስጥ የሚገኙ የተለያዩ ቁሳቁሶች (መጽሀፍት፣ ማጥኛ ጠረጴዛና ወንበር፣ የግል ክፍል፣ የግል አልጋ፣ ሞባይልና የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች)፣ የቤተሰብ የወር ገቢ፣ ገቢው ከአካባቢው ነዋሪ ጋር ሲነጻጸር፣ በቀን የሚመገቡት ጊዜ በድግግሞሽ፣ የቤተሰብ ማህበራዊ ተሳትፎ (እድር፣ እቁብ፣ ማህበር) በአጠቃላይ ከማንበብ ተነሳሽነት ጋር 20.5% የልይይት መጠን ይጋራሉ፡፡ ወይም በማንበብ ተነሳሽነት ላይ 20.5% አወንታዊና አሉታዊ ተጽዕኖ ያሳድራሉ ማለት ይቻላል፡፡

ከአጠቃላዩ 20.5% ውስጥ ጉልህ ተጽዕኖ የሚያሳድሩት የቤተሰብ ድጋፍና ገቢው ከአካባቢ ጋር ሲነጻጸር 4.57% ይጋራሉ፡፡ የቤተሰብ ድጋፍ የተዛምዶ ክፍል ድርሻው -0.154 ሲሆን በራሱ ተባዝቶ ወደ100 ሲቀየር 2.37% ይወስዳል፡፡ በኢኮኖሚ ስር ከቀረቡት ገቢ ከአካባው ሰው ጋር ሲነጻጸር የሚለው ተላውጦ የተዛምዶ ክፍሉ 0.149 ሲሆን በራሱ ተባዝቶ ወደ 100 ፐርሰንት ሲቀየር 2.62% የልይይት መጠንን ይጋራል፡፡ ቀሪውን ሌሎች ጉልህ ያልሆኑት ተላውጦዎች ይጋሩታል፡፡

በአጠቃላይ በቤተሰብ ዳራ ስር ከቀረቡት ሰላሳሶስት ተላውጠዎች በማንበብ ተነሳሽነት ላይ አሉታዊና አወንታዊ ድርሻ ቢኖራቸውም በማንበብ ተነሳሽነት ላይ ጉልህ ተጽዕኖ እንዳላቸው የተረጋገጡት ግን የቤተሰብ ድጋፍና ገቢው ከአካባው ጋር ሲነጻጸር የሚሉት ብቻ ናቸው፡፡ የቤተሰብ ድጋፍ አሉታዊና ጉልህ ተጽዕኖ ሲኖረው የቤተሰብ ገቢ ከአካባቢው ጋር ሲነጻጸር የሚለው ማህበረ ኢኮኖሚያዊ ተላውጦ ተጽዕኖ ጉልህና

አወንታዊ መሆኑን የድህረት ትንተናው ያመለክታል፡፡ ቀሪዎቹ ሰላሳአንድ ተላውጦዎች የመተንበይ ድርሻቸው ጉልህ ሆኖ አልተገኘም፡፡ በመቀጠል በማንበብ ተነሳሽነትና በአንብቦ መረዳት ችሎታ መካከል ያለው ተዛምዶ ታይቷል፡፡ ዝርዝሩ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

ሶስተኛው የጥናቱ መሰረታዊ ጥያቄ ***በማንበብ ተነሳሽነትና በአንብቦ መረዳት ችሎታ መካከል ያለው ተዛምዶ ምን ይመስላል***? የሚል ሲሆን ይህንን ጥያቄ ለመመለስ የተሰበሰበው መረጃ በፒርሰን ተዛምዶ መወሰኛ /Pearson correlation coefficient/ ተሰልቷል፡፡ ውጤቱም በሰንጠረዥ 3 ላይ እንደሚከተለው ተመልክቷል፡፡

**ሰንጠረዥ 4.3፡-**

**የማንበብ ተነሳሽነትና የአንብቦ መረዳት ችሎታ ተዛምዶ በፒርሰን የተዛምዶ መወሰኛ /Pearson correlation coefficient/**

| ተ.ቁ | የማንበብ ተነሳሽነት | አማካይ | መደበኛ ልይይት | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 | 6 | 7 | 8 | 9 | 10 | 11 | 12 |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | በራስ መተማመን | 5.8287 | 1.79749 | 1 | .410$^{**}$ | .455$^{**}$ | .126 | .353$^{**}$ | -.080 | .300$^{**}$ | .267$^{**}$ | .283$^{**}$ | .266$^{**}$ | .354$^{**}$ | .061 |
| 2 | ተግዳሮት | 8.5926 | 3.09700 | | 1 | .560$^{**}$ | .403$^{**}$ | .531$^{**}$ | .094 | .429$^{**}$ | .407$^{**}$ | .379$^{**}$ | .393$^{**}$ | .455$^{**}$ | -.043 |
| 3 | ጠንካራ ፍላጎት | 9.6944 | 3.73160 | | | 1 | .374$^{**}$ | .613$^{**}$ | .077 | .557$^{**}$ | .495$^{**}$ | .431$^{**}$ | .375$^{**}$ | .477$^{**}$ | .017 |
| 4 | ተሳትፎ | 13.6574 | 4.24847 | | | | 1 | .211$^{**}$ | .222$^{**}$ | .264$^{**}$ | .335$^{**}$ | .273$^{**}$ | .385$^{**}$ | .254$^{**}$ | -.038 |
| 5 | ጥቅም | 2.5139 | 1.16531 | | | | | 1 | .092 | .632$^{**}$ | .504$^{**}$ | .506$^{**}$ | .333$^{**}$ | .548$^{**}$ | .010 |
| 6 | ከስራ ለመራቅ | 10.0694 | 4.05655 | | | | | | 1 | .117 | .155$^{*}$ | .152$^{*}$ | .209$^{**}$ | .139$^{*}$ | .087 |
| 7 | ተወዳዳሪነት | 9.7824 | 3.25989 | | | | | | | 1 | .592$^{**}$ | .619$^{**}$ | .395$^{**}$ | .590$^{**}$ | -.108 |
| 8 | እውቅና | 9.1019 | 3.34647 | | | | | | | | 1 | .567$^{**}$ | .546$^{**}$ | .542$^{**}$ | .064 |
| 9 | ውጤት | 6.5509 | 2.55492 | | | | | | | | | 1 | .492$^{**}$ | .590$^{**}$ | -.094 |
| 10 | ማህራዊ | 14.9306 | 5.14350 | | | | | | | | | | 1 | .543$^{**}$ | .017 |
| 11 | ለመከበር | 8.0787 | 2.95364 | | | | | | | | | | | 1 | -.023 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 12 | የአንብቦ መረዳት ችሎታ | 17.39 | 5.342 | | 1 |

/N=216/ የጉልህነት ደረጃ P*< 0.05

በሰንጠረዥ 3 እንደተመለከተው በፒርሰን የተዛምዶ መወሰኛ መሰረት በተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ችሎታና በማንበብ ተነሳሽነት መካከል የጎላ ተዛምዶ አልታየም፡፡ ሆኖም ግን አስራአንዱ የማንበብ ተነሳሽነት መለኪያዎች እርስበርስ ጉልህ ተዛምዶ አሳይተዋል፡፡ በማንበብ ተግባር በራስ መተማመን ከማንበብ ተግዳሮት፣ ከማንበብ ጠንካራ ፍላጎት፣ ከማንበብ ጥቅም፣ ለመወዳደር ከማንበብ፣ ለእውቅና ከማንበብ፣ ለውጤት ከማንበብ፣ ለማህበራዊ ምክንያቶች ከማንበብና ለመከበር ከማንበብ ጋር ጉልህ ተዛምዶ አሳይቷል፡፡ በተመሳሳይ የማንበብ ተግዳሮት ከማንበብ ጠንካራ ፍላጎት፣ ከማንበብ ተሳትፎ፣ ለጥቅም ከማንበብ፣ ለመወዳደር ከማንበብ፣ ለእውቅና ከማንበብ. ለውጤት ከማንበብ፣ ለማህበራዊ ምክንያቶች ከማንበብና ለመከበር ከማንበብ ጋር ጉልህ ተዛምዶም አሳይቷል፡፡ እንዲሁም በጠንካራ ፍላጎት ማንበብ ለተሳትፎ ከማንበብ፣ ለተጠቃሚነት ከማንበብ፣ ለተወደዳሪነት ከማንበብ፣ ለእውቅና ከማንበብ፣ ለውጤት ከማንበብ፣ ለማህበራዊ ምክንያቶች ከማንበብና ለመከበር ከማንበብ ጋር ጉልህ ተዛምዶ ሲያሳይ ለተሳትፎ ማንበብም ለጥቅም ከማንበብ፣ ከስራ ለመራቅ ከማንበብ፣ ለተወዳዳሪነት ከማንበብ፣ ለእውቅና ከማንበብ፣ ለውጤት ከማንበብ፣ ለማህበራዊ ምክንያቶች ከማንበብና ለመከበር ከማንበብ ጋር ጉልህ ተዛምዶ አሳይቷል፡፡ ለጥቅም ማንበብ ለተወዳዳሪነት ከማንበብ፣ ለእውቅና ከማንበብ፣ ለውጤት ከማንበብ፣ ለማህበራዊ ምክንያቶች ከማንበብ ጋርና ለመከበር ከማንበብ ጋር ጉልህ ተዛምዶ አሳይቷል፡፡ ከስራ ለመሸሽ ማንበብም ለእውቅና ማንበብ፣ ለውጤት ማንበብ፣ ለማህበራዊ ተራክቦ ማንበብና ለመከበር ማንበብ ከሚሉት መለኪያዎች ጋር ጉልህ ተዛምዶ አሳይቷል፡፡ ለተወዳዳሪነት ማንበብ ለእውቅና ከማንበብ፣ ለውጤት ከማንበብ፣ ለማህበራዊ ተራክቦ ከማንበብና ለመከበር ከማንበብ ጋር ጉልህ ተዛምዶ ሲያሳይ ለእውቅና ማንበብም ለውጤት ከማንበብ፣ ለማህበራዊ ጉዳዮች ከማንበብና ለመከበር ከማንበብ ጋር ጉልህ ተዛምዶ አሳይቷል፡፡ ለውጤት በማንበብና፣ ለማህበራዊ ጉዳዮችና ለመከበር በማንበብ መካከል ጉልህ ተዛምዶ የታየ ሲሆን ለማህበራዊ ጉዳዮች በማንበብና ለመከበር በማንበብ መካከልም በስታስቲክስ ጉልህ ተዛምዶ ታይቷል፡፡

በሰንጠረዥ 3 የፒርሰን የተዛምዶ ውጤት እንደሚያሳየው በተማሪዎች የማንበብ ተነሳሽነት ከሚገለጹት ዘርፎች መካከል በራስ ለመተማመን ማንበብ በሚለውና ለተግዳሮት ማንበብ በሚለው መካከል ጉልህ ተዛምዶ /r=0.410, p<0.01/ ታይቷል፡፡ በእነዚህ ሁለት ተላውጦዎች መካከል ያለው ግንኙነት ወይም የሚጋሩት ባህርይ በመቶኛ ሲሰላ 16.81% ነው፡፡ ይህም የሚሳየው ሁለቱ ተላውጦዎች 16.81% ግንኙነት እንዳላቸው ነው፡፡ በራስ ለመተማመን ማንበብና ጠንካራ ፍላጎት ስላለ ማንበብ ሁለቱ ጉልህ ተዛምዶ /r=0.455, p<0.01/ አሳይተዋል፡፡ ተላውጦዎቹ የሚጋሩት የጋራ ባህርይ 20.7% ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ይህ በሁለቱ ተላውጦዎች መካከል ያለውን የተዛምዶ መጠን ያመለክታል፡፡

በሰንጠረዥ 3 እንደተመለከተው በራስ ለመተማመን በማንበብና ለተጠቃሚነት በማንበብ መካከል ጉልህ ተዛምዶ /r=0.353, p<0.01/ ታይቷል፡፡ ይህ ማለት በራስ ለመተማመን ማንበብ በጨመረ ቁጥር የተጠቃሚነት ይጨምራል፡፡ እነዚህ ተላውጦዎች የሚጋሩት የጋራ ባህርይ 12.46% ነው፡፡ በተመሳሳይ በራስ ለመተማመን በማንበብና ለተወዳዳሪነት በማንበብ መካከል ጉልህ ተዛምዶ /r=0.300, p<0.01/ ታይቷል፡፡ የሁለቱ ተላውጦዎች የተጋርቶ መጠን 9% ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ይህ አሃዝ የግንኙነት ደረጃቸውን ያመለክታል፡፡

በራስ ለመተማመን በማንበብና ለእውቅና በማንበብ መካከል ጉልህ ተዛምዶ /r=0.267, p<0.01/ ታይቷል፡፡ ይህም ማለት ለራስ ያለ ግምትን ከፍ ለማድረግ በተነበበ ቁጥር እውቅናውም ይጨምራል፡፡ የተላውጦዎቹ የተጋርቶ መጠን በመቶኛ 7.13% ነው፡፡ ይህ የሚያሳየው ሁለቱ ተላውጦዎች 7.13% ግንኙነት እንዳላቸው ነው፡፡ በለራስ ያለ ግምትን ከፍ ለማድረግ በማንበብና ለውጤት በማንበብ መካከል ጉልህ ተዛምዶ /r=0.283, p<0.01/ ታይቷል፡፡ እነዚህ ተላውጦዎች የሚጋሩት የጋራ ባህርይ 8.1% ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ይህም በሁለቱ ተላውጦች መካከል ያለውን የተዛምዶ መጠን ያመለክታል፡፡

በራስ ያለግምትን ከፍ ለማድረግ ማንበብና ለማህበራዊ ምክንያቶች ማንበብ በሚለው ተላውጦ መካከል ጉልህ ተዛምዶ /r=0.266, p<0.01/ ታይቷል፡፡ የተላውጦዎቹ የተጋርቶ መጠን 7.07% ነው፡፡ ይህም የሚያሳየው ሁለቱ ተላውጦዎች ግንኙነት እንዳላቸው ነው፡፡ በተመሳሳይ ለራስ ያለ ግምትን ከፍ ለማድረግ በማንበብና ለመከበር በማንበብ መካከል ጉልህ ተዛምዶ /r=0.354, p<0.01/ እንዳለ ከሰንጠረዥ 3 መረዳት

ይቻላል፡፡ የትምህርት አቀባበልና የእውነተኛ ተግባራት የተጋርቶ መጠን 12.53% ነው፡፡ ይህም በሁለቱ መካከል ያለውን የግንኙነት ደረጃ ያመለክታል፡፡

በሰንጠረዥ 3 እንደተመለከተው በማንበብ ተግዳሮትና በለማንበብ ያለ ጠንካራ ፍላጎት መካከል ጉልህ ተዛምዶ /r=0.560, p<0.01/ አለ፡፡ የሁለቱ ተላውጦዎች የተጋርቶ መጠን 31.36% ነው፡፡ ይህም ሁለቱ ተላውጦዎች 31.36% ግንኙነት አላቸው ማለት ነው፡፡ በተመሳሳይ በማንበብ ተግዳሮትና በማንበብ ተሳተፎ መካከል ጉልህ ተዛምዶ /r=0.403, p<0.01/ ታይቷል፡፡ እነዚህ ተላውጦዎች የሚጋሩት የጋራ ባህርይ 16.24% ነው፡፡ ይህም ማለት ሁለቱ ተላውጦች 16.24% ያህል ግንኙነት አላቸው ማለት ነው፡፡ በማንበብ ተግዳሮትና በተጠቃሚነት በማንበብ መካከልም ጉልህ ተዛምዶ /r=0.531, p<0.01/ አለ፡፡ የማንበብ ተግዳሮትና የለተጠቃሚነት ማንበብ የተጋርቶ መጠን 28.2% ነው፡፡ ይህም በሁለቱ ተላውጦዎች መካከል ያለውን የግንኙነት ደረጃ ያመለክታል፡፡ በማንበብ ተግዳሮትና ለተወዳዳሪነት በማንበብ መካከል ጉልህ ተዛምዶ /r=0.429, p<0.0/ ታይቷል፡፡ በእነዚህ ሁለት ተላውጦዎች ያለው ግንኙነት ወይም የተጋርቶ መጠን 18.40% ነው፡፡ ይህ በመቶኛ የተገለጸ አሃዝ ተላውጦዎቹ የሚጋሩትን የግንኙነት መጠን ያመለክታል፡፡

በሌሎች ተላውጦዎች እንደታየው ሁሉ በማንበብ ተግዳሮትና ለእውቅና በማንበብ መካከል ጉልህ ተዛምዶ /r=0.407, p<0.01/ መኖሩን ሰንጠረዥ 3 ያመለክታል፡፡ የሁለቱ ተላውጦዎች የተጋርቶ መጠን 16.56% ነው፡፡ ይህም ማለት ሁለቱ ተላውጦዎች 16.56% ተዛምዶ አላቸው ማለት ነው፡፡ በተመሳሳይ በማንበብ ተግዳሮትና ለውጤት በማንበብ መካከል ጉልህ ተዛምዶ /r=0.379, p<0.01/ ታይቷል፡፡ በእነዚህ ሁለት ተላውጦዎች መካከል ያለው ግንኙነት ወይም የተጋርቶ መጠን 14.36% ነው፡፡ እንዲሁም በማንበብ ተግዳሮትና ለማህበራዊ ተራክቦ ማንበብ መካከል ጉልህ ተዛምዶ /r=0.393, p<0.01/ ታይቷል፡፡ የተላውጦዎቹ የተጋርቶ መጠን በመቶኛ ሲሰላ 15.44% ነው፡፡ ይህ አሃዝ ተላውጦዎቹ የሚጋሩትን የግንኙነት መጠን ያመለክታል፡፡ በማንበብ ተግዳሮትና ለመከበር በማንበብ መካከልም ጉልህ ተዛምዶ /r=0.455, p<0.01/ ታይቷል፡፡ ተላውጦዎቹ የሚጋሩት የጋራ ባህርይ 20.7% ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ይህም በሁለቱ ተላውጦዎች መካከል ያለውን የተዛምዶ መጠን ያሳያል፡፡

በሰንጠረዡ እንደታየው ጠንካራ ፍላጎት ስላለ በማንበብና ለተሳትፎ በማንበብ መካከል ጉልህ ተዛምዶ /r=0.374, p<0.01/ ታይቷል፡፡ የሁለቱ ተላውጦዎች የተጋርቶ መጠን 13.99% ነው፡፡ በተመሳሳይ  ጠንካራ ፍላጎት ስላለ በማንበብና ለተጠቃሚነት በማንበብ መካከል ጉልህ ተዛምዶ /r=0.613, p<0.01/ ታይቷል፡፡ በእነዚህ ሁለት ተላውጦዎች መካከል ያለው ግንኙነት ወይም የተጋርቶ መጠን 37.58% ነው፡፡ እንዲሁም  ጠንካራ ፍላጎት ስላለ በማንበብና ለተወዳዳሪነት በማንበብ መካከል ጉልህ ተዛምዶ /r=0.557, p<0.01/ ታይቷል፡፡ የተላውጦዎቹ የተጋርቶ መጠን በመቶኛ ሲሰላ 31.02% ነው፡፡ ይህ አሃዝ ተላውጦዎቹ የሚጋሩትን የግንኙነት መጠን ያመለክታል፡፡ ጠንካራ ፍላጎት ስላለ በማንበብና ለእውቅና በማንበብ መካከልም ጉልህ ተዛምዶ /r=0.495, p<0.01/ ታይቷል፡፡ ተላውጦዎቹ የሚጋሩት የጋራ ባህርይ 24.5% ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ይህም በሁለቱ ተላውጦዎች መካከል ያለውን የተዛምዶ መጠን ያሳያል፡፡ በተመሳሳይ  ጠንካራ ፍላጎት ስላለ በማንበብና ለውጤት በማንበብ መካከል ጉልህ ተዛምዶ /r=0.431, p<0.01/ ተመዝግቧል፡፡ የሁለቱ ተላውጦዎች የተጋርቶ መጠን በመቶኛ ሲሰላ 18.58% ነው፡፡ ጠንካራ ፍላጎት ስላለ በማንበብና ለማህበራዊ ጉዳዮች በማንበብ መካከል ጉልህ ተዛምዶ /r=0.375, p<0.01/ ታይቷል፡፡ እነዚህ ተላውጦዎች የሚጋሩት የጋራ ባህርይ 14.06% ነው፡፡ ይህም ሁለቱ ተላውጦዎች 14.06% ግንኙነት እንዳላቸው ያሳያል፡፡ ጠንካራ ፍላጎት ስላለ ማንበብና ለመከበር ማንበብም ጉልህ ተዛምዶ /r=0.477, p<0.01/ አላቸው፡፡ የሁለቱ ተላውጦዎች የተጋርቶ መጠን በመቶኛ ሲሰላ 22.75% ነው፡፡ ይህም በሁለቱ ተላውጦዎች መካከል ያለውን የግንኙነት ደረጃ ያመለክታል፡፡

በሰንጠረዥ 3 እንደተመለከተው  በማንበብ ተሳትፎና ለተጠቃሚነት በማንበብ መካከል ጉልህ ተዛምዶ /r=0.211, p<0.01/ አለ፡፡ የሁለቱ ተላውጦዎች የግንኙነት ደረጃ በመቶኛ ሲሰላ 4.45% ነው፡፡ ለተሳትፎ ማንበብና ከስራ ለመራቅ ማንበብ ጉልህ ተዛምዶ /r=0.222, p<0.01/ አላቸው፡፡ የሁለቱ ተላውጦዎች የተጋርቶ መጠን 4.92% ነው፡፡ ይህም በሁለቱ መካከል ያለውን የግንኙነት ደረጃ ያመለክታል፡፡ በተሳትፎና በተወዳዳሪነት መካከል ጉልህ ተዛምዶ /r=0.264, p<0.01/ ታይቷል፡፡ የተላውጦዎቹ የተጋርቶ መጠን 6.97% ነው፡፡ ይህም የሁለቱን ተላውጦዎች የግንኙነት ደረጃ ያመለክታል፡፡ በተመሳሳይ ለተሳትፎ በማንበብና ለእውቅና በማንበብ መካከል ጉልህ ተዛምዶ /r=0.335, p<0.01/ ታይቷል፡፡ እነዚህ ሁለት ተላውጦዎች የሚጋሩት ባህርይ

በመቶኛ ሲሰላ 11.22% ነው፡፡ ይህም የሚያሳየው ሁለቱ ተላውጦዎች 11.22% ግንኙነት እንዳላቸው ነው፡፡ እንዲሁም በማንበብ ተሳትፎና ለውጤት በማንበብ መካከል ጉልህ ተዛምዶ /r=0.273, p<0.01/ ታይቷል፡፡ ተላውጦዎቹ የሚጋሩት የጋራ ባህርይ 7.45% ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ይህም በሁለቱ ተላውጦዎች መካከል ያለውን የግንኙነት ደረጃ ያመለክታል፡፡ በተመሳሳይ የማንበብ ተሳትፎ ለማህበራዊ ጉዳዮችና ለመከበር ከማንበብ ጋር ጉልህ ተዛምዶ ያሳየ ሲሆን የፒርሰን ውጤቱ /r=0.385, p<0.01/ና /r=0.254, p<0.01/ በተከታታይ ነው፡፡ የተላውጦዎቹ የተጋርቶ መጠን ተሳትፎ ከማህበራዊ ጉዳዮች ጋር 14.82%ና ለመከበር ማንበብ 6.45 % ናቸው፡፡ ይህ አሀዝ የሚያሳየው የተላውጦዎችን የጋራ ባህሪ ነው፡፡

ለጥቅም በማንበብና ለተወዳዳሪነት በማንበብ መካከል ጉልህ ተዛምዶ /r=0.632, p<0.01/ መኖሩን ሰንጠረዥ 3 ያመለክታል፡፡ በሁለቱ ተላውጦዎች መካከል ያለው የተጋርቶ መጠን 39.94% ነው፡፡ ሁለቱ ተላውጦዎች 39.94% ግንኙነት አላቸው ማለት ነው፡፡ በተመሳሳይ ለተጠቃሚነት በማንበብና ለእውቅ በማንበብና መካከል ጉልህ ተዛምዶ /r=0.504, p<0.01/ ታይቷል፡፡ የተላውጦዎቹ የተጋርቶ መጠን 25.4% ሆኖ ተገኝቷል፡፡ እንዲሁም ለተጠቃሚነት በማንበብና ለውጤት በማንበብ መካከል ጉልህ ተዛምዶ /r=0.506, p<0.01/ ታይቷል፡፡ የሁለቱ ተላውጦዎች የጋራ ባህርይ 25.6% ነው፡፡ ይህም በሁለቱ ተላውጦዎች መካከል ያለውን የግንኙነት ደረጃ ያመለክታል፡፡ ለተጠቃሚነት በማንበብና ለማህበራዊ ጉዳዮች በማንበብ መካከል ጉልህ ተዛምዶ /r=0.333, p<0.01/ ታይቷል፡፡ የሁለቱ ተላውጦዎች የጋራ ባህርይ በመቶኛ ሲሰላ 11.08% ነው፡፡ ለመከበር ማንበብም ለጥቅም ከማንበብ ጋር ጉልህ ተዛምዶ /r=0.548, p<0.01/ ያሳየ ሲሆን የተጋርቶ መጠናቸውም 30.03 % ያክል ነው፡፡

በሰንጠረዥ 3 እንደተመለከተው ከስራ ለመሸሽ ማንበብ ለእውቅና ከማንበብ ጋር ጉልህ ተዛምዶ /r=0.155, p<0.01/ አሳይቷል፡፡ የእነዚህ ሁለት ተላውጦዎች የተጋርቶ መጠን 2.4% ነው፡፡ ይህ በመቶኛ የተገለጸ አሀዝ ተላውጦዎቹ የሚጋሩትን የግንኙነት መጠን ያመለክታል፡፡ በተመሳሳይ ከስራ ለመሸሽ በማንበብና ለውጤት በማንበብ መካከል ጉልህ ተዛምዶ /r=0.152, p<0.01/ ታይቷል፡፡ የሁለቱ ተላውጦዎች የተጋርቶ መጠን 2.31% ነው፡፡ እንዲሁም ከስራ ለመሸሽ በማንበብና ለማህበራዊ ጉዳዮች በማንበብ መካከል ጉልህ ተዛምዶ /r=0.209, p<0.01/ ታይቷል፡፡ ተላውጦዎቹ የሚጋሩት የጋራ ባህርይ

40.19% ነው፡፡ ይህም ማለት ተላውጦዎቹ 4.36% ግንኙነት አላቸው፡፡ ለመከበር ማንበብም ከስራ ለመሸሽ ማንበብ ጋር ጉልህ ተዛምዶ /r=0.139, p<0.01/ አሳይቷል፡፡ የግንኙነት ደረጃው 1.93% ነው፡፡

በሰንጠረዥ 3 እንደተመለከተው ለተወዳዳሪነት ማንበብና ለእውቅና ማንበብ ጉልህ ተዛምዶ /r=0.592, p<0.01/ አሳይተዋል፡፡ የሁለቱ ተላውጦዎች የግንኙነት ደረጃ በመቶኛ ሲሰላ 35.05% ነው፡፡ ለተወዳዳሪነት ማንበብና ለውጤት ማንበብ ጉልህ ተዛምዶ /r=0.619, p<0.01/ አላቸው፡፡ የሁለቱ ተላውጦዎች የተጋርቶ መጠን 38.32% ነው፡፡ ይህም በሁለቱ መካከል ያለውን የግንኙነት ደረጃ ያመለክታል፡፡ ለተወዳዳሪነት በማንበብና ለማህበራዊ ጉዳዮች በማንበብ መካከል ጉልህ ተዛምዶ /r=0.395, p<0.01/ ታይቷል፡፡ የተላውጦዎቹ የተጋርቶ መጠን 15.6% ነው፡፡ ይህም የሁለቱን ተላውጦዎች የግንኙነት ደረጃ ያመለክታል፡፡ በተመሳሳይ ለተሳትፎ ለተወዳዳሪነት በማንበብና ለለማህበራዊ ጉዳዮች በማንበብ መካከል ጉልህ ተዛምዶ /r=0.590, p<0.01/ ታይቷል፡፡ እነዚህ ሁለት ተላውጦዎች የሚጋሩት ባህርይ በመቶኛ ሲሰላ 34.81% ነው፡፡ ይህም የሚያሳየው ሁለቱ ተላውጦዎች 34.81% ግንኙነት እንዳላቸው ነው፡፡ እንዲሁም ለተወዳዳሪነት በማንበብና ለመከበር በማንበብ መካከል ጉልህ ተዛምዶ /r=0.139, p<0.01/ ታይቷል፡፡ ተላውጦዎቹ የሚጋሩት የጋራ ባህርይ 1.93% ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ይህም በሁለቱ ተላውጦዎች መካከል ያለውን የግንኙነት ደረጃ ያመለክታል፡፡ በተመሳሳይ ለእውቅና ማንበብ ለውጤት ከማንበብ፣ ለማህበራዊ ጉዳዮችከማንበብና ለመከበር ከማንበብ ጋር ጉልህ ተዛምዶ ያሳየ ሲሆን የፒርሰን ውጤቱ /r=0.567, p<0.01/፣ /r=0.546, p<0.01/ና /r=0.542, p<0.01/ በተከታታይ ነው፡፡ የተላውጦዎቹ የተጋርቶ መጠን እውቅና ከውጤት ጋር 32.15% ከማህበራዊ ጉዳዮች ጋር 29.81%ና ለመከበር ከማንበብ ጋር 29.38% ናቸው፡፡ ይህ አሀዝ የሚያሳየው የተላውጦዎችን የጋራ ባህሪ ነው፡፡

በሌሎች ተላውጦዎች እንደታየው ሁሉ ለውጤት በማንበብና ለማህበራዊ ተራክቦ በማንበብ መካከል ጉልህ ተዛምዶ /r=0.492, p<0.01/ መኖሩን ሰንጠረዥ 3 ያመለክታል፡፡ ለውጤት ማንበብና ለማህበራዊ ጉዳይ ማንበብ ያላቸው የተጋርቶ መጠን 24.21% ነው፡፡ ይህም የሚያሳየው ሁለቱ ተላውጦዎች 24.21% ግንኙነት እንዳላቸው ነው፡፡ በተመሳሳይ ለውጤት በማንበብና ለመከበር በማንበብ መካከል ጉልህ ተዛምዶ

/r=0.590, p<0.01/ ታይቷል፡፡ በሁለቱ ተላውጦዎች መካከል ያለው የግንኙነት ደረጃ በመቶኛ ሲገለጽ 34.81% ነው፡፡ በሰንጠረዥ 3 እንደሰፈረው ለማህበራዊ ጉዳዮች በማንበብና ለመከበር በማንበብ መካከል ጉልህ ተዛምዶ /r=0.543, p<0.01/ ታይቷል፡፡ የሁለቱ ተላውጦዎች የተጋርቶ መጠን 29.48% ነው፡፡ ይህም የሁለቱን ተላውጦዎች የግንኙነት ደረጃ ያመለክታል፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ በሰንጠረዥ 3 እንደተመለከተው ከላይ በቀረቡት ብዙ ተላውጦዎች መካከል ጉልህነት የመታየቱን ያህል ጉልህ ያልሆኑ ተዛምዶዎችም አሉ፡፡ በራስ ለመተማመን ማንበብና ለተሳትፎ ማንበብ አወንታዊ ተዛምዶ /r=0.126, p>0.05/ ቢኖርም ጉልህ ግን አይደለም፡፡ እንዲሁም በራስ ለመተማመን ማንበብ ከስራ ለመሸሽ ከማንበብ ጋር ያለው ተዛምዶ /r=-0.080, p>0.05/ አሉታዊ ቢሆንም ጉልህ አይደለም፡፡ በተመሳሳይ ከስራ ለመሸሽ ከጠንካራ ፍላጎት ስላለ ከማንበብ፣ ከማንበብ ተግዳሮት፣ ለተወዳዳሪነት ከማንበብና ለተጠቃሚነት ከማንበብ ጋር ያለው ተዛምዶ አወንታዊ ቢሆንም ጉልህ ግን አይደለም /r=0.094, p>0.05፣ r=0.077, p>0.05፣ r=0.117, p>0.05ና r=0.092, p>0.05/፡፡

ከላይ ሰንጠረዥ 3ን መሰረት በማድረግ በቀረበው ትንታኔ የማንበብ ተነሳሽነት ዝርዝር ተላውጦዎች እርስበርሳቸው እንዲሁም ከጥገኛ ተለዋዋጩ የአንብቦ መረዳት ችሎታ ጋር ያላቸው ዝምድና፣ የዝምድናቸው የጉልህነት ደረጃ ወይም በመካከላቸው የታየው የባህርይ ግንኙነትና የተጋርቶ መጠን ምን እንደሚመስል ተዳሷል፡፡ በመቀጠል የተማሪዎች የማንበብ ተነሳሽነትና የአንብቦ መረዳት ችሎታ በጾታ ልዩነት ያሳያል? የሚል ጥያቄ የተነሳ ሲሆን በነጠላ የልይየት ትንተና ተሰርቶ የተገኘው ውጤቱ ዝርዝር እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

የዚህ ጥናት አራተኛ መሰረታዊ ጥያቄ ***"የተማሪዎች የማንበብ ተነሳሽነትና የአንብቦ መረዳት ችሎታ ከጾታ አንጻር ልዩነት ያሳያል****?"* የሚል ሲሆን፤ ይህንን ለመመለስም ነጠላ የልይይት ትንተና (one way ANOVA) ተግባራዊ ሆኗል፡፡ ውጤቱም እንደሚከተለው በሰንጠረዥ 5 ቀርቧል::

**ሰንጠረዥ 4.4፡- በሴትና ወንድ ተማሪዎች መካከል የማንበብ ተነሳሽነትና የአንብቦ መረዳት ችሎታ አማካይ ልዩነት ንጽጽር በነጠላ የልይይት ትንተና (one way ANOVA)**

| ተላውጦዎች | ወንድ= 89 | | ሴት= 127 | | የቲ- ዋጋ | የጉልህነት ደረጃ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | አማካይ | መደበኛ ልይይት | አማካይ | መደበኛ ልይይት | | |
| የማንበብ ተነሳሽነት | 99.42 | 25.032 | 98.37 | 21.723 | -2.46 | .816 |
| የአንብቦ መረዳት ችሎታ | 18.45 | 5.983 | 16.65 | 4.728 | -.327 | .002 |

በሰንጠረዥ 4 እንደተመለከተው የወንድ ተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ችሎታ አማካይ ውጤት ከሴት ተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ችሎታ በጉልህ ደረጃ (ቲ= -0.327፣ $p<0.05$) በልጠው ተገኝተዋል፡፡ የወንዶች የአንብቦ መረዳት ችሎታ አማካይ ነጥብ (M=18.45, SD= 5.983) ሲሆን የሴቶቹ ደግሞ (M=16.65, SD= 4.728) ሆኖ ተገኝቷል፡፡

በተመሳሳይ በማንበብ ተነሳሽነትም ወንዶች ከሴቶች የተሻለ ተነሳሽነት እንዳላቸው የነጠላ ትንተናው ያሳያል፡፡ ነገር ግን ልዩነቱ ጉልህ አይደለም፡፡ የወንዶች የማንበብ ተነሳሽነት በአማካይ (M=99.42, SD= 25.032) ሲሆን የሴቶቹ ደግሞ (M=98.37, SD=21.723 ሆኖ ተገኘቷል፡፡ የጉልህነት ደረጃው ((ቲ= -2.46፣ $p>0.05$) በመሆኑ ልዩነቱ ተቀባይነት አይኖረውም፡፡ በአስራአንዱ ዝርዝር መለኪያዎች ሲታይም ልዩነታቸው ጉልህ አለመሆኑን የነጠላ ልይይት ትንተናው ያሳያል፡፡

በአጠቃላይ የተማሪዎች የማንበብ ተነሳሽነት በጾታ ያለው ልዩነት ጉልህ አይደለም ብሎ መደምደም ይቻላል፡፡ ነገር ግን በአንብቦ መረዳት ችሎታ ወንዶች ከሴቶች የተሻለ ውጤት እንዳላቸውና ልዩነታቸውም ጉልህ መሆኑ ውጤቱ አረጋግጧል፡፡ በመሆኑም የሴቶችን የአንብቦ መረዳት ችሎታ ከወንዶች ጋር ተቀራራቢ ለማድረግ የተለያዩ ስልጠናዎችና ድጋፎች መሰጠት አለባቸው፡፡ በመቀጠል የማንበብ ተነሳሽነት በክፍል

ደረጃ ልዩነት እንዳለው ለማረጋገጥ በነጠላ የልይይት ትንተና ተሰርቶ ልዩነቱ በዝርዝር ተመልክቷል፡፡

የዚህ ጥናት አምስተኛ መሰረታዊ ጥያቄ ***"የተማሪዎች የማንበብ ተነሳሽነት ከክፍል ደረጃ አንጻር ልዩነት ያሳያል?"*** የሚል ሲሆን፤ ይህንን ጥያቄ ለመመለስም ነጠላ የልይይት ትንተና (one way ANOVA) ተግባራዊ ሆኗል፡፡ ውጤቱም እንደሚከተለው በሰንጠረዥ አምስት ቀርቧል::

**ሰንጠረዥ 4. 5፡- በተማሪዎች የክፍል ደረጃ መካከል የማንበብ ተነሳሽነት አማካይ ልዩነት ንጽጽር በነጠላ የልይይት ትንተና (one way ANOVA)**

| የክፍል ደረጃ | የተማሪ ቁጥር | አማካይ | መደበኛ | (I) grade | (J) grade | መደበኛ የአማካይ ልዩነት Mean Difference (I-J) | መደበኛ የአማካይ ስህተት (Standared error Mean) | የጉልህነት ደረጃ Sig. | *95% የአስተማማኝነት ልዩነት ደረጃ (confidence interval of the Difference) | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | | | | ዝቅተኛ lower | ከፍተኛ upper |
| 5 | 52 | 98.02 | 30.076 | | 6 | 2.126 | 4.398 | .963 | -9.26 | 13.5 |
| | | | | 5 | 7 | 3.078 | 4.501 | .903 | -8.58 | 14.7 |
| | | | | | 8 | -7.805 | 4.380 | .285 | -19.15 | 3.5 |
| 6 | 56 | 95.89 | 21.644 | | 5 | -2.126 | 4.398 | .963 | -13.52 | 9.2 |
| | | | | 6 | 7 | .952 | 4.421 | .996 | -10.50 | 12.4 |
| | | | | | 8 | -9.932 | 4.297 | .099 | -21.06 | 1.2 |
| 7 | 51 | 94.94 | 20.448 | | 5 | -3.078 | 4.501 | .903 | -14.73 | 8.5 |
| | | | | 7 | 6 | -.952 | 4.421 | .996 | -12.40 | 10.5 |
| | | | | | 8 | -10.883 | 4.402 | .067 | -22.28 | .5 |
| 8 | 57 | 105.82 | 17.816 | | 5 | 7.805 | 4.380 | .285 | -3.54 | 19.1 |
| | | | | 8 | 6 | 9.932 | 4.297 | .099 | -1.20 | 21.0 |
| | | | | | 7 | 10.883 | 4.402 | .067 | -.52 | 22.2 |

የጉልህነት ደረጃ P<0.05

የክፍል ደረጃ በተማሪዎች የማንበብ ተነሳሽነት ላይ ያለውን ተጽዕኖ ለመለየት ነጠላ የልይይት ትንተና ተግባራዊ ተደርጎ የተገኘው ውጤት እንደሚያሳየው በጥናቱ ተሳታፊ በሆኑት የአምስተኛ፣ የስድስተኛ፣ የሰባተኛና የስምንተኛ ክፍል ተማሪዎች መካከል

ጉልህ የሆነ የማንበብ ተነሳሽነት ልዩነት አልታየም፡፡ ወይም የክፍል ደረጃ በማንበብ ተነሳሽነት ላይ ላለው ተጽዕኖ ዝቅተኛ ነው ማለት ይቻላል፡፡

የአምስተኛ ክፍል ተማሪዎች የማንበብ ተነሳሽነት አማካይ ውጤት(M=98.02, SD= 30.076)፣ የስድስተኛ ክፍል ተማሪዎች የማንበብ ተነሳሽነት አማካይ ውጤት(M=95.89, SD= 21.644)፣ የሰባተኛ ክፍል ተማሪዎች የማንበብ ተነሳሽነት አማካይ ውጤት(M=94.94, SD= 20.448)ና የስምንተኛ ክፍል ተማሪዎች የማንበብ ተነሳሽነት አማካይ ውጤት(M=105.82, SD= 17.816) ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በአምስተኛና በስድስተኛና ክፍል ተማሪዎች መካከል የታየው መደበኛ የኣማካይ ልዩነት 2.129 ቢሆንም ልዩነታቸው ግን ጉልህ አይደለም፡፡ በአምስተኛና በሰባተኛ ክፍል ተማሪዎች መካከል የታየው የአማካይ ልዩነት 3.078 ሲሆን በአምስትና በስምንተኛ ክፍል ተማሪዎች መካከል የታየው ልዩነት 7. 807 ሆኖ ቢታይም በሁለቱም መካከል የታየው ልዩነት ጉልህ አይደለም፡፡

በተመሳሳይ በስድስተኛ ክፍልና በሰባተኛ ክፍል መካከል የ0.932፣ በስድስተኛና በስምንተኛ ክፍል መካከል የ9.93ና በሰባተኛና በስምንተኛ ክፍል መካከል የ10.883 ልዩነት የታየ ቢሆንም ጉልህ ሆኖ ባለመገኘቱ ግን የክፍል ደረጃ በተማሪዎች የማንበብ ተነሳሽነት ላይ የሚያደርሰው ተጽዕኖ የለም ወይም ተጽዕኖው ጉልህ አይደለም፡፡ በመቀጠል አይነታዊ በሆነ መንገድ የተተነተነው የመጨረሻው ጥያቄ መልስ የቀረበበት ነው፡፡ ጥያቄው ተማሪዎች የማንበብ ተነሳሽነቴን ያዳብርልኛል ብለው የሚያስቧ ነገሮች ምን ምን ናቸው? የሚለው ሲሆን በክፍት ጥያቄ የተሰበሰበው መረጃ እንደሚከተለው ተቀናብሯል፡፡

ስድስተኛው የጥናቱ መሰረታዊ ጥያቄ ***ተማሪዎች ከቤተሰብ ዳራ ጋር በተያያዘ የማንበብ ተነሳሽነቴንና የአንብቦ መረዳት ችሎታየን ያዳብርልኛል ብለው የሚያስቧቸው ነገሮች ምን ምን ናቸው?*** የሚል ሲሆን ይህንን ጥያቄ ለመመለስ አይነታዊ የመተንተኛ ዘዴ ተግባራዊ ተደርጓል፡፡ ለአተናተን እንዲመች ተመሳሳይ መልስ የመለሱ ሰዎች ባንድ ላይ በመሰብሰብ ተደራጅቶ እንደሚከተለው ተተንትኗል፡፡

ከቤተሰብ ዳራ ጋር ተያይዘው ከቀረቡላቸው ጥያቄዎች ተማሪዎች የማንበብ ተነሳሽነቴን ያዳብሩልኛል ያሏቸው ነገሮች ውስጥ ትምህርታዊ፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ነገሮች በዋናነት ይጠቀሳሉ።

የመጀመሪያውና በአብዛኛው ተማሪ የተጠቀሰው ከትምህርታዊ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ነገሮች ናቸው። ሁሉም የሰጡትን ምላሽ በማዋሀድ ሲታይ በሁለት አበይት ክፍሎች ይከፈላል። አንደኛው በአካባቢው የተማረ ሰው መኖር የሚሰጠውን ጠቀሜታ መሰረት በማድረግ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ በተቃራኒው አለመማር የሚያደርሰውን ጉዳት በማየት ለማንበብ የሚተጉ ናቸው።

በዙሪያ የተማረ ሰው መኖር ሲባል አብዛኛው ተማሪ በአካባቢው ያሉት ሰዎች በመማራቸው ያገኙትን ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ሀገራዊ ጥቅም በመመልከት እኔም ጠንክሬ ባነብ እንደነዚህ ሰዎች መሆን እችላለሁ የሚል አስተሳስብ እንዲያዳብሩ እንደረዳቸው ገልጸዋል። ለዚህም እንደ ሮል ሞዴል የሚያዩት በአብዛኛው የቤተሰባቸውን አባል ነው። አባትና እናት የመጀመሪያውን ድርሻ ሲምስዱ እህት፣ ወንድምና ዘመድ በመቀጠል ይጠቀሳሉ። አልፎ አልፎ ትልልቅ ቦታ የደረሱ የአካባቢ ሰዎችም ልጆች በትምህርታቸው ጠንክረው እንዲሰሩ በተለይም በርትተው በማንበብ አንብቦ የመረዳት ችሎታቸውና የማንበብ ተነሳሽነታቸው ከፍ እንዲል እንደረዳቸው አብራርተዋል።

ከዚሁ ጋር በተያያዘ ነገርግን ከመጀመሪያው ሀሳብ በተለየ የቤተሰቦቻቸው አለመማር ጠንክረው አንብበው የአንብቦ መረዳታ ችሎታቸውን ከፍ እንዳደረገው የገለጹ ተማሪዎችም አሉ። ይህም ማለት ቤተሰቦቻቸው ባለመማራቸው የደረሰባቸውን የኢኮኖሚ ችግር በመመልከት የነሱን አይነት ኑሮ ላለመኖር ጠንክረው ያነባሉ ማለት ነው። እንዲሁም ያልተማሩት ወላጆች ጊዜያቸውን ሙሉ የጉልበት ስራ ሲሰሩ መዋላቸውን በማስተዋል ከዚህ ድካም ለመገላገል ማንበብ እንደሚገባቸው እራሳቸውን አሳምነው የአንብቦ መረዳት ችሎታቸውን ያሳድጋሉ፤ የማንበብ ተነሳሽነታቸውንም ከፍ ያደርጋሉ።

በአጠቃላይ ከሁለቱም ሀሳቦች መረዳት እንደሚቻለው የተማሪዎችን የአንብቦ መረዳት ችሎታ ለማሳደግ የቤተሰብ የትምህርት ደረጃ ከፍተኛ አስተዋጽዖ አለው። መማር

በሚሰጠው በርካታ ጥቅም ወይም አለመማር በሚያመጣው ጉዳት መነሻነት ለማንበብ እንደሚተጉ መረዳት ይቻላል፡፡

ሁለተኛውና በአብዛኛው ተማሪ የተጠቀሰው ሌላው ጉዳይ ማህበረ ኢኮኖሚያዊ ነገሮችን የሚመለከት ነው፡፡ እንደተማሪዎቹ ገለጻ ቤተሰብ ለትምህርት የሚረዱ የተለያዩ መጽሀፍትን፣ መርጃ መሳሪያዎችንና የማጥኛ ወንበርና ጠረጴዛ ባሟሉሏቸው ቁጥር የማንበብ ተነሳሽነታቸው እንደሚጨምር ገልጸዋል፡፡ በተለይም የተለያየ ታሪክ የያዙ የተረት፣ የልቦለድና የእውነተኛ ታሪክ የያዙ መጽሀፍት በተገዙላቸው ቁጥር ታሪኩን ለማንበብ ካላቸው ፍላጎት የተነሳ በርትተው እንደሚያነቡ ያም የማንበብ ተነሳሽነታቸውን እንደሚያዳብርላቸው ያብራራሉ፡፡ በተለይም የማንበብ ተነሳሽነታቸውን እንደሚጨምርላቸው ገልጸዋል፡፡

ከማህበረ ኢኮኖሚያዊ ደረጃ ጋር ተያይዞ የሚጠቀሰው ሌላው ነጥብ የቤተሰቡ ማህበራዊ አኗኗርና ከጎረቤቱ ጋር ያለው ኢኮኖሚያዊ መስተጋብር ሲሆን ይህ ነገር የአንብቦ መረዳታቸውንና የማንበብ ተነሳሽነታውን እንዳዳበረላቸው የገለጹ ተማሪዎች አሉ፡፡ ከማብራሪያቸው መረዳት እንደሚቻለው ከአካባቢው ሰው የተሻለ ለመባል እንዲሁም በሰፈሩ የተሻለ ተማሪ ሆኖ ለመገኘትና በተለያዩ ማህበራዊ ጉዳዮች ላይ በወላጆች ለመከበርና ለመሞገስ ሲባል ጠንክረው እንደሚያነቡ እንዲሁም እንዲህ አይነት ሙገሳዎችን ሲሰሙ የማንበብ ተነሳሽነታቸው እንደሚጨምር ገልጸዋል፡፡

በሶስተኛ ደረጃ የተጠቀሰው የቤተሰብ ማበረታቻ ሲሆን በአብዛኛው ተማሪ የተጠቀሰ ጉዳይ ነው፡፡ የቤተሰብ ድጋፍ ወይም ማበረታቻ በተለያዩ መልኩ የተገለጸ ሲሆን በከፊል ከላይ ከትምህርታዊ ጉዳዮች ከተጠቀሰው ጋር ይመሳሰላል፡፡ ማለትም እንደኔ እንድትሆን ወይም ከኔ የተሻለ እንድትሆን የሚሉ ናቸው፡፡ ሌሎች ማበረታቻዎች ደግሞ ሽልማት ከመሸለም፣ በማስረዳትና የተለያዩ ቁሳቁሶችን በማሟላት የሚገለጹ ናቸው፡፡ ቁሳቁሶች የተባሉት በአብዛኛው ከዝግ ጥያቄው የቀረቡትን የግል መጽሀፍ መኖር፣ የግል ክፍልና አልጋ መኖር፣ የግል ማጥኛ ጠረጴዛና ወንበር መኖርን የሚመለከቱ መልሶች ቀርበዋል፡፡

በአይነታዊ ከተሰበሰቡት መረጃዎች መረዳት እንደሚቻለው የተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ችሎታና የማንበብ ተነሳሽነት ከቤተሰብ የትምህርት ደረጃ፣ የማህበረ

ኢኮኖሚያዊ ደረጃና ድጋፍ ጋር የተዛመደ መሆኑንና የተማሪዎች የማንበብ ተነሳሽነት በአብዛኛው ውጫዊ ተነሳሽነት ላይ ያዘነበለ መሆኑን መረጃው ያሳያል፡፡

በአጠቃላይ በውጤት ትንተናው ስድስት አላማዎች ተነስተው በተለያዩ የስታስቲክስ መተንተኛ ዘዴዎች ተተንትነው ሁሉም መልስ አግኝተዋል፡፡ የመጀመሪያዎቹ ሁለቱ በህብረድህረት ትንተና፣ ቀጣዩ በፒርሰን የተዛምዶ መወሰኛ ቀመር፣ አራተኛውና አምስተኛው በነጠላ የልይየት ትንተና እንዲሁም የመጨረሻው በአይነታዊ መንገድ ተተንተነዋል፡፡ በመቀጠል እነዚህ ውጤቶች ከነማን የምርምር ውጤትና የማንበብ ንድፈሀሳብ ጋር እንደሚጣጣም እንዲሁም እንደሚለያይ የተለያዩ ጥናቶችን በመጥቀስ አጭር ማብራሪያ ቀርቧዋል፡፡

## 4.9. ከሙከራ ጥናቱ የተገኙ ተሞክሮዎች

ከሙከራ ጥናቱ በርካታ ተሞክሮዎች ተገኝተዋል፡፡ የተገኙት አንደኛ ከተጠኝ ተማሪዎች አንጻር፣ ሁለተኛ ከመረጃ መሰብሰቢያ አንጻር፣ ሶስተኛ ከመረጃ መተንተኛ አንጻርና አራተኛ ከመረጃ አሰባበሰብ አንጻር ናቸው፡፡

1. በዚህ የሙከራ ጥናት በተጠኝነት የተመረጡት ተማሪዎች ከአምስተኛ እስከ ስምንተኛ ክፍል የሚገኙ ተማሪዎች ነበሩ፡፡ ይህንን ማድረግ ያስፈለገው በክፍል ደረጃ ያለውን ልዩነት ለማየት ነበር፡፡ ነገር ግን በትንተና ወቅት በአራት የተለያዩ የክፍል ደረጃዎች የሚገኙትን ተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ውጤት ደምሮ መስራት እንደማይቻል ግንዛቤ ስለተገኘና በተናጠል መስራቱ ደግሞ በጣም ሰፊ ስለሚያደርገው ዋናው ጥናት በሁለት የክፍል ደረጃዎች ላይ ብቻ መሰራት እንደሚቻል ልምድ ተገኝቷል፡፡
2. ለሙከራ ጥናቱ አገልግሎት የሰጡ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች የአንብቦ መረዳት ፈተና፣ የቤተሰብ ዳራ የሚለካ መጠይቅና የማንበብ ተነሳሽነትን የሚለካ መጠይቅ ነበሩ፡፡ ነገር ግን የቡድን ውይይት አስፈላጊ እንደሆነ በሙከራ ጥናቱ ሂደት ስለተረጋገጠ በዋናው ጥናት የቡድን ውይይት አገልግሎት ላይ ውሏል፡፡
3. ፈተናው የተሰጠው ከመደበኛው ክፍለ ጊዜ ተቀንሶ ከመምህራን ጋር በመነጋገር ነበር፡፡ ይህም ተማሪዎች ፈተናውን በአግባቡ እንዳይሰሩ አድርጓቸዋል፡፡ ምክንያቱም

አንደኛው በመጀመሪያ አካባቢ ሲሆን ለሚቀጥለው ክፍለ ጊዜ ስለሚጨነቁ ተረጋግተው አይሰሩም፡፡ ወደ መጨረሻ አካባቢ ሲሆን ደግሞ የመድከም ስሜት ይታይባቸው ነበር፡፡ በመሆኑም በዋናው ጥናት በአማርኛ ክፍለ ጊዜ ብቻ ሳይሆን ከሌሎች መምህራንም ጋር በመነጋገር ረጅም ጊዜ ተሰጥቷቸው ተረጋግተው እንዲሰሩ ማድረግ እንደሚገባ ተሞክሮ ተገኝቶበታል፡፡

4. የአንብቦ መረዳት ችሎታና የማንበብ ተነሳሽነት ያሳዩት ተዛምዶ ደካማ ስለሆነ የማንበብ ተነሳሽነት የሚለውን ተላውጦ ማስወጣት እንደሚገባ ግንዛቤ ተገኝቶበታል፡፡
5. ተዘጋጅተው የቀረቡት ምንባቦች ምንም እንኳን መማሪያ መጽሀፉን መሰረት በማድረግ ቢሆንም ልጆቹ አንብበው ለመጨረስ ጊዜ ሲወስድባቸው ተስተውሏል፡፡ በመሆኑም የምንባቡን መጠን ዝቅ ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል፡፡
6. በማስረዳት ሂደቱ ወቅት የተጠኝዎችን መብት ለመጠበቅ ሲባል ፍላጎት የሌላቸው እንዲወጡ የተደረገ ቢሆንም መብታቸውን እንዲጠቀሙ የተነገራቸው ስለምርምሩ አላማና አስፈላጊነት በደንብ ከመገለጹ በፊት በመሆኑ ብዙ ተማሪዎች እንዲያቋርጡ ምክንያት ሆኗል፡፡ ስለዚህ አስቀድሞ ፍላጎታቸውን ከመጠየቅ በፊት ስለምርምሩ አላማና አስፈላጊነት በደንብ ማብራራት ወሳኝ ሆኖ ተገኝቷል፡፡
7. የጥናቱ ተሳታፊ ተማሪዎች ቁጥር ጥናቱ ተጀምሮ እስኪያልቅ በተለያዩ ምክንያቶች እየቀነሰ ስለሚሄድ ይህን ታሳቢ በማድረግ በጥናቱ መጀመሪያ ላይ ብዙ ተማሪዎችን በጥናቱ ማካተትና እንዳያቋርጡም አስፈላጊውን ጥንቃቄ ማድረግ አስፈላጊ መሆኑን ለመረዳት ተችሏል፡፡
8. ከላይ የተገለጹት ተሞክሮዎች በአግባቡ ተቀምረውና ተዘጋጅተው በዋናው ጥናት ተግባራዊ ከተደረጉ ጥናቱ አስተማማኝ በሆነ መንገድ ሊከናወን እንደሚችል ልምድ ተገኝቶበታል፡፡ ስለሆነም እነዚህን ልምዶች በዋናው ጥናት ላይ በአግባቡ ለመተግበር መከናወን ያለባቸው ተግባራት በቂ ዝግጅት ተደረጎባቸው የዋናው ጥናት ተከናውኗል፡፡

# ምዕራፍ አምስት

# የዋናው ጥናት ውጤት ትንተናና ማብራሪያ

## 5.1. መግቢያ

በምዕራፍ ሶስት ለዋና ጥናቱ የተመረጡት ተሳታፊዎች ማንነትና የአመራረጥ ስልት፣ ለዋናው ጥናት መረጃ ለመሰብሰብ ተግባራዊ የተደረጉት የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ብዛት፣ አይነት፣ አዘገጃጀት፣ አቀራረብና አስተማማኝነት እንዲሁም የተገኙት መረጃዎችን ለመተንተን የሚያስፈልጉት የመረጃ መተንተኛ ዘዴዎች ተመርጠው እንዴት እንደሚተገበሩ ተገልጿል፡፡ በዚህ ምዕራፍም የተገኙት መረጃዎች በተመረጡት የትንተና ስልቶች በመሰረታዊ የጥያቄ ቅደም ተከተል መሰረት ተተንትነዋል፡፡ ከትንተናው የተገኙት ውጤቶችም ከዚህ በፊት የተጠኑ ጥናቶችን ውጤትና ንድፈ ሀሳቦች መሰረት በማድረግ ማብራሪያ ተሰጥቷቸዋል፡፡

## 5.2. የዋናው ጥናት የውጤት ትንተና

በአንብቦ መረዳት ችሎታ መለኪያ ፈተና የተሰበሰቡት የፈተና ውጤቶችና በቤተሰብ ዳራና በማንበብ ተነሳሽነት መለኪያ የጽሁፍ መጠይቅ የተገኙት ምላሾች ተሰብስበውና ተጣርተው እንደ የባሕሪያቸውና አይነታቸው ተደራጅተዋል፤ ኮድ ተደርገዋል፡፡ መረጃው ከተጣራና ከተደራጀ በኋላ የመረጃው የውጤት የስርጭት ወጥነት ተሰርቷል፡፡ የተሰበሰበው መረጃ የውጤት ስርጭቱ ወጥ መሆኑ በኮሞግሮቭ (Kolmogorov-Smirnov) ና በሂስቶግራም ስለተረጋገጠ የፓራሜትሪክ ፍተሻ መሰራት የሚችል በመሆኑ የተገኘው መረጃ በፓራሜትሪክ የመፈተሻ ዘዴ በመጠቀም ተተንተኗል፡፡

በመቀጠል በገላጭ እስታትስቲክስ የተማሪዎቹ የወንድና የሴት መጠን በሁለቱም የክፍል ደረጃዎች በመቶኛ ተሰልቷል፡፡ እንዲሁም የጥገኛ ተላውጦዎቹ አማካይና መደበኛ ልይይት እንዲሁም ከፍተኛና ዝቅተኛው ውጤት ተሰልቷል፡፡ በመጨረሻም የመሰረታዊ ጥያቄዎችን መሰረት በማድረግ በቅደም ተከተል እንደ ሚከተለው ተተንትነው

ተብራርተዋል። የተለየ ሁኔታ ሲኖር ሌላ የጉልህነት ደረጃ ካልተገለጸ በስተቀር በሁሉም ትንታኔዎች ለስታትስቲካዊ ስሌቶቹ ፍተሻ የጉልህነት ደረጃ (Level of significance) $p < 0.05$ ተመርጧል። በተጨማሪም በእያንዳንዱ ስታትስቲካዊ ቴስት ፍተሻ የተካሄደው እንደ የመተንተኛ ዘዴው ባህርይ እሙኖቹ (Assumptions) መሟላታቸው ከተረጋገጠ በኋላ ነው። ለዚህ ጥናት በሁለት የክፍል ደረጃ የሚገኙ የ321 (የ151 አምስተኛ ክፍልና 170 ሰባተኛ ክፍል) ተማሪዎች የፈተና ውጤትና የሁለቱም መጠይቆች ምላሽ ተወስዷል። መረጃዎቹ ወደ ትንተና ከመውሰድ በፊት በክፍል ደረጃው የሚገኙ ተማሪዎች የጾታ ተመጣጣኝነት ማወቅ አስፈላጊ በመሆኑ ተመጣጣኝነታቸው በፐርሰንታይል ተሰርቶ እንደሚከተለው በሰንጠረዥ ቀርቧል።

**ሰንጠረዥ 5.1**

***ጾታ በክፍል ደረጃ ያለው ስብጥር ብዛትና መቶኛ ስሌት***

| የክፍል ደረጃ | ጾታ | | |
|---|---|---|---|
| | ወንድ | ሴት | ጠቅላላ ድምር |
| 5 | 78 (51.65%) | 73(48.35%) | 151 (40.04%) |
| 7 | 82 (48.23%) | 88(51.77%) | 170 (52.96 %) |
| **ድምር** | **160 (49.84%)** | **161 (50.16%)** | **321 (100%)** |

በሰንጠረዥ 5.1 እንደሚታየው ሁለቱም የክፍል ደረጃዎች በጾታም ሆነ በጠቅላላ ተሳታፊ ቁጥር የተራራቁ አይደሉም። በጥናቱ 160 ወንድና 161 ሴት እንዲሁም 151 የአምስተኛና 170 የሰባተኛ ክፍል ተማሪዎች በድምሩ 321 ተማሪዎች በጥናቱ ተሳትፈዋል። በጥናቱ የተካተተው ሌላው ተላውጦ የቤተሰብ መዋቅር ነው። የቤተሰብ መዋቅር በአራት የተለያዩ አማራጮች ተወስኖ ቀርቦ የተሰጠው ምላሽ እንደሚከተለው በድግግሞሽና በፐርሰንታይል ቀርቧል።

ሰንጠረዥ 5.2.

**የቤተሰብ መዋቅር በድግግሞሽና በፐርሰንታይል**

| | ከእናት አባት ጋር የሚኖሩ | | ከእናት ጋር የሚኖሩ | | ከአባት ጋር የሚኖሩ | | ከሌሎች ጋር | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | 5ኛ ክፍል | 7ኛ ክፍል | 5ኛ ክፍል | 7ኛ ክፍል | 5ኛ ክፍል | 7ኛ ክፍል | 5ኛ ክፍል | 7ኛ ክፍል |
| **የመላሾች ብዛት** | 99 | 89 | 24 | 38 | 4 | 3 | 23 | 38 |
| **ፐርሰንታይል** | 65.6 | 52.4 | 15.9 | 22.4 | 2.6 | 1.8 | 15.2 | 22.4 |

ሰንጠረዡ እንደሚያሳየው በሁለቱም የክፍል ደረጃዎች አብዛኛው ተማሪ ከእናት አባቱ ጋር የሚኖር (የአምስተኛ ክፍል 65% ሲሆን የሰባተኛ ክፍል 52.4%)፣ ከእናት ጋርና ከተለያዩ ሰዎች ጋር መኖር የሚለው ተከታዩን ደረጃ ይይዛል፡፡ ከአባታቸው ጋር ብቻ የሚኖሩ በጣም ጥቂት የየሚባሉ ናቸው፡፡ አማራጮቹ በዴሚ ተላውጦነት ተመዝግበው በአብዛኛው የተመረጠው ከእናት አባት ጋር መኖር የሚለው ስለሆነ እንደማነጻጸሪያ ተወስዶ የድህረት ትንተናና ተሰርቷል፡፡ በተከታይነት የተነሳው ተላውጠ የቤተሰብ ብዛት የሚለው ተላውጦ ነው፡፡ የቤተሰብ ብዛት በቁጥር የተገለጸ ሲሆን ዝቅተኛው አንድ ከፍተኛው ስምንት ነው፡፡ የአብዛኘው ተማሪ ቤተሰብ 4 (የአምስተኛ ክፍል 26.5%ና የሰባተኛ ክፍል 27.1%) ሆኗል፡፡ ዝርዝሩን በተከታዩ ሰንጠረዥ ይመልከቱት፡፡

**ሰንጠረዥ 5.3**

***የቤተሰብ ብዛት ምላሽ ድግግሞሽና በፐርሰንታይል***

| **ብዛት በቁጥር** | **5ኛ ክፍል** | | **7ኛ ክፍል** | |
|---|---|---|---|---|
| | **ድግግሞሽ** | **ፐርሰንት** | **ድግግሞሽ** | **ፐርሰንት** |
| **1** | 1 | 7 | - | - |
| **2** | 14 | 9.3 | 9 | 5.3 |
| **3** | 10 | 6.6 | 23 | 13.5 |
| **4** | 40 | 26.5 | 46 | 27.1 |
| **5** | 34 | 22.5 | 35 | 20.6 |
| **6** | 27 | 17.9 | 34 | 20 |
| **7** | 14 | 9.3 | 18 | 10.6 |
| **8** | 11 | 7.3 | 5 | 2.9 |
| **ድምር** | 151 | 100 | 170 | 100 |

የቤተሰብ የትምህርት ደረጃ የቤተሰብ ተላውጦ ሆኖ በዚህ ጥናት የተነሳ ነው፡፡ የቤተሰብ የትምህርት ደረጃ በሶስት አማራጮች ተወስኖ ቀረቧል( የአባት የትምህርት ደረጃ፣ የእናት የትምህርት ደረጃና የቤተሰብ የትምህርት ደረጃ)፡፡ የአባት የትምህርት ደረጃና የእናት የትምህርት ደረጃ አምስት አምስት አማራጮች ሲኖራቸው የቤተሰብ የትምህርት ደረጃ አራት አማራጮች አሉት፡፡ እያንዳንዳቸው ያላቸው ምላሽ ድግግሞሽና ፐርሰንታይል እንደሚከተለው በሰንጠረዥ 5.4 ቀርቧል፡፡

**ሰንጠረዥ 5.4.**

***የቤተሰብ የትምህርት ደረጃ ምላሽ በድግግሞሽና በፐርሰንታይል***

| | የአምስተኛ ክፍል | | | | | | የሰባተኛ ክፍል | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | የአባት የት/ት ደረጃ | | የእናት የት/ት ደረጃ | | የቤተሰብ የት/ት ደረጃ | | የአባት የት/ት ደረጃ | | የእናት የት/ት ደረጃ | | የቤተሰብ የት/ት ደረጃ | |
| | ድግግሞሽ | ፐርሰንት | ድግግሞሽ | ፐርሰንት | ድግግ | ፐርሰንት | ድግግሞሽ | ፐርሰንታይል | ድግግሞሽ | ፐርሰንት | ድግግሞሽ | ፐርሰንት |
| **መደበኛ ትምህርት ያልተማረ** | 6 | 4.0 | 15 | 9.9 | - | - | 8 | 4.7 | 73 | 42.9 | - | - |
| **አንደኛ ደረጃ** | 10 | 6.6 | 28 | 18.5 | 14 | 9.3 | 55 | 32.4 | 41 | 24.9 | 51 | 30 |
| **ከፍተኛ ሁለተኛ** | 74 | 49.0 | 72 | 47.7 | 66 | 43.7 | 71 | 41.8 | 30 | 17.6 | 65 | 38.2 |
| **ሰርትፍኬት /ዲፕሎማ** | 49 | 32.5 | 32 | 21.2 | 54 | 35.8 | 25 | 14.7 | 22 | 12.9 | 38 | 22.4 |
| **የመጀመሪያ ዲግሪ** | 12 | 7.9 | 4 | 2.6 | 17 | 11.3 | 11 | 6.5 | 4 | 2.4 | 16 | 9.4 |
| **ድምር** | 151 | 100 | 151 | 100 | 151 | 100 | 170 | 100 | 170 | 100 | 170 | 100 |

ከሰንጠረዡ እንደሚታየው የአምስተኛ ክፍሎችና የሰባተኛ ክፍሎች የአባት የትምህርት ደረጃ አብዛኛው የከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ላይ (የአምስተኛ 49.0%ና የሰባተኛ 41.8%) የሚገኙ ናቸው፡፡ የአባት የትምህርት ደረጃ ከሚለው ተላውጦ ከሰባተኛ ክፍል በቀጣይነት የሚገኘው የአንደኛ ደረጃ የሚለው ሲሆን ከአጠቃላዩ 32.4% ያክል ይወስዳል፡፡ የአምስተኛ ክፍል ደግሞ ሰርትፍኬት ወይም ዲፕሎማ የሚለው በ32.5% ተከታዩን ደረጆ ይዟል፡፡ የመጀመሪያ ዲግሪ በሶስተኛ ደረጃ፣ የአንደኛ ደረጃ የሚለው

በአራተኛነትና መደበኛ ትምህርት ያልተማረ የሚለው አማራጭ ከአባት የትምህርት ደረጃ የመጨረሻውን ፐርሰንት ይሸፍናል፡፡

ከቤተሰብ የትምህርት ደረጃ መለኪያ ሆኖ የቀረበው የእናት የትምህርት ደረጃ በሁለቱ የክፍል ደረጃዎች የተለያየ ምላሽ ተገኝቷል፡፡ በሰባተኛ ክፍል ተማሪዎች የአብዛኞቹ (ከአጠቃለዩ ተማሪ 73ቱ ወይም 42.9%) የተማሪዎች እናቶች መደበኛ ትምህርት ያለተማሩ ናቸው፡፡ የትምህርት ደረጃ እየጨመረ ሲሄድ የእናቶች የትምህርት ደረጃ እየቀነሰ ይሄዳል፡፡ በአምስተኛ ክፍል ከአባት የትምህርት ደረጃ ጋር ተቀራራቢ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ የቤተሰብ የትምህርት ደረጃ ከአባት የትምህርት ደረጃ ተቀራራቢ ውጤት አሳይቷል፡፡ በመሆኑም በትንተናው ወቅት አማካይ ተደርጎ የተወሰደው የአባት የትምህርት ደረጃ ነው፡፡ በቀጣይ የተሰራው የቤተሰብ የስራ ሁኔታ ነው፡፡ የቤተሰብ የስራ ሁኔታ የእናትና የአባት ተብሎ በሁለት ተከፍሎ የተሰራ ነው፡፡ የአባት በአራት አማራጭ የእናት ከአራቱ በተጨማሪየቤት እመቤትን ጨምሮ በአምስት አማራጮች ቀርቦ ከተማሪዎች የተገኘው ምላሽ በድግግሞሽና በፐርሰንታል እንደሚከተለው በሰንጠረዥ 5.5. ቀርቧል፡፡

**ሰንጠረዥ 5.5.**

***የእናትና የአባት ስራ ምላሽ በድግግሞሽና በፐርሰንታይል***

| | **የአባት ስራ** | | **ድግግሞሽ** | **ፐርሰንት** | **የእናት ስራ** | | **ድግግሞሽ** | **ፐርሰንት** |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | **ገበሬ** | 5ኛ | 32 | 21.2 | **የቤት እመቤት** | 5ኛ | 90 | 59.6 |
| | | 7ኛ | 45 | 26.5 | | 7ኛ | 120 | 70.6 |
| 2 | **ነጋዴ** | 5ኛ | 47 | 31.1 | **ገበሬ** | 5ኛ | 8 | 5.3 |
| | | 7ኛ | 42 | 24.7 | | 7ኛ | 5 | 29 |
| 3 | **የመንግስት ሰራተኛ** | 5ኛ | 20 | 13.2 | **ነጋዴ** | 5ኛ | 15 | 9.9 |
| | | 7ኛ | 32 | 18.8 | | 7ኛ | 17 | 10.5 |
| 4 | **ሌላ** | 5ኛ | 51 | 33.8 | **የመንግስት ሰራተኛ** | 5ኛ | 17 | 11.3 |
| | | 7ኛ | 50 | 29.4 | | 7ኛ | 10 | 5.9 |
| 5 | | | | | **ሌላ** | 5ኛ | 20 | 13.2 |
| | | | | | | 7ኛ | 15 | 8.8 |

የቤተሰብ ስራ እንደ ቤተሰብ መዋቅር በዱሚ ተላውጦ የተመዘገበ ነው፡፡ በመሆኑም ከአባት ስራ በብዛት የተመረጠው ልዩ ልዩ ስራዎች (ከአምስተኛ ክፍል 51/33.8%ና ከሰባተኛ ክፍል 50/29.4%) ነው፡፡ ከእናት ስራ የቤት እመቤት ከፍተኛ ምላሽ አግኝቷል (ከአምስተኛ ክፍል 90/ 59.6%ና ከሰባተኛ ክፍል 120/70%)፡፡ በመሆኑም በህብረ ድህረት ትንተና መሰረት በብዛት የተመረጡት እንደማነጻጸሪያ ተወስደው መሰራት ስላለባቸው ከአባት ልዩ ልዩ ስራዎችና ከእናት ስራ የቤት እመቤት ማነጻጸሪያ ተሰርተዋል፡፡ በቀጣይነት የቤት ውስጥ ግብዓት የሚለው ተላውጦ ቀርቧል፡፡

**ሰንጠረዥ 5.6.**

***የቤት ውስጥ ግብዓት ምላሽ በድግግሞሽና በፐርሰንታል***

| | 5ኛ ክፍል | | | | 7ኛ ክፍል | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | አዎ | | የለም | | አዎ | | የለም | |
| | ድግግሞሽ | ፐርሰንት | ድግግሞሽ | ፐርሰንት | ድግግሞሽ | ፐርሰንት | ድግግሞሽ | ፐርሰንት |
| የግል መጻጎፍት | 63 | 41.7 | 88 | 58.3 | 86 | 50.6 | 84 | 49.4 |
| የማጥኛ ጠረጴዛና ወንበር | 57 | 37.7 | 94 | 62.3 | 89 | 52.4 | 81 | 47.6 |
| የግል ክፍል | 20 | 13.2 | 131 | 86.8 | 36 | 21.2 | 134 | 78.8 |
| የግል አልጋ | 43 | 28.5 | 108 | 71.5 | 66 | 38.8 | 103 | 60.6 |
| የት/ት መሳሪያዎች | 66 | 43.7 | 83 | 55.0 | 89 | 52.4 | 81 | 47.6 |

የቤት ውስጥ ግብዓት መለኪያ ሆነው የቀረቡት የግል መጻህፍት መኖር፣ የማጥኛ ጠረጴዛና ወንበር መኖር፣ የግል ክፍል፣ የግል አልጋና የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች መኖር ናቸው፡፡ የአምስተኛ ክፍል ተማሪዎች ምላሽ ሲታይ በሁሉም አማራጮች ከ50% በላይ የለኝም የሚል ምላሽ ተሰጥቷል፡፡ በሰባተኛ ክፍሎች የግል አልጋ መኖርና የግል ክፍል መኖር በሚለው የለኝም የሚለው ምላሽ ከግማሽ በላይ ሆኖ ሲገኝ የግል መጽሀፍት መኖር (50.6%)፣ የማጥኛ ጠረጴዛና ወንበር መኖር(52.4%) ና የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች መኖር (52.4 )በሚሉት ከግማሽ ፐርሰንት በላይ የሚሆኑ ተማሪዎቸ አለኝ ብለዋል፡፡ በቀጣይነት የቤተሰብ የኢኮኖሚ ደረጃ መለኪያ የሆኑት ወርሀዊ ገቢና ገቢ ከአካባቢ ጋር ሲነጻጸር የሚሉት ተላውጦዎች የተሰጣቸው ምላሽ መሰረት በድግግሞሽና በፐርሰንታል ያላቸው ነጥብ በሰንጠረዥ 5.7 ቀርቧል፡፡

**ሰንጠረዥ 5.7**

***የቤተሰብ የኢኮኖሚ ደረጃ በድግግሞሽና በፐርሰንታይል***

| | 5ኛ ክፍል | | 7ኛ ክፍል | |
|---|---|---|---|---|
| | **ድግግሞሽ** | **ፐርሰንት** | **ድግግሞሽ** | **ፐርሰንት** |
| **ከ1000 ብር በታች** | 12 | 7.9 | 7 | 4.1 |
| **ከ 1000 -3000 ብር** | 27 | 17.9 | 67 | 39.4 |
| **ከ3000- 5000 ብር** | 69 | 45.7 | 38 | 22.4 |
| **ከ 5000- 10000 ብር** | 30 | 19.9 | 37 | 21.8 |
| **ከ 10000 በላይ** | 13 | 8.6 | 21 | 12.4 |
| ***ገቢ ከአካባቢ ጋር ሲነጻጸር*** | | | | |
| **ከፍተኛ** | 22 | 14.6 | 18 | 10.6 |
| **ተመሳሳይ** | 104 | 68.9 | 51 | 30.0 |
| **ዝቅተኛ** | 25 | 16.6 | 101 | 59.4 |

የቤተሰብ የኢኮኖሚ መለኪያ የሆነው ወርሃዊ ገቢ በአምስት አማራጮች ቀርቦ አብዛኛው ወላጅ መካከለኛ ገቢ እንዳለው ከተማሪዎች ምላሽ መረዳት ይቻላል፡፡ ከምስተኛ ክፍል ወላጆች 45.7% ና ከሰባተኛ ክፍል 22.4% ያህሉ ከ3000- 5000 ብር በወር የሚያገኙ ሲሆን ከሰባተኛ ክፍል 39.4% ከአምስተኛ ክፍል ደግሞ 17.9% ያህሉ ከ100- 3000 ብር ገቢ ያላቸው ናቸው፡፡ ገቢ ከአካባቢው ነዋሪ ጋር ሲነጻጸር የሚለው የቤተሰብ የኢኮኖሚ መለኪያ ከአምስተኛ ክፍል 68.9% ያህሉ ተመሳሳይ ነው የሚል ምላሽ ሲሰጡ ከሰባተኛ ክፍል 30% ያህሉ ተመሳሳይ 59.4% ያህሉ ዝቅተኛ የሚል ምላሽ ሰጥተዋል፡፡

በሰንጠረዥ 5.8 የቤተሰብ ማህበራዊ ደረጃ የሚለው ተላውጦ ምላሽ በድግግሞሽና በፐርሰንታይል ቀርቧል፡፡ በዚህ ጥናት የቤተሰብ ማህበራዊ ደረጃ መለኪያ ሆነው የቀረቡት ወላጅ ከትምህርት ቤት ጋር በሚያደርጋቸው ተሳትፎዎች መሰረት በማድረግ ነው፡፡ እነሱም በወላጅ ስብሰባ መገኘት፣ በልማት ኮሚቴነት መሳተፍ እንዲሁም በዲሲፒሊን ኮሚቴነት መሳተፍ ናቸው፡፡ የጥያቄ አቀራረቡ አዎና የለም በሚሉ ምላሾች መሰረት ነው፡፡

በሶስት ጥያቄዎች የቀረበው የቤተሰብ ማህበራዊ ተሳትፎ በትምህርት ቤት ውስጥ ከሚለወ በትምህርት ቤት የወላጅ ስብሰባ መገኘት ብዙ ምላሹ አዎ የሚል ነው

(ከአምስተኛ ክፍል 88.1%ና ከሰባተኛ ክፍል 92.9%)፡፡ በትምህርት ቤት የልማት ጉዳዮች መሳተፍና በዲሲፒሊን ኮሚቴነት መሳተፍ የሚሉት በአብዛኛው የለም የሚል ምላሽ ተሰጥቷቸዋል፡፡ የእያንዳንዳቸው ድግግሞሽና ፐርንታይል በሰንጠረዝ 5.8 ቀርቧል፡፡

**ሰንጠረዝ 5.8.**

***የቤተሰብ ማህበራዊ ደረጃ በድግግሞሽና ፐርሰንታይል***

| | 5ኛ ክፍል | | | | 7ኛ ክፍል | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | አዎ | | የለም | | አዎ | | የለም | |
| | ድግግ ሞሽ | ፐርሰ ንት | ድግግ ሞሽ | ፐር ሰንት | ድግግ ሞሽ | ፐር ሰንት | ድግግ ሞሽ | ፐርሰን ት |
| የወላጅ ስብሰባ | 133 | 88.1 | 18 | 11.9 | 158 | 92.9 | 12 | 7.1 |
| በት/ት የልማት ጉዳዮች | 35 | 23.2 | 116 | 76.8 | 61 | 35.9 | 109 | 64.1 |
| የዲሲፒሊን ኮሞቴ | 18 | 11.9 | 133 | 88.1 | 15 | 8.8 | 155 | 91.2 |

ወደ ዋናው የትንተና ክፍል ከመገባቱ በፊት በገላጭ ስታትስቲክስ መታየት የሚገባው ሌላው ነጥብ የጥገኛ ተላውጦዎቹ አማካይና መደበኛ ልይይት በመሆኑ በዚህ ጥናት የታየው ጥገኛ ተላውጦ ፈተና አጠቃላይና ዝርዝር ነጥብ እንደሚከተለው በሰንጠረዥ አምስት ነጥብ ዘጠኝ ላይ ቀርቧል፡፡

**ሰንጠረዥ 5.9.**

***የተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ችሎታ አማካይ በክፍል ደረጃና በጾታ***

| የክፍል ደረጃ | ጾታ | የናሙና ብዛት | ከፍተኛ | ዝቅተኛ | አማካይ | መደበኛ ልይይት |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 5ኛ ክፍል | ወ | 78 | 29 | 15 | 22.51 | 2.855 |
| | ሴ | 73 | 30 | 14 | 21.63 | 3.545 |
| | ድ | 151 | 30 | 14 | 22.09 | 3.227 |
| 7ኛ ክፍል | ወ | 82 | 25 | 10 | 17.774 | 3.307 |
| | ሴ | 88 | 25 | 10 | 17.06 | 4.092 |
| | ድምር | 170 | 25 | 10 | 17.39 | 3.739 |

ሰንጠረዥ 5.9 በሁለቱም የክፍል ደረጃዎች የአንብቦ መረዳት ችሎታ አማካይና መደበኛ ልይይት በሁለቱም ጾታዎች ላይ የተመለከተውን ይመስላል፡፡ ይህ ውጤትም አስተማማኝነቱ፣ ውጤት ስርጭት ወጥነቱና ትክክለኝነቱ ተረጋግጦ በመጨረሻ ለትንተና የዋለው የመጨረሻ ውጤት ነው፡፡ የእያንዳንዱ ተማሪ ተናጠላዊ የአንብቦ መረዳት ውጤትና የማንበብ ችሎታ ድምር ውጤት አባሪ 1.5ን ይመልከቱ፡፡ በሁለተኛነት የተነሳው ጥገኛ ተላውጦ የማንበብ ተነሳሽነት በክፍል ደረጃና በጾታ የታየው አማካይ ነጥብና መደበኛ ልይይት በሰንጠረዥ 12 ላይ ቀርቧል፡፡

በሰንጠረዡ በተገለጸው ሁኔታ የተማሪዎቹ የጾታ ስብጥር የጎላ ልዩነት እንደሌላቸው ከተረጋገጠ በኂላ የጥገኛ ተላውጦዎቹ (የአንብቦ መረዳት ችሎታና የማንበብ ተነሳሽነት) አማካኝ ነጥብና መደበኛ ልይይት በጾታና በክፍል ደረጃ ተገልጿል፡፡ በመቀጠል የተደረገው የተሰበሰበው መረጃ የተነሱትን ጥያቄዎች መሰረት በማድረግ የመጀመሪያውና ሁለተኛው በህብረ ድህረት ትንተና፣ ሶስተኛው በፒርሰን የተዛምዶ መወሰኛ ቀመርና በነጻ ናሙና ቲ-ቴስት መሰራት መቻሉን ለማረጋገጥ የተለያዩ እሙኖች ተረጋግጠዋል (ዝርዝሩን 3.7 ላይ ይመልከቱ)፡፡ በመጨረሻም የጥናቱ መሰረታዊ ጥያቄዎችን ለመመለስ የተደረገው የውጤት ትንተና የሚከተለውን ይመስላል፡፡

የጥናቱ የመጀመሪያ መሰረታዊ ጥያቄ **"የቤተሰብ ዳራ የአንብቦ መረዳት ችሎታን የመተንበይ ድርሻው ምን ያክል ነው?"** የሚል ሲሆን ይህን ጥያቄ ለመፈተሽ የህብረ ድህረት ትንተና (Multiple Regression Analysis) ተግባራዊ ተደርጓል፡፡ የህብረ ድህረት ትንተና ተግባራዊ የተደረገው የቤተሰብ ዳራ የአንብቦ መረዳት ችሎታን የመተንበይ ድርሻ ለመለካት የሚያስችል ተገቢ መተንተኛ ዘዴ በመሆኑ ነው፡፡

ትንተናው በሁለት የተለያዩ ክፍሎች በመክፈል ተሰርቷል፡፡ ምክንያቱም በዚህ ጥናት የተካተቱት ተሳታፊዎች ከሁለት የተለያየ የክፍል ደረጃ (ከአምስተኛና ከሰባተኛ) የመጡ በመሆናቸው የአንብቦ መረዳት ችሎታቸውን ለመለካት የተዘጋጀው የተለያየ ፈተና ነው (ዝርዝሩ በምዕራፍ ሶስት 3.4.2 ላይ ይመልከቱ)፡፡ በመሆኑም በተለያየ የመረጃ መሰብሰቢያ ተሰብስቦ የተገኘውን ውጤት አንድ ላይ ከመስራት ይልቅ በክፍል ደረጃ ከፋፍሎ መስራት ተገቢ በመሆኑ በተናጠል ተሰርተዋል፡፡

ሰንጠረዥ 5.10

*የቤተሰብ ዳራ ለአንብቦ መረዳት ችሎታ ያለው አስተዋጽኦና የጉልህነት ደረጃ በህብረ ድህረት ትንተና (የአምስተኛ ክፍል)*

| ሞዴል | መደበኛ ያልሆነ የቤታ ዋጋ | መደበኛ የአማካይ ስህተት | መደበኛ የሆነ የቤታ ዋጋ | ቲ ስሌት | የጉልህነት ደረጃ. |
|---|---|---|---|---|---|
| (የጋራ) | 10.945 | .845 | | 12.956 | .000 |
| ከአባት ጋር ብቻ | .018 | .370 | .001 | .050 | .960 |
| ከእናት ጋር ብቻ | -.086 | .252 | -.010 | -.342 | .733 |
| ከተለያዩ ሰዎች ጋር | -.051 | .228 | -.006 | -.223 | .824 |
| የቤተሰብ መጠን | .002 | .054 | .001 | .032 | .975 |
| የአባት የትምህርት ደረጃ | 1.415 | .193 | .382* | 7.349 | .000 |
| የአባት ስራ ገበሬ | .063 | .217 | .008 | .289 | .773 |
| የአባት ስራ ነጋዴ | -.031 | .200 | -.004 | -.154 | .878 |
| የአባት ስራ የመንግስት ሰራተኛ | .060 | .285 | .006 | .210 | .834 |
| የእናት ስራ ገበሬ | -.129 | .375 | -.009 | -.345 | .731 |
| የእናት ስራ ነጋዴ | .210 | .266 | .020 | .789 | .431 |
| የእናት ሰራ የመንግስት ሰራተኛ | .125 | .289 | .012 | .433 | .666 |
| የእናት ስራ የተለያዩ የግል ስራዎች | -.200 | .261 | -.021 | -.767 | .444 |
| ቁሳ1. መጽሀፍት | -.069 | .178 | -.011 | -.388 | .698 |
| ቁሳ2. ጠረጴዛና ወንበር | .025 | .173 | .004 | .143 | .887 |
| ቁሳ 3. የግል ክፍል | -.161 | .257 | -.017 | -.627 | .532 |
| ቁሳ4. የግል አልጋ | .365 | .201 | .051 | 1.811 | .072 |
| ቁሳ5. የት/ት መሳሪያዎች | .101 | .161 | .016 | .628 | .531 |
| የቤተሰብ የኢኮኖሚ ደረጃ | 1.579 | .190 | .500* | 8.291 | .000 |
| የቤተሰብ ገቢ | .688 | .258 | .119* | 2.667 | .009 |

$p$**<0.05**

**ጥገኛ ተላውጦ:- የፈተና ውጤት (5ኛ ክፍል)**

ከላይ በሰንጠረዥ 13 የሰፈረው የህብረ ድህረት ትንተና ውጤት እንደ ሚያሳየው የቤተሰብ ዳራ ዝርዝር ተላውጦዎቹ የቤተሰብ የትምህርት ደረጃ፣ የቤተሰብ ብዛት፣ የቤተሰብ መዋቅር፣ የቤተሰብ የስራ ሁኔታ፣ የቤተሰብ የኢኮኖሚ ደረጃ፣ የቤት ውስጥ ግብዓት፣ የቤተሰብ ገቢና ቤተሰብ በትምህርት ቤቱ ማህበራዊ እንቅስቃሴ ላይ ያላቸው

ተሳትፎ በአጠቃላይ በአንብቦ መረዳት ችሎታ ላይ የሚያበረክቱት አስተዋጽኦ ($F$= 84.982, $p$< 0.05) ጉልህ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ የቤተሰብ ዳራ ተላውጦዎች እያንዳንዳቸው ያላቸው ተናጠላዊ አስተዋጽዖ የተለያየ በመሆኑ ዝርዝሩ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

ከቤተሰብ ዳራ ዝርዝር ተላውጦዎች የአምስተኛ ክፍል የአንብቦ መረዳት ችሎታን በከፍተኛ ደረጃ ከሚተነብዩት ተላውጦዎች የአባት የትምህርት ደረጃ፣ የቤተሰብ የኢኮኖሚ ደረጃ መለኪያ የሆኑት የቤተሰብ ገቢና ገቢው ከአካባቢው ጋር ሲነጻጸር ናቸው፡፡ የአባት የትምህርት ደረጃ ($ß$= 0.382, $t$= 7.349, $p$< 0.05) በሚል የተመለከተው ትንተና የተላውጦው የተጽዕኖ መጠን ጉልህና አዎንታዊ መሆኑን ያሳያል፡፡ ይህም ማለት የአባት የትምህርት ደረጃ እየጨመረ በሄደ ቁጥር የተማሪዎችን የአንብቦ መረዳት ችሎታ እየጨመረው ይሄዳል ማለት ነው፡፡ በሌላ አገላለጽ በአጠቃላይ ከተዘረዘሩት የቤተሰብ ዳራ ተላውጦዎች የመተንበይ ድርሻ በሁለተኛ ደረጃ ከፍተኛና ልዩ አስተዋጽዖ ያለው የአባት የትምህርት ደረጃ ነው፡፡ በአንደኛና በሶስተኛ ደረጃ የአንብቦ መረዳት ችሎታን የሚተነብዩት የቤተሰብ የኢኮኖሚ ደረጃን የሚለኩት ወርሀዊ ገቢና የገቢ ሁኔታ ከአካባቢው ጋር ሲነጻጸር የሚሉት ተላውጦዎች ናቸው፡፡ ከቤተሰብ የኢኮኖሚ ደረጃ ወርሀዊ ገቢ የሚለው ($ß$= 0.5, $t$=8.291, $p$< 0.05) ና ገቢ ከአካባቢ ጋር ሲነጻጸር ($ß$= 0.119, $t$=2.667, $p$<0.05) በሚል በሰንጠረዥ 13 ላይ የተመለከተው ትንተና ተላውጦዎቹ በአንብቦ መረዳት ላይ ያላቸው ተጽዕኖ በስታትስቲክስ ጉልህና አወንታዊ መሆኑን ያሳያል፡፡ በተለይም ወርሀዊ ገቢ ከተዘረዘሩት የቤተሰብ ዳራ ተላውጦዎች መካከል አምሳ ፐርሰንቱን በመውሰድ በጣም ከፍተኛ አስተዋጽዖ ያበረክታል፡፡

የቤታ ዋጋው ($ß$= 0.5) እንደሚያሳየው ከአጠቃላዩ ሀያሁለት ተላውጦዎች ጉልህና በጣም ከፍተኛ አስተዋጽዖ ያለው የቤተሰብ ወርሀዊ ገቢ ነው፡፡ በተመሳሳይ ጉልህ አስተዋጽዖ ያለው ከኢኮኖሚ ስር የሚጠቀሰው የቤተሰብ ገቢ ከአካባቢ ጋር ሲነጻጸር ሲሆን የቤታ ዋጋው ($ß$= 0.119) ከሌሎች ጋር ሲወዳደር በሶስተኛ ደረጃ በመገኘት የራሱን አስተዋጽዖ ያበረክታል፡፡ የ ፒ ዋጋውም ከ0.05 በታች መሆኑ ጉልህነቱ ተቀባይነት እንዲያገኝ ያደርገዋል፡፡

የቤተሰብ መዋቅር፣ የአባትና የእናት ስራ፣ የቤት ውስጥ ግብዓትና የቤተሰብ ማህበራዊ ደረጃ ያላቸው አስተዋጽዖ ዝቅተኛ እንዲሁም ጉልህ ያለመሆኑን የድህረት ትንተና ውጤቱ ያሳያል፡፡ በዴሚ ተላውጦ የተመዘገቡት የቤተሰብ መዋቅር ከማን ጋር ትኖራለህ/ሽ የሚለው አብዛኛው ተማሪ ከእናት አባት ጋር የሚል ምላሽ በመስጠቱ ከዛ ጋር ተነጻጽሮ የቀረቡት ከአባት ጋር ብቻ( *ß* = 0.001, *t*= 0.05, *p*> 0.05)፣ ከእናት ጋር ብቻ (*ß* = -0.01, *t*= -0.342, *p*> 0.05) ና ከሌሎች ዘመዶች ጋር (*ß* = -0.006, *t*= -0.223, *p*> 0.05) በማምጣታቸው በተጽዕኗቸው መካከል ጉልህ ልዩነት እንደሌለው ውጤቱ ያሳያል፡፡ ከቤተሰብ መዋቅር ጋር በተያያዘ የሚነሳው ሌላው ነጥብ የቤተሰብ ቁጥር ሲሆን (*ß*= 0.001, *t*= 0.032, *p*> 0.05) በሚል በሰንጠረዡ ላይ የተመለከተው ትንተና ተጽዕኖው ጉልህ ያለመሆኑን ያሳያል፡፡ በተከታይነት የሚነሳው ሌላው ነጥብ የቤተሰብ የስራ ሁኔታ የሚል ሲሆን የአባት ወይም የወንድ አሳዳጊ ስራና የእናት ወይም የሴት አሳዳጊ ስራ በሚል የሰፈረው ተላውጦ በዴሚ ተላውጦ ተመዝግቦ ከአባት ስራ ልዩ ልዩ ስራዎች የሚለው እንደ ማወዳደሪያ ተወስዶ ገበሬ (*ß* = 0.008, *t*= 0.289, *p*> 0.05)፣ ነጋዴ (*ß* = -0004, *t*= -0.154, *p*> 0.05)ና የመንግስት ሰራተኛ (*ß* = 0.006, *t*= 0.21, *p*> 0.05) በሚል የተመለከተው የድህረት ትንተና ውጤት ተጽዕኗቸው ጉልህ ያለመሆኑን ያሳያል፡፡ የእናት ስራ ከሚለው የብዛኛው የእናቶች ስራ ተብሎ የተመረጠው የቤት እመቤት እንደ ማነጻጸሪያ ተወስዶ ገበሬ (*ß* = -0.009, *t*= -0.345, *p*> 0.05)፣ ነጋዴ (*ß* =0.020, *t*= 0.789, *p*> 0.05)፣ የመንግስት ሰራተኛ ( *ß* = 0.012, *t*= 0.433, *p*> 0.05) ና ልዩ ልዩ ስራዎች (*ß* = -0.021, *t*= -0.767, p> 0.05) የሚል ውጤት ያሳዩ ሲሆን የመተንበይ ድርሻቸው ዝቅተኛ መሆኑን ያመለክታል፡፡

ከኢኮኖሚያዊ ደረጃ ጋር የተገናኙት የቤት ውስጥ ግብዓቶች የግል መጽሀፍት (*ß* =-0.011, *t*=-0.388, *p*>0.05)፣ የማጥኛ ጠረጴዛና ወንበር (*ß* =0.004, *t*=0.143, *p*>0.05)፣ የግል ክፍል (*ß* =-0.017, *t*=-0.627, *p*>0.05)፣ የግል አልጋ (*ß* =0.051, *t*=1.811, *p*>0.05) ና የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች (*ß* =0.016, *t*=0.628, *p*> 0.05) ያሳዩ ሲሆን ወላጆች በትምህርት ቤት ማህበራዊ ጉዳዮች ከሚያደርጉት ተሳትፎ ደግሞ በትምህር ቤት ልማታዊ ጉዳዮች (*ß* = -0.011, *t*=-0.458, *p*> 0.05) ና በተለያዩ የስነምግባር ኮሚቴዎች ላይ (*ß* = -0.002, *t*= -0.069, *p*> 0.05) በመሆኑ ተጽዕኗቸው ጉልህ ያለመሆኑን የድህረት ትንተና ውጤቱ ያሳያል፡፡

ከሰንጠረዥ 13 መረዳት እንደሚቻለው በዚህ የህብረ ድህረት ትንተና የነጻ ተላውጦዎቹ የተጋርቶ መጠን መለኪያ $R^2$ (Coefficient Of Determination) 0.925 ወይም 92.5% ነው፡፡ ማለትም በአጠቃላይ የቤተሰብ ዳራ ተላውጦዎቹ የቤተሰብ መዋቅር፣ የቤተሰብ የትምህርት ደረጃ፣ የቤተሰብ ስራ፣ የቤት ውስጥ ግብዓት፣ የቤተሰብ የኢኮኖሚ ደረጃና የቤተሰብ ማህበራዊ ደረጃ በትምህርት ቤት ውስጥ 92.5% ያክል ግንኙነት አላቸው፡፡ በሌላ አገላለጽ የቤተሰብ መዋቅር፣ የቤተሰብ ቁጥር (አባላት ብዛት)፣ የወላጅ ወይም ያሳዳጊ የትምህርት ደረጃ፣ በቤት ውስጥ የሚገኙ የተለያዩ ቁሳቁሶች (መጽሀፍት፣ ማጥኛ ጠረጴዛና ወንበር፣ የግል ክፍል፣ የግል አልጋና የተለያዩ የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች)፣ የቤተሰብ የወር ገቢ፣ ገቢው ከአካባቢው ጋር ሲነጻጸርና የቤተሰብ ማህበራዊ ተሳትፎ በትምህርት ቤት ውስጥ በአጠቃላይ ከአንብቦ መረዳት ችሎታ ጋር 92.5% የልይይት መጠን ይጋራሉ ማለት ነው፡፡ ከነዚህም ውስጥ ጉልህና ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያላቸው የቤተሰብ ወርሀዊ ገቢ፣ የአባት የትምህርት ደረጃና የቤተሰብ ገቢ ከአካባቢው ጋር ሲነጻጸር በቅደም ተከተል ናቸው፡፡

ጉልህ ተጽዕኖ የሚያሳድሩት የቤተሰብ ወርሀዊ ገቢ፣ የአባት የትምህርት ደረጃና የቤተሰብ ገቢ ከአካባቢው ጋር ሲነጻጸር ከአጠቃላዩ 92.5% ውስጥ 6.56% ያክል ይጋራሉ፡፡ የቤተሰብ ወርሀዊ ገቢ የተዛምዶ ክፍል ድርሻው 0.186 ሲሆን በራሱ ተባዝቶ ወደ 100 ፐርሰንት ሲቀየር 3.5%ይሆናል፡፡ የአባት የትምህርት ደረጃ የተዛምዶ ክፍሉ 0.164 ሲሆን በራሱ ተባዝቶ ወደ መቶ ፐርሰንት ሲቀየር 2.7% እንዲሁም ከመጀመሪያው ተላውጦ ጋር ተያያዥነት ያለው ገቢ ከአካበቢ ጋር ሲነጻጸር የተዛምዶ ድርሻው 0.06 ሲሆን ወደ ፐርሰንት ሲቀየር 0.36% ይሆናል፡፡ በአጠቃላይ 6.56% ያህል የሚጋሩ መሆኑን የተዛምዶ ክፍል ድርሻቸው ያሳያል፡፡ ምክንያቱም የተዛምዶ ክፍል ማለት የእያንዳንዱን ተላውጦ ድርሻ የሚያሳይ በመሆኑ ነው፡፡

በአጠቃላይ በቤተሰብ ዳራ ስር ከቀረቡት ሀያ ሁለት ዝርዝር ተላውጦዎችና ስድስት አበይት ተላውጦዎች በአምስተኛ ክፍል የአንብቦ መረዳት ችሎታ ላይ የመተንበይ ድርሻቸው ጉልህ ሆኖ የተገኘው የአባት የትምህርት ደረጃና የቤተሰብ የኢኮኖሚ ደረጃ መለኪያ የሆኑት ወርሀዊ ገቢና ገቢ ከአካባቢ ጋር ሲነጻጸር ናቸው፡፡ በመቀጠል የሰባተኛ

ክፍል ተማሪዎችን የአንብቦ መረዳት ችሎታ እንደጥገኛ ተላውጦ በመውሰድ የቤተሰብ ዳራ የሚኖረውን የመተንበይ ድርሻ እንደሚከተለው ተብራርቷል፡፡

**ሰንጠረዥ 5.11.**

***የቤተሰብ ዳራ ለአንብቦ መረዳት ችሎታ ያለው አስተዋጽኦና የጉልህነት ደረጃ በህብረድህረት ትንተና (የሰባተኛ ክፍል)***

| ሞዴል | መደበኛ ያልሆነ የቤታ ዋጋ | መደበኛ የአማካይ ስህተት | መደበኛ ሆነ የቤታ ዋጋ | የቲስሴት | የጉልህነት ደረጃ |
|---|---|---|---|---|---|
| (የጋራ) | 4.492 | .989 | | 4.542 | .000 |
| ከአባት ጋር ብቻ | -1.168 | .718 | -.042 | -1.627 | .106 |
| ከእናት ጋር ብቻ | -.481 | .244 | -.054 | -1.970 | .051 |
| ከተለያዩ ሰዎች ጋር | -.470 | .235 | -.053 | -1.998 | .048 |
| የቤተሰብ መጠን | .003 | .068 | .001 | .048 | .962 |
| የአባት የትምህርት ደረጃ | .833 | .174 | .214* | 4.788 | .000 |
| የአባት ስራ ገበሬ | -.020 | .247 | -.002 | -.080 | .936 |
| የአባት ስራ ነጋዴ | -.371 | .254 | -.043 | -1.463 | .146 |
| የመንግስት ሰራተኛ | -.237 | .280 | -.025 | -.844 | .400 |
| የእናት ስራ ገበሬ | -.196 | .537 | -.009 | -.365 | .716 |
| የእናት ስራ ነጋዴ | .112 | .294 | .009 | .379 | .705 |
| የእናት ሰራ የመንግስት ሰራተኛ | -.597 | .382 | -.038 | -1.565 | .120 |
| የእናት ስራ የተለያዩ የግል ስራዎች | .022 | .361 | .002 | .062 | .951 |
| ቁሳ1. መጽሀፍት | -.470 | .910 | -.064 | -.516 | .606 |
| ቁሳ2. ጠረጴዛና ወንበር | -.354 | .663 | -.048 | -.534 | .594 |
| ቁሳ 3. የግል ክፍል | -.156 | .244 | -.017 | -.640 | .523 |
| ቁሳ4. የግል አልጋ | .172 | .203 | .024 | .847 | .398 |
| ቁሳ5. የት/ት መርጃ መሳሪያዎች | .997 | .649 | .135 | 1.536 | .127 |
| የቤተሰብ የኢኮኖሚ ደረጃ | 1.730 | .153 | .528* | 11.315 | .000 |
| የቤተሰብ ገቢ | 1.536 | .205 | .282* | 7.487 | .000 |
| የወላጅ ተሳትፎ 1 | .359 | .366 | .025 | .981 | .328 |
| የወላጅ ተሳትፎ 2 | .257 | .193 | .033 | 1.331 | .185 |
| የወላጅ ተሳትፎ 3 | .467 | .327 | .036 | 1.427 | .156 |

**$p<0.05$**

**ጥገኛ ተላውጦ፡- የፈተና ውጤት (ሰባተኛ ክፍል)**

የድህረት ትንተና ውጤት እንደሚያመለክተው በዝርዝር የቀረቡት የቤተሰብ ዳራ ተላውጦዎቹ በአጠቃላይ በሰባተኛ ክፍል ተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ችሎታ ላይ ያላቸው አስተዋጽዖ ጉልህ ($F$= 87.496, $p$< 0.05) ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ማለትም የቤተሰብ ዳራ በአጠቃላይ የአንብቦ መረዳት ችሎታን ይተነብያል ማለት ነው፡፡ በአምስተኛ ክፍል ተማሪዎች ውጤት ላይ እንደተስተዋለው ሁሉ በዚህኛው የህብረ ድህረት ትንተና ሰንጠረዥ ከቀረቡት የቤተሰብ ዳራ ተላውጦዎች ከፍተኛና ጉልህ አስተዋጽዖ ያለው የቤተሰብ የኢኮኖሚ ደረጃ ነው፡፡

የቤተሰብ የኢኮኖሚ ደረጃ በተለያዩ ሁለት መለኪያዎች የቀረበ ሲሆን የመጀመሪያው የቤተሰብ ወርሀዊ ገቢና ሁለተኛው ገቢው ከአካባቢ ጋር ሲነጻጸር የሚለው ነው፡፡ ሁለቱም መለኪያዎች የአንብቦ መረዳት ችሎታን የመተንበይ ድርሻቸው ከፍተኛና ጉልህ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በቀጣይ የመተንበይ ድርሻው ከፍተኛና ጉልህ ሆኖ የተገኘው የአባት ወይም የወንድ አሳዳጊ የትምህርት ደረጃ ነው፡፡ የቤት ውስጥ ግብዓት በሚለው ስር ከተዘረዘሩት አማራጮች የተለያዩ የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች መኖር የሚለው በአራተኛ ደረጃ ቢገኝም የፒ ዋጋው ግን ከ0.05 በላይ በመሆኑ የመተንበይ ድርሻው ጉልህ አይደለም፡፡

መደበኛ የሆነው የቤታ ዋጋ እንደሚያመለክተው ከአጠቃላዩ የቤተሰብ ዳራ ተላውጦ ከፍተኛውን የመተንበይ ድርሻ የሚወስደው ከቤተሰብ የኢኮኖሚ ደረጃ የሚመደበው ወርሀዊ ገቢ ($ß$ = 0.528, $t$= 11.315, $p$< 0.05) ሲሆን በሁለተኛ ደረጃ የሚነሳው ደግሞ ገቢ ከአካባቢ ጋር ሲነጻጸር የሚለው ($ß$ = 0.282, $t$= 7.487, $p$< 0.05) እንደሆነ የድህረት ትንተናው ውጤት ያሳያል፡፡ ማለትም የቤተሰብ የኢኮኖሚ ደረጃ ከፍ ባለ ቁጥር በተማሪዎቹ የአንብቦ መረዳት ችሎታ ላይ አዎንታዊ ተጽዕኖ ይኖረዋል፤ በተመሳሳይ ዝቅ ባለ ቁጥር ደግሞ አሉታዊ ተጽዕኖ ይኖረዋል ማለት ነው፡፡ ከፍና ዝቅ ማለቱ ብቻ ሳይሆን በአካባቢው ካሉ ጎረቤቶች ጋር በኢኮኖሚ መብለጥና ማነስም አወንታዊና አሉታዊ ተጽዕኖ እንዳለው የድህረት ትንተና ውጤቱ ያሳያል፡፡

በሶስተኛ ደረጃ የተማሪዎችን የአንብቦ መረዳት ችሎታን የሚተነብየው የትምህርት ደረጃ መለኪያ የሆነው የአባት የትምህር ደረጃ ሲሆን ($ß$= 0.214, $t$= 4.788, $p$< 0.05) በሚል

የተመለከተው ትንተና የተላውጦው የተጽዕኖ መጠን ከፍተኛና ጉልህ መሆኑን ያመለክታል፡፡ በአራተኛ ደረጃ የቤታ ዋጋው ከፍተኛ ሆኖ የታየው የቤት ውስጥ ግብዓት ከሚለው ውስጥ በአራተኛ ደረጃ በአማራጭነት የቀረበው የተለያዩ የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች መኖር የሚለው ($ß$ = 0.135, $t$= 1.536, $p$> 0.05) እንደሆነ የድህረት ትንተና ውጤቱ ያሳያል፡፡

ከቤት ውስጥ ግብዓት የተለያዩ የግል መጽሀፍት መኖር ($ß$ = -0.064, $t$= -0.516, $p$> 0.05)፣ የማጥኛ ጠረጴዛና ወንበር መኖር ($ß$ = -0.048, $t$= -0.534, $p$> 0.05) ከቤተሰብ መዋቅር ከእናት ጋር መኖር ($ß$ = -0.054, $t$= -1.97, $p$> 0.05) ና ከዘመድ ጋር መኖር ($ß$= -0.053, $t$= -1.998, p> 0.05) ና ከአባት ጋር መኖር ($ß$= -0.042, $t$= -1.627, $p$> 0.05) እንዲሁም ከአባት ስራ ገበሬ ($ß$= -0.043, $t$= -1.463, $p$> 0.05) ና የመንግስት ሰራተኛ ($ß$= -0.025, $t$= -0.844, $p$> 0.05) በተከታታይ መካከለኛ የቤታ ዋጋ ያሳዩ ተላውጦዎች ናቸው፡፡ ነገር ግን የቤታ ዋጋቸውን ጉልህነት ከ 0.05 በታች ሆኖ በመገኘቱ የመተንበይ ድርሻቸው ጉልህ ነው ማለት አይቻልም፡፡

ቀሪዎቹ ተላውጦዎች ማለትም የእናት ስራ (ገበሬ፣ ነጋዴ፣ የመንግስት ሰራተኛና ልዩ ልዩ ስራዎች) የማህበራዊ ጉዳይ የሆኑት ቤተሰብ በትምህርት ቤት ጉዳዮች የሚያደርጓቸው ተሳትፎዎች (የወላጅ ስብሰባ፣ የትምህርት ቤት ልማትና የዲሲፕሊን ኮሚቴ) ዝቅተኛ የቤታ ዋጋ ያሳዩና ጉልህ ያልሆነ ተጽዕኖ ያላቸው መሆኑ ተስተውሏል፡፡ እንዲሁም የቤተሰብ ቁጥር (ብዛት) ($ß$= 0.001, $t$= 0.048, $p$> 0.05) እጅግ በጣም ትንሽ ተጽዕኖ እንዳሳየ የድህረት ትንተና ውጤቱ ያሳያል፡፡

ከህብረ ድህረት ትንተና ውጤቱ እንደተመለከተው የነጻ ተላውጦዎቹ የተጋርቶ መጠን መለኪያ $R^2$ (Coefficient Of Determination) 0.929 ወይም 92.9% ነው፡፡ ማለትም በአጠቃላይ የቤተሰብ ዳራ ተላውጦዎቹ የቤተሰብ መዋቅር፣ የቤተሰብ የትምህርት ደረጃ፣ የቤተሰብ ስራ፣ የቤት ውስጥ ግብዓት፣ የቤተሰብ የኢኮኖሚ ደረጃና የቤተሰብ ማህበራዊ ደረጃ በትምህርት ቤት ውስጥ 92.9% ያክል ግንኙነት አላቸው፡፡ ወይም ከአንብቦ መረዳት ችሎታ ጋር 92.9% የልይይት መጠን ይጋራሉ፡፡ ከአጠቃላዩ 92.9% የቤታ ዋጋቸው ከፍተኛ የሆኑት የቤተሰብ የኢኮኖሚ ደረጃና የቤተሰብ የትምህርት ደረጃ

10.1% ያክል ይጋራሉ፡፡ ይህ ውጤት የተገኘው የእያንዳንዳቸው የተዛምዶ ክፍል በራሳቸው ተባዝቶ ወደ መቶ ፐርሰንት ሲቀየር ነው፡፡

በአጠቃላይ ከሁለቱም የድህረት ትንተና ውጤት ሰንጠረዦች (ከአምስተኛ ክፍልና ከሰባተኛ ክፍል) የቤተሰብ ዳራ በአጠቃላይ የአንብቦ መረዳት ችሎታን እንደሚተነብይ መረዳት ይቻላል፡፡ ማለትም የቤተሰብ ዳራ የክፍል ደረጃ ልዩነት ሳያመጣበት በሁለቱም የክፍል ደረጃዎች በተቀራራቢ መጠን ተንባይ ተላውጦ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በዝርዝር ከቀረቡት ተላውጦዎች ደግሞ የቤተሰብ የኢኮኖሚ ደረጃ (ወርሀዊ ገቢና ገቢ ከአካባቢው ጋር ሲነጻጸር) እንዲሁም የቤተሰብ የትምህርት ደረጃ የተማሪዎችን የአንብቦ መረዳት ችሎታ የመተንበይ ድርሻቸው ከፍተኛና ጉልህ እንደሆነ የድህረት ውጤቱ ያሳያል፡፡ የአንብቦ መረዳት ችሎታን በከፍተኛ ደረጃ የሚተነብየው የቤተሰብ የኢኮኖሚ ደረጃ ሲሆን በተከታይነት ተንባይ የሆነው የቤተሰብ የትምህርት ደረጃ ነው፡፡ ከሰንጠረዡ የቀረበው የአባት የትምህርት ደረጃ የቤተሰብ የትምህርት ደረጃ ወካይ ሆኖ የቀረበ ነው፡፡ ምክንያቱም በእሙን ፍተሻ ወቅት በሶስቱ የቤተሰብ የትምህርት ደረጃ መለኪዎች የአባት ወይም የወንድ አሳዳጊ የትምህርት ደረጃ፣ በእናት ወይም በሴት አሳዳጊ የትምህርት ደረጃና በቤተሰብ ከፍተኛው የትምህርት ደረጃ መካከል ከ0.7 በላይ ጉልህና ከፍተኛ ተዛምዶ በመታየቱ አማካይ የሆነው የአባት የትምህርት ደረጃ ተወስዶ ድህረት ትንተናው ተሰርቷል፡፡

በሁለተኛ ደረጃ የተነሳው ጥያቄ ***የቤተሰብ ዳራ የአንብቦ መረዳት ችሎታን የመተንበይ ድርሻው በክፍል ደረጃ ልዩነት ያሳያል?*** የሚል ነው፡፡ በጥያቄ አንድ በተሰሩት ሁለቱ የህብረ ድህረት ትንተና ውጤቶች እንደታየው የቤተሰብ በሁለቱም የክፍል ደረጃዎች የመተንበይ ድርሻው ተመሳሳይ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ከዝርዝር የቤተሰብ ዳራ ተላውጦዎች የቤተሰብ የኢኮኖሚ ድርሻና የቤተሰብ የትምህርት ደረጃ መለኪያ የሆነው የአባት የትምህርት ደረጃ ከሌሎች ተላውጦች በተለየ ከፍተኛ የመደበኛ ቤታ ዋጋ በማምጣት ጉልህ ተንባይ ሆነው ተገኝተዋል፡፡

የዚህ ጥናት ሶስተኛ መሰረታዊ ጥያቄ *"የተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ችሎታ ከጾታ አንጻር ልዩነት ያሳያል?"* የሚል ሲሆን፤ ይህንን ለመመለስም የነጻ ናሙና ቲ ቴስት ተግባራዊ ሆኗል፡፡ ውጤቱም እንደሚከተለው በሰንጠረዥ 5.12 ቀርቧል::

ሰንጠረዥ 5.12.

***በሴትና ወንድ ተማሪዎች መካከል የአንብቦ መረዳት ችሎታ አማካይ ልዩነት ንጽጽር በነጻ ናሙና ቲ ቴስት***

| የክፍል ደረጃ | ተላውጦዎች | ወንድ= 78ና 82 | | ሴት=73ና 88 | | የቲ ዋጋ | የጉልህነት ደረጃ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | አማካይ | መደበኛ ልይይት | አማካይ | መደበኛ ልይይት | | |
| 5ኛ ክፍል | ፈተና | 22.51 | 2.855 | 21.63 | 3.545 | 1.69 | 0.093 |
| 7ኛ ክፍል | ፈተና | 17.74 | 3.307 | 17.13 | 4.039 | 1.089 | 0.278 |

Df = 149& 168 * $p<0.05$

በሰንጠረዥ 5.12 እንደተመለከተው በሁለቱም የክፍል ደረጃዎች የወንዶች የአንብቦ መረዳት ችሎታ አማካይ ከሴቶች ተሽሎ ቢገኝም በስታትስቲክስ ግን ጉልህ አይደለም፡፡ በተመሳሳይ የማንበብ ተነሳሽነት አማካይ የወንዶች ከሴቶች የተሻለ ነጥብ ቢኖረውም የጉልህነት ደረጃው ከ0.05 በላይ መሆኑ ልዩነቱ ተቀባይነት እንዳይኖረው ያደርጋል፡፡

የአምስተኛ ክፍል ወንዶች የአንብቦ መረዳት ችሎታ አማካይ ውጤት 22.51 ሲሆን የሴቶቹ 21. 63 መሆኑ ተስተውሏል፡፡ በሁለቱ ጾታዎች መካከል የ0.88 ያክል አማካይ ልዩነት ቢታይም ልዩነታቸው ግን ጉልህ አይደለም፡፡ የሰባተኛ ክፍል ወንድ ተማሪዎች አማካይ ነጥብ 17.74 ሲሆን ሴቶቹ 17.13 መሆኑ ተስተውሏል፡፡ ሁለቱ ጾታዎች የ0.61 ያክል ልዩነት ቢኖራቸውም ልዩነታቸው ግን ጉልህ አለመሆኑን የነጻ ናሙና ቲ-ቴስት ውጤቱ ያሳያል፡፡

አራተኛው የጥናቱ መሰረታዊ ጥያቄ ተማሪዎች ከቤተሰብ ዳራ ጋር በተያያዘ የማንበብ ተነሳሽነቴንና የአንብቦ መረዳት ችሎታየን ያዳብርልኛል ብለው የሚያስቧቸው ነገሮች ምን ምን ናቸው? የሚል ሲሆን ይህንን ጥያቄ ለመመለስ በቡድን ውይይት የተገኘውን መረጃ ለመተንተን አይነታዊ ዘዴ ተግባራዊ ተደርጓል፡፡

በሁለቱም የክፍል ደረጃ የተመረጡት 24 ተማሪዎች በክፍል ደረጃቸው መሰረት በሁለት የተለያዩ ቡድኖች ተከፍለው በክፍሉ የአማርኛ መምህርትና በተመራማሪዋ መሪነት ከቤተሰብ ዳራ ጋር ተያይዘው ከሚነሱት ማህበራዊ ትምህርታዊና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች ውስጥ የትኞቹ ነገሮች ለአንብቦ መረዳት ችሎታቸውና ለማንበብ ተነሳሽነታቸው እንደሚጠቅሟቸውና ይጠቅሙኛል ሲሉ ምክንያታቸው ምን እንደሆነ በውይይቱ እንዲናገሩ በተጠየቁት መሰረት ከሰጧቸው ምላሾች አንብቦ መረዳት ችሎታየንና የማንበብ ተነሳሽነቴን ያዳብሩልኛል ካሏቸው ነገሮች ትምህርታዊ፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ነገሮች በዋናነት ይጠቀሳሉ፡፡

የመጀመሪያውና በውይይቱ ላይ አብዛኛው ተማሪ የጠቀሰው ከትምህርታዊ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ነገሮች ናቸው፡፡ ሁሉም የሰጡትን ምላሽ በማዋሀድ ሲታይ በሁለት አበይት ክፍሎች ይከፈላል፡፡ አንደኛው በአካባቢው የተማረ ሰው መኖር የሚሰጠውን ጠቀሜታ መሰረት በማድረግ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ በተቃራኒው አለመማር የሚያደርሰውን ጉዳት በማየት ለማንበብ የሚተጉ ናቸው፡፡

በዙሪያ የተማረ ሰው መኖር ሲባል አብዛኛው ተማሪ በአካባቢው ያሉት ሰዎች በመማራቸው ያገኙትን ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ሀገራዊ ጥቅም በመመልከት እኔም ጠንክሬ ባነብ እንደነዚህ ሰዎች መሆን እችላለሁ የሚል አስተሳሰብ እንዲያዳብሩ እንደረዳቸው ገልጸዋል፡፡ ለዚህም እንደ ሮል ሞዴል የሚያዩት በአብዛኛው የቤተሰባቸውን አባል ነው፡፡ አባትና እናት የመጀመሪያውን ድርሻ ሲወስዱ እህት፣ ወንድምና ዘመድ በመቀጠል ይጠቀሳሉ፡፡ አልፎ አልፎ ትልልቅ ቦታ የደረሱ የአካባቢ ሰዎችም ልጆች በትምህርታቸው ጠንክረው እንዲሰሩ በተለይም በርትተው በማንበብ አንብቦ የመረዳት ችሎታቸውና የማንበብ ተነሳሽነታቸው ከፍ እንዲል እንደሚረዳቸው አብራርተዋል፡፡

ከዚሁ ጋር በተያያዘ ነገር ግን ከመጀመሪያው ሀሳብ በተለየ የቤተሰቦቻቸው አለመማር ጠንክረው አንብበው የአንብቦ መረዳት ችሎታቸውን ከፍ እንዳደረገው የገለጹ ተማሪዎችም አሉ፡፡ ይህም ማለት ቤተሰቦቻቸው ባለመማራቸው የደረሰባቸውን የኢኮኖሚ ችግር በመመልከት የነሱን አይነት ኑሮ ላለመኖር ጠንክረው ያነባሉ ማለት ነው፡፡ እንዲሁም ያልተማሩት ወላጆች ጊዜያቸውን ሙሉ የጉልበት ስራ ሲሰሩ መዋላቸውን በማስተዋል ከዚህ ድካም ለመገላገል ማንበብ እንደሚገባቸው እራሳቸውን አሳምነው የአንብቦ መረዳት ችሎታቸውን ያሳድጋሉ፤ የማንበብ ተነሳሽነታቸውንም ከፍ ያደርጋሉ፡፡

ከ7ኛ ክፍል የመጣች አንዲት ተማሪ በሰው ቤት ውስጥ በቤት ሰራተኝነት የምትሰራ ስትሆን በውይይቱ ላይ እንዲህ ስትል ሀሳቧን ገልጻለች "ቤተሰቦቼ ትምህርት የተማሩ አይደሉም፡፡ እኔን የማስተማር ፍላጎትም የላቸውም እኔን እንዲያስተምሩኝ ብጠይቃቸውም ሀሳባቸውን ቀይረው ሊያስተምሩኝ ስላልቻሉ ጠፍቼ መጥቼ ሰው ቤት እየሰራሁ እማራለሁ፡፡ አለመማራቸውን ሳስበው ስለሚቆጨኝ በርትቼ አነባለሁ፡፡ የማንበብ ተነሳሽነቴም ይጨምራል" ብላለች፡፡ በዚሁ የክፍል ደረጃ የሚገኝ ሌላ ተማሪ እንዲህ ሲል ገልጾታል፡ "ከኛ ቤተሰብ የተማረ ሰው የለም ቤተሰቦቼ የቀን ስራ እየሰሩ የሚተዳደሩ ናቸው፡፡ አለመማራቸው ስለሚቆጨኝ ከነሱ የተሻልሁ ለመሆን በርትቼ አጠናለሁ፡፡ ጨዋታ ልጫዎት አስቤ ትቼው ወደ ንባቤ የሚመልሰኝ የቤተሰቦቼ አለመማር ያስከተለውን ችግር ስለማስተውል ነው" ብሏል፡፡ ከነዚህ ልጆች ንግግር የቤተሰቦቻቸው አለመማር የማንበብ ተነሳሽነታውንና የአንብቦ መረዳት ችሎታቸውን ከፍ እንዳደረገው መረዳት ይቻላል፡፡

በሌላ መልኩ ደግሞ ከቤተሰቦቻቸው የተማረ ሰው መኖር ጠንክረው እንዲያነቡ እንደረዳቸው የገለጹ አሉ፡፡ የአምስተኛ ክፍል ተማሪ የሆነው አንድ ተማሪ ከቤተሰቡ የተማረ ሰው መኖር እንዴት የማንበብ ተነሳሽነቱን እንዳሳደገለት እንዲህ ብሎ ገልጾታል "ወንድሜ ጎበዝ ተማሪ ነው‹፣ ጎበዝ ተማሪ ስለሆነ ወላጆቻችን ይወዱታል፡፡ ዘመዶቻችንም የተለያዩ ነገሮችን እየገዙ ይሰጡታል፡፡ ይህንን ሳይ እኔም አነባለሁ፡፡ ለማንበብም እነሳሳለሁ"፡፡

በአጠቃላይ ከሁለቱም ሀሳቦች መረዳት እንደሚቻለው የተማሪዎችን የአንብቦ መረዳት ችሎታ ለማሳደግ የቤተሰብ የትምህርት ደረጃ ከፍተኛ አስተዋጽዖ አለው፡፡ መማር በሚሰጠው በርካታ ጥቅም ወይም አለመማር በሚያመጣው ጉዳት መነሻነት ለማንበብ እንደሚተጉ መረዳት ይቻላል፡፡ ይህ አይነታዊ ውጤት በቁጥር ተሰብስቦ በህብረ ድህረት ትንተና ከተተነተነው ውጤት ጋር ያመሳስለዋል፡፡ በመጠን የተገኘው ውጤት እንደሚያሳየው የትምህርት ደረጃ ከኢኮኖሚያዊ ደረጃ ቀጥሎ የአንብቦ መረዳት ችሎታንና የማንበብ ተነሰሳሽነትን ተንባይ ተላውጦ ነው፡፡ ሁለተኛውና በአብዛኛው ተማሪ የተጠቀሰው ሌላው ጉዳይ ማህበረ ኢኮኖሚያዊ ነገሮችን የሚመለከት ነው፡፡ እንደ ተማሪዎቹ ገለጻ ቤተሰብ ለትምህርት የሚረዱ የተለያዩ መጽሀፍትን፣ መርጃ መሳሪያዎችንና የማጥኛ ወንበርና ጠረጴዛ ባሟሉላቸው ቁጥር የማንበብ ተነሳሽነታቸው እንደሚጨምር ገልጸዋል፡፡ በተለይም የተለያየ ታሪክ የያዙ የተረት፣ የልቦለድና የእውነተኛ ታሪክ የያዙ መጽሀፍት በተገዙላቸው ቁጥር ታሪኩን ለማንበብ ካላቸው ፍላጎት የተነሳ በርትተው እንደሚያነቡ ያም የማንበብ ተነሳሽነታቸውን እንደሚያዳብርላቸው ያብራራሉ፡፡ በተለይም የማንበብ ተነሳሽነታቸውን እንደሚጨምርላቸው ገልጸዋል፡፡

ከማህበረ ኢኮኖሚያዊ ደረጃ ጋር ተያይዞ የሚጠቀሰው ሌላው ነጥብ የቤተሰቡ ማህበራዊ አኗኗርና ከጎረቤቱ ጋር ያለው ኢኮኖሚያዊ መስተጋብር ሲሆን ይህ ነገር የአንብቦ መረዳታቸውንና የማንበብ ተነሳሽነታውን እንዳዳበረላቸው የገለጹ ተማሪዎች አሉ፡፡ ከማብራሪያቸው መረዳት እንደሚቻለው ከአካባቢው ሰው የተሻለ ለመባል እንዲሁም በሰፈሩ የተሻለ ተማሪ ሆኖ ለመገኘትና በተለያዩ ማህበራዊ ጉዳዮች ላይ በወላጆች ለመከበርና ለመሞገስ ሲባል ጠንክረው እንደሚያነቡ እንዲሁም እንዲህ አይነት ሙገሳዎችን ሲሰሙ የማንበብ ተነሳሽነታቸው እንደሚጨምር ገልጸዋል፡፡

በሶስተኛ ደረጃ የተጠቀሰው የቤተሰብ ማበረታቻ ሲሆን በአብዛኛው ተማሪ የተጠቀሰ ጉዳይ ነው፡፡ የቤተሰብ ድጋፍ ወይም ማበረታቻ በተለያዩ መልኩ የተገለጸ ሲሆን በከፊል ከላይ ከትምህርታዊ ጉዳዮች ከተጠቀሰው ጋር ይመሳሰላል፡፡ ማለትም እንደኔ እንድትሆን ወይም ከኔ የተሻለ እንድትሆን የሚሉ ናቸው፡፡ ሌሎች ማበረታቻዎች ደግሞ ሽልማት ከመሸለም፣ በማስረዳትና የተለያዩ ቁሳቁሶችን በማሟላት የሚገለጹ ናቸው፡፡ ቁሳቁሶች

የተባሉት በአብዛኛው በጽሑፍ መጠይቁ የቀረቡትን የግል መጽሀፍ መኖር፣ የግል ክፍልና አልጋ መኖር፣ የግል ማጥኛ ጠረጴዛና ወንበር መኖርን የሚመለከቱ መልሶች ቀርበዋል፡፡

በአይነታዊ ከተሰበሰቡት መረጃዎች መረዳት እንደሚቻለው የተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ችሎታና የማንበብ ተነሳሽነት ከቤተሰብ የትምህርት ደረጃ፣ የማህበረ ኢኮኖሚያዊ ደረጃና ድጋፍ ጋር የተዛመደ መሆኑንና የተማሪዎች የማንበብ ተነሳሽነት በአብዛኛው ውጫዊ ተነሳሽነት ላይ ያዘነበለ መሆኑን መረጃው ያሳያል፡፡ በአጠቃላይ በውጤት ትንተናው ስድስት አላማዎች ተነስተው በተለያዩ የስታትስቲክስ መተንተኛ ዘዴዎች ተተንትነው ሁሉም መልስ አግኝተዋል፡፡ የመጀመሪያዎቹ ሁለቱ በህብረ ድህረት ትንተና፣ ቀጣዩ በፒርሰን የተዛምዶ መወሰኛ ቀመር፣ አራተኛውና አምስተኛው በነጻ የናሙና ቲ ቴስት እንዲሁም የመጨረሻው በአይነታዊ መንገድ ተተንትነዋል፡፡ በመቀጠል እነዚህ ውጤቶች ከነማን የምርምር ውጤትና የማንበብ ንድፈ ሀሳብ ጋር እንደሚጣጣሙ እንዲሁም እንደሚለያይ የተለያዩ ጥናቶችን በመጥቀስ ማብራሪያ ተሰጥቶባቸዋል፡፡

## 5.3. የዋናው ጥናት የውጤት ማብራሪያ

የዚህ ጥናት ዋና አላማ የቤተሰብ ዳራ የአንብቦ መረዳት ችሎታን የመተንበይ ድርሻ መለየት ነው፡፡ ይህን ዋና አላማ መሰረት በማድረግም የተለያዩ ንዑሳን አላማዎች ተነድፈው ምላሽ አግኝተዋል፡፡ የመጀመሪያው አላማ የቤተሰብ ዳራ የአንብቦ መረዳት ችሎታን የመተንበይ ድርሻውን መለየት ነው፡፡ ለዚህ አላማ ምላሽ ለመስጠት እሙኑ የተረጋገጠው መረጃ በህብረ ድህረት የመተንተኛ ዘዴ ተተንትኗል፡፡ ለዚህ ጥናት የተመረጡት ተሳታፊዎች ከአምስተኛና ከሰባተኛ የክፍል ደረጃ የተወሰዱ በመሆናቸው የተዘጋጀላቸው የአንብቦ መረዳት ችሎታ መለኪያ ፈተና የተለያየ ነበር፡፡ በመሆኑም በተለያየ መለኪያ የተለካውን ውጤት በአንድ ላይ ደምሮ ከመተንተን ይልቅ ለያይቶ መተንተኑ ተገቢ በመሆኑ ሁለት የተለያዩ የህብረ ድህረት ትንተናዎች ተሰርተዋል፡፡

ግኝቱም የሚያሳየው የቤተሰብ ዳራ የአንብቦ መረዳት ችሎታን ጉልህ ተንባይ እንደሆነ ነው፡፡ የቤተሰብ ዳራ ተላውጦዎቹ በአጠቃላይ በቤተሰብ ዳራ ላይ ያላቸው አስተዋጽኦ የአምስተኛ ክፍል ($F$=84.982, $p$<0.05) ና የሰባተኛ ክፍል ($F$=87.496, $p$<0.05) ከፍተኛና ጉልህ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ዝርዝር ተላውጦዎቹ ያላቸው ተናጠላዊ የመተንበይ ድርሻ ሲታይ በሁለቱም የክፍል ደረጃዎች የቤተሰብ የኢኮኖሚ ደረጃና የትምህርት ደረጃ ከፍተኛ ጉልህ አስተዋጽኦ አበርክተዋል፡፡ የቤተሰብ የኢኮኖሚ ደረጃ በአምስተኛ ክፍል ላይ 3.5% ያክል ድርሻ ሲኖረው በሰባተኛ ክፍል ላይ ደግሞ ß= 0.382 ያክል የቤታ ዋጋ በማምጣት 2.7% ያክል የመተንበይ ድርሻ ይወስዳል፡፡

ይህም ማለት የቤተሰብ የኢኮኖሚ ደረጃና የትምህርት ደረጃ በጨመረ ቁጥር የአንብቦ መረዳት ችሎታ እየጨመረ ይሄዳል፡፡ የቤተሰብ ዳራ የአንብቦ መረዳት ችሎታን በሁለቱም የክፍል ደረጃዎች ይተነብያል የሚለው ውጤት የቤተሰብ ዳራ የአንብቦ መረዳት ችሎታን አይተነብይም በሚል የተነደፈውን አልቦ መላምት ውድቅ ያደርገዋል፡፡ ይህ ውጤትም የቤተሰብ የትምህርት ደረጃ በተማሪዎች የመጀመሪያዎቹ የማንበብ ደረጃዎች ላይ የሚኖረው ሚና ከፍተኛ ነው፤ በቤት ውስጥ የሚገኙት የተለያዩ ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮችም በተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ሚናው የሚናቅ አይደለም ብለው ካገኙት የRetelsdorf et al. (2011) የጥናት ውጤት ጋር የሚደጋገፍ ይሆናል፡፡ ምክንያቱም በመጀመሪያዎቹ የአንብቦ መረዳት ችሎታዎች ሲባል በታዳጊነት እድሜያቸው ማለት ሲሆን በዚህ ጊዜ ልጆች አብዛኛው ነገራቸው በወላጆቻው ጥገኝነት ላይ የተመሰረት ስለሆነ የማንበብ ችሎታውም በቤተሰባቸው ተጽዕኖ ሊደርስበት ይችላል፡፡ ይህ አባባል ከ ቫይጎስቲክ የማህረ ባህላዊ ንድፈ ሀሳብ ጋርም ይጣጣማል፡፡ እንደ ቫይጎስትኪ የማህበረ-ባህላዊ ንድፈ ሀሳብ የማንኛውም ሰው እድገት በማህረሰቡና በቤተሰቡ ተራክቦ የተገነባ ነው፡፡ ይህም ማለት የቤተሰብ ማንኛውም ጉዳይ በልጆች እድገት ላይ ተጽዕኖ  ይኖራዋል፡፡

የ Retelsdorf et al. (2011) ጥናት የቤተሰብ ዳራ ከማንበብ ብቃት ጋር ከፍተኛ ተዛምዶ እንዳለው ውጤቱ ያመለክታል፡፡ በተለይም የቤተሰብ የትምህርት ደረጃ የማንበብ ብቃትን የመጀመሪያ ደረጃ ተንባይ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ይህም ከዚህ የጥናት ውጤት ጋር ያመሳስለዋል፡፡ የተመሳሰሉት ይህ ጥናት የሚለካው አንብቦ መረዳት ችሎታና የ

Retelsdorf et al. (2011) ጥናት የማንበብ ብቃት የመጀመሪያ ደረጃ ብለው የለኩት ችሎታ ተመሳሳይነት ስላለው ነው፡፡

የጥቁርና የነጭ የውጤት ልዩነት በሚል Jencks& Phillips (1998) የሰሩት ምርምር የቤተሰብ ኢኮኖሚ በተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ችሎታ ላይ ተጽዕኖ ይፈጥራል ማለታቸው ከዚህ የጥናት ውጤት ጋር ያመሳስላቸዋል፡፡ ነገር ግን Jencks& Phillips (1998) የቤተሰብ የትምህርት ቤት ተሳትፎ በተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ችሎታ ላይ ተጽዕኖ ይፈጠራል ማለታቸው ከዚህ ጥናት ጋር ተቃራኒ ውጤት አሳይቷል፡፡ በዚህ ጥናት ወላጆች በትምህርት ቤት የሚያደርጉት ተሳትፎ አንብቦ መረዳት ችሎታን የመተንበይ ድርሻው በጣም ዝቅተኛ ነው ወይም ምንም አይነት አስተዋጽኦ የለውም ማለት ይቻላል፡፡ ሁለቱ ልዩነት ያመጡት በተተኳሪዎች ልዩነት ሊሆን ይችላል፡፡ ማለትም የዚህ ጥናት ተተኳሪ ተማሪዎች ከአንድ አይነት ቀለምና ዘር የመጡ ሲሆኑ የ Jencks& Phillips ጥናት ግን በጥቁርና ነጭ ተማሪዎች ላይ በንጽጽር የተሰራ ጥናት በመሆኑ ነው፡፡

በዚህ ጥናት የተገኘው የቤተሰብ ዳራ በአጠቃላይ የአንብቦ መረዳት ውጤትን ይተነብያል የሚለው ውጤት ከ Lindo (2007) ጥናት ውጤት ጋርም ተመሳሳይነት አለው፡፡ የ Lindo ጥናት ከ2ኛ ክፍል እስከ 6ኛ ክፍል ባሉ የመጀመሪያ ደረጃ ተማሪዎች ላይ የቤተሰብ ዳራ አንብቦ መረዳትን የመተንበይ ድርሻው ምን ያክል ነው ብለው ካጠኑት ጥናት የተገኘው ውጤት ከዚህ ጥናት ውጤት ጋር ተቀራራቢ ነው፡፡ በጥናቱ የቤተሰብ ዳራን በሶስት አበይት ተላውጦዎች ከፍሎ አይቷቸዋል፡፡ እነሱም ኢኮኖሚያዊ አቅም Financial Capital (ሀብት፣ ገቢና ድህነት)፣ የሰው አቅም /human capital/ (ትምህርት፣ ስራ፣ የቤት ውስጥ ሁኔታና አዕምሯዊ/ የማንበብ ችሎታ) ና ማህበራዊ አቅም /Social Capital/ የማህበራዊ ኔትወርክ፣ የቤተሰብ እርዳታ ወይም ተሳትፎና ከልጆች የሚጠብቁት ውጤት) ናቸው፡፡ እነዚህ ተላውጦዎች በአንብቦ መረዳት ችሎታ ላይ የሚኖራቸው ድርሻ በህብረ ድህረት ትንተና አስልተው የሰሩት ውጤት የሀብት መጠንና የገቢ መጠን ጉልህ ተንባይ ሆነው መገኘታቸው ከዚህ ጥናት ጋር ያመሳስላቸዋል፡፡

በተመሳሳይ ከሰው አቅም አንጻ ተላውጦ የሆነው ትምህርት በዚህ ጥናት እንደተስተዋለው ሁሉ ጉልህ ተንባይ እንደሆነ የቤታ ዋጋውና የፒ ዋጋው ያሳያል፡፡ የቤት ውስጥ ግብዓት በሁለቱም ጥናቶች የተካተተ ተላውጦ ሲሆን የሁለቱም ጥናቶች ግኝት የቤት ውስጥ ግብዓት ጉልህ ተንባይ አለመሆኑን ያሳያል፡፡ እነዚህ ሁለት ጥናቶች በውጤት የመመሳሰላቸው ምክንያት ሶስት ናቸው ተብሎ ይገመታል፡፡ አንደኛው የጥናቱ ተሳታፊዎች የክፍል ደረጃ ተቀራራቢ መሆን ነው፡፡ ይህ ጥናት በአምስተኛና በሰባተኛ ክፍል ላይ ሲያተኩር የ lindo ጥናት ከሁለተኛ እስከ ስድስተኛ ያተኩራል ይህም በመጠኑ ስለሚያቀራርባቸው ውጤታቸው ለመመሳሰሉ ምክንያት ይሆናል፡፡ ሁለተኛው የተጠቀሙት የቤተሰብ ዳራ መለኪያ መጠይቅ መቀራረብ ሊሆን ይችላል፡፡ በዚህ ጥናት የቤተሰብ ዳራ መለኪያ መጠይቁ ሲዘጋጅ ከተቃኙት የተዛማጅ ጽሁፍ ወስጥ የlindo ይጠቀሳል፡፡ ሶስተኛው ደግሞ ለጥናቱ መሰረት ያደረጉት ንድፈ ሀሳባዊ ማዕቀፍ በከፊል ተመሳሳይ መሆኑ ናቸው፡፡ ይህ ጥናት ከንድፈሀሳብ አንጻር መሰረት የያደረገው የብሮንፈርነርን የስነምህዳር ስርዓት ንድፈሀሳብ ሲሆን የlindo ጥናትም ከሚከተላቸው ንድፈ ሀሳባዊ ጽንሰ ሀሳቦች አንዱ የብሮንፈርነር የስነ ምህዳር ስርዓት ነው፡፡

የ Lindo (2007)ን ጥናት ውጤት ከዚህ ጥናት የሚለየው ከዝርዝር ተላውጦዎቹ የቤተሰብ የስራ ሁኔታ በሚል በዚህ ጥናት የተካተተው ተላውጦ የመተንበይ ድርሻው ጉልህ ሆኖ አልተገኘም ነገር ግን በ Lindo ጥናት ከኢኮኖሚና ከትምህርት ባሻነሰ የስራ ሁኔታ ጉልህ ተንባይ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ይህ ልዩነት የመጣው ምናልባት የቤተሰብ የስራ ሁኔታ የተለካበት መንገድ የተለያየ ስለሆነ ሊሆን ይችላል፡፡ ምንም እንኳን የ Duncan& Magnuson (2005) ጥናት በዘርና ጎሳ ላይ አተኩሮ ቢሰራም ውጤቱ እንደሚያሳየው የቤተሰብ ማህበረ ኢኮኖሚያዊ ደረጃ ተጽዕኖ እንዳለው ነው፡፡ Duncan& Magnuson (2005) በጥናታቸው ያተኮሩባቸው የቤተሰብ ዳራ ተላውጦዎች ገቢ፣ ትምህርት፣ የቤተሰብ መዋቅርና የጎረቤት ሁኔታ ናቸው፡፡ እነዚህ ተላውጦዎች ተጽዕኖ እንደሚፈጥሩ ገልጸው ይህንን ለመቀነስ የእናት የትምህርት ደረጃን ማሳደግ፣ የልጆቹን አካባቢ በማጤን ድጎማ መስጠትና ኢኮኖሚያቸውን የሚያሳድጉበትን መንገድ መፈለግ እንደ መፍትሄ መጠቆማቸው ከዚህ ጥናት ጋር ያመሳስላቸዋል፡፡

የገቢ መጠን፣ ጾታ፣ ዘርና በቤት ውስጥ ጽሁፍ መኖር ተማሪዎች ከትምህርት ቤት ጋር ተያይዘው የሚነሱ ችሎታዎችን የመተንበይ ድርሻ በሚል Patterson et al (1990) ምርምር ሰርተው የተገኘው ውጤት ከዚህ ጥናት ውጤት ጋር በመጠኑ ተመሳሳይነት አለው፡፡ ተመሳሳይ የሚያደርጋቸው ኢኮኖሚ የተማሪዎችን የአንብቦ መረዳት ችሎታ የመተንበይ ድርሻ እንዳለው በጥናታቸው ማረጋገጣቸው ነው፡፡ ሁለቱ ጥናቶች የሚለያዩት ይህ ጥናት በአንብቦ መረዳት ችሎታ ላይ ብቻ ማተኮሩ ሲሆን የ Patterson et al (1990) ጥናት ግን በአጠቃላይ ተማሪዎች በትምህርት ቤት በሚያደርጉት እንቅስቃሴ ላይ ማተኮሩ የውጤት ልዩነት እንዲፈጠር አስችሏል፡፡

በሶስተኛነት የታቀደው አላማ የአንብቦ መረዳት ችሎታ በጾታ ልዩነት እንዳለውና እንደሌለው መለየት ነበር፡፡ በሁለቱም የክፍል ደረጃዎች የወንዶች የአንብቦ መረዳት ችሎታ አማካይ ከሴቶች ተሽሎ ቢገኝም በስታትስቲክስ ግን ጉልህ አይደለም፡፡ ይህ ውጤት አብዛኞቹ ጥናቶች በአብዛኛው በቋንቋ ትምህርት ሴቶች ከወንዶች የተሻሉ ናቸው ከሚለው የማህበረ ባህላውያን ንድፈ ሀሳብና በአንብቦ መረዳት ችሎታ የሴቶቹ ከወንዶች የተሻለ ነው ከሚሉት ከ Campbell, et al (2001)፣ Steinmayr & Spinath (2008)፣ Baker & Wigfild (1999)ና ጥናት ውጤት ጋር አልተደጋገፈም፡፡ ውጤቶቹ ያልተደጋገፉበት ምክንያት በሀገራችን ለሴት ልጅ ያለው አስተሳሰብ ገና ያልዳበረና አሁንም ድረስ ዝቅ ተደርጋ የምትታይ በመሆኗ ከወንዶች ተሽላ መገኘቷ ቀርቶ እኩል ውጤት ማምጣት አለመቻሏ የሚጠበቅ እንደሆነ ይገመታል፡፡

በ Campbell, et al (2001) ጥናት ከተሳተፉት 35 ሀገራት በሁሉም ሴቶች ከወንዶች በሁሉም የማንበብ ሂደቶች የተሻለ ውጤት አምጥተዋል፡፡ ልዩነታቸውም ጉልህ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በተመሳሳይ በ2006 በተሰራው ተመሳሳይ የ PIRLS ጥናት የሴቶች ከወንዶች በ17 የአማካይ ልዩነት በልጦ ተገኝቷል (Mullis et al., 2006)፡፡ PIRLS ተከታታይ ጥናት እስከ 2016 ድረስ ሲያካሂድ በሁሉም ጥናቶች የታየው ውጤት ሴቶች ከወንዶች የበለጠ የአንብቦ መረዳት ውጤት እንዳላቸው ነው፡፡

በመጨረሻ የታየው በቡድን ተኮር ውይይት ተሰብስቦ የተገኘው ተማሪዎች ለአንብቦ መረዳት ችሎታየና ለማንበብ ተነሳሽነቴ ይጠቅመኛል ብለው የሚያስቧቸው ነገሮች ምን

ምን ናቸው ለሚለው ጥያቄ የተገኘው አይነታዊ ውጤት ነው፡፡ በሁለት የተለያዩ ቀናት ሁለት ቡድኖች በማዘጋጀት ውይይቱ ተካሂዶ በተገኘው መረጃ መሰረት ተማሪዎች ከቤተሰባቸው የኢኮኖሚ ደረጃና ከትምህርት ደረጃ ጋር የተያያዙ ጉዳዮችን ለአንብቦ መረዳት ችሎታና ለማንበብ ተነሳሽነታቸው እንደሚጠቅማቸው ዘርዝረዋል፡፡ Wigfield & Guthrie (1997) በሰሩት ምርምር የተገኘው ውጤት ይህንን ሃሳብ የሚደግፍ ነው፡፡ የሚለየው በዚህ ውይይት የተነሱት ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች ከደብተር፣ ከመጽሀፍ፣ ከልብስ ከምግብና ከመጠለያ የዘለሉ አይደሉም፡፡ ነገር ግን በ Wigfield & Guthrie (1997) ጥናት የተነሱት ከቴክኖሎጂ፣ ከተጨማሪ መጽሀፍትና ከመዝናኛ መጽሀፍት ጋር የተያያዙ ናቸው፡፡ ነገር ግን በሁሉም ጥናቶች የተነሱት ጥያቄዎች ሲጠቃለሉ ኢኮኖሚያዊና ትምህርታዊ ጉዳዮች ናቸው፡፡

# ምዕራፍ ስድስት

# ማጠቃለያ፣ መደምደሚያና የመፍትሄ ሀሳቦች

## 6.1. ማጠቃለያ

የዚህ ጥናት ዋና አላማ የቤተሰብ ዳራ የአንብቦ መረዳት ችሎታን የመተንበይ ድርሻው ምን ያክል እንደሆነ መለየት እንደሆነ በቀደምት ምዕራፎች ተገልጿል፡፡ በዚህም መሰረት በጥናቱ በቀዳሚነት መልስ እንዲገኝባቸው የተነሱት መሰረታዊ ጥያቄዎች የሚከተሉት ነበሩ፡፡

1. የቤተሰብ ዳራ የአንብቦ መረዳት ችሎታን በመተንበይ ረገድ ድርሻው ምን ያህል ነው?
   1.1. የቤተሰብ መዋቅር የአንብቦ መረዳት ችሎታን በመተንበይ ረገድ ድርሻው ምን ያህል ነው?
   1.2. የቤተሰብ የትምህርት ደረጃ የአንብቦ መረዳት ችሎታን በመተንበይ ረገድ ድርሻው ምን ያህል ነው?
   1.3. የቤተሰብ የስራ ሁኔታ የአንብቦ መረዳት ችሎታን በመተንበይ ረገድ ድርሻው ምን ያህል ነው?
   1.4. የቤት ውስጥ ግብዓት የአንብቦ መረዳት ችሎታን በመተንበይ ረገድ ድርሻው ምን ያህል ነው?
   1.5. የቤተሰብ የኢኮኖሚ ደረጃ የአንብቦ መረዳት ችሎታን በመተንበይ ረገድ ድርሻው ምን ያህል ነው?

1.6. የቤተሰብ የማህበራ ደረጃ የአንብቦ መረዳት ችሎታን በመተንበይ ረገድ ድርሻው ምን ያህል ነው?

H1= የቤተሰብ ዳራ የአንብቦ መረዳት ችሎታን የመተንበይ ድርሻው አለው፡፡

2. የቤተሰብ ዳራ የአንብቦ መረዳት ችሎታን የመተንበይ ድርሻው በክፍል ደረጃ ልዩነት አለው?

   Ho= የቤተሰብ ዳራ የአንብቦ መረዳት ችሎታን የመተንበይ ድርሻው በክፍል ደረጃ ልዩነት የለውም፡፡

3. የተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ችሎታ ከጾታ አንጻር ልዩነት ያሳያል?

   Ho= የተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ችሎታ ከጾታ አንጻር ልዩነት አያሳይም፡፡

   H1= በአንብቦ መረዳት ችሎታ በሴቶችና በወንዶች አማካይ መካከል ልዩነት አለ፡፡

4. ከቤተሰብ ዳራ ተላውጦዎች ተማሪዎች ለአንብቦ መረዳት ችሎታየና ለማንበብ ተነሳሽነቴ ይጠቅሙኛል ብለው የሚያስቧቸው ነገሮች ምን ምን ናቸው?

ከላይ የቀረቡትን መላምቶች ለመፈተሽና ጥያቄዎችን መልስ ለመስጠት የምርምርን አካሄድ በመከተል ተሳታፊዎች ተመርጠዋል፤ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ተዘጋጅተዋል፤ ተሰብስበዋል፤ የመተንተኛ ዘዴዎች ተመርጠው መረጃዎቹ ተተንትነዋል፤ ማብራሪያም ተሰጥቶባቸዋል፡፡

ለዚህ ጥናት በተጠኝነት የተመረጡት በባህርዳር ከተማ አስተተዳደር ስር የሚገኙ የአንደኛ ደረጃ የሁለተኛ እርከን የአምስተኛና የሰባተኛ ክፍል ተማሪዎች ናቸው፡፡ ትምህርት ቤቶችና ቦታው የተመረጡት በዕጣ ንሞና ሲሆን በአጠቃላይ ለዚህ ጥናት ሶስት ትምህርት ቤቶች ተመርጠዋል፡፡ የመጀመሪያው የቅድመ ሙከራ ጥናት ለማካሄድ፣ ሁለተኛው ለሙከራ ጥናት ሶስተኛው ደግሞ ለዋናው ጥናት የተመረጡ ናቸው፡፡ የተመረጡት ትምህርት ቤቶች የድል ችቦ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት፣

የቁልቋል ሜዳ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤትና የዶና በርበር የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ናቸው፡፡

ለዋናው ጥናት የተካተቱት ተጠኝዎች በ2010 ዓ.ም በዶና በርበር የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት ትምህርታቸውን በመከታተል ላይ የሚገኙት የአምስተኛና የሰባተኛ ክፍል ተማሪዎች ናቸው፡፡ ከአካላዩ ውስጥ 151 (ሴት 73፣ ወንድ 78) የአምስተኛና 170 (ሴት 88፣ ወንድ 82) የሰባተኛ ክፍል ተማሪዎች የዋና ጥናቱ ተሳታፊ ሆነዋል፡፡ የተመረጡት ተማሪዎች በመጀመሪያ ስለምርምሩ አላማ ማብራሪያ በተመራማሪዋ፣ በአማርኛ መምህራቸውና በርዕሰ መምህሩ ተሰጥቷቸዋል፤ በመቀጠልም በፍላጎት እንዲሳተፉ ተጠይቀዋል፡፡ ፈቃደኛ ሆነው የተገኙት በመጀመሪያ የቤተሰብ ዳራ የሚለካውን መጠይቅ እንዲሞሉ ተደርገዋል፡፡ በመቀጠል የአንብቦ መረዳት ችሎታ መለኪያ ፈተናውን እንዲፈተኑ ተደርገዋል፡፡ የተወሰኑት ብቻ ተመርጠው የቡድን ውይይት አካሂደዋል፡፡

ለዚህ ጥናት የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ሆነው ያገለገሉት የጽሁፍ መጠይቅ፣ ፈተናና የቡድን ውይይት ናቸው፡፡ የመጀመሪያው የቤተሰብ ዳራን የሚለካ የጽሁፍ መጠይቅ ነው፡፡ የቤተሰብ ዳራ የሚለካው መጠይቅ አስራ ሁለት ጥያቄዎችን ይዟል፡፡

ሌላው የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ፈተና ነው፡፡ ፈተና የተማሪዎችን የአንብቦ መረዳት ችሎታ ለመለካት ጥቅም ላይ የዋለ ነው፡፡ ለአምስተኛና ለሰባተኛ ክፍል ሁለት የተለያዩ ፈተናዎች ተዘጋጅተዋል፡፡ አስተማማኝነታቸውን ለመለካት የተሰበሰበው መረጃ ወደ ትንተና ከመግባቱ በፊት ተጣርቶ አስተማማኝነቱ ተሰልቷል፡፡ በክሮንባች አልፋ የተደረገው ስሌት እንደሚያሳየው የአምስተኛ ክፍል 0.811ና የሰባተኛ ክፍል 0.814 ተቀባይነት ያለው አስተማማኝነት በማሳየታቸውና በባለሙያዎች የተደረገው ግምገማ ተገቢነቱን ስለሚያሳይ ወደ ትንተናው ተገብቷል፡፡ ሌላው የመረጃ መሰብሰቢያ የቡድን ውይይት ሲሆን ተማሪዎች ከቤተሰብ ዳራ ጋር በተያያዘ ለአንብቦ መረዳት ችሎታየና ለማንበብ ተነሳሽነቴ ይጠቅሙኛል ብለው የሚያስቧቸው ነገሮች ምን ምን ናቸው የሚሉ ሲሆኑ እነሱን ለመመለስ አገልግሎት ላይ ውሏል፡፡ የተገኘው መረጃም አይነታዊ በሆነ መንገድ ተተንትኗል፡፡

ከላይ በተገለጹት የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች መረጃ ከተሰበሰብ በኋላ የተለያዩ እሙኖች ተፈትሸዋል፡፡ መጀመሪያ የተደረገው የመረጃው የውጤት ስርጭት ወጥነት መፈተሽ ነው፡፡ በኮሞግሮቭ ስሞግሮቭ በተደረገው ፍተሻ የአምስተኛ ክፍል የአንብቦ መረዳት ችሎታ ውጤትና የሰባተኛ ክፍል የአንብቦ መረዳት ችሎታ ውጤት የውጤት ስርጭት ወጥነት ተረጋግጧል፡፡ የውጤት ስርጭቱ ወጥ ሆኖ መገኘት በስታትስቲክስ ህግ ፓራሜቲራዊ የስታትስቲክስ መፈተሻ ዘዴዎችን ለመጠቀም በማስቻሉ የዚሁ አካል የሆኑትን የህብረ ድህረት ትንተናና የነጻ ናሙና ቲቴስት ለመተንተኛነት አገልግለዋል፡፡ ወደ ዋናው ትንተና ከመገባቱ በፊት በገላጭ እስታትስቲክስ የጾታ ምጥጥን፣ የአንብቦ መረዳት ችሎታ ውጤት አማካይ ተሰልቷል፡፡ የቤተሰብ ዳራ የሚለኩት ጥያቄዎች ምላሽ በድግግሞሽና በፐርሰንታይል ተሰልቷል፡፡ በመጨረሻም በጥያቄዎቹ ቅደም ተከተል መሰረት ትንተና ተካሂዷል፡፡

በመጀመሪያ የተነሳው የተማሪዎች የቤተሰብ ዳራ የአንብቦ መረዳት ችሎታን ይተነብያልን? ከተነበየስ ድርሻው ምን ያክል ነው፣ የሚል ነው፡፡ ይህንን ጥያቄ ለመመለስ ህብረ ድህረት ትንተና የመተንተኛ ዘዴ ተግባራዊ ተደርጓል፡፡ የህብረ ድህረት ትንተና ውጤቱ እንደሚያሳየው የቤተሰብ ዳራ የአንብቦ መረዳት ችሎታን ተንባይ ተላውጦ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በዚህ ጥናት የተካተቱት የአምስተኛና የሰባተኛ ክፍል ተማሪዎች በመሆናቸው የተለያዩ መለኪያዎችን ለመጠቀም ግድ ይላል፡፡ ይህም ተነጣጥለው መሰራት እንዳለባቸው የሚያሳይ በመሆኑ ተነጣጥለው ተሰርተዋል፡፡ ምንም እንኳን በተናጠል ቢሰሩም ውጤታቸው ግን ተመሳሳይ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በሁለቱም የክፍል ደረጃዎች የአምስተኛ ($F$=84.982, $p$<0.05) ና የሰባተኛ ክፍል ($F$=87.496, $p$<0.05) በሆነ ውጤት የቤተሰብ ዳራ የአንብቦ መረዳት ችሎታን ተንባይ ተላውጦ መሆኑን ትንተናው ያሳያል፡፡

ዝርዝር ተላውጦዎቹ የሚኖራቸው ተናጠላዊ ባህርይም ተሰልቷል፡፡ ከቤተሰብ ዳራ ዝርዝር ተላውጦዎችም ከፍተኛ የቤታ ዋጋ በማምጣት የአንብቦ መረዳት ችሎታን የሚተነብየው የቤተሰብ የኢኮኖሚ ደረጃና የቤተሰብ የትምህርት ደረጃ ናቸው፡፡ የቤተሰብ የኢኮኖሚ ደረጃ በአምስተኛ ክፍል 0.500*ና በሰባተኛ ክፍል 0.528* የመደበኛ ቤታ ዋጋ በማምጣት ከቤተሰብ ዳራ ተንባዩች ቀዳሚውን ስፍራ ይይዛል፡፡ ቀጣይ ተንባይ የሆነው

የቤተሰብ የትምህርት ደረጃ ነው፡፡ የቤተሰብ የትምህርት ደረጃ በአምስተኛ ክፍል 0.382* ና በሰባተኛ ክፍል 0.214* የቤታ ዋጋ በማምጣት በሁለተኛ ደረጃ ጉልህ ተንባይ መሆኑን ትንተናው ያሳያል፡፡

አራተኛው የጥናቱ መሰረታዊ ጥያቄ የአንብቦ መረዳት ችሎታ በጾታ ልዩነት ያመጣል የሚል ነበር፡፡ ይህንን ለመመለስም የነጻ ናሙና ቲ-ቴስት ተግባራዊ ተደርጓል፡፡ የቲቴስት ውጤቱ የሚያሳየው የአንብቦ መረዳት ችሎታ በጾታ ልዩነት እንደሌለው ነው፡፡ በሁለቱም የክፍል ደረጀዎች በማንበብ ተነሳሽነትም በአንብቦ መረዳት ችሎታም የወንዶች አማካይ ከሴቶች የተሻለ አማካይ እንዳለው ቢያሳይም ልዩነታቸው ግን በስታትስቲክስ ጉልህ ሆኖ አልተገኘም፡፡ የአምስተኛ ክፍል የአንብቦ መረዳት ችሎታ የወንዶች 22.51 ሲሆን የሴቶቹ 21.63 ነው፡፡ በመካከላቸው የታየው የአማካይ ልዩነት ግን ጉልህ አይደለም፡፡ በሰባተኛ ክፍል የአንብቦ መረዳት ችሎታ ላይ የወንዶች ከሴቶች ብዙም የተለየ አይደለም፡፡ የወንዶች አማካይ 17.74 ሲሆን የሴቶች ደግሞ 17.13 ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ስድስተኛው የጥናቱ መሰረታዊ ጥያቄ ከቤተሰብ ዳራ ጋር በተያያዘ ተማሪዎች ለአንብቦ መረዳት ችሎታየና ለማንበብ ተነሳሽነቱ ይጠቅመኛል ብለው የሚያስቧቸው ነገሮች ምን ምን ናቸው የሚል ነበር፡፡ በቡድን ተኮር ውይይት የተሰበሰበው መረጃ  እንደሚያሳየው ተማሪዎች የቤተሰብ የትምህርት ደረጃና የኢኮኖሚ ደረጃ ማነስና መብዛት አስተዋጽዖ እንዳበረከተላቸው ተናግረዋል፡፡ ማለትም ቤተሰቦቻቸው የተሻለ ገቢ ካላቸው የተለያዩ ማበረታቻዎችን ስለሚሰጧቸው የማንበብ ተነሳሽነታቸው ከፍ እንደሚልና የተማረ ሰው በቤቱ ውስጥ መገኘትም እንደዚሁ ተማሪዎች እንዲያነቡ እንደሚገፋፋቸው በውይይቱ ላይ ተናግረዋል፡፡

በአጠቃላይ ሲታይ በባህርዳር ልዩ ከተማ የአንደኛ ደረጃ የሁለተኛ እርከን ተማሪዎች የሆኑት የዶና በርበር የአምስተኛ ክፍልና የሰባተኛ ክፍል የተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ችሎታ በቤተሰብ ዳራ ተጽዕኖ ስለሚደርስበት በዚህ ጥናት የብሮንፊርነር ንድፈሀሳብና የቫይጎትስኪ የማህበረ-ባህላዊ ንድፈሀሳብ ተቀባይነት አግኝቷል ማለት ይቻላል፡፡ እንዲሁም  ጥናቱ ይዞት የተነሳው ሞዴልም ተቀባይነት አግኝቷል፡፡ ከዚህ በመቀጠል

ይህንን የጥናት ውጤት ማጠቃለያ መሰረት በማድረግ ጥናቱ የደረሰበት መደምደሚ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

## 6.2. መደምደሚያ

የጥናቱን የውጤት ትንተናና ማብራሪያ መሰረት በማድረግ ከሚከተሉት መደምደሚያዎች ላይ ተደርሷል፡፡

1. የቤተሰብ ዳራ በአጠቃላይ የአንብቦ መረዳት ችሎታን ይተነብያል፡፡ የቤተሰብ ዳራ ተላውጦዎች በዝርዝር ያላቸው ተናጠላዊ አስተዋጽዖ ሲታይም የቤተሰብ የትምህርት ደረጃና የቤተሰብ የኢኮኖሚ ደረጃ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አለው ወይም በከፍተኛ ደረጃ ይተነብያል፡፡
2. የቤተሰብ ዳራ የአንብቦ መረዳት ችሎታን የመተንበይ ድርሻው በክፍል ደረጃ ልዩነት የለውም፡፡

3. የአንብቦ መረዳት ችሎታ በጾታ ልዩነት የላቸውም፡፡ ወይም በሌላ አገላለጽ በዚህ ጥናት በወንድና ሴት ተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ችሎታ መካከል ልዩነት የለም፡፡ ወይም ልዩነታቸው ጉልህ አይደለም፡፡ በአምስተኛም ሆነ በሰባተኛ ክፍል የአንብቦ መረዳት ችሎታ ጾታ ልዩነት አያመጣም፡፡

4. ተማሪዎች ከቤተሰብ ዳራ ጋር በተገናኘ የአንብቦ መረዳት ችሎታቸውንና የማንበብ ተነሳሽነታቸውን የሚያዳብርላቸው የቤተሰብ የትምህርት ደረጃና የቤተሰብ የኢኮኖሚ ደረጃ ናቸው ብለው ያስባሉ፡፡

## 1.3. የመፍትሄ ሀሳቦች

ለሌሎች ክሂሎችም ጭምር መሰረት የሆነው የማንበብ ክሂል በጣም አስፈላጊ በተለይም አሁን አሁን የግድ ሊዳብር የሚገባ ክሂል እንደሆነ እሙን ነው፡፡ ነገር ግን በበርካታ ምክንያቶች ስኬታማ ሲሆን አይስተዋልም፡፡ ለዚህም ይመስላል አብዛኞቹ ምርምሮች በዚያ ዙሪያ እየተሰሩ ይገኛሉ፡፡ ከዚህም ውስጥ የአንብቦ መረዳት ችሎታ ላይ ተጽዕኖ የሚፈጥሩ ነገሮች ይጠቀሳሉ፡፡ አነዚህ ተጽዕኖ ፈጣሪዎች የአንባቢው ማንነት፣ የመማር ማስተማር ሁኔታውና የጽሁፉ ባህርይ ናቸው፡፡ ይህ ጥናትም ከአንባቢው ማንነት በቤተሰብ ዳራና የማንበብ ተነሳሽነቱ ላይ በማተኮር የተሰራ ነው፡፡ በግኝቱም የቤተሰብ ዳራ የአንብቦ መረዳት ችሎታንና የማንበብ ተነሳሽነት እንደሚተነብይ አረጋግጧል፡፡ በተመሳሳይ የአንብቦ መረዳት ችሎታና የማንበብ ተነሳሽነት በከፍተኛ ደረጃ አወንታዊ ተዛምዶ እንዳላቸው ግኝቱ ያሳያል፡፡ የአንብቦ መረዳት ችሎታና የማንበብ ተነሳሽነት በጾታ ልዩነት እንደሌላቸው ጥናቱ አረጋግጧል፡፡ እንዲሁም የክፍል ደረጃ በጨመረ ቁጥር የማንበብ ተነሳሽነት እየጨመረ እንደሚሄድ በአምስተኛና በሰባተኛ ክፍል ተማሪዎች የታየው የማንበብ ተነሳሽነት አማካይ ውጤት አመላክቷል፡፡

በማጠቃለያው ከተዘረዘሩት ውጤቶችና የውጤት ትንተናዎች በመነሳት እንዲሁም የቀረቡትን ድምዳሜዎች መሰረት በማድረግ የሚከተሉት ስነትምህርታዊ አንድምታዎች፣ የመፍትሄ ሀሳቦችና የምርምር ጥቆማዎች ተሰጥተዋል፡፡

የቤተሰብ ዳራ በተለይም የቤተሰብ የኢኮኖሚ ደረጃና የትምህርት ደረጃ የአንብቦ መረዳት ችሎታን ይተነብያል፡፡ በመሆኑም ትምህርት ቤቶች ተማሪዎች ልዩነት እንዳይሰማቸው ሲባል በትምህርት ቤት በሚያደርጓቸው እንቅስቃሴዎች ተመሳሳይ ነገር እንዲያደርጉ ማበረታታት፤ አቅም የሌላቸውን ተማሪዎች የኢኮኖሚ ድጋፍ ማድረግ፣ ላልተማሩ ወላጆች የተለያዩ መሰረታዊ ትምህርቶችን እንዲያገኙ መርዳት ተገቢ ነው፡፡ በአብዛኛው ትምህርት ቤቶች ልጆች በልብስ ልዩነት የሚመጣባቸውን የስሜት መጎዳት ለመከላከል ተመሳሳይ ልብስ እንዲለብሱ እንደሚደረገው ሁሉ ትምህርት ቤት ይዘዋቸው የሚመጡትን መጽሀፍትና የተለያዩ ቁሳቁሶች ተመሳሳይ እንዲሆኑ የበኩሉን አስተዋጽዖ ማድረግ ይገባል፡፡ በወላጅ፣ በትምህርት ቤት፣ በስርዓተ ትምህርት ቀራጮችና

የትምህርት ቢሮ ሀላፊዎች በጋራ ሆነው ልዩነትን የሚያጠቡ መፍትሄዎች ላይ መነጋገር ይጠበቅባቸዋል የሚል የመፍትሄ ሀሳብ ተጠቁሟል፡፡

ለምሳሌ፡- በፊንላንድ ሀገር ተማሪዎች ከቤታቸው ምግብ ይዘው መምጣት እንዲሁም በወላጅ መኪና መምጣት አይፈቀድላቸውም፡፡ የሚጠቀሙበት የትምህርት መሳሪያ ሁሉም ነገር ተመሳሳይ ነው፡፡ ምንም እንኳን በኢትዮጵያ ይህንን ማድረግ ባይቻልም በመጠኑ ግን መቅረፍ ይቻላል፡፡

በተነሳሽነትና በአንብቦ መረዳት መካከል የሚገኝ ጠንካራ ዝምድና መምህራን ቀጥታ ችሎታውን ለማዳበር በመረዳቱ ላይ ከማተኮር ይልቅ በተነሳሽነቱ ላይ መስራት እንዳለባቸው የሚያሳይ ነው፡፡ በዚህ ጥናት ውጤት መሰረት የአንብቦ መረዳት ችሎታና የማንበብ ተነሳሽነት ከፍተኛ ቁርኝት ስላላቸው መምህራን ተማሪዎችን በሚያስተምሩበት ጊዜ የተማሪዎችን የማንበብ ተነሳሽነት የሚያሳድጉ የተለያዩ ማነቃቂያዎች መጠቀም አለባቸው፡፡ ማበረታቻም መስጠት ይጠበቅባቸዋል፡፡

አንብቦ መረዳት ችሎታን የሚያስተምሩ መምህራን ብቻ ሳይሆን በአንብቦ መረዳት ችሎታ ላይ የሚሰሩ ተመራማሪዎች ከችሎታው በተጨማሪ በማንበብ ተነሳሽነታቸው ላይም ማተኮር አለባቸው፡፡ የማንበብ ተነሳሽነታውን ከፍ ማድረግ የመረዳት ችሎታውንም ማሳደግ በመሆኑ በማስተማሪያ ዘዴ፣ በመማሪያ ዘዴ፣ በብልሀት ስልጠናና በስልት ላይ ሙከራዊ ምርምር የሚያደርጉ ሰዎች ለማንበብ ተነሳሽነት ትኩረት መስጠት አለባቸው፡፡

የአንብቦ መረዳት ችሎታ በጾታ ያለው ልዩነት ጉልህ ባይሆንም የወንዶች ከሴቶች በአማካይ ነጥብ የተሻለ ሆኗል፡፡ ይህንን ልዩነት ለማጥበብ መምህራንና ትምህርት ቤቶች ለሴቶች በተጨማሪነት የተለያዩ ድጋፎችን መስጠት አለባቸው፡፡ የማንበብ ተነሳሽነት በክፍል ደረጃ ጉልህ ልዩነት እንዳለው ተስተውሏል፡፡ በተለይም አስፈላጊ የሆነው ውስጣዊ የማንበብ ተነሳሽነት በዝቅተኛ የክፍል ደረጃ ላይ ዝቅተኛ መሆኑ ተስተውሏል፡፡ ስለዚህ ተነሳሽነታቸው ገና ከጅምሩ እንዲዳብር ስርዓተ ትምህርት ቀራጮች መጽሀፍት ሲያዘጋጁ የተማሪዎችን ውስጣዊ ተነሳሽነት የሚያነሳሱ ይዘቶችን ማካተት አለባቸው፡፡ ትምህርት ቤቶች የተማሪዎችን የንባብ ፍላጎት የሚያሳድጉ

ክበቦችን ማቋቋም ይጠበቅባቸዋል፡፡ ለምሳሌ፡- የንባብ ክለብ የመሳሰሉትን ማለት ነው፡፡ እንዲሁም መምህራን የተማሪዎችን ውስጣዊ ተነሳሽነት የሚያዳብሩ ምንባቦችንና ምሳሌዎችን እየሰጡ ማስተማር አለባቸው፡፡

ከተዘረዘሩት ትምህርታዊ አንድምታዎች በተጨማሪ ይህንን ጥናት መሰረት በማድረግ የሚከተሉት ጥቆማዎች ተሰጥተዋል፡፡ እነሱም አንደኛ ይህ ጥናት ያካተተው የአምስተኛ ክፍልና የሰባተኛ ክፍል ተማሪዎችን ብቻ ነው፡፡ ነገር ግን ከአንደኛ ደረጃ የመጀመሪያ ሳይክል ጀምሮ እስከ ሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች ድረስ ያሉትን በማካተት ጥናቱ መሰራት ይችላል፡፡ እንዲሁም በረጅም ጊዜ የጥናት ስልት አንዱን ቡድን ከመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ጀምሮ እስከ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ድረስ እየተከታተሉና የተለያዩ ድጋፎችን እያደረጉ ለውጡን በመከታተል ማጥናት ይቻላል፡፡

ሌላው ጥቆማ ተንባይ ሆነው የቀረቡት የቤተሰብ ዳራ ተላውጦዎች ውስን ናቸው፡፡ ስለዚህ በስፋት ብዙ የቤተሰብ ዳራ ተላውጦዎች ተወስደው መጠናት ይችላል፤ ለምሳሌ የቤተሰብ የአዕምሯዊ እድገት፣ ለትምህርት ያላቸው አመለካከት፣ በንባብ ዙሪያ ያላቸው ልምድ፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ጥናቱ መረጃውን ያገኘው ከተማሪዎች ብቻ ነው ወላጆችን የጥናቱ ተሳታፊ በማድረግ መረጃ መሰብሰብ ይቻላል፡፡ እንዲሁም መምህራንና የትምህርት ቤቱ ሀላፊዎችን ተሳታፊ በማድረግ ሰፊ ምርምር ማድረግ ይቻላል፡፡ ከአንብቦ መረዳት ችሎታ አንጻርም ተማሪዎችን ጠንካራ፣ ደካማና መካከለኛ ብሎ በመክፈል ከእያንዳንዱ የማንበብ ተነሳሽነት መለኪያና ከቤተሰብ ዳራ ጋር ያለውን የተዛምዶ መጠን መፈተሽ ይቻላል፡፡

## ዋቢ መጽሀፍት /References/


ማስተዋል ውበቱ፡፡ (1989)፡፡ "የከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች በአማርኛ የአንብቦ መረዳት ችሎታ በአዲስ አበባ በሚገኙ በአራት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የአስራ አንደኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ የተካሄደ ጥናት"፡፡ ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ አዲስ አበባ ያልታተመ፡፡

በድሉ ዋቅጅራ፡፡ (1988)፡፡ "ተሳታፊነት ጭምትነት የስብዕና አይነት ከድርሰት መጻፍና ከአንብቦ መረዳት ችሎታ ጋር ያለው ተዛምዶ በሶስት ኮሌጆች ተማሪዎች ላይ የተሰራ ጥናት"፡፡ ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ አዲስ አበባ (ያልታተመ)፡፡

ብርሀን ስራጅ፡፡ (2003)፡፡ "የንባብ ልምድና የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት አንብቦ መረዳት ችሎታ ተዛምዶ፤ በውቅሮ፣ በነጋሽና አጉላዕ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በሚማሩ የ10ኛ ክፍል ተማሪዎች ናሙናነት"፡፡ ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ አዲስ አበባ (ያልታተመ)፡፡

ታምራት መኮንን፡፡ (2003)፡፡ "በአማርኛ ቋንቋ የማንበብ ችሎታ ከአካዳሚያዊ ውጤት ጋር ያለው ተዛምዶ"፡፡ ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ አዲስአበባ (ያልታተመ)፡፡

እንድሪስ አባይ፡፡ (2009)፡፡ "በቴክስት ውቅር ብልሃቶች በዐማርኛ ማንበብን መማር በተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ችሎታ ላይ ያለው ተጽዕኖ- በስድስተኛ ክፍል ተተኳሪነት"፡፡ ለሶስተኛ ዲግሪ ማሟያ ቀረበ ጥናት፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ አዲስአበባ (ያልታተመ)፡፡

እንግዳ ዘውዴ፡፡ (1990)፡፡ "የቶፐዳውን (top-down) የንባብ ማስተማሪያ ሞዴል በአማርኛ አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለማዳበር ያለው ተግባራዊነትና ውጤታማነት"፡፡ ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ አዲስአበባ (ያልታተመ)፡፡

ዘውዱ መብሬ፡፡ (2008)፡፡ “ሚና ለዋጭ ዘዴ የአማርኛ አፈፌት የሰባተኛ ክፍል ተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታና የማንበብ ተነሳሽነት ለማጎልበት ያለውን ሚና”፡፡ ለሶስተኛ ዲግሪ ማሟያ ቀረበ ጥናት፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ አዲስአበባ (ያልታተመ)፡፡

የሽጥላ ምንይልሽዋ፡፡ (2000)፡፡ “በ9ኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መጽሀፍ ውስጥ አንብቦ የመረዳት ትምህርት አቀራረብ ግምገማ”፡፡ ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ አዲስአበባ (ያልታተመ)፡፡

የኔሰው ደሴ፡፡ (1990)፡፡ “በኦሮምኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ አንብቦ የመረዳት ክሂላቸውን ለማዳበር ተራክቧዊ የንባብ ክሂል ማስተማሪያ ሞዴልን በክፍል ውስጥ ተጠቅሞ ማስተማር ያለው አስተዋጽኦ”፡፡ ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ አዲስአበባ (ያልታተመ)፡፡

የኢፌዲሪ የትምህርት ሚኒስቴር እና አብክመ ትምህርት ቢሮ፡፡(2007)፡፡ *አማርኛ እንደ አፍ መፍቻ ቋንቋ የተማሪ መጽሀፍ 5ኛ ክፍል*፡፡ የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የትምህርት ሚኒስቴር ፡፡

የኢፌዲሪ የትምህርት ሚኒስቴር እና አብክመ ትምህርት ቢሮ፡፡(2007)፡፡ *አማርኛ እንደ አፍ መፍቻ ቋንቋ የማስተማሪያ መጽሀፍ 5ኛ ክፍል*፡፡ የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የትምህርት ሚኒስቴር ፡፡

የኢፌዲሪ የትምህርት ሚኒስቴር እና አብክመ ትምህርት ቢሮ፡፡(2007)፡፡ *አማርኛ እንደ አፍ መፍቻ ቋንቋ የተማሪ መጽሀፍ 6ኛ ክፍል*፡፡ የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የትምህርት ሚኒስቴር ፡፡

የኢፌዲሪ የትምህርት ሚኒስቴር እና አብክመ ትምህርት ቢሮ፡፡(2007)፡፡ *አማርኛ እንደ አፍ መፍቻ ቋንቋ የማስተማሪያ መጽሀፍ 6ኛ ክፍል*፡፡ የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የትምህርት ሚኒስቴር ፡፡

የኢፌዲሪ የትምህርት ሚኒስቴር እና አብክመ ትምህርት ቢሮ፡፡(2007)፡፡ *አማርኛ እንደ አፍ መፍቻ ቋንቋ የተማሪ መጽሀፍ 7ኛ ክፍል*፡፡ የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የትምህርት ሚኒስቴር ፡፡

የኢፌዲሪ የትምህርት ሚኒስቴር እና አብክመ ትምህርት ቢሮ፡፡(2007)፡፡ *አማርኛ እንደ አፍ መፍቻ ቋንቋ የማስተማሪያ መጽሀፍ 7ኛ ክፍል*፡፡ የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የትምህርት ሚኒስቴር ፡፡

የኢፌዲሪ የትምህርት ሚኒስቴር እና አብክመ ትምህርት ቢሮ፡፡(2007)፡፡ *አማርኛ እንደ አፍ መፍቻ ቋንቋ የተማሪ መጽሀፍ 8ኛ ክፍል*፡፡ የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የትምህርት ሚኒስቴር ፡፡

የኢፌዲሪ የትምህርት ሚኒስቴር እና አብክመ ትምህርት ቢሮ፡፡(2007)፡፡ *አማርኛ እንደ አፍ መፍቻ ቋንቋ የማስተማሪያ መጽሀፍ 8ኛ ክፍል*፡፡ የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የትምህርት ሚኒስቴር ፡፡

ይሻሙ ጌራዎርቅ፡፡ (2002)፡፡ "በአዲስ አበባ መስተዳድር በሚገኙ በሁለት የግልና በሁለት የመንግስት አጸደ ህጻናት ውስጥ እድሜያቸው ከ4-6 ለሆኑ ህጻናት የንግግርና የንባብ ትምህርት አተገባበር ንጽጽራዊ ጥናት"፡፡ ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ አዲስአበባ (ያልታተመ)፡፡

ይታያል ወርቁ፡፡ (2003)፡፡ "የንባብ ትምህርት አተገባበር ግምገማ በቡለን ወረዳ በተመረጡ ሶስት አንደኛ ደረጃ ሙሉ ሳይክል ትምህርት ቤቶች"፡፡ ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ አዲስአበባ (ያልታተመ)፡፡

ጌታቸው አዱኛ፡፡ (1986)፡፡ "ለአስረኛ ክፍል የተመረጡ አማርኛ ቋንቋ ማስተማሪያ ምንባቦች የብቃት ደረጃ"፡፡ ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ አዲስአበባ (ያልታተመ)፡፡

ግሩም ጥበቡ:: (2003)፡፡ "የታችላይ (Bttom up) የንባብ ማስተማሪያ ሞዴል በአማርኛ ቋንቋ አንብቦ መረዳት ክሂልን ለማዳበር ያለው ውጤታማነት"፡፡ ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ አዲስአበባ (ያልታተመ)፡፡

Aarnoutse, C., & van Leeuwe, J. (1998). Relation between reading comprehension, vocabulary, reading pleasure, and reading frequency. *Educational Research and Evaluation*, *4*(2), 143–166. doi:10.1076/edre.4.2.143.6960

Aarnoutse, C., van Leeuwe, J., Voeten, M., & Oud, H. (2001). Development of decoding, reading comprehension, vocabulary and spelling during the elementary school years. *Reading and Writing*, *14*(1/2), 61–89. doi:10.1023/A:1008128417862

Abebe Damtew. (2012). Teaching Reading Skills in English as a Foreign Language through Interactive Classroom Teaching Versus Plasma Teaching with reference to Grade Ten Students in Addis Ababa. Ph.D Dissertation. Addis Ababa University, Addis Ababa.

Anderson, M. A., Tollefson, N. A., & Gilbert, E. C. (1985). Giftedness and Reading: A Cross-Sectional View of Differences in Reading Attitudes and Behaviors. *Gifted Child Quarterly*, 29, 186–189

Anderson, N. J. (2003). Teaching reading. In D. Nunan (Ed.), *Practical English language teaching* (pp. 67-86). New York: McGraw Hill Publishers.

Andreassen, R., & Bråten, I. (2010). Examining the Prediction of Reading Comprehension on Different Multiple Choice Tests. *Journal of Research in Reading*, *33*(3), 263–283.

Anmarkrud,O.,& Braten,I. (2009). Motivation for Reading Comprehension. *Learning and Individual Differences*, 19(2),252-256.

Aselefech G/kidan.(2014). The Role of Ethiopian Orthodox Church in the Development of Adult Education: The Case of Ye'abnet Timhirt Bet. Unpublished MA Thesis, AAU.

Ayele Gota.(2012). Effects of Parenting Styles, Academic Self-Efficacy, and Achievement Motivation on the Academic Achievement of University Students in Ethiopia. Ph.D Dissertation. Addis Ababa University, Addis Ababa.

Baker, L.(2003). The Role of Parents in Motivating Struggling Readers. *Reading and Writing Quarterly*, 19:87-106.

Baker,L, Scher,D & Mackler,K. (1997). Home and Family Influence on Motivations for Reading. *Educational Psychologist*,32:2, 69-82.

Baker,L.& Wigfield, A. (1999). Dimensions of Children's Motivation for Reading and Their Relations to Reading Activity and Reading Achievement. *Reading Research Quarterly*, 34(4),452-477.

Bank, B.J., Biddle, B.J. & Good, T.L. (1980). Sex roles, classroom instruction, and reading achievement.Journal of Educational Psychology, 72(2), 119–132.

Becker, G. S., & Tomes, N. (1986). Human Capital and the Rise and Fall of Families. *Journal of Labor Economics, 4* (3), S1-S39.

Berese, F & Mirazchiyski, P.(2010). Measuring Students' Family Background in Large-Scale Education Studies. Paper for the 4th IEA International Research Conference July 1-3, Gothenburg, Sweden.

Berk, L.E., Rose, M.H. & Stewart, D. (1970). Attitudes of English and American children towards their school experiences. Journal of Educational Psychology, 61, 33–40.

Bong, M. (2004). Academic motivation in Self-efficacy, Task value, Achievement Goal Orientations, and Attributional beliefs. *Journal of Educational Research*, 97, 287–297.

Bronfenbrenner, U. (1979). *The Ecology of Human Development.* Cambridge: Harvard University Press.

Bronfenbrenner, U. (1986). Ecology of the Family as a Context for Human Development: Research Perspectives. *Developmental Psychology, 22*(6), 723-742.

Burgess, S. (1997). The role of shared reading in the development of phonological awareness: A longitudinal study of middle to upper middle class children. *Early Child Development and Care, 127-128,* 191-199.

Burnett, P. (1996). Gender and grade differences in elementary school children's descriptive and evaluative self statements and self-esteem. School Psychology International, 17, 159–170.

Campbell, J., Kelly, D., Mullis, I.V.S., Martin, M.O., & Sainsbury, M. (2001). *Framework and specifications for PIRLS assessment 2001, second edition.* Chestnut Hill, MA: TIMSS & PIRLS International Study Center, Boston College.

Campbell, J.R., Kelly, D.L., Mullis, I.V.S., Martin, M.O., & Sainsbury, M. (2001). Framework and specifications for PIRLS assessment 2001 (2nd ed.). Chestnut Hill, MA: Boston College.

Carpenter, P.A., Miyake, A., & Just, M.A. (1995). Language comprehension: Sentence and discourse processing. *Annual Review of Psychology*, *46*, 91–120. doi:10.1146/annurev.ps.46.020195 .000515.

Carver, R.P., & Leibert, R.E. (1995). The effect of reading library books at different levels of difficulty upon gain in reading ability. *Reading Research Quarterly*, *30*(1), 26–48. doi:10.2307/747743

Chapman, J. W., & Tunmer, W. E. (1997). A longitudinal study of beginning reading achievement and reading self-concept. *British Journal of Educational Psychology,* 67, 279e291.

Chapman, J. W., Tunmer, W. E., & Prochnow, J. E. (2000). Early reading related skills and performance, reading self-concept, and the development of academic self-concept: a longitudinal study. *Journal of Educational Psychology*, 92, 703e708.

Chapman, J.W., & Tunmer, W.E. (1995). Development of Young Children's Reading Self-Concepts: An Examination of Emerging Subcomponents and Their

Relationship with Reading Achievement. *Journal of Educational Psychology*, *87*(1), 154–167. (Experiment 4).

Chesters J, Daly A. Do peer effects mediate the association between family socio-economic status and educational achievement? Aust J Soc Issues. 2017;52:63–77. doi: 10.1002/ajs4.3.

Cipielewski, J., & Stanovich, K.E. (1992). Predicting growth in reading ability from children's exposure to print. *Journal of Experimental Child Psychology*, *54*(1), 74–89. doi:10.1016/0022-0965(92)90018-2

Conlon, E.G., Zimmer-Gembeck, M.J., Creed, P.A., & Tucker, M.(2006). Family history, self-perceptions, attitudes and cognitive abilities are associated with early adolescent reading skills. *Journal of Research in Reading*, *29*(1), 11–32. doi:10.1111/j.1467-9817.2006 .00290.x.

Cox, K.E., & Guthrie, J.T. (2001). Motivational and Cognitive Contributions to Students' Amount of Reading. *Contemporary Educational Psychology*, *26*(1), 116–131.

Doolittle, P.; Hicks, D.; Triplett, C.; Nichols, W. and Young, C. (2006). Reciprocal Teaching for Reading Comprehension in Higher Education: A Strategy for Fostering the Deeper Understanding of Texts. *International Journal of Teaching and Learning in Higher Education. 17*(2), 106-118.

Dörnyei, Z. ( 2001). *Teaching and Researching Motivation*. London: Longman.

Dörnyei, Z. (1994). Motivation and Motivating in the Foreign Language Classroom. *The Modern Language Journal*, 78, 273-284.

Duke, N.K., & Carlisle, J. (2011). The development of comprehension. In M.L. Kamil, P.D. Pearson, E.B. Moje, & P. Afflerbach (Eds.), *Handbook of reading research* (Vol. 4, pp. 199–228). New York: Routledge.

Duncan, G. J., & Magnuson, K. (2005). Can Family Socioeconomic Resources Account for Racial and Ethnic Test Score Gaps? *The Future of Children*, *15*(1), 35-54.

Durik, A.M., Vida, M., & Eccles, J.S. (2006). Task Values and Ability Beliefs as Predictors of High School Literacy Choices: A developmental analysis. *Journal of Educational Psychology*, *98*(2), 382–393.

Eccles, J.S., & Wigfield, A. (2002). Motivational beliefs, values, and goals. *Annual Review of Psychology*, *53*, 109–132. doi:10.1146/ annurev.psych.53.100901.135153

Eccles, J.S., Wigfield, A., & Schiefele, U. (1998). Motivation to succeed. In N. Eisenberg (Ed.), *Handbook of child psychology* (Vol. IV, 5th ed., pp. 1017–1095). New York: John Wiley.

Eccles, J.S., Wigfield, A., Harold, R.D., & Blumenfeld, P.B. (1993). Age and gender differences in children's self- and task perceptions during elementary school. *ChildDevelopment*, *64,* 830–847.

Elley, W.B. (1992). *How in the world do students read?* The Hague, The Netherlands: IEA.

Elliot, A.J. (2006). The hierarchical model of approach–avoidance motivation. *Motivation and Emotion*, *30*(2), 111–116. doi:10.1007/ s11031-006-9028-7

Elliott, E.S., & Dweck, C.S. (1988). Goals: An approach to motivation and achievement. *Journal of Personality and Social Psychology*, *54*(1), 5–12. doi:10.1037/0022-3514.54.1.5

Fox, E., & Alexander, P. A. (2009). Text Comprehension: A Retrospective, Perspective, and Prospective. In S. E. Israel & G. G. Duffy (Eds.), *Handbook of Research on Reading Comprehension* (pp. 227-239). New York: Routledge.

Gaffney, J. S., & Anderson, R. C. (2000). Trends in Reading Research in United State: Changing Intellectual Currents Over Three Decades. In M. L. Kamil, P. B. Mosenthal, P. D. Pearson & R. Barr (Eds.), *Handbook of Reading Research* (Vol. III, pp. 53-98). Mahwah, New Jersey: Lawrence Erlbaum Associates, Publishers.

Gardner, R.C. (1985). *Social Psychology and Second Language Learning. The Role of Attitude and Motivation*. London: Arnold.

Gardner, R.C. (2001). Language Learning Motivation: the Student, the Teacher, and the Researcher. *Texas Papers in Foreign Language Education*, 6, 1–18.

Gonzalez, E.J. (2003). Scaling the PIRLS Reading Assessment Data. In M. Martin, I. Mullis, & A. Kennedy (Eds.), PIRLS 2001 technical report (pp. 151-168). Chestnut Hill, MA: Boston College.

Gottfried, A. E. (1990). Academic intrinsic motivation in young elementary school children. *Journal of Educational Psychology*, 82(3), 525–538.

Graham, S. (1994). Motivation in African Americans. *Review of Educational Research*, *64*, 55–118

Greaney, V., & Neuman, S.B. (1990). The Functions of Reading: A Cross- Cultural Perspective. *Reading Research Quarterly*, 25(3),172–195.

Guay, F., Marsh, H. W., & Boivin, M. (2003). Academic Self-concept and Academic Achievement: Developmental Perspectives on Their Causal Ordering. *Journal of Educational Psychology*, 95, 124–136.

Gutherie, J. T., Wigfield, A., Metsala, J. L., & Cox, K. E. (1999). Motivational and Cognitive Predictors of Text Comprehension and Reading Amount. *Scientific Studies of Reading*, 3(3), 231-256.

Guthrie, J., Wigfield, A., & You,W. (2012). Instructional Contexts for Engagement and Cognitive Predictors of Text Comprehension in Reading. In S.L. Christenson et al. (eds.), *Handbook of Research on Student Engagement*, (pp. 601-634). New York: Springer.

Guthrie, J.T., & Wigfield, A. (1999). How Motivation Fits into a Science of Reading: *A special issue of scientific studies of reading.* 3:3,199-205.

Guthrie, J.T., & Wigfield, A. (2000). Engagement and motivation in reading. In M.L. Kamil, P.B. Mosenthal, P.D. Pearson, & R. Barr (Eds.), *Handbook of reading research:* Volume III (pp. 403-422). New York, NY: Erlbaum.

Guthrie, J.T., Hoa, L.W., Wigfield, A.,Tonks, S.M, Humenick, N.M.,& Littles, E.(2007). Reading Motivation and Reading Comprehension Growth in the Latter Elementary Years. *Contemporary Educational Psychology*, 32(3),282-313.

Guthrie, J.T., McGough, K., & Wigfield, A. (1994). Measuring reading activity: An inventory. Athens, GA: *National Reading Research Center*. Instructional Resource No. 4.

Guthrie, J.T., McGough, K., Bennett, L., & Rice, M.E. (1996). Concept-oriented Reading Instruction: An Integrated Curriculum to Develop Motivations and Strategies for Reading. In L. Baker, P. Afflerbach, & D. Reinking (Eds.), *Developing engaged readers in school and home communities* (pp. 165-190). Hillsdale, NJ: Erlbaum.

Guthrie, J.T., McRae, A.C., & Klauda, S.L. (2007). Contributions of Concept-Oriented Reading Instruction to Knowledge About Interventions for Motivations in Reading. *Educational Psychologist*, *42*(4), 237–250.

Guthrie, J.T., Wigfield, A., Humenick, N. M., Perencevich, K. C., Taboada, A., & Barbosa, P.(2006). Influences of stimulating tasks on reading motivation and comprehension. *The Journal of Educational Research*, *99*(4), 232-245

Havenman, R., & Wolfe, B. (1995). The determinants of children's attainments: A review of methods and findings. *Journal of Economic Literature, 33*, 1829-1878.

Heibert, E. H., & Kamil, M. L. (2005). *Teaching and learning vocabulary : Bring research to practice.* Mahwah, NJ: Lawrence Erlbaum.

Hidi, S. (1990). Interest and its Contribution as a Mental Resource for Learning. *Review of Educational Research*, 60, 549–571.

Hidi, S., & Harackiewicz, J. M. (2000). Motivating the Academically Unmotivated: a Critical Issue for the 21st Century. *Review of Educational Research*, 70, 151–179.

Holt, N. J. (2001). Motivation as a contributing factor in second language acquisition. *The Internet TESL Journal*, 7, 66.

Hooper, M., Mullis, I.V.S.& Martin, M.O. (2017). PIRLS 2016 International Report. IEA's Progress in International Reading Literacy Study in Primary School in 40 Countries. Chestnut Hill, MA: TIMSS & PIRLS International Study Center, Boston College.

Huang, Qian (2009). Background knowledge and reading teaching. *Asian Social Science*, 5 (5), 138-139.

Ibrahim Endashaw. (2012). Practices and Contributions of Islamic Education to Modern Education in Ethiopia: the case of Bati Azhar Mesjid. Unpublished MA Thesis, AAU.

Janan, D. (2011). "Towards a New Model of Readability". Doctorial Dissertation University of Warwick institutional repository: http://go.warwick.ac.uk/wrap.

Jencks, C., & Phillips, M. (Eds.). (1998). *The black-white test score gap.* Washington, D.C.: Brookings Institution Press.

Kamil, M. L., Afflerbach, P., Pearson, P. D., & Moje, E. B. (2011). Preface: Reading Reseach in a Changing Era: An Introduction to the Handbook of Reading Research. In M. L. Kamil, P. Afflerbach, P. D. Pearson & E. B. Moje (Eds.), *Handbook of Reading Research* (Vol. IV, pp. xiii-xxvi). New York: Routledge.

Khalaji, Reza & Vafaeeseresht, Karim (2012). The impact of reading strategy trainining on the reading comprehension of Iranian EFL learners. *Journal of Language Teaching and Research, 3* (1), 135-140.

Khayyer, Mohammed. (1994)." Academic Achievement and Its Relation to Family background and Locus of Control". Doctor of Philosophy Thesis, Graduate

School of Education, University of Wollongong, 1994. http://ro.uow.edu.qu/theses/1873.

Knoll, C.L. (2000). "The Relationship Between Motivation and Reading Comprehension." Grand Valley State University .http:// scholar works. gvsu. edu/ theses.

Lau, K. (2009). Reading Motivation, Perceptions of Reading Instruction and Reading Amount: A Comparison of Junior and Senior Secondary School Students in Hong Kong. *Journal of Research in Reading*, *32*(4), 366–382.

Lau, K., & Chan, D.W. (2003). Reading Strategy Use and Motivation Among Chinese Good and Poor Readers in Hong Kong. *Journal of Research in Reading*, *26*(2), 177–190.

Law, Y. (2008). The Relationship Between Extrinsic Motivation, Home Literacy, Classroom Instructional Practices, and reading Proficiency in Second- Grade Chinese Children. *Research in Education*, *80*(1), 37–51.

Leslie, L., & Cladwell, J. (2009). Formal and Informal Measures of Reading Comprehension. In S. E. Israel & G. G. Duffy (Eds.), *Handbook of Research on Reading Comprehsion* (pp. 403). New York: Routledge.

Levy, B. A., Gong, Z., Hessels, S., Evans, M. A., & Jared, D. (2006). Understanding print: Early reading development and the contributions of home literacy experiences. *Journal of Experimental Child Psychology, 93,* 63-93.

Lin,D., Wong,K., & McBride-Chang.(2012). Reading motivation and reading comprehension in Chinese and English among bilingual students. *Read Writ* 25:717–737 DOI 10.1007/s11145-011-9297-8.

Lindo, E.J.(2007). "Family Background: A Predictor of Comprehension Difficulty in the Elementary Grades". Doctorial Dissertation. Vanderbilt University, Nashville, Tennessee.

Logan, S., Medford, E., & Hughes, N. (2011). The importance of intrinsic motivation for high and low ability readers' reading comprehension performance. *Learning and Individual Differences*, *21*(1),124–128.

Long, D.L., Oppy, B.J., & Seely, M.R. (1997). Individual differences in readers' sentence- and text-level representations. *Journal of Memory and Language*, *36*(1), 129–145. doi:10.1006/jmla.1996.2485.

Madsen, H.S.( 1983). Techniques in Testing. Oxford: Oxford: Oxford University Press.

Martin, M.O., Mullis, I.V.S., & Kennedy, A.M. (Eds.) (2003). PIRLS 2001 technical report. Chestnut Hill, MA: Boston College.

Mercurio, M. L. (2005). In Their Own Words: A Study of suburban Middle school Students Using a self Selection Reading Program. *Journal of Adolescent & Adult Literacy*, 49, 130–141.

Morgan, P. L., & Fuchs, D. (2007). Is There a Bidirectional Relationship Between Children's Reading Skills and Reading Motivation? *Exceptional Children*, 73, 165e183.

Mullis, I.V.S. & Martin, M.O. (Eds.). (2015). PIRLS 2016 Assessment Framework, 2nd Edition Chestnut Hill, MA: TIMSS & PIRLS International Study Center, Boston College.

Mullis, I.V.S., Kennedy, A., Martin, M.O., & Sainsbury, M. (2006). *PIRLS 2006 assessment framework and specifications, second edition.* Chestnut Hill, MA: TIMSS & PIRLS International Study Center, Boston College.

Mullis, I.V.S., Kennedy, A.M., Martin, M.O., Sainsbury, M. (2006). PIRLS 2006 Assessment Framework and Specifications, 2nd Edition. Chestnut Hill, MA: Boston College

Mullis, I.V.S., Martin, M.O., Foy, P. (with Olson, J.F., Preuschoff, C., Erberber, E., Arora, A., & Galia, J.) (2008). TIMSS 2007 International Mathematics Report:

Findings from IEA's Trends in International Mathematics and Science Study at the Fourth and Eighth Grades. Chestnut Hill, MA: TIMSS & PIRLS International Study Center, Boston College.

Mullis, I.V.S., Martin, M.O., Foy, P., & Drucker, K.T. (2012). *PIRLS 2011 international results in reading*. Chestnut Hill, MA: TIMSS & PIRLS International Study Center, Boston College.

Mullis, I.V.S., Martin, M.O., Gonzalez, E.J., & Kennedy, A.M. (2003). PIRLS 2001 international report: IEA's study of reading literacy achievement in primary schools in 35 countries. Chestnut Hill, MA: Boston College.

Mullis, I.V.S., Martin, M.O., Kennedy, A., Trong, K., & Sainsbury, M. (2009). *PIRLS 2011 assessment framework*. Chestnut Hill, MA: TIMSS & PIRLS International Study Center, Boston College.

Mullis, I.V.S., Martin, M.O., Kennedy, A.M., & Flaherty, C.L. (Eds.). (2002). PIRLS 2001 encyclopedia: A reference guide to reading education in the countries participating in IEA's Progress in International Reading Literacy Study (PIRLS). Chestnut Hill, MA: Boston College.

Mullis, I.V.S., Martin, M.O., Kennedy, A.M., Foy, P. (2007). PIRLS 2006 International Report. IEA's Progress in International Reading Literacy Study in Primary School in 40 Countries. Chestnut Hill, MA: TIMSS & PIRLS International Study Center, Boston College

Mullis, I.V.S., Martin, M.O., Minnich, C.A., Drucker, K.T., & Ragan, M.A. (Eds.). (2012). *PIRLS 2011 encyclopedia: Education policy and curriculum in reading (Volume 1 & 2)*. Chestnut Hill, MA: TIMSS & PIRLS International Study Center, Boston College.

Nolen, S.B. (2007). Young Children’s Motivation to Read and Write: Development in Social Contexts. *Cognition and Instruction*, *25*(2/3), 219–270.

Oakes, J. M., & Rossi, P. H. (2003). The measurement of SES in health research: Current practice and steps toward a new approach. *Social Science and Medicine*, *56,* 769-784.

Paris, S. G., & Hamilton, E. E. (2009). The Development of Children' Reading Comprehension. In S. E. Israel & G. G. Duffy (Eds.), *The Development of Children's Reading Comprehension* (pp. 32-53). New York: Routledge.

Paris, S.G., Wasik, B.A., & Turner, J.C. (1991). The development of strategic readers. In R. Barr, M.L. Kamil, P. Mosenthal, & P.D. Pearson (Eds)., *Handbook of reading research* (Vol. 2, pp. 609–640). White Plains, NY: Longman.

Patterson, C. J., Kupersmidt, J. B., & Vaden, N. A. (1990). Income Level, Gender, Ethnicity, and Household Composition as Predictors of Children's School- Based Competence. *Child Development, 61*, 485-494.

Pearson, P. D. (2009). The Roots of Reading Comprehension Instruction. In S. E. Israel & G. G. Duffy (Eds.), *Handbook of Research on Reading Comprehension* (pp. 3-31). New York: Routledge.

Ryan, R. M., & Deci, E. L. (2000). Intrinsic and Extrinsic Motivations: Classic Definitions and New Directions. *Contemporary Educational Psychology*, 25, 54–67.

Samuelstuen, M. S., & Bråten, I. (2007). Examining the Validity of Self-Reports on Scales
Measuring Students' Strategic Processing. *British Journal of Educational Psychology*, 77, 351–378.

Schaffner, E., Schiefele, U., & Ulferts, H. (2013). Reading Amount as a Mediator of the Effects of Intrinsic and Extrinsic Reading Motivation on Reading Comprehension. *Reading Research Quarterly*, 48(4) pp. 369–385.

Schiefele, U. (1999). Interest and Learning from Text. *Scientific Studies of Reading*, 3(3), 257–279.

Schiefele, U., Scheffner, E., Moller,.& Wigfield,A. (2012). Dimensions of Reading Motivation and Their Relations to Reading Behavior and Competence. *Reading Research Quarterly*,47(4), 427-463.

Schmidt, R. & Watanabe, Y. (2001). Motivation, strategy use, and pedagogical preferences inforeign language learning. In Z. Dörnyei & R. Schmidt (Eds.). *Motivation and secondlanguage acquisition* (Technical Report No. 23, pp. 313–359). Honolulu: University ofHawaii, Second Language Teaching and Curriculum Center.

Schunk, D. H. (1989). Self-efficacy and achievement behaviors. *Educational Psychology Review*, *1*(3),173-208. Retrieved from http://www.jstor.org/stable/23359217. Accessed: 07/11/ 2014 09:34

Schunk, D. H. (1995). Self-efficacy, motivation, and performance. *Journal of Applied Sport Psychology, 7*(2), 112-137. Retrieved from http://www.taylorandfrancis.com/

Sheridan, M, E. (1981). Theories of Reading and Implications for Teachers. *Reading Horizons*. 22, (1).

Sirin, S. R. (2005). Socioeconomic status and academic achievement: A meta-analytic review of research. *Review of Educational Research*, *75* (3), 417-453.

Solheim, O. J. (2011). The impact of reading self-efficacy and task value on reading comprehension scores in different item formats. *Reading Psychology*, *32*(1),1-27. doi:10.1080 /02702710903256601.

Stahl, S. A. (1998). Understanding Shifts in Reading and Its Instruction. *Peabody Journal of Education*, *73*(3/4), 31-67.

Steinmayr, R., & Spinath, B. (2008). Sex Differences in School Achievement: What are the Roles of Personality and Achievement Motivation? *European Journal of Personality*, 22, 185e209

Taboada, A. & Buehl, M. M. (2012). Teachers' conceptions of reading comprehension and motivation to read. *Teachers and Teaching: theory and practice*, *18*(1),101-122,doi: 10.1080/13540602.2011.622559.

Taboada, A., Tonks, S.M., Wigfield, A., & Guthrie, J.T. (2009). Effects of Motivational and Cognitive Variables on Reading Comprehension. *Reading and Writing*, *22*(1), 85–106.

Wainer, A& Piper, B. (2010). Ethiopian Early Grade Reading Assessment: Data Analytic Report: Language and Early Learning. United states Agency for International Development (USAID/ETHIOPIA).

Walcutt, C. C. (1967). Reading A Professional Definition. *The Elementary School Journal, 67*(7), 363-365.

Wang, J.H., & Guthrie, J.T. (2004). Modeling the Effects of Intrinsic Motivation, Extrinsic Motivation, Amount of Reading, and Past Reading Achievement on Text Comprehension Between U.S. and Chinese students. *Reading Research Quarterly*, *39*(2), 162–186. doi:10.1598/RRQ.39.2.2.

Wigfield, A. (1997). Reading Motivation: A domain- Specific Approach to Motivation. *Educational Psychologist,* 32,59-68.

Wigfield, A., & Eccles, J. S. (2000). Expectancy–value theory of achievement motivation. *Contemporary Educational Psychology*, 25, 68–81

Wigfield, A., & Guthrie J.T. (1997). Relations of Children's Motivation for Reading to the Amount and Breadth of Their Reading. *Journal of Educational psychology*, 89(3), 420-432.

Wigfield, A., Guthrie, J.T., Perencevich, K. C., Taboada, A., Lutzklauda, S., Mcrae, A., & Barbosa, P. (2008). Role of reading engagement in mediating effects of reading 219 comprehension instruction on reading outcomes. *Psychology in the Schools*, *45*(5),432- 445. doi: 10.1002/pits.20307.

Wigfield, A., Guthrie, J.T., Tonks, S., & Perencevich, K. C. (2004). Children's motivation for reading: Domain specificity and instructional influences. *The Journal of Educational Research*, *97*(6),299-309. Retrieved from http://www.jstor.org/stable/27548045. Accessed : 07/11/2014 09:33.

Wood, K. D., Edwards, A. T., Hill-Miller, P., & Vintinner, J. (2006). Research into practice: Motivation, self-efficacy, and the engaged reader. *Middle School Journal*, *37*(5),55-61. Retrieved from http://www.jstor.org/stable/23043941. Accessed: 07/11/2014 09:24

Zwaan, R.A., & Singer, M. (2003). Text comprehension. In A.C. Graesser, M.A. Gernsbacher, & S.R. Goldmann (Eds.), *Handbook of discourse processes* (pp. 83–121). Mahwah, NJ: Erlbaum.

# አባሪዎች (appendex)

## አባሪ ሀ፡- የዋናው ጥናት መረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች

### ሀ.1. የቤተሰብ ዳራ መጠይቅ

**አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ**

**የስነሰብ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና ኮሚኒኬሽን ኮሌጅ**

**የአማርኛ ቋንቋ፣ ስነጽሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል**

**ድህረ ምረቃ መርሀ ግብር**

በባህርዳር ወረዳ በሚገኙ የአንደኛ ደረጃ ሁለተኛ ሳይክል (በአምስተኛና በሰባተኛ) ክፍል ተማሪዎች የሚሞላ የጽሁፍ መጠይቅ፡-

**ውድ ተማሪዎች፡-** የቤተሰብ ዳራ የአንብቦ መረዳት ችሎታና የማንበብ ተነሳሽነትን የመተንበይ ድርሻ፤ በአምስተኛና በሰባተኛ ክፍል ተማሪዎች ተተኳሪነት በሚል ርዕስ ለሚጠና የዶክትሬት ዲግሪ ማሟያ ፅሁፍ በመረጃ ሰጭነት እንድትሳተፉ በክብር ተጋብዛችኋል፡፡

የዚህ መጠይቅ ዋና አላማም ለተጠቀሰው የጥናት ርዕስ መረጃ ለመሰብሰብ ነው፡፡ የሚገኘው መረጃ ለጥናቱ ከታሰበው ተግባር ውጭ የማይውል መሆኑን በቅድሚያ አረጋግጣለሁ፡፡ የምትሰጧቸው መልሶች በትክክል የእናንተን እውነተኛ ስሜትና እምነት የሚያንፀባርቁ እንዲሆኑ አደራ እላለሁ፡፡ ስለትብብራችሁና ታማኝነታችሁ በቅድሚያ አመሰግናለሁ፡፡

ይህ መጠይቅ ሁለት ክፍሎች አሉት የመጀመሪያው ክፍል ስለእናንተ አጠቃላይ መረጃ የሚጠይቅ ሲሆን ሁለተኛው ክፍል የቤተሰብ ዳራን የሚለካ መጠይቅ የያዘ ነው፡፡ አንዳቸው ካለአንዳቸው ሙሉ ስለማይሆኑ ሁሉንም ጥያቄዎች በትክክል እንድትመልሱ አደራ እላለሁ፡፡

**ማሳሳቢያ፡-** መጠይቁን ከጓደኛ ጋር ተመካክሮ መሙላት የተከለከለ ነው፡፡

**ክፍል አንድ፡- ግለሰባዊ መረጃ ስለእናንተ ትክክ የሆነውን በባዶ ቦታው ላይ ይህን(✓)**

ምልክት በማድረግ አረጋግጡ፤ትክክለኛውን መልስ ከፊት ለፊት አስፍሩ::

1. **ፆታ፡-** ሴት________ ወንድ________

3. **እድሜ፡-** ________

4. **የክፍል ደረጃ** ፡- ________

**ክፍል ሁለት፡- ቤተሰባዊ ዳራ የሚለካ መጠይቅ**

*መመሪያ፡-* ከዚህ ቀጥሎ የአንተን/የአንችን ቤተሰቦች የሚመለከቱ ጥያቄዎች ቀርበዋል፡፡ ለእያንዳንዱ ጥያቄ በምርጫ መልክ ከቀረቡት መልሶች በትክክል እኔን ይገልጻኛል የሚለውን አማራጭ በማክበብ መልስ ይስጡ፡፡

1. በአሁኑ ጊዜ ከማን ጋር ትኖራለህ/ትኖሪያለሽ?
   (1) ከአባቴ እና ከእናቴ ጋር
   (2) ከአባቴ ጋር
   (3) ከእናቴ ጋር
   (4) ከላይ ከተጠቀሱት ውጭ ከሆነ ግለጽ/ጪ ____________________________
2. በእናንተ ቤተሰብ ውስጥ ምን ያክል ሰው ይኖራል?

   ____________________________
3. የአባትህ/ሽ (የወንድ አሳዳጊህ/ሽ) የትምህርት ደረጃ፡-
   (1) መደበኛ ትምህርት ያልተማረ
   (2) አንደኛ/መለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ
   (3) ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ
   (4) ሠርቲፊኬት/ዲፕሎማ
   (5) የመጀመሪያ ዲግሪ እና/ወይም በላይ
4. የእናትህ/ሽ (የሴት አሳዳጊህ/ሽ) የትምህርት ደረጃ፡-
   (1) መደበኛ ትምህርት ያልተማረች
   (2) አንደኛ/መለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ
   (3) ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ
   (4) ሠርቲፊኬት/ዲፕሎማ
   (5) የመጀመሪያ ዲግሪ እና/ወይም በላይ

5. በቤተሰብህ/ሽ ከፍተኛው የትምህርት ደረጃ የትኛው ነው

(1) አንደኛ/መለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ

(2) ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ

(3) ሠርቲፊኬት/ዲፕሎማ

(4) የመጀመሪያ ዲግሪ እና/ወይም በላይ

6. የአባትህ/ሽ (የወንድ አሳዳጊህ/ሽ) ስራ

1. ገበሬ 2. ነጋዴ

3. የመንግስት ሰራተኛ 4. ሌላ ካለ ይገለጽ............

7. የእናትህ/ሽ (የሴት አሳዳጊህ/ሽ) ስራ፡-

1. የቤት እመቤት 2. ገበሬ 3. ነጋዴ

4. የመንግስት ሰራተኛ 5. ሌላ ካለ ይገለጽ .......

8. ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ነገሮች በቤትህ/ሽ ውስጥ አሉ

| | | | |
|---|---|---|---|
| 1. | የግል መጽሀፍት | 1. አለኝ | 2. የለኝም |
| 2. | የማጥኛ ጠረጴዛና ወንበር | 1. አለኝ | 2. የለኝም |
| 3. | የግል ክፍል | 1. አለኝ | 2. የለኝም |
| 4. | የግል አልጋ | 1. አለኝ | 2. የለኝም |

5. የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች (ዲክሽነሪ፣ ካልኩሌተር ወ.ዘ.ተ.)

1. አለኝ 2. የለኝም

9. የቤተሰቦችህ/ሽ ገቢ በወር ምን ያህል ነው?

1. ከ1000 ብር በታች 3. 3001- 5000 ብር 5. ከ10,000 ብር በላይ

2. ከ1000 እስከ 3000 ብር 4. 5001- 10,000 ብር

10. በቀን ስንት ጊዜ ትመገባለህ/ሽ

1. አንድ ጊዜ 2. ሁለት ጊዜ 3. ሶስት ጊዜ

11.የቤተሰቦችህ ገቢ ከጎረቤትና ከአካባቢው ጋር ሲነጻጸር

1. ከፍተኛ 2. ተመሳሳይ 3. ዝቅተኛ

12.ቤተሰቦችህ ከሚከተሉት በትምህርት ቤት ጉዳዮች ውስጥ በየትኞቹ ይሳተፋሉ?

| | | |
|---|---|---|
| 1. የወላጅ ስብሰባ | 1. አዎ | 2. የለም |
| 2. በትምህርትቤት የልማት ጉዳዮች | 1. አዎ | 2. የለም |
| 3. የተማሪዎች የዲሲፒሊን ኮሚቴ | 1. አዎ | 2. የለም |

## ሀ.2. የአምስተኛ ክፍል የአንብቦ መረዳት ችሎታ መለኪያ ፈተና

**አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ**

**የስነሰብ፣ የቋንቋዎችጥናት፣ የጆርናሊዝምና ኮሚኒኬሽን ኮሌጅ**

**የአማርኛቋንቋ፣ ስነጽሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል**

**ድህረ ምረቃ መርሀ ግብር**

**ለአምስተኛ ክፍል ተማሪዎች የተዘጋጀ የአንብቦ መረዳት መለኪያ ፈተና**

***ውድተማሪዎች***፡- ይህ የአንብቦ መረዳት መለኪያ ፈተና የተዘጋጀው "የቤተሰብ ዳራ አንብቦ መረዳት ችሎታንና የማንበብ ተነሳሽነትን የመተንበይ ድርሻ፤ በአምስተኛና በሰባተኛ ክፍል ተማሪዎች ተተኳሪነት" በሚል ርዕስ ለሚሰራው ምርምር መረጃ ለመሰብሰብ ነው፡፡ ስለዚህ ከዚህ በታች የቀረበውን ምንባብ መሰረት በማድረግ ለቀረቡት ጥያቄዎች በትክክል ምላሽ እንድትሰጡ እጠይቃለሁ፡፡

***መለያ ቁጥር*****.................................** ***መማሪያ ክፍል*****.......................**

### የአጋዘን አስተኔ

የአጋዘን አስተኔ ስምንት ዓይነት ዝርያዎች አሉት፡፡ ሁሉም ዝርያዎች በአፍሪካ ብቻ ይገኛሉ፡፡ ከእነዚህም መካከል አንዱ በኢትዮጵያ ብቻ የሚገኘው የደጋ አጋዘን ነው፡፡ በብዙ የአፍሪካ አገሮች የሚገኙት አጋዘን፣ አምባራይሌ፣ ድኩላና ውድንቢ የዚህ ቡድን አባሎች ናቸው፡፡ የአጋዘን አስተኔዎች ከሌሎች የዱር እንስሳት ተለይተው የሚታወቁባቸው የጋራ ባህርያት አሏቸው፡፡ ሁሉም ወንዶች ጥምዝ ቀንዶች አሏቸው፡፡ ከውድንቢ ሴቶች በስተቀር የሌሎቹ ሴት ዝርያዎች ቀንድ የላቸውም፡፡ በተጨማሪም የአጋዘን አስተኔዎች በሆዳቸውና በደረታቸው የሚወርዱ ነጫጭ መስመሮች አሏቸው፡፡ ቅጠላ ቅጠልም ይበላሉ፡፡

የአጋዘን አስተኔዎች እንደተመሳሰሏቸው ሁሉ ልዩነትም አላቸው፡፡ ይህንንም የደጋ አጋዘንን፣ ድኩላንና ውድንቢን በመመልከት መረዳት ይቻላል፡፡ የደጋ አጋዘኖች በኢትዮጵያ ብቻ የሚገኙ የአጋዘን አስተኔዎች ዝርያ ናቸው፡፡ ወንዶቹ ጥምዝ ቀንድ ሲኖራቸው ደረታቸውም አበጥ ያለ ሆኖ ባለሻኛ ናቸው፡፡ ሴቶቹ ግን ቀንድ የላቸውም፡፡ የወንዶቹ የሰውነት መጠን ከሴቶቹ ይበልጣል፡፡ ክብደታቸውም እጥፍ ይሆናል፡፡ የሁሉም የፀጉር ቀለም መደቡ **የገረጣ** ጉበት የመሰለ ቡናማ ቢጤ ነው፡፡ የተበታተኑ ነጫጭ ነጠብጣቦችና ከጀርባቸው ወደሆዳቸውና ወደደረታቸው የሚወርዱ ነጫጭ መስመሮች አላቸው፡፡ ከአርሲ ተራራዎች ጀምሮ በባሌ ተራራዎች አልፎ እስከ ሐረርጌ የጨርጨር ተራራዎች ድረስ ይገኛሉ፡፡

የደጋ አጋዘኖች በአብዛኛው ቅጠላቅጠል ቢበሉም አንዳንዴ ሣር ሲበሉ ይታያሉ፡፡ በተጨማሪም የቲማቲም ዝርያዎችንና በበጋ ወራት ደግሞ የረገፉ የኮሶ ቅጠሎችን ይበላሉ፡፡

**ድኩላ፡-** ድኩላዎች መካከለኛ የሰውነት መጠን ያላቸው፣ ከሰሃራ በስተደቡብ በብዙ ሥፍራዎች የሚገኙ እንስሳት ናቸው፡፡ ወንዶቹ ከ40-80 ኪ.ግ.፣ ሴቶቹ ደግሞ ከ25- 60 ኪ.ግ. ይመዝናሉ፡፡ ድኩላዎች ደኖች በሚበዙበት አካባቢ ይኖራሉ፡፡ ብቸኝነትን ስለሚመርጡ መንጋ ሠርተው አይገኙም፡፡ አብረው የሚኖሩት እናትና የመጨረሻ ልጇ ብቻ ናቸው፡፡ ራሳቸውን ከጠላቶቻቸው የሚከላከሉት በጫካ ውስጥ በመደበቅ ነው፡፡ የፀጉራቸው ቀለምም ከእይታ ለመከላከል ያመቻቸዋል፡፡ ድኩላዎች በአብዛኛው ቅጠላ ቅጠል የሚመገቡ ቢሆኑም **ጨሌ ሣርም** ይግጣሉ፡፡ ቀን ቀን ቅጠላ ቅጠል ሲበሉ፣ ሌሊት ሌሊት ደግሞ ሣር ይግጣሉ፡፡ አብዛኛውን ጊዜ ከውኃ ርቀው መኖር አይመርጡም፡፡

በኢትዮጵያ ሁለት ዓይነት ድኩላዎች ይገኛሉ፡፡ አንደኛው በባሌ ተራራዎችና በሌሎች ከፍተኛ ሥፍራዎች የሚገኘው የምኒሊክ ድኩላ የሚባለው ነው፡፡ ይህም በኢትዮጵያ ብቻ የሚገኝ የአጋዘን አስተኔ ቡድን አባል ነው፡፡ ሁለተኛው የድኩላ ዓይነት ግን ከኢትዮጵያ ውጭ በሌሎች አገሮች ይገኛል፡፡

**ውድንቢ**፡- ከአጋዘን አስተኔዎች ሁሉ ግዙፉ ውድንቢ ነው፡፡ ወንዱ በአማካይ ከ500-600 ኪ.ግ.፣ ሴቷ ከ340-445 ኪ.ግ. ይመዝናሉ፡፡ ሁለቱም ፆታዎች አጫጭር ጥምዝ

ቀንዶች አሏቸው፡፡ የወንዶቹ ቀንዶች ርዝመት 54 ሳ.ሜ. ነው፡፡ የሴቶቹ ደግሞ 60.5 ሳ.ሜ. ይሆናል፡፡ የሁለቱም ፆታዎች ጭራ እንደከብት ጅራት ረዘም ብሎ ከጫፉ ላይ ጎፈር አለው፡፡ የፀጉራቸው ቀለም ፈዛዛ ቡኒ ሆኖ ከዕድሜ መጨመር ጋር እየጠቆረ የሚሄድ ነው፡፡ ከ10-16 የሚሆኑ ነጫጭ መስመሮች ከጀርባቸው ይወርዳሉ፡፡ እንዲሁም ጠቆር ያለሻኛና በቅልጥሞቻቸው ላይ ነጫጭ ምልክቶች አሏቸው፡፡ ወንዶቹ ግን በግንባራቸውና በአፍንጫቸው ላይ ጥቋቁር ጎፈሬ አላቸው፡፡ በተጨማሪ አንገታቸው ግዙፍ ሆኖ **ከርዳዳ ጋማ** አለበት፡፡

ውድንቢዎች በኢትዮጵያ በኦሞ ፓርክ፣ ከኢትዮጵያ ውጪ ደግሞ በደቡብ ሱዳን፣ በደቡብ ሱማሌ፣ በኬንያና በታንዛንያ ይገኛሉ፡፡ በየትኛውም የአየር ንብረት ውስጥ መኖር ይችላሉ፡፡ የተለያዩ ዕፅዋትን ይመገባሉ፤ ላልተወሰነ ጊዜ ያለውኃ መኖር ይችላሉ፡፡ ሌሊትም፣ ቀንም ይመገባሉ፡፡ ኑሯቸው ማኅበራዊ ሲሆን እስከ 100 አባላት ያሉት መንጋ በብዙ ቦታዎች ማየት የተለመደ ነው፡፡

(ሰለሞን ይርጋ፡፡ 2000፡፡ አጥቢዎች፡፡ ከገፅ 8-24 ለውጥ ተደርጎበት የቀረበ፡፡)

**መለያ ቁጥር ………………………………… መማሪያ ክፍል ……………….**

## ትዕዛዝ አንድ፡- ትክክል የሆነውን እውነት ስህተት የሆነውን ደግሞ ሀሰት በማለት መልስ ስጡ፡፡

------------- 1. የደጋ አጋዘን በአፍሪካ ብቻ የሚገኝ የዱር እንስሳ ነው፡፡

------------- 2. ሴት አጋዘኖች ከሌሎች እንስሳት የሚለያቸው ጥምዝ ቀንድ ስላላቸው ነው፡፡

------------- 3. ወንድ የደጋ አጋዘን በክብደት ከሴቷ በእጥፍ ይበልጣታል፡፡

------------- 4. አጋዘኖች አንዳንዴ ስጋ ሊመገቡ ይችላሉ፡፡

------------- 5. ድኩላዎች ላልተወሰነ ጊዜ ከውሀ ርቀው መኖር ይችላሉ፡፡

------------- 6. የሚኒልክ ድኩላ በኢትዮጵያ ብቻ የሚገኝ የአጋዘን አስተኔ ዝርያ ነው፡፡

------------- 7. የሴት ውድንቢዎች ቀንድ እርዝመት ከወንዶች ይበልጣል፡፡

-------------- 8. ግዙፉ የአጋዘን ዝርያ ድኩላ በመባል ይታወቃል፡፡

------9. የውንዲቢዎች የጸጉር ቀለም እድሜያቸው እየጨመረ ሲሄድ እየጠቆረ ይሄዳል፡፡

------------- 10. ውንድቢዎች የሚመቻቸው ቆላማ የአየር ንብረት ነው፡፡

**ትዕዛዝ ሶስት፡- በ"ሀ" ስር ለተዘረዘሩት አረፍተ ነገሮች ትክክለኛውን መልስ ከ"ለ" በመምረጥ አዛምዱ፡፡**

| ሀ. | ለ. |
|---|---|
| -------- 11.ሁለቱም ፆታዎች አጫጭር ጥምዝ ቀንዶች አሏቸው | 1. ድኩላ |
| -------- 12.ለመኖር ተራራማ ቦታዎችን ይመርጣሉ | 2. የደጋ አጋዘን |
| -------- 13. ደኖች በሚበዙበት አካባቢ ይኖራሉ | 3. ውንዲቢ |
| -------- 14. በበጋ የረገፈ የኮሶ ቅጠል ይመገባሉ | |
| --------- 15.አንገታቸው ግዙፍ ሆኖ ከርዳዳ ጋማ አለበት | |
| ---------- 16. ጠቆር ያለሸኛና በቅልጥሞቻቸው ላይ ነጫጭ ምልክቶች አሏቸው | |
| ------------17.አብረው የሚኖሩት እናትና የመጨረሻ ልጇ ብቻ ናቸው | |
| ----------- 18.የጸጉራቸው ቀለም ራሳቸውን ለመደበቅ ይረዳቸዋል | |
| ----------- 19.የቲማቲም ዝርያ ይመገባሉ | |
| ---------- 20. ብቸኝነት ይመርጣሉ | |

**ትዕዛዝ ሶስት፡- ከዚህ በታች ለቀረቡት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ የያዘውን ፊደል በመምረጥ መልስ ስጡ፡፡**

----------- 21. በኢትዮጵያ ብቻ የሚገኘው የአጋዘን ዝርያ የትኛው ነው?

1. አምባራይሌ 2. የደጋ አጋዘን 3. ድኩላ 4. ውንድቢ

------------ 22. መደቡ <u>የገረጣ</u> ጉበት የመሰለ ነው፡፡ የተሰመረበት ቃል ትርጉም

1. የተበላሸ 2. የወየበ 3. የነጣ 4. የጠራ

-------------23. ቀንድ ያላቸው ሴት የአጋዘን ዝርያዎች ምን በመባል ይታወቃሉ፡፡

1. ውንድቢ 2. ድኩላ 3. ደጋአጋዘን 4. አምባራይሌ

--------- 24. አጋዘን አስተኔዎች የጋራ ባህርይ <u>**ያልሆነው**</u> የቱ ነው?

1. ቅጠላ ቅጠል ይበላሉ
2. በሆዳቸው የሚወርድ ነጭ መስመር አለ
3. ሁሉም ጥምዝ ቀንድ አላቸው
4. በደረታቸው የሚወርድ ነጭ መስመር አለ

--------- 25. የፀጉራቸው ቀለምም ከእይታ ለመከላከል ያመቻቸዋል ሲል ምን ማለቱ ነው?

1. ጸጉራቸው እንዳዩ ያደርጋቸዋል                3. እይታቸው ደካማ ነው
2. ቀለማቸው ጠላት እንዳያያቸው ይረዳቸዋል        4. ጸጉራቸው ቀለም የለውም

-----------26. **ጨሌ ሣርም** ይግጣሉ፡፡ የተሰመረበት ቃል ትርጉም ------ ነው፡፡

1. የጌጥ ሳር        2. ለምለም ሳር        3. ሙጃ ሳር        4. የቤት ሳር

-----------27. ውንዲቢዎች ከሚገኙባቸው ቦታዎች የማይጠቀሰው?

1. በኢትዮጵያ    2. ደቡብ ሱዳን    3. ግብጽ    4.ታንዛኒያ

----------- 28. ጠቆር ያለ ሻኛ አላቸው፡፡ የተሰመረበት ቃል ትርጉም

1. ደረት    2. ትከሻ    3. ጫንቃ    4. ፊሪምባ

----------29. ውንድቢዎች ኑሯቸው ማህበራዊ ነው ሲባል ምን ማለት ነው?

1. ማህበር ይጠጣሉ                3. በጋራ ይኖራሉ
2. እንደ ሰው ይኖራሉ              4. ጠላት ይፈራሉ

----------- 30. **ከርዳዳ ጋማ** ማለት ምን ማለት ነው

1. ጠንካራ ጀርባ 2. ጠንካራ ሻኛ    3. ሸካራ ማጅራት    4. ሸካራ አንገት

## ሀ.3. የሰባተኛ ክፍል የአንብቦ መረዳት ችሎታ መለኪያ ፈተና

**አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ**

**የስነሰብ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና ኮሚኒኬሽን ኮሌጅ**

**የአማርኛ ቋንቋ፣ ስነጽሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል**

**ድህረ ምረቃ መርሀግብር**

**ለሰባተኛ ክፍል ተማሪዎች የተዘጋጀ የአንብቦ መረዳት መለኪያ ፈተና**

**ውድ ተማሪዎች፡-**ይህ የአንብቦ መረዳት መለኪያ ፈተና የተዘጋጀው "የቤተሰብ ዳራ አንብቦ የመረዳት ችሎታንና የማንበብ ተነሳሽነትን የመተንበይ ድርሻ፤ በአምስተኛና በሰባተኛ ክፍል ተማሪዎች ተተኳሪነት" በሚል ርዕስ ለሚሰራው ምርምር መረጃ ለመሰብሰብ ነው፡፡ ስለዚህ ከዚህ በታች የቀረበውን ምንባብ መሰረት በማድረግ ለቀረቡት ጥያቄዎች በትክክል ምላሽ እንድትሰጡ እጠይቃለሁ፡፡

**የፈተና መለያ ኮድ…………………… መማሪያ ክፍል…………………..**

### ደጃዝማች በላይ ዘለቀ

ደጃዝማች በላይ ዘለቀ ከአባታቸው ከባሻ ዘለቀ ላቀውና ከእናታቸው ከወይዘሮ ጣይቱ አሰኔ በ1904 ዓ.ም. ተወለዱ፡፡ አባታቸው ጎጃም ውስጥ የብቸና ሰው ሲሆኑ፣ እናታቸው ደግሞ ወሎ የጫቀታ ተወላጅ ናቸው፡፡ ከፊታውራሪ እምቢአለ ጋር በተፈጠረ ግጭት በ1916 ዓ.ም. አባታቸው ከወንድማቸው ጋር ተገደሉባቸው፡፡ የአባታቸውን አሰቃቂ አገዳደል የተመለከቱት በላይ ዘለቀ አባይን ተሻግረው ወደ እናታቸው የትውልድ ቦታ፣ ወደ ጫቀታ ሄዱ፡፡ ከዚያም በደንብ ተዘጋጅተው የአባታቸውን ገዳዮች ለመፈለግ ወደ ጎጃም ተመለሱ ደጃዝማች በላይ ዘለቀ **በሽፍትነት ተሠማርተው** የአባታቸውን ገዳዮች በማፈላለግ ላይ እያሉ በ1928 ዓ.ም. ኢትዮጵያ በጣሊያን **ተወረረች**፡፡ ከዚያም ለአባታቸው ገዳይ **የታጠቁትን** መሣሪያ "አገሬ ትበልጥብኛለች" በማለት በጣሊያን ላይ አዞሩ፡፡ በወቅቱ በላይ ዘለቀ የ24 ዓመት ወጣት ስለነበሩ፣ ሀገር የወረረውን የጣሊያንን ጦር ለመውጋት ቆርጠው ተነሱ፡፡ ከዚያም ቁጥሩ ከ200 እስከ 300 የሚደርስ ጦር

በሥራቸው ማሰባሰብ ቻሉ። በመቀጠልም፣ "እናት ሀገሬ ኢትዮጵያ ስትደፈር ከማየት ሞቴን እመርጣለሁ። የፈራህ ልቀቀኝ! ለውድ እናት ሀገርህ መስዋዕት ለመሆን የምትፈልግ ሁሉ እኔን ተከተለኝ!" ብለው ቆራጥ ውሣኔያቸውን ሰጡ። በዚህ ጊዜ በታማኝነት አብረዋቸው የነበሩት ጓደኞቻቸው ወደ ጦርነቱ ባልገቡትና በላይ ዘለቀን ክደው ወደ ጠላት ጦር በገቡት ከሃዲ ጓደኞቻቸው ላይ የእንጉርጉሮ ግጥም ገጠሙባቸው።

ይህንን አንበሳ ጀግናውን ከድታችሁ፣

ኧረ ከምን ጊዜው ለጣሊያን ገባችሁ።

እምትወዱት ጣሊያን እሱ ካዋጣችሁ፣

ልቅምቅም አድርጎ ከነጫጬታችሁ፣

ከትውልድ ሀገሩ እዚያው ይውሰዳችሁ።

እኛ ለአገራችን ለኢትዮጵያ ባንዲራ፣

እንታገላለን በጭብጥ ሽንብራ።

እያሉ ተስፋቸውን ባለመቁረጥ ትግላቸውን ቀጠሉ። በላይ ዘለቀ ጎጃም ውስጥ የጠላት ጦር መቆሚያና መቀመጫ እንዳይኖረው በማድረግ ለኢትዮጵያ ከፍተኛ ውለታ ያበረከቱ ጀግና ናቸው። ለምሣሌ ለምጨን ከተባለ ቦታ በግንቦት ወር 1928 ዓ.ም. ከጣሊያን ፋሽስት ጋር ገጥመው ሲዋጉ ከወገን በኩል ጥቂት የቆሰለና የሞተ ቢኖርም ከጠላት በኩል ግን ብዙ ገድለውና አቁስለው የድሉ ባለቤት ሆነዋል። ደጃዝማች በላይ ዘለቀ ከጠላት ጋር መዋጋት እንደጀመሩ በጥቂት ጊዜ ውስጥ በአካባቢው ሕዝብ ዘንድ ታዋቂ የአርበኛ መሪ እየሆኑ መጡ።

በአምስት ዓመቱ የአርበኝነት ትግልም ደጃዝማች በላይን ለማግኘት ጠላት ባደረሰው ጥቃት በአካባቢው በርካታ ሕዝብ ፈጅቷል። ነገር ግን ተከታታይ ዘመቻ እያደረገ የውጊያ ተግባር ቢፈፅምም ደጃዝማች በላይን ለመግደል ሳይቻለው ቀረ። በዚህም ደጃዝማች በላይ ዘለቀ ድል አድራጊነታቸው መለያቸው እየሆነ መጣ።

ከአምስት ዓመቱ ተጋድሎ በኋላ ብዙም ሳይቆዩ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ደጃዝማች በላይ ዘለቀን የብቸና ገዥ አድርገው ሾሟቸው። ሆኖም በዚያ ወቅት ቀድሞ ከጣሊያን ወገን ተሰልፈው አርበኞቹን ሲዋጉ የነበሩ **ባንዳዎች** በአካባቢው ስለነበሩ፣ ደጃዝማች በላይ ዘለቀ ከንጉሡ ጋር ጤነኛ የሥራ ግንኙነት እንዳይፈጥሩ መሰናክል ሆኗቸው። እነዚህ ባንዳዎች ለንጉሡ የሆነ ያልሆነ ወሬ በማቀበል በደጃዝማች በላይ ዘለቀ ላይ ጦር እንዲዘምት አስደረጉ። ይህ ሁኔታ ለህይወታቸው አስጊ መሆኑን የተረዱት ደጃዝማች በላይ ጓደኞቻቸውን ይዘው ወደ ሶማ ተራራ ወጡ። ጠላቶቻቸው ከ25 ቀናት ተከታታይ ውጊያ በኋላ እነ ደጃዝማች በላይ ዘለቀን ሊረቱ እንደማይችሉ ገመቱ። ከዚያም ከንጉሡ መልዕክት እንደ ተላከ አስመስለው "ምረነዋል ይምጣ" የሚል የምሕረት ቃል በውሸት በማስላካቸው እነደጃዝማች በላይ ከሶማ ወርደው እጃቸውን ሰጡ። ሆኖም **እጅ ከሰጡ** በኋላ በእሥረኛ ደንብ ተይዘው ወደ አዲስ አበባ መጥተው በውጊያ ላይ እንደተማረከ ሰው በጥፋተኝነት ተከሰሱና ሞት ተፈረደባቸው። ሆኖም የሞት ፍርዱ አርበኞችን ስላስቆጣ ወደ ዕድሜ ይፍታህ ተለውጦ ከመስከረም 1936 ዓ.ም. ጀምሮ ወሊሶ በደጃዝማች በቀለ ወያ እጅ እንዲታሰሩ ተደረገ።

ከወሊሶ እሥር ቤት ሊያመልጡ ይችላሉ የሚል **ጭምጭምታ** ተሰማ ተብሎ ወደ አዲስ አበባ መጥተው ደጃዝማች ውቤ ሰፈር በነበረው ወህኒ ቤት ታሰሩ። የታሰሩትም የጣሊያን ሹም ሆኖ አሳራቸውን ሲያሳያቸው ከኖረው ከጣሊያኑ ደጃዝማች ማሞ ኃይለ ሚካኤል ጋር ነበር። እነዚህ ሁኔታዎች **ጎምዛዛ** ስለሆኑባቸው ለማምለጥ ሙከራ አደረጉ። ሆኖም ያደረጉት ሙከራ ሳይሳካ ቀርቶ ሱሉልታ ከተባለ ቦታ ተያዙ። በተደረገው የማምለጥ ሙከራ ሌሎች ሦስት ያህል ሰዎች ሞተው ነበርና ወንጀላቸው አለመጠን ከበደ። ታህሣሥ 23 ቀን 1937 ዓ.ም. የሞት ፍርድ ተፈርዶባቸው ጥር 5 ቀን 1937 ዓ.ም. በስቅላት ተቀጡ። በዚህ ሁኔታ ታሪካቸው ቢደመደምም ደጃዝማች በላይ ዘለቀ በአምስቱ ዓመት የነጻነት ተጋድሎ ከፊት የተሰለፉ አርበኛ ስለነበሩ በኢትዮጵያ ታሪክ ትልቅ ቦታ አላቸው።

(ፈንታሁን እንግዳ። 2002። ታሪካዊ መዝገበ ሰብ ከጥንት እስከ ዛሬ፡ ለክፍል ደረጃው እንዲመጥን ተደርጎ የተወሰደ)

**የፈተና መለያ ኮድ…………………… መማሪያ ክፍል …………..**

**ትዕዛዝ አንድ፡- ከዚህ በታች ለቀረቡት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ የያዘውን ፊደል በመምረጥ መልስ ስጡ፡፡**

1. ደጃች በላይ ዘለቀ የተወለዱት የት ነው?

   1.ወሎ 2. ጎጃም 3. ጫቀቻ 4. ደሴ

2. የበላይ ዘለቀ አባትና ወንድም የተገደሉት በማን ነው?

   1.በጣሊያን ጦር 2. በንጉሰ ነገስቱ

   3. በፊታውራሪ እምቢያለ 4. በሽፍቶች

3. በላይ ዘለቀ ወደእናታቸው ሀገር የሄዱት ለምንድነው?

   1.ለጉብኝት 2. ለበቀል ለመዘጋጀት

   3. ጣሊያንን ለመዋጋት 4. ዘመድ ለመጠየቅ

4. ከሚከተሉት አረፍተነገሮች አንዱን በላይ ዘለቀ አልተናገሩትም፡፡
   1. ሀገሬ ከምትደፈር ሞቴን እመርጣለሁ
   2. ከፈራህ አትከተለኝ
   3. ለሀገርህ መስዋዕት የምትሆን ተከተለኝ
   4. ያባቴን ገዳይ ተበቅየ እከተልሀለሁ

5. በላይ ዘለቀ ለአባታቸው ገዳይ የታጠቁትን መሣሪያ "አገሬ ትበልጥብኛለች" በማለት በጣሊያን ላይ አዞሩ ሲል ምን ማለቱ ነው?
   1. ከአባታቸው ገዳይ ጋር ተስማሙ
   2. ከአባታቸው ገዳይ ጋር ጣልያንን ለመዋጋት ሄዱ
   3. ከአባታቸው ይልቅ ሀገራቸውን አስቀደሙ
   4. የአባታቸውን ሞት አምነው ተቀበሉ

6. ልቅምቅም አድርጎ ከነጫጩታችሁ፣

   ከትውልድ ሀገሩ እዚያው ይውሰዳችሁ፡፡ ተብሎ የተገጠመላቸው እነማን ናቸው?
   1. ጣሊያኖች
   2. ባንዳዎች
   3. ያባቱ ገዳዮች
   4. ሽፍቶች

7. በላይ ዘለቀ ጎጃም ውስጥ የጠላት ጦር መቆሚያና መቀመጫ እንዳይኖረው አደረጉ ሲል ምን ማለቱ ነው?

1. በጦርነት ተረጋግቶ እንዳይቀመጥ አደረጉት
2. በወሬ ተረጋግቶ እንዳይቀመጥ አደረጉት
3. በነገር ተረጋግቶ እንዳይቀመጥ አደረጉት
4. አካሉን በመጉዳት ተረጋግቶ እንዳይቀመጥ አደረጉት

8. በላይ ዘለቀ በህዝብ ዘንድ ታዋቂ የሆኑት በምንድን ነው?

1. በባህሪያቸው　　2. በሽፍትነታቸው
3. በአርበኝነታቸው　　4. በጭካኔያቸው

9. ከሚከተሉት አረፍተነገሮች ስለ በላይ ዘለቀ ትክክል የሆነው የቱ ነው?

1. ጣሊያንን በተደጋጋሚ አሸንፈው ነበር
2. ባንዳ በመሆን አገልግለው ነበር
3. በጣሊያን ጦር ተማርከው ነበር
4. ከሀገር ወጥተው ነበር

10. ለምጨን በተባለ ቦታበደጃዝማች በላይ ዘለቀ ጦርና በጣሊያን ጦር መካከል ስለተደረገው ጦርነት <u>ስህተት</u> የሆነው የቱ ነው?

1. ያሸነፈው በላይ ዘለቀ ነው
2. ከበላይ ዘለቀ ወገን የቆሰለና የሞተ ሰው ነበር
3. ብዙ ሰው ያለቀው ከጣሊያን ወገን ነው
4. አሸናፊው ወገን አልታወቀም

11. ደጃዝማች በላይ ዘለቀን የቢቸና ገዢ አድርገው የሾሟቸው ማን ናቸው?

1. ቀዳማዊ ሀይለ ስላሴ
2. የጣሊያን መሪ
3. የጎጃም ህዝብ
4. ባንዳዎች

12. ደጃዝማች በላይ ዘለቀ ከንጉሡ ጋር ጤነኛ የሥራ ግንኙነት እንዳይፈጥሩ መሰናክል የሆኗቸው እነማን ናቸው፡፡

1. የአካባቢው ህዝብ　2. ጣልያኖች　3. ባንዳዎች　4. የንጉሱ ዘማቾች

13.ደጃዝማችበላይዘለቀ ወደሶማ ተራራ ጓደኞቻቸውን ይዘው የወጡት …

1. ለመዝናናት 2. ለአደን 3. ለጨዋታ 4. ለውጊያ

14.ደጃዝማች በላይ ዘለቀ እጃቸውን የሰጡት.

1. በውጊያው ስለተሸነፉ 3. የተሳሳተ መልዕክት ስለደረሳቸው
2. ንጉሳቸውን ስለሚወዱ 4. በጠላት ጦር ስለተማረኩ

15.ደጃዝማች በላይ ዘለቀ የተፈረደባቸው የሞት ፍርድ ወደ እድሜ ልክ እስራት የተቀየረው…

1. ፍርዱ ፍትሀዊ ስላልነበር 3. አርበኞች ስለተቆጡ
2. ንጉሱ ትዕዛዝ ስላስተላለፉ 4. እጃቸውን ስለሰጡ

16.ደጃዝማች በላይዘለቀ ለመጀመሪያ ጊዜ የታሰሩበት ሀገር…

1. ሱሉሉታ 2. ቢቸና 3. አዲስ አበባ 4. ወሊሶ

17.ደጃዝማች በላይ ዘለቀ ለሁለተኛ ጊዜ የሞት ፍርድ የተፈረደባቸው በስንት ዓ.ም ነው?

1. ታህሳስ 23፣ 19362. ጥር፣ 5 1937 3. ታህሳስ፣ 23 1937 4. ጥር 5፣ 1936

18.በላይ ዘለቀ በአምስቱ ዓመት የነጻነት ተጋድሎ ከፊት የተሰለፉ አርበኛ ነበሩ ማለት…

1. ታዋቂ ናቸው 2. ዝነኛ ናቸው 3. አጭር ናቸው 4. ጀግና ናቸው

**ትዕዛዝ ሁለት፡- ከዚህ በታች ከምንባቡ ለወጡ ቃላትና ሀረጋት ከተሰጡት አማራጮች በፍች *<u>የሚለየውን/የማይስማማውን/</u>* በመምረጥ መልስ ስጡ፡፡**

19.በሽፍትነት ተሰማርተው 1. ጫካ ገብተው 3. በአደን ተሰማርተው
2.ከህግ ሸሽተው 4. ጠላት አፍርተው

20.ተወረረች 1. ተከበበች 2. ተያዘች 3. ተወደደች 4.ተገዛች

21.የታጠቁትን 1. የለበሱትን 2.የተሸከሙትን 3.የያዙትን 4. ያነገቱትን

22.ባንዳዎች 1.ከሀዲዎች 2.አስመሳዮች3. አርበኞች 4.አጭበርባሪዎች

23.እጅ ከሰጡ 1. ጉቦ ከሰጡ 2.ከተማረኩ 3. ከተሸነፉ 4. መሳሪያ ካስረከቡ

24.ጭምጭምታ 1. ሀሜት 2. አሉባልታ 3. ምሽት 4. ወሬ

25.ጎምዛዛ 1. ከባድ 2.ሻከራ 3. አስቸጋሪ 4. ፈታኝ

## ሀ.4. የዋናው ጥናት የአንብቦ መረዳት ችሎታ የፈተና ውጤት

### ሀ.4.1. የ5ኛ ክፍል ፈተና ድምር ውጤት

| መለያ ቁጥር | የፈተና ውጤት | | መለያ ቁጥር | የፈተና ውጤት | | መለያ ቁጥር | የፈተና ውጤት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | 27 | | 51 | 23 | | 101 | 22 |
| 2 | 25 | | 52 | 23 | | 102 | 21 |
| 3 | 14 | | 53 | 25 | | 103 | 21 |
| 4 | 19 | | 54 | 23 | | 104 | 22 |
| 5 | 20 | | 55 | 26 | | 105 | 28 |
| 6 | 22 | | 56 | 15 | | 106 | 25 |
| 7 | 25 | | 57 | 22 | | 107 | 21 |
| 8 | 23 | | 58 | 22 | | 108 | 24 |
| 9 | 17 | | 59 | 21 | | 109 | 23 |
| 10 | 24 | | 60 | 23 | | 110 | 23 |
| 11 | 19 | | 61 | 17 | | 111 | 21 |
| 12 | 24 | | 62 | 16 | | 112 | 21 |
| 13 | 22 | | 63 | 22 | | 113 | 22 |
| 14 | 18 | | 64 | 22 | | 114 | 29 |
| 15 | 30 | | 65 | 28 | | 115 | 21 |
| 16 | 25 | | 66 | 19 | | 116 | 21 |
| 17 | 20 | | 67 | 24 | | 117 | 21 |
| 18 | 19 | | 68 | 24 | | 118 | 16 |
| 19 | 18 | | 69 | 26 | | 119 | 19 |
| 20 | 17 | | 70 | 20 | | 120 | 16 |
| 21 | 25 | | 71 | 20 | | 121 | 27 |
| 22 | 23 | | 72 | 27 | | 122 | 21 |

| | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 23 | 21 | | 73 | 19 | | 123 | 23 |
| 24 | 20 | | 74 | 19 | | 124 | 25 |
| 25 | 19 | | 75 | 20 | | 125 | 24 |
| 26 | 18 | | 76 | 20 | | 126 | 19 |
| 27 | 25 | | 77 | 29 | | 127 | 19 |
| 28 | 16 | | 78 | 26 | | 128 | 20 |
| 29 | 15 | | 79 | 23 | | 129 | 20 |
| 30 | 24 | | 80 | 25 | | 130 | 28 |
| 31 | 24 | | 81 | 22 | | 131 | 21 |
| 32 | 21 | | 82 | 22 | | 132 | 21 |
| 33 | 26 | | 83 | 20 | | 133 | 17 |
| 34 | 24 | | 84 | 20 | | 134 | 20 |
| 35 | 23 | | 85 | 22 | | 135 | 20 |
| 36 | 23 | | 86 | 22 | | 136 | 26 |
| 37 | 27 | | 87 | 24 | | 137 | 25 |
| 38 | 18 | | 88 | 20 | | 138 | 18 |
| 39 | 24 | | 89 | 24 | | 139 | 18 |
| 40 | 22 | | 90 | 21 | | 140 | 18 |
| 41 | 22 | | 91 | 25 | | 141 | 19 |
| 42 | 22 | | 92 | 23 | | 142 | 19 |
| 43 | 22 | | 93 | 23 | | 143 | 25 |
| 44 | 23 | | 94 | 25 | | 144 | 23 |
| 45 | 23 | | 95 | 21 | | 145 | 24 |
| 46 | 24 | | 96 | 21 | | 146 | 20 |
| 47 | 24 | | 97 | 22 | | 147 | 20 |
| 48 | 29 | | 98 | 26 | | 148 | 15 |
| 49 | 24 | | 99 | 26 | | 149 | 23 |
| 50 | 27 | | 100 | 22 | | 150 | 26 |
| | | | | | | 151 | 28 |

## ሀ.4.1. የ5ኛ ክፍል የአንብቦ መረዳት ፈተና የውጤት ስርጭት

**Tests of Normality**

| | Kolmogorov-Smirnov[a] | | | Shapiro-Wilk | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | Statistic | Df | Sig. | Statistic | Df | Sig. |
| test | .066 | 151 | .200* | .989 | 151 | .274 |






### ሀ.4.2. የአምስተኛ ክፍል ፈተና የቅለት ክብደት መጠን

| የፈተና የጥያቄ ቁጥር | መልሱን በትክክል ያገኙት ተማሪዎች ብዛት | የፈተና<br>የቅለት ክብደት መጠን |
|---|---|---|
| 1 | 64 | 0.42 |
| 2 | 95 | 0.63 |
| 3 | 31 | 0.2 |
| 4 | 123 | 0.81 |
| 5 | 110 | 0.73 |
| 6 | 115 | 0.76 |
| 7 | 100 | 0.66 |
| 8 | 108 | 0.71 |
| 9 | 119 | 0.78 |
| 10 | 100 | 0.66 |
| 11 | 104 | 0.68 |
| 12 | 72 | 0.47 |
| 13 | 105 | 0.69 |
| 14 | 103 | 0.67 |
| 15 | 104 | 0.68 |
| 16 | 89 | 0.58 |
| 17 | 117 | 0.77 |
| 18 | 75 | 0.49 |
| 19 | 121 | 0.8 |
| 20 | 107 | 0.7 |
| 21 | 104 | 0.68 |
| 22 | 34 | 0.22 |
| 23 | 79 | 0.52 |
| 24 | 83 | 0.54 |
| 25 | 99 | 0.65 |
| 26 | 75 | 0.49 |
| 27 | 75 | 0.49 |
| 28 | 64 | 0.42 |
| 29 | 108 | 0.71 |
| 30 | 42 | 0.27 |

### ሀ.4.3. የአምስተኛ ክፍል ፈተና የመለየት ብቃት /አቅም

| የፈተና የጥያቄ ቁጥር | መልሱን በትክክል ያገኙት ተማሪዎች ብዛት | | የፈተና የመለየት ብቃት |
|---|---|---|---|
| | ከከፍተኛ | ከዝቅተኛ | |
| 1 | 24 | 12 | 0.23 |
| 2 | 44 | 20 | 0.47 |
| 3 | 46 | 35 | 0.21 |
| 4 | 46 | 35 | 0.21 |
| 5 | 44 | 27 | 0.34 |
| 6 | 47 | 33 | 0.28 |
| 7 | 42 | 25 | 0.34 |
| 8 | 47 | 26 | 0.41 |
| 9 | 47 | 28 | 0.37 |
| 10 | 40 | 27 | 0.25 |
| 11 | 49 | 19 | 0.59 |
| 12 | 38 | 19 | 0.37 |
| 13 | 48 | 25 | 0.45 |
| 14 | 49 | 23 | 0.50 |
| 15 | 47 | 18 | 0.56 |
| 16 | 44 | 16 | 0.54 |
| 17 | 48 | 27 | 0.41 |
| 18 | 44 | 12 | 0.62 |
| 19 | 47 | 29 | 0.35 |
| 20 | 48 | 24 | 0.47 |
| 21 | 45 | 26 | 0.37 |
| 22 | 18 | 7 | 0.21 |
| 23 | 42 | 11 | 0.6 |
| 24 | 37 | 22 | 0.29 |
| 25 | 42 | 25 | 0.34 |
| 26 | 29 | 24 | 0.09 |
| 27 | 42 | 11 | 0.6 |
| 28 | 29 | 14 | 0.29 |
| 29 | 48 | 33 | 0.29 |
| 30 | 21 | 6 | 0.29 |

## ሀ.4.4. የ7ኛ ክፍል የአንብቦ መረዳት ችሎታ ድምር ውጤት

| መለያ ቁጥር | የፈተና ውጤት | | መለያ ቁጥር | የፈተና ውጤት | | መለያ ቁጥር | የፈተና ውጤት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | 22 | | 61 | 19 | | 121 | 15 |
| 2 | 19 | | 62 | 15 | | 122 | 14 |
| 3 | 17 | | 63 | 13 | | 123 | 18 |
| 4 | 16 | | 64 | 22 | | 124 | 16 |
| 5 | 12 | | 65 | 12 | | 125 | 17 |
| 6 | 21 | | 66 | 15 | | 126 | 23 |
| 7 | 11 | | 67 | 18 | | 127 | 18 |
| 8 | 11 | | 68 | 16 | | 128 | 14 |
| 9 | 13 | | 69 | 17 | | 129 | 15 |
| 10 | 15 | | 70 | 19 | | 130 | 17 |
| 11 | 14 | | 71 | 20 | | 131 | 20 |
| 12 | 17 | | 72 | 18 | | 132 | 18 |
| 13 | 10 | | 73 | 21 | | 133 | 20 |
| 14 | 17 | | 74 | 23 | | 134 | 18 |
| 15 | 20 | | 75 | 14 | | 135 | 16 |
| 16 | 19 | | 76 | 13 | | 136 | 17 |
| 17 | 25 | | 77 | 25 | | 137 | 15 |
| 18 | 23 | | 78 | 19 | | 138 | 19 |
| 19 | 22 | | 79 | 18 | | 139 | 14 |
| 20 | 12 | | 80 | 12 | | 140 | 12 |
| 21 | 11 | | 81 | 13 | | 141 | 15 |
| 22 | 16 | | 82 | 16 | | 142 | 22 |
| 23 | 15 | | 83 | 20 | | 143 | 12 |
| 24 | 21 | | 84 | 20 | | 144 | 24 |

| | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| **25** | 24 | | **85** | 15 | | **145** | 13 |
| **26** | 17 | | **86** | 14 | | **146** | 14 |
| **27** | 22 | | **87** | 23 | | **147** | 12 |
| **28** | 20 | | **88** | 22 | | **148** | 22 |
| **29** | 19 | | **89** | 18 | | **149** | 25 |
| **30** | 17 | | **90** | 18 | | **150** | 20 |
| **31** | 16 | | **91** | 17 | | **151** | 11 |
| **32** | 10 | | **92** | 16 | | **152** | 21 |
| **33** | 13 | | **93** | 17 | | **153** | 19 |
| **34** | 23 | | **94** | 24 | | **154** | 17 |
| **35** | 18 | | **95** | 19 | | **155** | 11 |
| **36** | 11 | | **96** | 18 | | **156** | 15 |
| **37** | 16 | | **97** | 17 | | **157** | 14 |
| **38** | 13 | | **98** | 14 | | **158** | 13 |
| **39** | 19 | | **99** | 16 | | **159** | 20 |
| **40** | 21 | | **100** | 21 | | **160** | 19 |
| **41** | 21 | | **101** | 19 | | **161** | 21 |
| **42** | 19 | | **102** | 18 | | **162** | 10 |
| **43** | 20 | | **103** | 20 | | **163** | 11 |
| **44** | 18 | | **104** | 17 | | **164** | 12 |
| **45** | 17 | | **105** | 16 | | **165** | 14 |
| **46** | 10 | | **106** | 18 | | **166** | 15 |
| **47** | 16 | | **107** | 14 | | **167** | 17 |
| **48** | 16 | | **108** | 13 | | **168** | 21 |
| **49** | 23 | | **109** | 15 | | **169** | 22 |
| **50** | 22 | | **110** | 19 | | **170** | 24 |
| **51** | 24 | | **111** | 18 | | | |
| **52** | 13 | | **112** | 16 | | | |
| **53** | 12 | | **113** | 18 | | | |
| **54** | 20 | | **114** | 21 | | | |
| **55** | 17 | | **115** | 22 | | | |
| **56** | 18 | | **116** | 25 | | | |
| **57** | 21 | | **117** | 15 | | | |
| **58** | 23 | | **118** | 18 | | | |
| **59** | 20 | | **119** | 17 | | | |
| **60** | 19 | | **120** | 21 | | | |

### ሀ.4.5. የ7ኛ የአንብቦ መረዳት ችሎታ ፈተና ውጤት የውጤት ስርጭት ወጥነት

**Tests of Normality**

| | Kolmogorov-Smirnov[a] | | | Shapiro-Wilk | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | Statistic | Df | Sig. | Statistic | Df | Sig. |
| Test | .066 | 151 | .200* | .989 | 151 | .274 |






## ሀ.4.6. የሰባተኛ ክፍል ፈተና የቅለት ክብደት መጠን

| የፈተና የጥያቄ ቁጥር | መልሱን በትክክል ያገኙት ተማሪዎች ብዛት | የፈተና የቅለት ክብደት መጠን |
|---|---|---|
| 1 | 126 | 0.74 |
| 2 | 132 | 0.77 |
| 3 | 132 | 0.77 |
| 4 | 128 | 0.75 |
| 5 | 100 | 0.58 |
| 6 | 73 | 0.42 |
| 7 | 131 | 0.7 |
| 8 | 120 | 0.7 |
| 9 | 110 | 0.67 |
| 10 | 114 | 0.67 |
| 11 | 82 | 0.48 |
| 12 | 137 | 0.8 |
| 13 | 101 | 0.59 |
| 14 | 65 | 0.38 |
| 15 | 105 | 0.61 |
| 16 | 95 | 0.55 |
| 17 | 119 | 0.7 |
| 18 | 90 | 0.52 |
| 19 | 49 | 0.29 |
| 20 | 107 | 0.62 |
| 21 | 48 | 0.28 |
| 22 | 110 | 0.64 |
| 23 | 95 | 0.55 |
| 24 | 119 | 0.7 |
| 25 | 118 | 0.69 |

ሀ.4.7 የሰባተኛ ክፍል ፈተና የመለየት ብቃት /አቅም

| የፈተና የጥያቄ ቁጥር | መልሱን በትክክል ያገኙት ተማሪዎች ብዛት | | የፈተና የመለየት ብቃት |
|---|---|---|---|
| | ከከፍተኛ | ከዝቅተኛ | |
| 1 | 52 | 35 | 0.3 |
| 2 | 56 | 29 | 0.48 |
| 3 | 55 | 32 | 0.41 |
| 4 | 56 | 25 | 0.55 |
| 5 | 54 | 39 | 0.26 |
| 6 | 43 | 15 | 0.5 |
| 7 | 53 | 33 | 0.35 |
| 8 | 55 | 45 | 0.17 |
| 9 | 53 | 40 | 0.23 |
| 10 | 54 | 24 | 0.53 |
| 11 | 56 | 46 | 0.17 |
| 12 | 55 | 37 | 0.32 |
| 13 | 56 | 43 | 0.23 |
| 14 | 54 | 30 | 0.42 |
| 15 | 54 | 16 | 0.67 |
| 16 | 44 | 18 | 0.46 |
| 17 | 54 | 28 | 0.46 |
| 18 | 54 | 37 | 0.3 |
| 19 | 27 | 9 | 0.32 |
| 20 | 51 | 23 | 0.5 |
| 21 | 27 | 9 | 0.32 |
| 22 | 50 | 19 | 0.55 |
| 23 | 51 | 15 | 0.62 |
| 24 | 55 | 27 | 0.5 |
| 25 | 55 | 27 | 0.5 |

## ሀ. 2. የአንብቦ መረዳት ፈተናዎችን የይዘት ትክክለኝነት ለመገምገም ለባለሙያዎች የቀረበ ማሳከሪያ ቅጽ

የዚህ መገምገሚያ ቅጽ ዋና አላማ የቤተሰብ ዳራ የአንብቦ መረዳት ችሎታንና የማንበብ ተነሳሽትን የመተንበይ ድርሻ በአምስተኛና በሰባተኛ ክፍል ተማሪወች ተተኳሪነት በሚል ርዕስ ለሚካሄድ ምርምር ለአምስተኛና ለሰባተኛ ክፍል ተማሪዎች የተዘጋጀውን የአንብቦ መረዳት ችሎታ መለኪያ ፈተና ተገቢነት በተመለከተ መረጃ ለማግኘት ነው፡፡

ግምገማዎች በመጀመሪያ በማመሳከሪያ ቅጹ በቀረቡ 13 መስፈርቶች አማካኝነት እንዲያካሂዱ በትህትና እጠይቃለሁ፡፡ የርስዎ ትክክለኛ ግምገማ የጥናቱ ውጤት ተቀባይነት እንዲኖረው ያደርጋል፡፡ ስለሆነም ከመስፈርቱ ጋር ተያይዘው የቀረቡትን ሁለት ፈተናዎች በትዕግስት አንብበው እንዲገመግሙልኝ ስጠይቅ በቅድሚያ ለሚያደርጉልኝ ቀና ትብብር በቅድሚያ አመሰግናለሁ፡፡

አማራጭ መልሶቹ በቁጥር የተሰየሙ ሲሆኑ ቁጥሮቹም የሚከተሉትን የመስማማት ደረጃ ይወክላሉ፡፡

4=በጣም ከፍተኛ፣

3=ከፍተኛ፣

2=መካለኛ

1=ዝቅተኛ ለእያንዳንዱ ጥያቄ በሚመርጡት አማራጭ ትይዩ ምልክት ያድርጉ ፡፡

| ተ.ቁ | መገምገሚያ ነጥብ | መለኪያ | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 1 | ፈተናው ከአድልዎ የጸዳ ነው፡፡ (ጾታ፣ ሀይማኖት፣ …) | | | | |
| 2 | ትዕዛዞች ግልጽ ናቸው | | | | |
| 3 | የቋንቋ አጠቃቀሙ ከተማሪዎች አቅም ጋር ይሄዳል፡ | | | | |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 4 | ጥያቄዎቹ የአንብቦ መረዳት ንዑሳን ክሂሎችን የመወከል ደረጃ | | | | |
| 5 | ጥያቄዎቹ ምንባቡን መሰረት አድርገው ሊመለሱ የመቻላቸው ሁኔታ | | | | |
| 6 | ጥያቄዎቹ ከምንባቡ ይዘቶች ጋር ያላቸው ዝምድና | | | | |
| 7 | ጥያቄዎች የአንብቦ መረዳት ችሎታን ብቻ መለካት መቻላቸው | | | | |
| 8 | የጥያቄዎቹ አገላለጽ ከአሻሚነት የጸዳ መሆኑ | | | | |
| 9 | ጥያቄዎች ለመልስ ፍንጭ የሚሰጡ አለመሆናቸው | | | | |
| 10 | ለእያንዳንዱ ጥያቄ አንድ ትክክለኛ መልስ ብቻ ያለው መሆን | | | | |
| 11 | የአማራጮች የአሳሳችነት መጠን ተገቢነት | | | | |
| 12 | የጥያቄዎች አቀራረብ ከቀላል ወደ ከባድ የመደራጀት ሁኔታ | | | | |
| 13 | ፈተናው ቀላል፣ ከባድና መካከለኛ ጥያቄዎችን የማካተት ሁኔታ | | | | |
| | | | | | |

### ሀ.2.1. ስለአንብቦ መረዳት ፈተናዎቹ የይዘት ትክክለኛነት የባለሙያዎች ግምገማ

| የክፍል ደረጃ | የገምጋሚ መለያ | የማመሳከሪያ ጥያቄዎች ምላሽ | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 | 6 | 7 | 8 | 9 | 10 | 11 | 12 | 13 |
| 5ኛ ክፍል | 1 | 4 | 3 | 2 | 3 | 4 | 3 | 2 | 3 | 3 | 2 | 3 | 3 | 3 |
| | 2 | 4 | 3 | 2 | 3 | 2 | 3 | 2 | 3 | 3 | 3 | 3 | 3 | 2 |
| | 3 | 3 | 3 | 2 | 2 | 3 | 2 | 2 | 3 | 2 | 3 | 3 | 2 | 2 |
| 7ኛ ክፍል | 1 | 4 | 3 | 4 | 3 | 2 | 4 | 3 | 3 | 4 | 2 | 3 | 3 | 3 |
| | 2 | 3 | 3 | 4 | 2 | 2 | 3 | 2 | 3 | 3 | 3 | 2 | 3 | 4 |
| | 3 | 2 | 3 | 3 | 2 | 3 | 3 | 2 | 2 | 2 | 3 | 2 | 3 | 3 |

# አባሪ ለ. የሙከራ ጥናቱ መረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች

## ለ.1. የቤተሰብ ዳራን የሚለካ የጽሁፍ መጠይቅ

**አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ**

**የስነሰብ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና ኮሚኒኬሽን ኮሌጅ**

**የአማርኛ ቋንቋ፣ ስነጽሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል**

**ድህረ ምረቃ መርሀግብር**

በባህርዳር ወረዳ በሚገኙ የአንደኛ ደረጃ ሁለተኛ ሳይክል (ከአምስተኛ እስከ ስምንተኛ) ተማሪዎች የሚሞላ የጽሁፍ መጠይቅ፡-

**ውድ ተማሪዎች፡-** የቤተሰብ ዳራ፣ የማንበብ ተነሳሽነትና የአንብቦ መረዳት ችሎታ ተዛምዶ በሚል ርዕስ ለሚጠና የዶክትሬት ዲግሪ ማሟያ ፅሁፍ በመረጃ ሰጭነት እንድትሳተፉ በክብር ተጋብዛችኋል፡፡

የዚህ መጠይቅ ዋና አላማም ለተጠቀሰው የጥናት ርዕስ መረጃ ለመሰብሰብ ነው፡፡ የሚገኘው መረጃ ለጥናቱ ከታሰበው ተግባር ውጭ የማይውል መሆኑን በቅድሚያ አረጋግጣለሁ፡፡ የምትሰጧቸው መልሶች በትክክል የእናንተን እውነተኛ ስሜትና እምነት የሚያንፀባርቁ እንዲሆኑ አደራ እላለሁ፡፡ ስለትብብራችሁና ታማኝነታችሁ በቅድሚያ አመሰግናለሁ፡፡

ይህ መጠይቅ ሶስት ክፍሎች አሉት የመጀመሪያው ክፍል ስለእናንተ አጠቃላይ መረጃ የሚጠይቅ ነው፡፡ ሁለተኛው ክፍል የቤተሰብ ዳራን የሚለካ ሲሆን ሶስተኛው ደግሞ የማንበብ ተነሳሽነትን የሚለካ መጠይቅ የያዘ ነው፡፡ አንዳቸው ካለአንዳቸው ሙሉ ስለማይሆኑ ሁሉንም ጥያቄዎች በትክክል እንድትመልሱ አደራ እላለሁ፡፡

**ማሳሳቢያ፡-** ስም መፃፍ አያስፈልግም፡፡

መጠይቁን ከጓደኛ ጋር ተመካክሮ መሙላት የተከለከለ ነው፡፡

**ክፍል አንድ፡-** ግለሰባዊ መረጃ ስለእናንተ ትክክል የሆነውን በባዶ ቦታው ላይ ይህን(✓)

ምልክት በማድረግ አረጋግጡ፡፡

2. **ፆታ፡-** ሴት________ ወንድ________
3. **እድሜ፡-** ________
4. **የክፍል ደረጃ** ፡- 5ኛ ________ 6ኛ________7ኛ________ 8ኛ________
5. ባለፈው አመት አሁን ወዳለህ/ሽ/በት ስትዘዋወር/ሪ/ የነበረው አጠቃላይ ውጤት (አማካኝ ውጤት) ______________

**ክፍል ሁለት፡- ቤተሰባዊ ዳራ የሚለካ መጠይቅ**

*መመሪያ፡-* ከዚህ ቀጥሎ የአንተን/የአንችን ቤተሰቦች የሚመለከቱ ጥያቄዎች ቀርበዋል፡፡ ለእያንዳንዱ ጥያቄ በምርጫ መልክ ከቀረቡት መልሶች በትክክል እኔን ይገልጸኛል የሚለውን አማራጭ በማክበብ መልስ ይስጡ፡፡

1. የወላጆችህ/ሽ/ ሀይማኖት

   1. ኦርቶዶክስ 2. ፕሮቴስታንት 3. እስልምና 4. ሌላ

2. በአሁኑ ጊዜ ከማን ጋር ትኖራለህ/ትኖሪያለሽ?

   (1) ከአባቴ እና ከእናቴ ጋር

   (2) ከአባቴ ጋር

   (3) ከእናቴ ጋር

   (4) ከአባቴ እና ከእንጀራ እናቴ ጋር

   (5) ከእናቴ እና ከእንጀራ አባቴ ጋር

   (6) ከሌሎች ዘመዶቼ ጋር (ምሳሌ፡- ከአያት፣አክስት፣አጎት… ወዘተ ጋር)

   (7) የሥጋ ዝምድና ከሌላቸው አሳዳጊዎች ጋር

   (8) ከላይ ከተጠቀሱት ውጭ ከሆነ ግለጽ/ጪ

   ______________________________

3. በእናንተ ቤተሰብ ውስጥ ምን ያክል ሰው ይኖራል

   (1) ከ1 እስከ 3 (2) ከ4 እስከ 6 (3) ሰባትና ከዚያ በላይ

4. የት ትኖራለህ/ትኖሪያለሽ? (1) ገጠር (2) መለስተኛ ከተማ (3) ከተማ
5. የአባትህ/ሽ (የወንድ አሳዳጊህ/ሽ) የትምህርት ደረጃ፡-

   (1) መደበኛ ትምህርት ያልተማረ

(2) አንደኛ/መለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ

(3) ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ

(4) ሠርቲፊኬት/ዲፕሎማ

(5) የመጀመሪያ ዲግሪ እና/ወይም በላይ

6. የእናትህ/ሽ (የሴት አሳዳጊህ/ሽ) የትምህርት ደረጃ፡-

(1) መደበኛ ትምህርት ያልተማረች

(2) አንደኛ/መለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ

(3) ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ

(4) ሠርቲፊኬት/ዲፕሎማ

(5) የመጀመሪያ ዲግሪ እና/ወይም በላይ

7. በቤተሰብህ/ሽ መደበኛ ትምህርት የተማረ የቤተሰብ አባል አለ?

(1) አለ (2). የለም

8. በቤተሰብህ/ሽ መደበኛ ትምህርት የተማረ ሰው ካለ ብዛት ስንት ነው?

1. ከአንድ እስከ ሶስት
2. ከአራት እስከ ስድስት
3. ከስድስት በላይ

9. በቤተሰብህ/ሽ ከፍተኛው የትምህርት ደረጃ የትኛው ነው

(1) አንደኛ/መለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ

(2) ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ

(3) ሠርቲፊኬት/ዲፕሎማ

(4) የመጀመሪያ ዲግሪ እና/ወይም በላይ

10.የአባትህ/ሽ (የወንድ አሳዳጊህ/ሽ) ስራ

1.ገበሬ

2. ነጋዴ

3.የመንግስት ሰራተኛ

4. ሌላ ካለ ይገለጽ…………

11.የእናትህ/ሽ (የሴት አሳዳጊህ/ሽ) ስራ፡-

1.የቤት እመቤት

2. ገበሬ

3. ነጋዴ

4. የመንግስት ሰራተኛ

5. ሌላ ካለ ይገለጽ …….

12. ቤተሰቦችህ/ሽ/ እንድታነብ/ቢ ምን ያክል ይረዱሀል/ሻል/ያበረታቱሀል/ሻል?

1. ምንም አያበረታቱኝም
2. በመጠኑ ያበረታቱኛል
3. በጥሩ ሁኔታ ያረታቱኛል
4. በጣም ያበረታቱኛል
5. እጅግ በጣም ያበረታቱኛል

13. ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ነገሮች በቤትህ/ሽ ውስጥ አሉ

(1) የግል መጽሀፍት 1. አለኝ 2. የለኝም

(2) የማጥኛ ጠረጴዛና ወንበር 1. አለኝ 2. የለኝም

(3) የግል ክፍል 1. አለኝ 2. የለኝም

(4) የግል አልጋ 1. አለኝ 2. የለኝም

(5) ሞባይል (ተንቀሳቃሽ ስልክ) 1. አለኝ 2. የለኝም

(6) የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች (ዲክሽነሪ፣ ካልኩሌተር ወ.ዘ.ተ.)

1. አለኝ 2. የለኝም

14.የቤተሰቦችህ/ሽ ገቢ በወር ምን ያህል ነው?

1. ከ1000 ብር በታች 3. 3001- 5000 ብር 5. ከ10,000 ብር በላይ

2. ከ1000 እስከ 3000 ብር 4. 5001- 10,000 ብር

15.በቀን ስንት ጊዜ ትመገባለህ/ሽ

1.አንድ ጊዜ 2. ሁለት ጊዜ 3. ሶስት ጊዜ

16.የቤተሰቦችህ ገቢ ከጎረቤትና ከአካባቢው ጋር ሲነጻጸር

1. ከፍተኛ 2. መካከለኛ 3. ዝቅተኛ 4. ተመሳሳይ

17.ቤተሰቦችህ ከሚከተሉት ማህበራዊ ጉዳዮች ውስጥ በየትኞቹ ይሳተፋሉ?

(1) እድር 1. አዎ 2. የለም

(2) እቁብ 1. አዎ 2. የለም

(3) ማህበር 1. አዎ 2. የለም

18.ከላይ ከ1 አስከ 17 ለቀረቡት ጥያቄዎች ከሰጠሀ/ሽ/አቸው መልሶች ውስጥ አንብቦ ለመረዳትና ለማንበብ ተነሳሽነቴ ይጠቅሙኛል ወይም የጎላ ድርሻ አላቸው የምትላቸውን/ያቸውን/ ሶስት አበይት መልሶች ከታች ካው ክፍት ቦታ ላይ አስፍር/ሪ/፡፡

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

________________________________________________________.

## ለ.2. የማንበብ ተነሳሽነትን የሚለካ የጽሁፍ መጠይቅ

**ክፍል ሶስት ፡-** ከዚህ ቀጥሎ በሰንጠረዥ ውስጥ አረፍተነገሮች ቀርበዋል፡፡ ዐ.ነገሮችን አንብበህ/ሽ/ ከዐ.ነገሮቹ ፊት ለፊት የስምምነት ደረጃህን/ሽን/ እንድትገልጽ/ጭ/ ለአንተ/ለአንች ተስማሚ ሆነው ከቀረቡት አማራጭ መልሶች የመረጥከ/ሽ/ውን በማክበብ ስምምነትህን/ሽን/ ግለጽ/ጭ/፡፡

**መግለጫ፡- የማንበብ ተነሳሽነትን የሚለካ መጠይቅ**

1 ከጓደኞቸ የበለጠ ትክክለኛ መልሶችን ለመመለስ እሞክራለሁ

1. ሙሉ በሙሉ አይገልጸኝም 2. በመጠኑ አይገልጸኝም 3. በመጠኑ ይገልጸኛል 4. ሙሉበሙሉ ይገልጸኛል

2 ጠንካራና ብዙ ጥረትን የሚጠይቁ /አድካሚ/ መጽሀፍትን እወዳለሁ

1. ሙሉ በሙሉ አይገልጸኝም 2. በመጠኑ አይገልጸኝም 3. በመጠኑ ይገልጸኛል 4. ሙሉ በሙሉ ይገልጸኛል

3 የፈተና ውጤቶች በማንበብ ላይ ምን ያክል እንደተሰራ የሚያሳዩ ናቸው፡፡

1. ሙሉ በሙሉ አይገልጸኝም 2. በመጠኑ አይገልጸኝም 3. በመጠኑ ይገልጸኛል 4. ሙሉ በሙሉ ይገልጸኛል

4 መምህሩ ስለአንድ ሳቢ ነገር ካስተማረ ተጨማሪ ነገር ለማንበብ እጥራለሁ

1. ሙሉ በሙሉ አይገልጸኝም 2. በመጠኑ አይገልጸኝም 3. በመጠኑ ይገልጸኛል 4. ሙሉ በሙሉ ይገልጸኛል

5 የተሰጠኝ ስራ ደስ የሚል ከሆነ ከባድ መጽሀፍትን ሁሉ ማንበብ እችላለሁ

1. ሙሉ በሙሉ አይገልጸኝም 2. በመጠኑ አይገልጸኝም 3. በመጠኑ ይገልጸኛል 4. ሙሉ በሙሉ ይገልጸኛል

6 ከእውነታ በራቁ እምነቶች ላይ የተመሰረቱ ታሪኮችን ማንበብና ማመን እወዳለሁ፡፡

1. ሙሉ በሙሉ አይገልጸኝም 2. በመጠኑ አይገልጸኝም 3. በመጠኑ ይገልጸኛል 4. ሙሉ በሙሉ ይገልጸኛል

7 በሚቀጥለው አመት በማንበብ ጥሩ መስራቴን እርግጠኛ አይደለሁም፡፡

1. ሙሉ በሙሉ አይገልጸኝም 2. በመጠኑ አይገልጸኝም 3. በመጠኑ ይገልጸኛል 4. ሙሉ በሙሉ ይገልጸኛል

8 በመጽሀፍ የሚገኙት ጥያቄዎች እንዳስብ የሚያደርጉኝ ከሆነ ደስ ይለኛል፡፡

1. ሙሉ በሙሉ አይገልጸኝም 2. በመጠኑ አይገልጸኝም 3. በመጠኑ ይገልጸኛል 4. ሙሉ በሙሉ ይገልጸኛል

9 ምርጥ አንባቢ መሆን እፈልጋለሁ፡፡

1. ሙሉ በሙሉ አይገልጸኝም 2. በመጠኑ አይገልጸኝም 3. በመጠኑ ይገልጸኛል 4. ሙሉ በሙሉ ይገልጸኛል

10 በተለየ ስለምወዳቸው የትምህርት አይነቶች ማንበብ እወዳለሁ

1. ሙሉ በሙሉ አይገልጸኝም 2. በመጠኑ አይገልጸኝም 3. በመጠኑ ይገልጸኛል 4. ሙሉ በሙሉ ይገልጸኛል

11 ከቤተሰቦቸ ጋር በአብዛኛው ወደ ቤተ መጽሀፍት እሄዳለሁ

1. ሙሉ በሙሉ አይገልጸኝም 2. በመጠኑ አይገልጸኝም 3. በመጠኑ ይገልጸኛል 4. ሙሉ በሙሉ ይገልጸኛል

12 ሚስጥር የሆኑ (የተደበቁ) ነገሮችን ማንበብ እወዳለሁ

1. ሙሉ በሙሉ አይገልጸኝም 2. በመጠኑ አይገልጸኝም 3. በመጠኑ ይገልጸኛል 4. ሙሉ በሙሉ ይገልጸኛል

13 የቃላት ጥያቄዎችን አልወድም

1. ሙሉ በሙሉ አይገልጸኝም 2. በመጠኑ አይገልጸኝም 3. በመጠኑ ይገልጸኛል 4. ሙሉ በሙሉ ይገልጸኛል

14 በሚስቡኝ ርዕሶች የሚገኙ ኣዳዲስ መረጃዎችን ለመማር አነባለሁ

1. ሙሉ በሙሉ አይገልጸኝም 2. በመጠኑ አይገልጸኝም 3. በመጠኑ ይገልጸኛል 4. ሙሉ ይገልጸኛል

15 እኔ ጥሩ አንባቢ ነኝ ብየ አስባለሁ

1. ሙሉ በሙሉ አይገልጸኝም 2. በመጠኑ አይገልጸኝም 3. በመጠኑ ይገልጸኛል 4. ሙሉ በሙሉ ይገልጸኛል

16 በጣም አስቸጋሪ ሁኔታዎችን የምማረው በማንበብ ነው

1. ሙሉ በሙሉ አይገልጸኝም 2. በመጠኑ አይገልጸኝም 3. በመጠኑ ይገልጸኛል 4. ሙሉ በሙሉ ይገልጸኛል

17 ጥሩ አንባቢ መሆኔ ለኔ በጣም ይጠቅመኛል

1. ሙሉ በሙሉ 2. በመጠኑ 3. በመጠኑ 4. ሙሉ በሙሉ

አይገልጸኝም አይገልጸኝም ይገልጸኛል ይገልጸኛል

18 አነባለሁ የሚል መምህር ሲኖር ደስ ይለኛል

1. ሙሉ በሙሉ አይገልጸኝም 2. በመጠኑ አይገልጸኝም 3. በመጠኑ ይገልጸኛል 4. ሙሉ በሙሉ ይገልጸኛል

19 ስለተሰጥዖየ የበለጠ ለማዎቅ አነባለሁ

1. ሙሉ በሙሉ አይገልጸኝም 2. በመጠኑ አይገልጸኝም 3. በመጠኑ ይገልጸኛል 4. ሙሉ በሙሉ ይገልጸኛል

20 መጽሀፍ ሳቢ ከሆነ ምንም ያክል ቢከብድ ከማንበብ ወደ ኋላ አልልም

1. ሙሉ በሙሉ አይገልጸኝም 2. በመጠኑ አይገልጸኝም 3. በመጠኑ ይገልጸኛል 4. ሙሉ በሙሉ ይገልጸኛል

21 በክፍልውስጥከሚገኙትሌሎችተማሪዎችበተሻለከማንበብብዙእማራለሁ

1. ሙሉ በሙሉ አይገልጸኝም 2. በመጠኑ አይገልጸኝም 3. በመጠኑ ይገልጸኛል 4. ሙሉ በሙሉ ይገልጸኛል

22 በማነብበት ጊዜ በምናቤ ምስል ለመፍጠር እሞክራለሁ፡፡

1. ሙሉ በሙሉ አይገልጸኝም 2. በመጠኑ አይገልጸኝም 3. በመጠኑ ይገልጸኛል 4. ሙሉ በሙሉ ይገልጸኛል

23 በንባብ የሚሰሩ የትምህርት ቤት ተግባራትን በተቻለኝ አቅም እሰራለሁ፡፡

1. ሙሉ በሙሉ አይገልጸኝም 2. በመጠኑ አይገልጸኝም 3. በመጠኑ ይገልጸኛል 4. ሙሉ በሙሉ ይገልጸኛል

24 ውስብስብ ታሪኮች ማንበብ አያስደስተም

1. ሙሉ በሙሉ አይገልጸኝም 2. በመጠኑ አይገልጸኝም 3. በመጠኑ ይገልጸኛል 4. ሙሉ በሙሉ ይገልጸኛል

25 ስለአዳዲስ ነገሮች ማንበብ እወዳለሁ

1. ሙሉ በሙሉ አይገልጸኝም 2. በመጠኑ አይገልጸኝም 3. በመጠኑ ይገልጸኛል 4. ሙሉ በሙሉ ይገልጸኛል

26 ለወንድሞቸ ወይም ለእህቶቼ በአብዛኛው አነብላቸዋሁ

1. ሙሉ በሙሉ አይገልጸኝም 2. በመጠኑ አይገልጸኝም 3. በመጠኑ ይገልጸኛል 4. ሙሉ በሙሉ ይገልጸኛል

27 ከሌሎች ተግባራት ጋር ሲነጻጸር ጥሩ አንባቢ መሆን በጣም ይጠቅመኛል፡፡

1. ሙሉ በሙሉ አይገልጸኝም 2. በመጠኑ አይገልጸኝም 3. በመጠኑ ይገልጸኛል 4. ሙሉ በሙሉ ይገልጸኛል

28 አንዳንዶ ጓደኞቸ ጥሩ አንባቢ እንደሆንኩ ይነግሩኛል፡፡

1. ሙሉ በሙሉ አይገልጸኝም 2. በመጠኑ አይገልጸኝም 3. በመጠኑ ይገልጸኛል 4. ሙሉ በሙሉ ይገልጸኛል

29 በህይወት ስላሉ ነገሮች ማንበብ ያዝናናኛል፡፡

1. ሙሉ በሙሉ አይገልጸኝም 2. በመጠኑ አይገልጸኝም 3. በመጠኑ ይገልጸኛል 4. ሙሉ በሙሉ ይገልጸኛል

30 በመጽሀፍት ውስጥ ጥሩ ገጸባህሪያት ሲጋጥሙኝ ጓደኛ ያገኘሁ መስሎ ይሰማኛል፡፡

1. ሙሉ በሙሉ አይገልጸኝም 2. በመጠኑ አይገልጸኝም 3. በመጠኑ ይገልጸኛል 4. ሙሉ በሙሉ ይገልጸኛል

31 እኔና ጓደኞቼ የሚነበብ ነገር እንዋዋሳለን፡፡

1. ሙሉ በሙሉ አይገልጸኝም 2. በመጠኑ አይገልጸኝም 3. በመጠኑ ይገልጸኛል 4. ሙሉ በሙሉ ይገልጸኛል

32 ቃላቶቹ ከባድ ሲሆኑ ማንኛውንም ነገር ማንበብ ያስጠላኛል፡፡

1. ሙሉ በሙሉ አይገልጸኝም 2. በመጠኑ አይገልጸኝም 3. በመጠኑ ይገልጸኛል 4. ሙሉ በሙሉ ይገልጸኛል

33 ብዙ የጀግንነት መጽሀፍትን አንብቢያለሁ

1. ሙሉ በሙሉ አይገልጸኝም 2. በመጠኑ አይገልጸኝም 3. በመጠኑ ይገልጸኛል 4. ሙሉ በሙሉ ይገልጸኛል

34 ማንበብ ስላለብኝ አነባለሁ

1. ሙሉ በሙሉ አይገልጸኝም 2. በመጠኑ አይገልጸኝም 3. በመጠኑ ይገልጸኛል 4. ሙሉ በሙሉ ይገልጸኛል

35 በልቦለድ መጽሀፍት እዝናናለሁ፡፡

1. ሙሉ በሙሉ አይገልጸኝም 2. በመጠኑ አይገልጸኝም 3. በመጠኑ ይገልጸኛል 4. ሙሉ በሙሉ ይገልጸኛል

36 መምህሬ የሚሰጠኝን የማንበብ ተግባራት እሱ በሚፈልገው መንገድ እሰራለሁ፡፡

1. ሙሉ በሙሉ አይገልጸኝም 2. በመጠኑ አይገልጸኝም 3. በመጠኑ ይገልጸኛል 4. ሙሉ በሙሉ ይገልጸኛል

37 በማንበቤ መመስገን እወዳለሁ

1. ሙሉ በሙሉ አይገልጸኝም 2. በመጠኑ አይገልጸኝም 3. በመጠኑ ይገልጸኛል 4. ሙሉ በሙሉ ይገልጸኛል

38 በማነብበት ጊዜ ወደ ፊት የማገኘውን ውጤት አስባለሁ፡፡

1. ሙሉ በሙሉ አይገልጸኝም 2. በመጠኑ አይገልጸኝም 3. በመጠኑ ይገልጸኛል 4. ሙሉ በሙሉ ይገልጸኛል

39 ለወላጆቼ አልፎ አልፎ አነብላቸዋለሁ፡፡

1. ሙሉ በሙሉ አይገልጸኝም 2. በመጠኑ አይገልጸኝም 3. በመጠኑ ይገልጸኛል 4. ሙሉ በሙሉ ይገልጸኛል

40 በታሪኩ ውስጥ በርካታ ሰዎች ካሉበት ማንበብ አልወድም

1. ሙሉ በሙሉ አይገልጸኝም 2. በመጠኑ አይገልጸኝም 3. በመጠኑ ይገልጸኛል 4. ሙሉ በሙሉ ይገልጸኛል

41 ከሌሎች ተማሪዎች በፊት አንብቤ መጨረስ ያስደስተኛል

1. ሙሉ በሙሉ አይገልጸኝም 2. በመጠኑ አይገልጸኝም 3. በመጠኑ ይገልጸኛል 4. ሙሉ በሙሉ ይገልጸኛል

42 ስላነበብኩት ነገር ከጓደኞቸ ጋር አወራለሁ

1. ሙሉ በሙሉ አይገልጸኝም 2. በመጠኑ አይገልጸኝም 3. በመጠኑ ይገልጸኛል 4. ሙሉ በሙሉ ይገልጸኛል

43 ማንበቤን የሆነ ሰው ሲያሳውቅልኝ ደስ ይለኛል

1. ሙሉ በሙሉ አይገልጸኝም 2. በመጠኑ አይገልጸኝም 3. በመጠኑ ይገልጸኛል 4. ሙሉ በሙሉ ይገልጸኛል

44 በጋራ ባነበብነው ነገር ውስጥ መልሱን የማውቀው እኔ ብቻ ብሆን ደስተኛ ነኝ

1. ሙሉ በሙሉ አይገልጸኝም 2. በመጠኑ አይገልጸኝም 3. በመጠኑ ይገልጸኛል 4. ሙሉ በሙሉ ይገልጸኛል

45 ጓዋደኞቼ የሚሰጣቸውን የምንባብ ስራ መርዳት እወዳለሁ

1. ሙሉ በሙሉ በሙሉ አይገልጸኝም 2. በመጠኑ አይገልጸኝም 3. በመጠኑ ይገልጸኛል 4. ሙሉ ይገልጸኛል

46 የተሰጡኝን የማንበብ ተግባራት በአግባቡ መጨረስ ለኔ በጣም ጠቃሚ ነው፡፡

1. ሙሉ በሙሉ በሙሉ አይገልጸኝም 2. በመጠኑ አይገልጸኝም 3. በመጠኑ ይገልጸኛል 4. ሙሉ ይገልጸኛል

47 ቤተሰቦች ሳነብ ካገኙኝ ሁሌም ጥሩ እየሰራሁ እንደሆነ ይነግሩኛል፡፡

1. ሙሉ በሙሉ በሙሉ አይገልጸኝም 2. በመጠኑ አይገልጸኝም 3. በመጠኑ ይገልጸኛል 4. ሙሉ ይገልጸኛል

48 ስላነበብኩት ነገር ለቤተሰቦቼ መንገር እወዳለሁ

1. ሙሉ በሙሉ በሙሉ አይገልጸኝም 2. በመጠኑ አይገልጸኝም 3. በመጠኑ ይገልጸኛል 4. ሙሉ ይገልጸኛል

49 ጥሩ አንባቢ በሚባሉት ተማሪዎች ተርታ ውስጥ መገኘት ለኔ ጠቃሚ ነው፡፡

1. ሙሉ በሙሉ በሙሉ አይገልጸኝም 2. በመጠኑ አይገልጸኝም 3. በመጠኑ ይገልጸኛል 4. ሙሉ ይገልጸኛል

50 የማነበው ውጤቴን ለማሻሻል ነው፡፡

1. ሙሉ በሙሉ በሙሉ አይገልጸኝም 2. በመጠኑ አይገልጸኝም 3. በመጠኑ ይገልጸኛል 4. ሙሉ ይገልጸኛል

51 ሁልጊዜ ምንባቤን የምጨርሰው በተሰጠኝ ጊዜ ነው፡፡

1. ሙሉ በሙሉ በሙሉ አይገልጸኝም 2. በመጠኑ አይገልጸኝም 3. በመጠኑ ይገልጸኛል 4. ሙሉ ይገልጸኛል

52 ከጓደኖቸበበለጠጠንክሬለማንበብፈቃደኛነኝ

1. ሙሉ በሙሉ በሙሉ አይገልጸኝም 2. በመጠኑ አይገልጸኝም 3. በመጠኑ ይገልጸኛል 4. ሙሉ ይገልጸኛል

53 ቤተሰቦቸ ስለንባብ ውጤቴ ይጠይቁኛል፡፡

1. ሙሉ በሙሉ በሙሉ አይገልጸኝም 2. በመጠኑ አይገልጸኝም 3. በመጠኑ ይገልጸኛል 4. ሙሉ ይገልጸኛል

## ለ.3. የስምንተኛ ክፍል የአንብቦ መረዳት መለኪያ ፈተና

**አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ**

**የስነሰብ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና ኮሚኒኬሽን ኮሌጅ**

**የአማርኛ ቋንቋ፣ ስነጽሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል (ድህረ ምረቃ መርሀግብር)**

**ለስምንተኛ ክፍል ተማሪዎች የተዘጋጀ የአንብቦ መረዳት መለኪያ ፈተና**

***ውድ ተማሪዎች፡-*** *ይህ የአንብቦ መረዳት መለኪያ ፈተና የተዘጋጀው "የቤተሰብ ዳራ የማንበብ ተነሳሽነትና የአንብቦ መረዳት ችሎታ ተዛምዶ" በሚል ርዕስ ለሚሰራው ምርምር መረጃ ለመሰብሰብ ነው፡፡ ስለዚህ ከዚህ በታች የቀረበውን ምንባብ መሰረት በማድረግ ለቀረቡት ጥያቄዎች በትክክል ምላሽ እንድትሰጡ እጠይቃለሁ፡፡*

**የሕፃናት ጉልበት ብዝበዛ**

*በአሁኑ ዘመን አሳሳቢ ከሆኑ ጉዳዮች መካከል አንደኛው የሕጻናት ጉልበት ብዝበዛ ነው:: የሕፃናት ጉልበት ብዝበዛ ከሕፃናት ሥራ የተለየ ነው:: የሕፃናት ሥራ በቤተሰብ እገዛ ቀላል ሥራን የሚለማመዱበትን፣ ትምህርታቸውን፣ ጤንነታቸውንና ዕድገታቸውን በማይፈታተን መልኩ የሚሠሩትን ይመለከታል:: ይህም የማኅበራዊ ሕይወትን በማሻሻል የሥራ ፍቅር ኖሯቸው እንዲያድጉ የማድረግ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አለው:: የሕፃናት ጉልበት ብዝበዛ ግን ሕፃናት ዕድሜያቸው ለሥራ ሳይደርስና ጉልበታቸው ሳይጠነክር ያለማንም እገዛና ሥልጠና* ***በግዳጅ*** *የሚያከናውኑት ተግባር ነው:: የሕጻናት ጉልበት ብዝበዛ የብዙ ሀገሮች ችግር ቢሆንም በታዳጊ ሀገራት ችግሩ ከባድ ነው:: በአፍሪካ በተለይም ከሰሀራ በታች ባሉ ሀገሮች ደግሞ ችግሩ የበለጠ የከፋ ነው:: ኢትዮጵያም የችግሩ ተጠቂ ናት:: ሕጻናትን ከትምህርት* ***በማሰናከል*** *አእምሮአዊ እድገታቸውን በሚጎዱ ሥራዎች ላይ ማሰማራት የተለመደ ነው:: በርካታ ሕጻናት ዕድሜያቸው በማይፈቅድላቸው ተግባራት ውኃ በመቅዳት፣ እንጨት በመልቀም፣ ከብት በመጠበቅ ወዘተ… ሥራዎች ይሰማራሉ:: ሌሎች ደግሞ በእርሻ ሥራና በቤት ውስጥ ተግባራት ቤተሰባቸውን ይረዳሉ:: ዕድሜያቸው በማይፈቅደው ሥራ በመሰማራታቸውም አካላዊም ሆነ* ***መንፈሳዊ እድገታቸው*** *በጣም ይጎዳል:: በከተሞች በጫማ ጠራጊነት፣ በመኪና አጣቢነት፣ በተሸካሚነት፣ በሱቅ በደረቴነት፣ በሎተሪ አዟሪነት፣ በታክሲ*

ረዳትነት፣ የተሰማሩ ሕጻናት በርካታ ናቸው:: በቤት ሠራተኛነት፣ በልጅ አሳዳጊነትና፣ በተላላኪነት ሥራ የተሰማሩትም ቁጥራቸው ቀላል አይደለም:: በተለይ በልጅ አሳዳጊነት የሚቀጠሩ ሕጻናት ከፍተኛ ጥንቃቄ በሚጠይቁ ተግባራት ተሰማርተው እንዲይዙ፣ እንዲንከባከቡና እንዲያጫውቱ ኃላፊነት ይጣልባቸዋል:: እነሱ የጨዋታ ፍቅራቸውን ተነጥቀው በጊዜያቸው **ሳይፈነጥዙ** ሌሎችን እንዲያጫውቱ ይገደዳሉ:: ከመንከባከብ በተጨማሪም የሕፃናቱን ልብሶች፣ ቁሳቁሶች እንዲያጸዱ፣ እንዲሁም የቤት ውስጥ ሥራዎችን እንዲሠሩ ይደረጋሉ:: እነዚህንና የመሣሰሉትን ከባድ ሥራዎች ቀን ተሌት ስለሚሠሩ በእንቅልፍና በዕረፍት **እጦት** የሚሰቃዩት በርካታ ናቸው::

ሕፃናትን ለጉልበት ብዝበዛ ከሚያጋልጣቸው ምክንያቶች መካከል አንዱ ድህነት ነው:: ድህነት ባለበት ቤተሰብ ውስጥ ወላጆች ምግባቸውን፣ ልብሳቸውንና ፍላጎታቸውን አሟልተው ልጆቻቸውን ለማሳደግ አቅም ስለሚያጡ ለልጆቻቸው የተሻለ ሕይወትን በመመኘት “ልጄን ያስተምሩልኛል፣ ሥራ ያለማምዱልኛል” በማለት ልጆቻቸውን ለዘመድም ሆነ ለባዕድ አሳልፈው ይሰጣሉ:: ይሁን እንጂ ሕፃናቱ የታሰበውን የትምህርትና የሥልጠና ዕድል በማግኘት ፈንታ ለከፍተኛ የሥራ ጫናና ጉልበት ብዝበዛ ይጋለጣሉ:: በሌላ መልኩም ሕፃናቱ በራሳቸው የተሻለ ኑሮ ፍለጋ ከወላጆቻቸው በመነጠል ወደሌላ አካባቢ ይሰደዳሉ:: በደረሱበትም ህይወታቸውን ለማቆየት ሲሉ አቅማቸውን በማይመጥን ሥራ ለመሠማራት ይገደዳሉ:: ድህነት የከፋ መስዋዕትነት ያስከፍላቸዋል::

የወላጆች የተዛባ አመለካከት ሌላው ሕፃናትን ለጉልበት ብዝበዛ የሚዳርግ ጉዳይ ነው:: ወላጆች ለሕፃናት አስተዳደግ ከፍተኛ ኃላፊት አለባቸው:: ሕፃናትን በጥሩ ሥነምግባር አንፆና አስተምሮ ለወግ **ለማዕረግ** ማብቃት ለሕፃናቱም ሆነ ለወላጆች ይጠቅማል:: ሆኖም አንዳንድ ወላጆች ኃላፊነታቸውን ከመወጣት ይልቅ ልጆችን ወደሌላ ቦታ በመላክ በጉልበታቸው ለመጠቀም ይፈልጋሉ:: ሕፃናቱም በወላጆቻቸው ግፊትና ተፅዕኖ ወደአልፈለጉት ቦታ ይሄዳሉ:: በማይችሉት ሥራ በመሰማራትም ለከፋ ችግርና ስቃይ ይዳረጋሉ:: ከቤተሰብ ተነጥለው በመኖራቸው ለብቸኝነት ይጋለጣሉ:: እንደሕፃናት ተጫውተው ባለማደጋቸው ደስታና ፍቅር ይርቃቸዋል:: ሠርተው ወላጆቻቸውን መርዳት ቀርቶ ለራሳቸውም የተስተካከለ ኑሮን ለመምራት ይቸገራሉ:: በየጊዜው

በሚፈፀምባቸው በደልና የሥራ ጫና መንፈሳቸውና አካላቸው ይጎዳል። በመጨረሻም ለቤተሰባቸውም ሆነ ለሀገራቸው ሸክም ይሆናሉ።

ህገወጥ የሰዎች አዘዋዋሪዎችም ለሕፃናት ጉልበት ብዝበዛ ዋና ምክንያት ናቸው። ሕፃናትን በማታለል ወይም በመስረቅ ከቤተሰቦቻቸውና ከትውልድ መንደራቸው **በማስኮብለል** ለግል ፍላጎታቸው መጠቀሚያ ያደርጓቸዋል። አንዳንዶች በሌሎች ቤት በማስቀጠር የሕፃናቱን የጉልበት ዋጋ በመቀበል ኑሯቸውን ይመራሉ። ሌሎች ደግሞ በራሳቸው ቤት ሰው እንዳያያቸው በመዝጋት ለረጅም ሰዓት ያሠሯቸዋል። ሰዓት ጠብቀውም ምግብ አያቀርቡላቸውም። የሚያቀርቡላቸውም ምግብ ለድካማቸው የሚመጥን አይደለም። በዚህም አካላቸው ይጎዳል። ለምሳሌ፡- በአብዛኛው የሽመና ሥራ በብዛት በሚከናወንባቸው አካባቢዎች በተለያዩ ቦታዎች በሽማ ሥራ የተሰማሩት ሕፃናት በሰዎች አዘዋዋሪዎች ለዚህ ችግር የተጋለጡ ናቸው። እነዚህ ሕፃናት ለረጅም ሰዓት በጠባብ ክፍል ውስጥ ጥበብ ልብሶችን ይሠራሉ። ሥራው ትኩረትን የሚሻ በመሆኑ የፀሐይ ብርሃን ሳያገኙ ይቆያሉ። አቀርቅረው ስለሚውሉ አጥንታቸው ይጎዳል፤ **ዕይታቸው ይዳከማል**፤ እነዚህና ተደራራቢ ችግሮች በጤንነታቸው ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ ያሳድራሉ።

የተመድ የሕጻናት ጉልበት ብዝበዛ ለመከላከል የሕጻናት መብት ኮንቬንሽንን አጽድቋል። ኢትዮጵያም እ.አ.አ. 1991 ይህንን ኮንቬንሽን ፈርማለች። ኮንቬንሽኑ በአንቀጽ “32” ሕጻናትን አደገኛ በሆነ ሥራ ላይ ማሰማራት፣ ከትምህርታቸው ማሰናከል፣ ለጤንነታቸው፣ ለአካል፣ ለአእምሮ፣ ለመንፈሳዊ፣ ለሞራላዊና ማኅበራዊ እድገታቸው እንቅፋት የሚሆኑ ሥራዎችን ማሠራት የሕጻናት ጉልበት ብዝበዛ እንደሚባል ይደነግጋል። የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገመንግሥትም በአንቀጽ “36” “ሕጻናት ጉልበትን ከሚበዘብዙ ልማዶች የመጠበቅ፣ በትምህርታቸው፣ በጤናቸውና በደህንነታቸው ላይ ጉዳት ከሚያደርሱ ሥራዎች የመጠበቅ መብት እንዳላቸው ደንግጓል።

(የኢትዮጵያ የሰብዓዊ መብት ኮሚሽን። 1999። ዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብት ሠነዶች (የአማርኛ ትርጉም) ለምንባብ እንዲያመች ተደርጎ የተወሰደ።)

**የፈተና መለያ ኮድ…………………… መማሪያ ክፍል…………..**

**ትዕዛዝ አንድ፡- ከዚህ በታች ለቀረቡት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ የያዘውን ፊደል በመምረጥ መልስ ስጡ፡፡**

1. የህጻናት ጉልበት ብዝበዛ ከህጻናት ስራ የሚመሳሰለው በ… ነው::
   1. በስራው ክብደት 3. በቤተሰብ ሊታገዝ በመቻሉ
   2. ለአካል በሚሰጠው ጥቅም 4. በወላጅ ትዕዛዝ ሊሰራ በመቻሉ
2. ከሚከተሉት አማራጮች የህጻናት ስራ የሚሰጠውን ጥቅም **አይመለከትም**::
   1. ለጤንነት 2. ለአዕምሮ እድገት 3. ገቢ ለማስገኘት 4. . ለስራ ፍቅር
3. የህጻናት ጉልበት ብዝበዛ የሚባለው ምን ሲደረግ ነው?
   1. እገዛ ሲደረግላቸው 2. በግዴታ ሲከናወን 3. ስልጠና ሲሰጣቸው 4. ምግብ ሲያንሳቸው
4. የህጻናት ጉልበት ብዝበዛ በጣም ጎልቶ የሚታየው በምን አይነት ሀገራት ላይ ነው?
   1. ከሰሀራ በታች ባሉት ሀገራት 2. በታዳጊ ሀገራት 3. በአፍሪካ 4. በኢትዮጵያ
5. በገጠር የሚገኙ ህጻናት ከሚሰሯቸው ስራዎች <u>**የማይመደበው**</u> የቱ ነው?
   1. ጫማ መጥረግ 2. እርሻ ማረስ 3. ከብት ማገድ 4. ውሀ መቅዳት
6. ከሚከተሉት አማራጮች ልዩ የሆነው የቱ ነው?
   1. ሱቅ በደረቴ 2. እንጨት መስበር 3. መኪና ማጠብ 4. ሎተሪ ማዞር
7. ህጻናት ከሚሰሯቸው ከባድ ስራዎች ውስጥ ጥንቃቄን የሚጠይቀው የትኛው ነው?
   1. መኪና ማጠብ 2. ከብት ማገድ 3. ህጻናትን መንከባከብ 4. ውሀ መቅዳት
8. እነሱ የጨዋታ ፍቅራቸውን ተነጥቀው ሌሎችን እንዲያጫውቱ ይገደዳሉ ማለት ምን ማለት ነው?
   1. መጫወቻቸውን ይቀማሉ 3. እንዳይጫወቱ ይደረጋሉ
   2. ሲጫዎቱ ይቀጣሉ 4. እንዲያጫውቱ ይታዘዛሉ
9. ህጻናት ለእንቅልፍ እጦት የሚሰቃዩት በምን ምክንያት ነው?
   1. ጨዋታ ስለሚያበዙ 2. ቀን ከሌት ስለሚሰሩ 3. እረፍት ስለማያደርጉ 4. እንዳይተኙ ስለሚደረጉ
10. ድህነት ህጻናትን ለጉልበት ብዝበዛ የሚያጋልጠው በምን ምክንያት ነው?
    1. ወላጆች ስራ ስለማይሰሩ

2. ወላጆች ልጆችን ለሌላ ሰው አሳልፈው ስለሚሰጡ

3. ድሆች ብዙ ስራ እንዲሰሩ ስለሚደረጉ

4. የድሀ ልጆች ስለማይማሩ

11. ድህነት የከፋ መስዋዕትነት ያስከፍላቸዋል ማለት…

1. ኑሯቸውን ለማሸነፍ ካቅማቸው በላይ ይሰራሉ

2. በድህነታቸው ምክንያት ይሞታሉ

3. ድህነት ወላጅ አልባ ያደርጋቸዋል

4. ከፍለው መማር አይችሉም

12. ህጻናትን ለጉልበት ብዝበዛ ከሚዳርጉ ምክንያቶች በዋናነት የሚጠቀሰው፡፡

1. ድህነት 2. የወላጅ የተዛባ አመለካከት 3. ህገወጥ አዘዋዋሪዎች 4. ስደት

13. በምንባቡ መሰረት ህገወጥ የሰው አዘዋዋሪዎች በህጻናት ላይ ከሚያደርሱት ጉዳት ውስጥ የማይጠቀሰው የቱ ነው?

1. ሰው ቤት ማስቀጠር 2. ውጭ ሀገር መላክ 3. ሽማ ማሰራት 4. በቂ ምግብ አለመስጠት

14. ህገወጥ የሰው አዘዋዋሪዎች ህጻናትን የሚወስዱት በምን መንገድ ነው?

1. በማታለል 2. በመስረቅ 3. በማባበል 4. ሁሉም

15.ህጻናትን ለጸሀይ ብርሀን እጥረት የሚያጋልጣቸው የትኛው የስራ ዘርፍ ነው?

1. ከብት አገዳ 2. የሰው ቤት ስራ 3. የሽማ ስራ 4. ህጻናትን መንከባከብ

16.ህገ ወጥ አዘዋዋሪዎች ህጻናቱን በር የሚዘጉባቸው ለምንድን ነው?

1. ለአደጋ እንዳይጋለጡ 3.ምግብ እንዳይበሉ

2. ሰው እንዳያያቸው 4. ከጸሀይ ለመከላከል

17.በምንባቡ መሰረት ለህጻናት ጉልበት ብዝበዛ ዋና ተጠያቂው አካል ማን ነው ትላላችሁ?

1. ወላጆች 2. ህገወጥ የሰዎች አዘዋዋሪ 3. መንግስት 4. ህጻናት እራሳቸው

18.በሽማ ስራ ላይ የተሰማሩ ህጻናት ከሚደርስባቸው ጉዳት የማይጠቀሰው የቱ ነው?

1. እይታቸው ይደክማል 2. ቆዳቸው ይጠቁራል 3. አጥንታቸው ይጎዳል 4. ወገባቸው ይጎብጣል

19. ኢትዮጵያ የህጻናት መብት ኮንቬንሽንን የፈረመችው እንደ አውሮፓውን አቆጣጠር በስንት ዓ. ም ነው

1. በ1997 2. 1998 3. 1991 4. 1999

20. ስለህጻናት መብት በህገመንግስቱ የተደነገገው በስንተኛው አንቀጽ ላይ ነው?

1. በአንቀጽ “32” 2. በአንቀጽ “36” 3. በአንቀጽ “52” 4. በአንቀጽ “38”

21. ኮንቬንሽኑ የህጻናትን ጉልበት ብዝበዛ ምን ማለት እንደሆነ የደነገገው በስንተኛው አንቀጽ ላይ ነው?

1. በአንቀጽ “38” 2. በአንቀጽ “32” 3. በአንቀጽ “37” 4. በአንቀጽ “36”

**ትዕዛዝ ሁለት፡- ከዚህ በታች ከምንባቡ ለወጡ ቃላትና ሀረጋት ከተሰጡት አማራጮች በፍች *<u>የሚለየውን/የማይስማማውን/</u>* በመምረጥ መልስ ስጡ፡፡**

22. በግዳጅ 1. በግዴታ 2. ያለፍላጎት 3. በማስገደድ 4. በትዕዛዝ

23. ማሰናከል 1. ማደናቀፍ 2. ማሯሯጥ 3. ማበላሸት 4. ማስቀረት

24. መንፈሳዊ እድገት 1. የስሜት እድገት 2. የአስተሳሰብ እድገት 3. የሀይማኖት እድገት

25. መፈንጠዝ 1. መደሰት 2. መጫወት 3. መዝለል 4. መሮጥ

26. እጦት 1. ችግር 2. ማነስ 3. እጥረት 4. ወሰን

27. ማዕረግ 1. ስልጣን 2. ደረጃ 3. እድገት 4. ትምህርት

28. ማስኮብለል 1. ማጥፋት 2. መውሰድ 3. ማሸሽ 4. ማግለል

29. ዕይታ 1. አመለካከት 2. ራእይ 3. አስተሳሰብ 4. የአይን ብርሀን

30. ደነገገ 1. ህግ አወጣ 2. ሰራ 3. ገዛ 4. ወሰነ

## ሰ.4. የሰባተኛ ክፍል የአንብቦ መረዳች ችሎታ መለኪያ ፈተና

**አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ**

**የስነሰብ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና ኮሚኒኬሽን ኮሌጅ**

**የአማርኛ ቋንቋ፣ ስነጽሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል**

**ድህረ ምረቃ መርሀግብር**

**ለሰባተኛ ክፍል ተማሪዎች የተዘጋጀ የአንብቦ መረዳት መለኪያ ፈተና**

**ውድ ተማሪዎች፡-** ይህ የአንብቦ መረዳት መለኪያ ፈተና የተዘጋጀው "የቤተሰብ ዳራ የማንበብ ተነሳሽነትና የአንብቦ መረዳት ችሎታ ተዛምዶ" በሚል ርዕስ ለሚሰራው ምርምር መረጃ ለመሰብሰብ ነው፡፡ ስለዚህ ከዚህ በታች የቀረበውን ምንባብ መሰረት በማድረግ ለቀረቡት ጥያቄዎች በትክክል ምላሽ እንድትሰጡ እጠይቃለሁ፡፡

### ደጃዝማች በላይ ዘለቀ

ደጃዝማች በላይ ዘለቀ ከአባታቸው ከባሻ ዘለቀ ላቀውና ከእናታቸው ከወይዘሮ ጣይቱ አሰኔ በ1904 ዓ.ም. ተወለዱ፡፡ አባታቸው ጎጃም ውስጥ የብቸና ሰው ሲሆኑ፣ እናታቸው ደግሞ ወሎ የጫቀታ ተወላጅ ናቸው፡፡ ከፊታውራሪ እምቢአለ ጋር በተፈጠረ ግጭት በ1916 ዓ.ም. አባታቸው ከወንድማቸው ጋር ተገደሉባቸው፡፡ የአባታቸውን አሰቃቂ አገዳደል የተመለከቱት በላይ ዘለቀ አባይን ተሻግረው ወደ እናታቸው የትውልድ ቦታ፣ ወደ ጫቀታ ሄዱ፡፡ ከዚያም በደንብ ተዘጋጅተው የአባታቸውን ገዳዮች ለመፈለግ ወደ ጎጃም ተመለሱ ደጃዝማች በላይ ዘለቀ **በሽፍትነት ተሠማርተው** የአባታቸውን ገዳዮች በማፈላለግ ላይ እያሉ በ1928 ዓ.ም. ኢትዮጵያ በጣሊያን **ተወረረች**፡፡ ከዚያም ለአባታቸው ገዳይ **የታጠቁትን** መሣሪያ "አገሬ ትበልጥብኛለች" በማለት በጣሊያን ላይ አዞሩ፡፡ በወቅቱ በላይ ዘለቀ የ24 ዓመት ወጣት ስለነበሩ፣ ሀገር የወረረውን የጣሊያንን ጦር ለመውጋት ቆርጠው ተነሱ፡፡ ከዚያም ቁጥሩ ከ200 እስከ 300 የሚደርስ ጦር በሥራቸው ማሰባሰብ ቻሉ፡፡ በመቀጠልም፣ "እናት ሀገሬ ኢትዮጵያ ስትደፈር ከማየት ሞቴን እመርጣለሁ፡፡ የፈራህ ልቀቀኝ! ለውድ እናት ሀገርህ መስዋዕት ለመሆን

የምትፈልግ ሁሉ እኔን ተከተለኝ!" ብለው ቆራጥ ውሣኔያቸውን ሰጡ፡፡ በዚህ ጊዜ በታማኝነት አብረዋቸው የነበሩት ጓደኞቻቸው ወደ ጦርነቱ ባልገቡትና በላይ ዘለቀን ክደው ወደ ጠላት ጦር በገቡት ከሃዲ ጓደኞቻቸው ላይ የእንጉርጉሮ ግጥም ገጠሙባቸው፡፡

ይህንን አንበሳ ጀግናውን ከድታችሁ፣
ኧረ ከምን ጊዜው ለጣሊያን ገባችሁ፡፡
እምትወዱት ጣሊያን እሱ ካዋጣችሁ፣
ልቅምቅም አድርጎ ከነጫጩታችሁ፣
ከትውልድ ሀገሩ እዚያው ይውሰዳችሁ፡፡
እኛ ለአገራችን ለኢትዮጵያ ባንዲራ፣

እንታገላለን በጭብጥ ሽንብራ፡፡

አባይ ከጨረቻው ወድቀን እንደገሣ፣

ይኸው አሁን አለን ሳንጠቁር ሳንከሣ፡፡

ጥንት በአባቶቻችን ታፍራና ተከብራ፣

እንዴት በኛ ጊዜ ይውረራት አሞራ፡፡

ይህ ነጭ አሞራ ቢሽከበከብ ቢያልፍ፣

አንሰጥም ኢትዮጵያን ህይወታችን ቢያልፍ፡፡

እያሉ ተስፋቸውን ባለመቁረጥ ትግላቸውን ቀጠሉ፡፡ በላይ ዘለቀ ጎጃም ውስጥ የጠላት ጦር መቆሚያና መቀመጫ እንዳይኖረው በማድረግ ለኢትዮጵያ ከፍተኛ ውለታ ያበረከቱ ጀግና ናቸው፡፡ ለምሣሌ ለምጨን ከተባለ ቦታ በግንቦት ወር 1928 ዓ.ም. ከጣሊያን ፋሽስት ጋር ገጥመው ሲዋጉ ከወገን በኩል ጥቂት የቆሰለና የሞተ ቢኖርም ከጠላት በኩል ግን ብዙ ገድለውና አቁስለው የድሉ ባለቤት ሆነዋል፡፡ ደጃዝማች በላይ ዘለቀ ከጠላት ጋር መዋጋት እንደጀመሩ በጥቂት ጊዜ ውስጥ በአካባቢው ሕዝብ ዘንድ ታዋቂ የአርበኛ መሪ እየሆኑ መጡ፡፡

በአምስት ዓመቱ የአርበኝነት ትግልም ደጃዝማች በላይን ለማግኘት ጠላት ባደረሰው ጥቃት በአካባቢው በርካታ ሕዝብ ፈጅቷል። ነገር ግን ተከታታይ ዘመቻ እያደረገ የውጊያ ተግባር ቢፈፅምም ደጃዝማች በላይን ለመግደል ሳይቻለው ቀረ። በዚህም ደጃዝማች በላይ ዘለቀ ድል አድራጊነታቸው መለያቸው እየሆነ መጣ።

ከአምስት ዓመቱ ተጋድሎ በኋላ ብዙም ሳይቆዩ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ደጃዝማች በላይ ዘለቀን የብቸና ገዥ አድርገው ሾሟቸው። ሆኖም በዚያ ወቅት ቀድሞ ከጣሊያን ወገን ተሰልፈው አርበኞቹን ሲዋጉ የነበሩ **ባንዳዎች** በአካባቢው ስለነበሩ፣ ደጃዝማች በላይ ዘለቀ ከንጉሡ ጋር ጤነኛ የሥራ ግንኙነት እንዳይፈጥሩ መሰናክል ሆኗቸው። እነዚህ ባንዳዎች ለንጉሡ የሆነ ያልሆነ ወሬ በማቀበል በደጃዝማች በላይ ዘለቀ ላይ ጦር እንዲዘምት አስደረጉ። ይህ ሁኔታ ለህይወታቸው አስጊ መሆኑን የተረዱት ደጃዝማች በላይ ጓደኞቻቸውን ይዘው ወደ ሶማ ተራራ ወጡ። ጠላቶቻቸው ከ25 ቀናት ተከታታይ ውጊያ በኋላ እነ ደጃዝማች በላይ ዘለቀን ሊረቱ እንደማይችሉ ገመቱ። ከዚያም ከንጉሡ መልዕክት እንደ ተላከ አስመስለው "ምረነዋል ይምጣ" የሚል የምሕረት ቃል በውሸት በማስላካቸው እነደጃዝማች በላይ ከሶማ ወርደው እጃቸውን ሰጡ። ሆኖም **እጅ ከሰጡ** በኋላ በእሥረኛ ደንብ ተይዘው ወደ አዲስ አበባ መጥተው በውጊያ ላይ እንደተማረከ ሰው በጥፋተኝነት ተከሰሱና ሞት ተፈረደባቸው። ሆኖም የሞት ፍርዱ አርበኞችን ስላስቆጣ ወደ ዕድሜ ይፍታህ ተለውጦ ከመስከረም 1936 ዓ.ም. ጀምሮ ወሊሶ በደጃዝማች በቀለ ወያ እጅ እንዲታሰሩ ተደረገ።

ከወሊሶ እሥር ቤት ሊያመልጡ ይችላሉ የሚል **ጭምጭምታ** ተሰማ ተብሎ ወደ አዲስ አበባ መጥተው ደጃዝማች ውቤ ሰፈር በነበረው ወህኒ ቤት ታሰሩ። የታሰሩትም የጣሊያን ሹም ሆኖ አሳራቸውን ሲያሳያቸው ከኖረው ከጣሊያኑ ደጃዝማች ማሞ ኃይለ ሚካኤል ጋር ነበር። እነዚህ ሁኔታዎች **ጎምዛዛ** ስለሆኑባቸው ለማምለጥ ሙከራ አደረጉ። ሆኖም ያደረጉት ሙከራ ሳይሳካ ቀርቶ ሱሉልታ ከተባለ ቦታ ተያዙ። በተደረገው የማምለጥ ሙከራ ሌሎች ሦስት ያህል ሰዎች ሞተው ነበርና ወንጀላቸው አለመጠን ከበደ። ታህሣሥ 23 ቀን 1937 ዓ.ም. የሞት ፍርድ ተፈርዶባቸው ጥር 5 ቀን 1937 ዓ.ም. በስቅላት ተቀጡ። በዚህ ሁኔታ ታሪካቸው ቢደመደምም ደጃዝማች በላይ ዘለቀ በአምስቱ ዓመት የነጻነት ተጋድሎ ከፊት የተሰለፉ አርበኛ ስለነበሩ በኢትዮጵያ ታሪክ ትልቅ ቦታ አላቸው።

(ፈንታሁን እንግዳ፡፡ 2002፡፡ ታሪካዊ መዝገበ ሰብ ከጥንት እስከ ዛሬ፡ ለክፍል ደረጃው እንዲመጥን ተደርጎ የተወሰደ)

**የፈተና መለያ ኮድ............... መማሪያ ክፍል.....**

**ትዕዛዝ አንድ፡- ከዚህ በታች ለቀረቡት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ የያዘውን ፊደል በመምረጥ መልስ ስጡ፡፡**

1. ደጃች በላይ ዘለቀ የተወለዱት የት ነው?

   1.ወሎ 2. ጎጃም 3. ጫቀቻ 4. ደሴ

2. የበላይ ዘለቀ አባትና ወንድም የተገደሉት በማን ነው?

   1.በጣሊያን ጦር 2. በንጉሰ ነገስቱ

   3. በፊታውራሪ እምቢያለ 4. በሽፍቶች

3. በላይ ዘለቀ ወደእናታቸው ሀገር የሄዱት ለምንድነው?

   1.ለጉብኝት 2. ለበቀል ለመዘጋጀት

   3. ጣሊያንን ለመዋጋት 4. ዘመድ ለመጠየቅ

4. ከሚከተሉት አረፍተነገሮች አንዱን በላይ ዘለቀ አልተናገሩትም፡፡
   1. ሀገሬ ከምትደፈር ሞቴን እመርጣለሁ
   2. ለሀገርህ መስዋዕት የምትሆን ተከተለኝ
   3. ከፈራህ አትከተለኝ
   4. ያባቴን ገዳይ ተበቅየ እከተልሀለሁ

5. በላይ ዘለቀ ለአባታቸው ገዳይ የታጠቁትን መሣሪያ "አገሬ ትበልጥብኛለች" በማለት በጣሊያን ላይ አዞሩ ሲል ምን ማለቱ ነው?
   1. ከአባታቸው ገዳይ ጋር ተስማሙ 3. ከአባታቸው ይልቅ ሀገራቸውን አስቀደሙ
   2. ከአባታቸው ገዳይ ጋር ጣልያንን ለመዋጋት ሄዱ 4. የአባታቸውን ሞት አምነው ተቀበሉ

6. ልቅምቅምአድርጎከነጫጩታችሁ፣

ከትውልድሀገሩእዚያውይውሰዳችሁ። ተብሎ የተገጠመላቸው እነማን ናቸው?

1. ጣሊያኖች 2. ባንዳዎች 3. ያባቱ ገዳዮች 4. ሽፍቶች

7. በላይዘለቀጎጃምውስጥየጠላትጦርመቆሚያናመቀመጫእንዳይኖረው አደረጉ ሲል ምን ማለቱ ነው?

1. በጦርነት ተረጋግቶ እንዳይቀመጥ አደረጉት 3. በነገር ተረጋግቶ እንዳይቀመጥ አደረጉት

2. በወሬ ተረጋግቶ እንዳይቀመጥ አደረጉት 4.አካሉን በመጉዳት ተረጋግቶ እንዳይቀመጥ አደረጉት

8. በላይ ዘለቀ በህዝብ ዘንድ ታዋቂ የሆኑት በምንድን ነው?

1. በባህሪያቸው 2. በሽፍትነታቸው 3. በአርበኝነታቸው 4. በጭካኔያቸው

9. ከሚከተሉት አረፍተነገሮች ስለበላይ ዘለቀ ትክክል የሆነው የቱ ነው?

1. ጣሊያንን በተደጋጋሚ አሸንፈው ነበር 3. ባንዳ በመሆን አገልግለው ነበር

2. በጣሊያን ጦር ተማርከው ነበር 4. ከሀገር ወጥተው ነበር

10.ለምጨን በተባለ ቦታ በደጃዝማች በላይ ዘለቀ ጦርና በጣሊያን ጦር መካከል ስለተደረገው ጦርነት <u>**ስህተት**</u> የሆነው የቱ ነው?

1. ያሸነፈው በላይ ዘለቀ ነው 3. ከበላይ ዘለቀ ወገን የቆሰለና የሞተ ሰው ነበር

2. ብዙ ሰው ያለቀው ከጣሊያን ወገን ነው 4. አሸናፊው ወገን አልታወቀም

11. ደጃዝማች በላይ ዘለቀን የቢቸና ገዢ አድርገው የሾሟቸው ማን ናቸው?

1. ቀዳማዊ ሀይለ ስላሴ 2. የጣሊያን መሪ 3. የጎጃም ህዝብ 4. ባንዳዎች

12.ደጃዝማች በላይ ዘለቀ ከንጉሡ ጋር ጤነኛ የሥራ ግንኙነት እንዳይፈጥሩ መሰናክል የሆኗቸው እነማን ናቸው።

1.የአካባቢው ህዝብ 2. ጣልያኖች 3. ባንዳዎች 4. የንጉሱ ዘማቾች

13.ደጃዝማች በላይ ዘለቀ ወደ ሶማ ተራራ ጓደኞቻቸውን ይዘው የወጡት …

1.ለመዝናናት 2. ለአደን 3. ለጨዋታ 4. ለውጊያ

14.ደጃዝማችበላይዘለቀ እጃቸውን የሰጡት.

1.በውጊያው ስለተሸነፉ 3. የተሳሳተ መልዕክት ስለደረሳቸው

2 ንጉሳቸውን ስለሚወዱ 4. በጠላት ጦር ስለተማረኩ

15. ደጃዝማች በላይ ዘለቀ የተፈረደባቸው የሞት ፍርድ ወደ እድሜ ልክ እስራት የተቀየረው…

1.ፍርዱ ፍትሀዊ ስላልነበር    3. አርበኞች ስለተቆጡ

2.ንጉሱ ትዕዛዝ ስላስተላለፉ    4. እጃቸውን ስለሰጡ

16.ደጃዝማች በላይ ዘለቀ ለመጀመሪያ ጊዜ የታሰሩበት ሀገር…

2. ሱሉሉታ   2. ቢቸና   3. አዲስ አበባ   4. ወሊሶ

17.ደጃዝማች በላይ ዘለቀ ለሁለተኛ ጊዜ የሞት ፍርድ የተፈረደባቸው በስንት ዓ.ም ነው?

2. ታህሳስ 23፣ 1936 2. ጥር፣ 5 1937 3. ታህሳስ፣ 23 1937   4. ጥር 5፣ 1936

18.በላይ ዘለቀ በአምስቱ ዓመት የነጻነት ተጋድሎ ከፊት የተሰለፉ አርበኛ ነበሩ ማለት…

1. ታዋቂ ናቸው   2. መሪ ናቸው   3. አጭር ናቸው   4. ጀግና ናቸው

**ትዕዛዝ ሁለት፡- ከዚህ በታች ከምንባቡ ለወጡ ቃላትና ሀረጋት ከተሰጡት አማራጮች በፍች *<u>የሚለየውን/የማይስማማውን/</u>* በመምረጥ መልስ ስጡ፡፡**

19.በሽፍትነት ተሰማርተው   1. ጫካ ገብተው   3. በሌብነት ተሰማርተው
2. ከህግ ሸሽተው   4. ጠላት አፍርተው

20.ተወረረች   1. ተከበበች   2. ተያዘች   3. ተወደደች   4. ተገዛች

21.የታጠቁትን   1. የለበሱትን   2.የተሸከሙትን   3. የያዙትን   4. ያነገቱትን

22.ባንዳዎች   1.ከሀዲዎች   2.ሌቦች   3. አርበኞች   4.ሽፍታዎች

23.እጅ ከሰጡ   1. ጉቦ ከሰጡ   2. ተማረኩ   3. ከተሸነፉ   4. መሳሪያ ካስረከቡ

24.ጭምጭምታ   1. ሀሜት   2. አሉባልታ   3. ምሽት   4. ወሬ

25.ጎምዛዛ   1. ከባድ   2. መራራ   3. አስቸጋሪ   4. ፈታኝ

## ለ.5. የስድስተኛ ክፍል የአንብቦ መረዳት ችሎታ መለኪያ ፈተና

**አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ**

**የስነሰብ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና ኮሚኒኬሽን ኮሌጅ**

**የአማርኛ ቋንቋ፣ ስነጽሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል**

**ድህረ ምረቃ መርሀግብር**

**ለስድስተኛ ክፍል ተማሪዎች የተዘጋጀ የአንብቦ መረዳት መለኪያ ፈተና**

**ውድ ተማሪዎች፡-** ይህ የአንብቦ መረዳት መለኪያ ፈተና የተዘጋጀው "የቤተሰብ ዳራ የማንበብ ተነሳሽነትና የአንብቦ መረዳት ችሎታ ተዛምዶ" በሚል ርዕስ ለሚሰራው ምርምር መረጃ ለመሰብሰብ ነው፡፡ ስለዚህ ከዚህ በታች የቀረበውን ምንባብ መሰረት በማድረግ ለቀረቡት ጥያቄዎች በትክክል ምላሽ እንድትሰጡ እጠይቃለሁ፡፡

## እቴጌ ጣይቱ ብጡል

ጣይቱ ከአባታቸው ከደጃዝማች ብጡልና ከእናታቸው ከወይዘሮ የውብዳር ነሐሴ 12 ቀን 1832 ዓ.ም. በአሁኑ ደቡብ ጎንደር ዞን ደብረታቦር ከተማ ተወለዱ፡፡ አባታቸው የጎንደርና የወሎ፣ እናታቸው ደግሞ የጎጃም ተወላጅ ናቸው፡፡ አባታቸው በጦርነት በመሞታቸው በ13 ዓመታቸው ደብረታቦርን ለቀው ወደ እናታቸው ትውልድ ቦታ ወደ ጎጃም ሄዱ፡፡ ጎንደር እያሉ፣ በማህደረ ማርያም፣ የጀመሩትን ትምህርታቸውን በጎጃም ደብረ መዊዕ ደብር ቀጠሉበት፡፡

### የጋብቻሕይወት

የአፄ ቴዎድሮስ ዘመን እንደተጋመሰ ጣይቱ የንጉሠ ነገሥቱ አዛዥ የነበሩትን አንዱን መኰንን አገቡ፡፡ የአፄ ቴዎድሮስ ዘመን ሲያበቃ የቀድሞ ባላቸውን ፈተው ከአፄ ዮሐንስ የጦር አለቆች አንዱን አግብተው ለተወሰነ ጊዜ ወደ ትግራይ ሄደው ተቀምጠዋል፡፡ ባለቤታቸው በአፄ ዮሐንስ ተይዘው ሲታሰሩ እንደገና ወደ ጎጃም ተመለሱ፡፡ ወደ ጎጃም እንደተመለሱም ያቋረጡትን ትምህርት ለሦስተኛ ጊዜ በመቀጠል ጽሕፈትን፣ ንባብን፣ ግዕዝንና የአማርኛ ቅኔን ተማሩ፡፡ ትምህርታቸውን እንዳጠናቀቁ በጥበብና በሕይወት

ፍልስፍና የላቀ ችሎታ እንዳላቸው እየታወቀ መጣ:: የጣይቱን ዝና ከሰሙት መካከል አንዱ አፄ ምኒልክ ናቸው:: ንጉስ ምኒልክ በሚያዚያ ወር 1869 ዓ.ም. ወደ ባህርዳር ተጉዘው በእናታቸው በወ/ሮ የውብዳር ቤት ዘመድ ወዳጅ በታደመበት ከወ/ሮ ጣይቱ ብጡል ጋር ተጫጩ:: ከዚያም ሚያዝያ 25 ቀን 1875 ዓ.ም. በአንኮበር መድኃኒዓለም ቤተክርስቲያን በቁርባን ተጋቡ:: ጥቅምት 27 ቀን 1882 ዓ.ም. ጣይቱ ብጡል "እቴጌ" ተብለው ተሰየሙ:: ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ስማቸው በመላው ሀገሪቱ ነገሠ::

## ፖለቲካ

እቴጌ ጣይቱ አፄ ምኒልክን ካገቡ በኋላ ያልተሰለፉበት ምጣኔ ሀብታዊ፣ ፖለቲካዊና ሀይማኖታዊ ጉዳይ አልነበረም:: አፄ ምኒልክ አዳዲስ ሥልጣኔዎችን ከውጪ ለማስገባት ቁርጠኛ አቋም ይዘው ሲሰሩ፣ ዋና አማካሪያቸውና አጋራቸው እቴጌ ጣይቱ ነበሩ:: የቴክኖሎጂ ውጤቶች ወደ ኢትዮጵያ ሲገቡ አፄ ምኒልክን ያበረታቱ ነበር:: ሌሎች ሰዎች ቴክኖሎጂውን ከሰይጣን ሥራ ጋር እያያያዙ ሲቃወሙ በግንባር ቀደምትነት የሚደግፏቸው እቴጌ ጣይቱ ነበሩ:: ፖለቲካዊና ሀይማኖታዊ ክርክሮች ላይ እየተገኙ የመንግሥታቸውን አቋም ያስረዱና ይከራከሩ ነበር:: አፄ ምኒልክ ወደ ዘመቻ ሲንቀሳቀሱ የመንግሥት ዓይንና ጆሮ ሆነው አገልግለዋል:: ስያሜዋን ከመስጠት ጀምሮ የአዲስአበባን ከተማ የመሠረቷት እቴጌ ጣይቱ ናቸው:: የመጀመሪያውን ዘመናዊ ሆቴልም ከፍተዋል:: እነዚህና ሌሎች ጉልህ ተግባሮቻቸው ስማቸው ዘላለማዊ ሆኖ እንዲታወስ አድርገዋቸዋል:: እቴጌ ጣይቱ በፖለቲካ ተግባራቸውም የሚታወስ ጠንካራ ታሪክ አላቸው:: ጣሊያኖች በውጫሌ ውል ካሰፈሯቸው ነጥቦች መካከል አንቀጽ "17" ሥር ያለው ሀሳብ በስህተት መተርጎሙን አጥብቀው ተቃውመዋል:: አንቀጽ "17" ን ጣሊያኖች ኢትዮጵያን በሚጎዳ መልኩ አዛብተው ጥቅም ላይ እንዲውል ባደረጉበት ጊዜ "ውሉን ከመቀበል ጦርነትን እመርጣለሁ" በማለት የማያወላውል አቋማቸውን አሳውቀዋል:: በዚህም በኢትዮጵያና በጣሊያን መካከል እሰጣገባው ተካርሮ ጦርነቱ አይቀሬ ሆነ:: አፄ ምኒልክ ምታ ነጋሪት ክተት ሠራዊት ብለው ወደ አድዋ ጦርነት ዘመቱ:: እቴጌ ጣይቱም በራሳቸው የሚመራ 3000 እግረኛ ጦርና 6000 ፈረሰኛ አስከትለው ከባለቤታቸው ጎን በመሠለፍ የካቲት 23 ቀን 1888 ዓ.ም. አድዋ ላይ ጠላትን ድል አደረጉ::

## የጦርነት ስልት

እቴጌ ጣይቱ ጦርነት ከመጀመሩ ከጥቂት ቀናት በፊት ለጦር አበጋዞች የጦርነት ስልት አቀረቡ። ይህም የጠላት ወታደሮች ውኃ የሚጠጡበትን ምንጭ በመቆጣጠር ማጥቃት እንደሚቻል ያቀረቡት ሀሳብ ነበር። ሀሳባቸውም በአፄ ምኒልክና በሁሉም የጦር አበጋዞች ዘንድ ተቀባይነትን ስላገኘ ጠላት ውኃ የሚጠጣበት ምንጭ በኢትዮጵያ ወታደሮች ቁጥጥር ሥር ዋለ። የጠላት ወታደሮችም እጃቸውን ከመስጠት ሌላ አማራጭ አልነበራቸውም። በአጠቃላይ እቴጌ ጣይቱ በተለያየ መልኩ አገራዊ ተልዕኳቸውን የተወጡና በኢትዮጵያ ታሪክ አሻራቸውን ያሳረፉ ታላቅ ሴት ነበሩ። የኢትዮጵያን ነጻነት ባስጠበቀው የአድዋ ድል ትልቅ ሚና ከመጫወታቸው በተጨማሪ ሌሎች ማህበራዊ ተግባሮቻቸውም የሚያኮሩ ናቸው። እቴጌ ጣይቱ የካቲት 4 ቀን 1910 ዓ.ም. ከዚህ ዓለም በሞት ቢለዩም፣ ስማቸውና ያከናወኗቸው ተግባራት ግን ከሌሎች እውቅ የኢትዮጵያ አርበኞች ጋር ዘላለም ሲወሳ ይኖራል።

(ፈንታሁንእንግዳ። 2002።ታሪካዊ መዝገበ- ሰብ ከጥንት እስከ ዛሬ ። ከገጽ 697-699፣መጠነኛ

**የፈተና መለያ ኮድ…………… መማሪያ ክፍል…..**

**ትዕዛዝ አንድ፡- ትክክል የሆነውን እውነት ስህተት የሆነውን ደግሞ ሀሰት በማለት መልስ ስጡ።**

------------ 1. ጣይቱ ብጡል በእናታቸው ጎንደሬና ወሎየ ናቸው።

------------2. ጣይቱ ትምህርታቸውን የጀመሩት በጎንደር ደብረመዊዕ ደብር ነበር።

------------ 3. ጣይቱ ብጡል ከአጼ ዮሀንስ የጦር አለቆች ያገቡት ሁለተኛ ባላቸውን ነው።

------------4. ጣይቱ ብጡል ወደትግራይ የሄዱት ትምህርት ለመማር ስለፈለጉ ነው።

------------5. በጥበብና በህይወት ፍልስፍና የላቀ ችሎታ እንዳላቸው የታወቀው የአጼ ሚኒሊክ ነው።

------------ 6. አጼ ሚኒሊክ የጣይቱ ብጡል ሶስተኛ ባል ናቸው።

------------ 7. የቴክኖሎጂ ውጤቶች ወደኢትዮጵያ ሲገቡ ጣይቱ ተቃውመው ነበር።

------------ 8. የአዲስአበባንከተማየመሠረቷትእቴጌጣይቱናቸው።

------------ 9. እቴጌ ጣይቱ በፖለቲካዊ ክርክሮች የሀገራቸውን አቋም ይገልጹ ነበር፡፡

------------ 10. እቴጌ ሀገራቸውን ማገልገል የጀመሩት በአጼ ቴወድሮስ ዘመን ነበር፡፡

**ትዕዛዝ ሶስት፡- በ"ሀ" ስር ለተዘረዘሩት አረፍተነገሮች ትክለኛውን መልስ ከ"ለ" በመምረጥ አዛምዱ፡፡**

| ሀ. | ለ. |
|---|---|
| ----------- 11. ከአባታቸው ደጃዝማች ብጡልና ከእናታቸው የውብዳር ተወለዱ | 1. 1845 |
| | 2. 1875 |
| ----------- 12. ወደእናታቸው ትውልድ ቦታ ሄዱ | 3. 1888 |
| ----------- 13. በንጉስ ሚኒሊክ ታጩ | 4. 1869 |
| ----------- 14. ከንጉስ ሚኒሊክ ጋር ተጋቡ | 5. 1910 |
| ----------- 15. እቴጌ ተብለው ተሰየሙ | 6.1908 |
| ----------- 16. ጦርነቱን በድል አጠናቀቁ | 7. 1832 |
| ----------- 17. ከዚህ አለም በሞት ተለዩ | 8. 1882 |
| | 9. 1901 |
| | 10. 1873 |

**ትዕዛዝ ሶስት፡- ከዚህ በታች ለቀረቡት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ የያዘውን ፊደል በመምረጥ መልስ ስጡ፡፡**

-------- 18. ጣይቱ ብጡል ወደእናታቸው ሀገር በ13 አመታቸው የሄዱት

